
ንጥቀቱ እውን ነበር!
እናም እናንተ ሳትወሰዱ ቀርታችኋል . . .
ታዲያ አሁን ምን መደረግ አለበት?
ኢየሱስ ተስፋና መመሪያ ሊሰጣችሁ
በክሌርና በህዝቅኤል ዱ ቡስ በኩል
መዕክት አስተላልፏል

ንጥቀቱ እውን ነበር!

እናም እናንተ ሳትወሰዱ ቀርታችኋል . . .
ታዲያ አሁን ምን መደረግ አለበት?

ተስፋና መመሪያ ሊሰጣችሁ
ኢየሱስ ለእናንተ ደብዳቤ አዘጋጅቷል
ይህም መልዕክት የተሰጠው በክሌርና በህዝቅኤል ዱ ቦስ
እንዲሁም በካሮል ጄንጊስ በኩል ነበር

መልዕክቱ የሚያጠቃልለው በፈረንጆች አቆጣጠር
ከሰፕቴምበር 2014 እስከ ኦክቶበር 2015 ዓ.ም ድረስ
ያለውን ነው

የአሳታሚው መብት የተጠበቀ ነው
Copyright © 2015 Clare and Ezekiel du Bois all rights reserved

ትርጉም በሲስተር ፀሐይ አባተ
Tsehaiabate332@gmail.com

ማስታወቂያ

እነዚህን መልዕክቶች በማንኛውም ዓይነት መልኩ

በኤልክትኖኒክስ ወይም በወረቀት አባዝቶ

ለሰዎች ተደራሽ እንድታደርጉ እናበረታታለን

መልእክቶቹን በከፊል ወይም በጥቅሉ  በዌብሳይታችሁ

ወይም በየትኛውም መንገድ መለጠፍ ትችላላችሁ

ነገር ግን የምንጠይቃችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው

ሌሎችም መልዕክቱን  ኮፒ በማድረግ ማሰራጨት እንደሚችሉ

ግንዛቤው እንዲኖራቸው ይህንን ማስታወቂያ እንድትጨምሩ ነው

ይህ መፅሐፍ በኤሌክትሮኒክስ መልክ በነፃ በሚቀጥለው ዌብሳይት ይገኛል

http://www.HeartDwellers.org
Other Still Small Voice venues are:
Still Small Voice Youtube channel:
https://www.youtube.com/user/claredubois/featured
Still Small Voice Facebook: Heartdwellers
Blog: https://heartdwellingwithjesus.wordpress.com/
Blog: www.stillsmallvoicetriage.org

# "ንጥቀቱ እውን ነበር"
# "The Rapture was real"

**ዝርዝር ርዕሶች**
**Table of Contents**


| መልዕክቶች | ገፅ |
|---|---|
| **መቅድም: ከንጥቀት ለቀሩት ደብዳቤ ከአዘጋጆቹ** {Rapture Letter to the Left Behind} | 7 |
| **መግቢያ ንጥቀት ለመሆኑ ምንድነው? የሚመለከተውስ ማንን ነው?** **{What WAS the Rapture, Anyway? And Who Was it For?}** | |
| 1. ትንቢታዊ መልዕክት ለሙሽራዬ- የንስሐ ጥሪ {Prophetic Message to My Bride} | 9 |
| 2. በኑኩላር ጦርነት ውስጥ ወደኋላ ለቀሩ መዝሙር {Left Behind in Nuclear War song and dramatization} | 11 |
| **ክፍል አንድ: የጌታ የራሱ ቃል ለእናንተ** {The Lord's Own Words for You} | |
| 1.1. ከንጥቀት በኋላ ቁጥር 1. ደብዳቤ ከጌታ ኢየሱስ {Post-Rapture letters from God #1 } | 14 |
| 1.2. ከንጥቀት በኋለ ቆጥር 2 ደብዳቤ ከጌታ ኢየሱስ {Post-Rapture letters from God #2} | 14 |
| 1.3. ከንጥቀት በኋላ ቁጥር 3 ደብዳቤ ከጌታ ኢየሱስ {Post-Rapture letters from God #3} | 15 |
| 1.4. አሁን ምን ማድረግ አለብኝ? {What Do I DO NOW?? Surrender to Love} | 16 |
| **ክፍል ሁለት: በንጥቀት ጊዜና ከንጥቀት በኋላ ወዲያው ስለሚከሰቱ ነገሮች በህልም የተገለጡ መልዕክቶች** {Prophetic Dreams of What Would Happen At the Rapture or Soon Afterward} | ይህ ክፍል አልተተረጎመም {This section is not translated} |
| **ክፍል ሦስት: ከንጥቀት ወደኋላ ለቀሩት የተሰጠ መልዕክት** {Messages For the Left Behind} | |
| 3.1. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው የክስተቶች ቅደም ተከተል ይናገራል-ክፍል 1 {Jesus speaks On: What is To Come After the Rapture **Order of Events** - part 1} | 18 |
| 3.2. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 2 {Jesus Speaks On: What is To Come **After the Rapture** – part 2} | 22 |
| 3.3. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 3&4 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **How to Stay Under God** - parts 3 & 4} | 25 |
| 3.4. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 5 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **Who I Can Protect** and Who I Cannot Protect - part 5} | 30 |
| 3.5. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 6 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **Demons, Aliens, Volcanoes** and Hell Expanded - part 6} | 33 |
| 3.6. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 7 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **The World Will Mourn** - part 7} | 37 |
| 3.7. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 8 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **The Day the Bombs Fall** - part 8 } | 42 |
| 3.8. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 9 {Jesus Speaks On: After the Rapture, **Prepare Packages** of Hope - part 9} | 46 |

3.9. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 10 51
{Jesus Speaks On: After the Rapture, Troubled **Waters** - part 10}
3.10. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት ይናገራል - ክፍል 11 54
{Jesus Speaks On: After the Rapture, Why Must **Revelation Be Fulfilled** - part 11}
3.11. ከንጥቀት በኋላ የሚሆነው ትልቁ መንፈሳዊ መነቃቃት 59
{The Great Revival After the Rapture }
3.12. የሚመጣውን የመከራ ዘመን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል 62
{Surviving the Coming Tribulation }

**ክፍል አራት ፡ ስለ ንጥቀት ለካሎር የተሰጠ መልዕክት**
{ Rapture Messages given to Carol Jennings}

4.1. በክርስቶስ ያለውን ህይወት ፈልጉ 66
{Seek LIFE In Jesus }

4.2. ሁሉን ነገር የምትተዉበት ጊዜ ነው 67
{It's Time to Let Go}

4.3. ኢየሱስን ተከተሉ - የአውሬውን ምልክት አትቀበሉ 69
{Follow Jesus – Do NOT Take the Mark of the Beast! }
4.4. የቀረው እጅግ ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው ወደእኔ ኑ 71
{There is Very Little Time...Come to Me}
4.5. ለእናንተ ያለን ፍቅር እጅግ ትልቅ ነው 73
{How Great is My Love for You}

4.6. ገንዘብ፣ በራስ መተማመን . . . ወይስ እኔን? አሁኑኑ መወሰን አለባችሁ 77
{Money, Self-Reliance...or Me. You Must Decide}

**ክፍል አምስት፡ ከጌታ ተጨማሪ ትምህርቶች**
{More Lessons From the Lord}

5.1. ሰርን እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ የለም 79
{CERN "I AM God and There Is None Other" }

5.2. ሁሉም እንደነበረው የሚቀጥል ይመስላል 80
{Everything Seems Business as Usual}
5.3. የአሜሪካ ሞት 84
{The Death of America}
5.4. ከንጥቀት ለቀሩት አቅርቦትና መመሪያ 86
{Provision and Instruction For Those Left Behind}
5.5. በስጋ ላይ አትታመኑ 89
{Put No Confidence in the Flesh}
5.6. የገሃነም መንጋዎች ወደምድር ክልል ተለቀዋል 92
{The Hordes of Hell Have Been Released}
5.7. ክብርን ለመጠበቅ የሰርን ክፋት መጨመር 94
{CERN Wickedness Increases, Pride Protection }
5.8. የመከሰስ ስሜት ይሰማችኋል? 99
{Do You Feel Condemned?}

**ክፍል ስድስት፡ ከጌታ መልዕክት እንዴት መስማት እንደምትችሉ**
{Messages to Help You Know How to Hear From the Lord}
6.1. ከጌታ ጋር ቅርበት ለመፍጠር የሚያስችል ፀሎት፣ 103
{Prayer That Prepares Us For Intimacy With Jesus: Dwelling Prayer}

6.2. ከጌታ ቃል መቀበል - ቃልህ ለእግሬ መብራት ነው 106
{Getting a Word From the Lord: Your Word is a Light Unto My Feet}
6.3. ስለመለየት የኢየሱስ ትምህርት 111
{Jesus Teaches on Discernment}

6.4. ኢየሱስ ሙሽራው እንዴት ሊያየው እንደሚችል የሰጠው መልስ 114
{Jesus Answers His Bride on How to See Him}

**ክፍል ሰባት፡ ኢየሱስ ከእኛ የሚፈልገው ባህርያት**
{Messages to Show You the Attitudes He is Looking for From You}

7.1. እናንተ የጠፋችሁና ብቸኞች ወደእኔ ኑ 119
{Come to Me, My Lost and Lonely Ones }
7.2. ወደ እኔ ተመለሱ -መዝሙር 123
{Song–Turn Back to Me}
7.3. የምፈልገው ያለተከፋፈለ ልባችሁን ነው 124
{"I Want Your Whole Heart," Jesus said}

**ክፍል ስምንት፡ አታላይ መንፈስ እንዴት እንደሚሰራና እንዴት መለየት እንደምንችል**
{Messages to Show You How Deceiving Spirits Work and How to Use discernment}

8.1. አታላይ መንፈስ እንዴት እንደሚሰራ 127
{Deceiving Spirits Work}
8.2. መንፈስን መለየት እንዴት እንደምንችል የኢየሱስ ትምህርት 140
{Jesus Teaches on Discernment}
8.3. በኃጢያት ስንወቅድ ከእኛ ተጣብቀው የሚጓዙ አጋንንቶች 143
{Tag-Along Monsters - When You Fall}
8.4. የሦስት ቀን የጨላማ ቀናት፣ በሚስጥር የሚደረግ ንጥቀት፣ የመለየት ሂደት፣ እውነት ወይስ ውሸት? 145
{Secret Rapture, Three Days of Darkness, Our Discernment Process: True or False? }
8.5. ከተለያዩ ሶስት ምንጮች የምትሰሟቸውን ድምፆችን መለየት 151
{Discerning Between the Three Voices You Hear }
8.6. ኢየሱስን እንዳትሰሙትና እንዳታዩት የሚከለክሉ አጋንንታዊ ተፅዕኖዎች 155
{Demonic Obstacles Against Hearing and Seeing Jesus }
8.7. በትክክል መለየት መቻል 164
{You Must Have TRUE Discernment}

**ክፍል ዘጠኝ፡ በመንግስተ ሰማይ የሚጠብቃችሁ - ተስፋ እንዳለ ለማመልከት የተሰጠ መልዕክት**
{Messages to Give You Hope: Heaven - What is Waiting for You}

9.1. እውነተኛ ቤታችሁ(የሙሽራዋ ክሮንክልስ ከሚለው የተወሰደ) 165
{Your True Home (a selection from *Chronicles of the Bride)*}
9.2. ከንጥቀት በኋላ መንግስተ ሰማይና የሚሊንየሙ መንግስት 166
{Heaven and the Millennium, After the Rapture }

**ክፍል አሥር፡ ፀሎት፣ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፣ ሥጋ ወደ ሙ፣ ከአጋንንት እሥራት ነፃ መውጣት**
{Prayer, Holy Spirit Baptism, Communion and Deliverance}

10.1. ጠላትን የማሰር ፀሎት 170
{Binding Prayer}
10.2. በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደምንመበቅ 174
{How to Receive the Baptism of the Holy Spirit}
10.3. ሥጋ ወደሙ 176
{Jesus teaches on Communion}
10.4. ከአጋንንት እሥራት ለመፈታት የሚደረግ ዝግጅት 179
{How to Prepare for Deliverance of Demonic Spirits}

# መቅድም/ Foreward

በጣም አዝናለሁ፡፡ አስቀድሜ ለመንገር በጣም እመኝ ነበር፡፡ በየትኛውም መንገድ ቢሆን እንድታዉቁ እመኝ ነበር፡፡ እንድትሰሙ በጣም አመኝ ነበር፡፡ ስለጉዳዩ ትኩረት እንድትሰጡት እመኝ ነበር፡፡ እንድታውቁ እጅግ ምኞቴ ነበር፡፡ በጣም በጣም አዝናለሁ፡፡ ነገር ግን መሄድ ነበረብን፡፡

ብዙ ጊዜ ብንተያይ፣ አብረን ብናሳልፍና የበለጠ ብናበረክትላችሁ በወደድን ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን በዚህ ምድር ላይ ታይቶ የማይታወቀውን እጅግ አሰቃቂውንና አስቸጋሪውን ጊዜ በቅርብ ልትጋፈጡት ነው፡፡ በእውነትም አላመናችሁንም ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን እንደዛው ሆነ፡፡ እናም ሌላው የቀረው ነገር ሁሉ መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እንደዛው ሊከናወን ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እውነት ነው፡፡ መልሳችሁም ዳግም እንዳትጠራጠሩት፡፡ የከፋውን ለማምለጥ አሁንም የሚቀረው  አንድ መንገድ ብቻ ነው፡፡ አሁን በምትችሉበት ጊዜ ወደ ኢየሱስ ተመለሱ፡፡ ስታስቡት ይህ ምንም ስሜት የማይሰጥ ይመስላል፡፡ ነገር ግን እንደ እውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔር ነገር የሚሰራው በእንዲህ ዓይነት ነው፡፡ ምክንያቱም ከእኛ አይምሮ ይልቅ እርሱ ትልቅ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በራሳችሁ ይህንን ማድረግ አትችሉም፡፡

እርሱ ብቻ ነው ሁሉን የሚያውቀው፡፡ እርሱ ብቻ ነው ሊያድናችሁ የሚችለው፡፡ የፈጠራችሁ እርሱ ነው፡፡ የፈጠራችሁም ስለወደዳችሁ ነው፡፡ እርሱ ብቻ ነው ከማንም የበለጠ እስካሁንም ሆነ ወደፊት በፍፁም ፍቅሩ ሊወዳችሁ የሚችል፡፡ ለእናንተ መልካም የሆነውንና የሚጎዳችሁን የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ደግሞም ምን እንደሚጎድላችሁ በትክክል ያውቃል፡፡ እርሱ ለእናንተ የሚፈልገው ደስታን፣ መጠበቅንና ነፃነትን ነው፡፡ እውነተኛ ነፃነት፣ ፍፁም ደስተኛና የተሳካላችሁ እንድትሆኑ ነው፡፡ ሁሉም ለእናንተ በዚህ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ እስካሁንም እናንተን ለመርዳት ሲጠብቅ. . ሲተብቅ ሲጠብቅ ነበር፡፡ ተጠምዳችሁ በጣም ወደሚያስፈራው ሥፍራ፣ ስቃዩ ለዘላለም ወደማያበቃበት ወደ ገሃናም እንዳትገቡ ተጠንቀቁ፡፡

አዎ ገሃነም ገሃነም እውነት ነው፡፡ ይህ ሥፍራ የተዘጋጀው ለእናንተ አይደለም፡፡

እናንተ የተፈጠራችሁት መቼም ቢሆን ወደዚያ ለመግባት አይደለም፡፡ እናንተ የተፈጠራችሁት እንድትጎዱ፣ ብቸኛ እንድትሆኑ፣ ድካም፣ ረሃብና ህመም እንዲያጠቃችሁ አይደለም፡፡ እናንተ የተፈጠራችሁት መገመት ከምትችሉት በላይ የበለጠ ደስተኛ እንድትሆኑ፣ ለሁልጊዜው ወጣትና በነፃነት የምትኖሩ እንድትሆኑ ነው፡፡ ለዘላለሙ የተፈጠራችሁት ለዚህ ነው፡፡ ነገር ግን ምርጫው የእናንተ ነው፡፡ አሁን ሁሉም ያለው በእጃችሁ ላይ ነው፡፡ መኖር ወይም መሞት፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስቃዩ እየባሰ የሚሄደውን መምረጥ ወይስ ለዘላለም በአስተማማኝ ደስታ፣ ፍቅርና ጥበቃ ውስጥ መኖር?

አሁን ልንጠይቃችሁ የምንችለው ይህንን ነው፡ ኢየሱስን እንዳዘናችሁና መጥቶ ህይታችሁን እንዲቆጣጠር አሁን ጠይቁት፡፡ ለእርሱ ህይወታችሁን ስጡ፡፡ እናንተን ለማዳን ጊዜም አይወስድበትም፡፡

የሚቀጥሉትን መልዕክቶች ከኢየሱስ በመቀበል ኢየሱስን እንዴት እንደምትከተሉ መመሪያ እንዲሆናችሁ ሰብስበን በአንድ ላይ አድርገናቸዋል፡፡ የመከራውን ዘመን በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት ኑሩ፡፡ አሁን ወደ እርሱ ከተመለሳችሁ እርሱ ይመራችኋል፣ ደህንነታችሁን ይጠብቃል፣ ጥበቃም ያደርግላችኋል፡፡ ለማወቅ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እርሱ

ያስተምራችኋል፡፡ የት መሄድ እንዳለባችሁ፣ እንዴት መኖር እንዳለባችሁ፣ ከጠላቶቻችሁ እንዴት ማምለጥ እንዳለባችሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ በሙሉ ልባችሁ በእርሱ ላይ ብቻ ከታመናችሁ ምግብ፣ አልባሳት፣ ህክምና ወይም ፈውስ እርሱ ያቀርብላችኋል፡፡

**በመጨረሻም የምናስጠነቅቃችሁ ነገር፣ ምንም ነገር ብታደርጉ፡ ምንም ዓይነት ምልክት አትቀበሉ፣ ወይም በመርፌ የሚሰጥ ነገር አትቀበሉ፡፡ ምግብ ለመግዛት ወይም ማንኛውንም ክፍያ ለመክፈል የሚጠቅም ነገር በሰውነታችሁ ላይ አትቀበሉ፡፡ ይህ ቺፕ በሰውነታችሁ የሚያስገባና መቼም ቢሆን ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እንዳትመለሱ የሚያደርግ ነው፡፡ መጨረሻችሁም ከሰይጣን ጋር ለዘላለም በገሃነም እንድትጣሉ የሚያደርግ ነው፡፡**

**ይህንንም ቺፕ/Chip/ የሚቀብሩት በአብዛኛው በቀኝ እጃችሁ ወይም በግንባራችሁ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን በየትኛውም ቦታ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡**

**ይህ እኛ የምናወራው የሴራ መላምት/Consipracy theory/ አይደለም፡፡ የምናወራው "ሃይማኖት" አይደለም፡፡ የምናወራው በጣም በጣም እውነተኛ የሆነ ነገር ነው፡፡ በሰውነታችሁ ውስጥ የሚቀበረው "ቺፕ" ስለ እግዚአብሔር ምንም እንዳታስቡ የሚያደርግ ነገር በውስጡ ተከቶበታል፡፡ ከተቀበላችሁት ከዚህ ነገር የተነሳ ለማምለጥም ፍላጎት አይኖራችሁም፡፡**

**ይህንን ነገር አንዴ ካስደረጋችሁ ወደኋላ መመለስ አይቻልም!!**

# መግቢያ
## ንጥቀት ለመሆኑ ምንድነው? የሚመለከተውስ ማንን ነው?

{What was the Rapture, Anyway? And who was it for?}

---

## ለሙሽራዬ የትንቢት ቃል
**ሰፕቴምበር 1 ቀን 2014 ዓ.ም**

{Prophetic word for My Bride}

*ጌታ ሙሽራውን ወይም ሙሽራ ለመሆን ለመታጨት የምትችለውን ለንስሐ እየጠራት ነው:: እሷ ለንጥቀት አልተዘጋጀችም እና ሊያዘጋጃት ይፈልጋል::በቀድሞው ትምህርት እንዳካፈልኳችሁ የዚህ አገር ኢኮኖሚው/የአሜሪካ/ እየወደቀ ያለበትና ጌታም እየፈቀደ ያለው አንዱ ምክንየታ ሙሽራውን ከአለም ለማውጣት ስለፈለገ ነው:: ይህም አይምሮዋን ከአለም ነገር አንስታ ወደ እርሱ እንድታደርግ ስለፈለገ ነው:: በዚህ አገር ብዙ ባለፀጋ ክርስቲያኖች አሉ:: ስለ ብልፅግና የሚያወሩ:: ለመበልፀግ እምነት ከሌላችሁ ውጤታማ ክርስያኖች አይደላችሁም የሚሉ:: ነገር ግን ምንም ነገር ከእውነት የራቀ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን ገንዘብና ብልፅግና በኢየሱስ ሐሳብ ውስጥ የመጨረሻውን ሥፍራ  የያዙ ነበሩ:: በብሉይ ኪዳን ባለፀግነት አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቸረ ልዩ ስጦታ ተደርጎ ይቆጠር ነበር:: በአዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር ልኬት አስቀምጧል:: ጌታ ኢየሱስ እንደ ንጉስ ወይም እንደ ንጉስ ልጅ መወለድን አልመረጠም:: ወይም እንደ ንጉሥ ወይም እንደ ንጉሥ ልጅ ለመኖር አልመረጠም:: እርሱ የመረጠው ቀላልና ግልፅ የሆነ ህይወትን ነበር:: እርሱ የመረጠው ከአለም ጋር ያልተቆራኘ ህይወትን ነበር:: ስለዚህ እሱ እየፈለገ ያለው እርሱን የምትመስል ሙሽሪት ነው:: ከዚህም የተነሳ በየቀኑ ልቤን በእርሱ ፊት ስመረምር የወደቅሁባቸውን ሁኔታዎች እንዳስተውል ያደርገኛል:: እነዚህን ነገሮች ለእናንተ ነው የምፅፈው:: ምክንያቱም እኔ እንደማስበው አንዳንደ ነገሮችን ስለራሳችን በመረዳትና ለሌሎች በማካፈል እርስ በርስ መረዳዳት እንችላለን:: ጌታ የሰጠኝ መልዕክት እንደሚከተለው ነው::*

"የቆንጆዎች በአንድ ላይ መሰባሰብ የኔ ሙሽራ ሙሆኗን አያመለክትም::እኔ የምፈልገው ተራዋንና የተዋረደችዋን፣ በፀፀት የተሞላችዋን፣ ታማኟንና በፅድቅ ምክንያት የምትሰደደዋን ነው:: እኔ የምፈልገው እኔን የምትመስለዋን ነው:: ሙሽራዬ የምትመስለው ይህንን ነው:: ለተዋረዱትና ለተገፉት ተስፋ መስጠት እፈልጋለሁ:: እነሱ ውብቶቼ ናቸው:: እነሱ ናቸው በዚህ ምድር ላይ እኔን በጣም የሚመስሉት:: ይህንን በማለቴ እያዘንኩ ነው:: ነገር ግን ብዙ የኔ ክርስቲያኖች የሚመስሉት የባቢሎናን ቆንጆ ነው:: ወይም ደግሞ የሚመስሉት በዚህ ዘመን ያሉትን የሆሊውድ ቆንጆዎችን ነው::

"አውቃለሁ በዚህ ንግግሬ እንደተሰላቻችሁ:: ነገር ግን ይህ ሆሊውድ አይደለም:: ይህ መንግስተ ሰማይ ነው:: እናም በመንግስተ ሰማይ ያለ የትኛውም ነፍስ በዚህ ምድር ያለውን ማንንም ሰው ሊመስል አይችልም::

"ስለዚህም የኔ ሙሽሮችና ህዝቤ ለንስሐ እጠራችኋለሁ:: እኔ በአለም ልኬት ቆንጆ የሆኑ ሰዎች የኔ ሙሽሮች ሊሆኑ አይችሉም አላልኩም:: ነገር ግን በግል ህይወቷ እኔን መምሰል አለባት ነው ያልኩት:: ይኸውም የተሰቀለች፣ የተገፋች፣ የተናቀች፣ ርህራሔ በሌለው መንገድ ሌሎች ያደረሱባትን ይህንን ሁሉ ጠባሳ በልቧ ይዛ ያለችዋ ነች እኔን የምትመስለው::

ልቤ በእደነዚህ አይነቶቹ ይሳባል፡፡ ህመማቸውን በዝምታ በክብር ይዘው እያለ በወጪ ግን ልታውቋቸው አትችሉም፡፡ እነዚህ ናቸው የኔ ምርጫዎች፡፡ ከእነዚህም ጋር ታናናሾች፣ ደካሞች፣የተገፉትና የተናቁት ይገኙበታል፡፡

“አውቃለሁ ራሴን እየደጋገምኩ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ የተሻለና ጠቃሚ የሆነ ነገር አይኖርም፡፡“

“ሁሉም ማወቅ ያለበት እኔ እየፈለግሁ ያለሁት እጩ ሙሽሪት እጅግ በደንብ ተበጥራ፣ አምራና ተስተካክላ ያለችውን አይደለም፡፡ በአንፃሩ ግን በጣም በጣም የበታች የሆነችውን ነው፡፡ እኔ ለንጉሡ አልገባም የሚሉትን እንደነዚህ ዓይነቶቹን አምጡልኝ፡፡  እነሱ የኔ መሆናቸውን እርግጠኞች በመሆን ለእኔ አምጡልኝ፣ እነዚህ ናቸው ለእኔ ሊሆኑ የሚገባቸው፡፡ እነዚህ ናቸው ለእኔ የተመረጡ ሙሽሮች፡፡

“ሥራ ለመቀጠር ገና እየተጠባበቁ ያሉት ለእኔ እጅግ ጠቃሚ ናቸው፡፡ የሚከፈላቸውም መጀመሪያ ከተመረጡት እኩል ዋጋ ነው፡፡ እናም ከሁሉም አስቀድሞ ደግሞ የተናቁትና የማይፈለጉት ለእኔ ጠቃሚዎች ናቸው፡፡"

*እንግዲህ ይህ ነው ለሙሽራውና ለቤተክርስቲያን የጌታ የጊዜው መልዕክት፡፡ እኔም የክርስቶስ ሙሽራ ማን እንደሆነች የሚያመለክት ተከታታይ መልዕክት እያዘጋጀሁ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይህንን በብዙ መልኩ ይገልጥልኛል ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ይህም ለመነጠቅ የሚያበቁ ባህርያትን የሚያመላክት ነው፡፡ ምክንያቱም እውነተኛ የሆነችው ሙሽሪት እርሱን ስለምትመስል ነው፡፡ እስከዚያው እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡*

# በኒኩላር ጦርነት ውስጥ የተተዉ

**ሰፕቴምበር 2 ቀን 2014 ዓ.ም**

{Left Behind in Nuclear War}

<u>የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። ማቴዎስ 24፡37</u>

<u>ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። ማቴዎስ 24፡6</u>

## <u>*መዝሙር*</u>

ፍቅርህ በማዕበል ስለማይናወጥ፣
ተራሮች ባህሩን ሲያናውጡት፣ ልታድነኝ ትመጣለህ፡፡
ብትንትናችን ሲወጣ ፣ በጦርነት የሞት ስጋት ውስጥ ስንሆን፣
የሰዎች ልብ በማዕበል ውስጥ በሚጥላቸው ጊዜ ፣
የሚሰቀጥጥ የመለከት ድምፅ ጩኸት ሲሰማ፣
ብልጭታ በሰማይ ሲበርቅ፣
እውነተኖች መሆናችንን ሰማይ ሁሉ ሲረጋግጥ፣
አንተን ስንጠብቅ የነበርን ሁሉ ቀና ስንል፡፡
እንደ ደመና በዙሪያችን የከበቡን ቅዱሳን በሰማይ ሲታዩ፣
ንጉሡ በታላቅነቱ፣ በብዙ ክብር ሙሽራዪቱን ይወስዳል፡፡

በቃሉ እንዲህ ተብሎ ተፅፏል <u>"እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።</u> . . ." 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51

<u>የሰው ልጅ በሚመጣ ጊዜ የሚሆነው እንዲህ ነው፡፡ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች። ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ። ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና። ይህ የጌታ የራሱ ቃል ነው፡፡ማቴዎስ 24፡40</u>

**መዝሙሩ ቀጠለ …**

በአረጀና በተበጣጠሰ ገመድ በተገመደ ጦርነት

በምድር የቀሩት በጨለማው ውስጥ … በማዕበል ውስጥ

በራቸው ላይ ቆመው ያለቅሳሉ፡፡

ብርሃን በሌለበት፣ በማዕበል ውስጥ፣ ለጥያቄያቸው መልስ ሲፈልጉ፣

መልሳቸውን ፍለጋ በታላቅ ጩኸት ሲጮሁ

የጠፉት በትክክል እንዲያስቡ ይሆናሉ፡፡

ከመደንበር ይልቅ ንስሐ ገብታችሁ ነገሩን አስሱ፣

ምህረቱ በማዕበል ውስጥ ያነሳችኋል፡፡

(ከዚህ በታች ያለው በወቅቱ ሊሆን የሚችለውን ለማሳየት  በድራማ መልክ የቀረበ ነው፡፡ አንዲት እናት የአንድ ዓመት ህፃን ልጇ ስለተነጠቀ ግራ ገብቷት ትታያለች)፡፡

"በጣም ግራ ገብቶኛል፣ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም፣ እጅግ ደንግጫለሁ፡፡ አንድ ሰው እባካችሁ እርዱኝ፡፡ እባካችሁ ምን እየሆነ ነው ያለው? በሁሉም ቦታ ስዘዋወር ወላጆች ተስፋ በመቁረጥና በምሬት እያለቀሱ የልጆቻቸውን ልብስ ይዘው ነው የማየው፡፡ አ! ይህ ሊሆን የማይችል ነገር ነው፡፡ እየቃዠሁ ነው፣ ከቅዠቴ እነቃለሁ!፤ ከተኛሁበት እነቃለሁ!! ነገር ግን ህልም ላይ አይደለሁም፡፡ እውነት ነው፡፡ ምን እንደሆነ ማንም ሰው አያውቅም፡፡ መንቀጥቀጤን ማስቆም አልቻልኩም፡፡ በትልቅ ድንጋጤ ላይ ነው ያለሁት፡፡  ከትንሽ ደቂቃ በፊት ልጄ በእጄ ታቅፌያት ደህና ነበረች፡፡ የፀሐዩ ነፀብራቅ ፀጉሯን ብድግ ሲያደርግ በንፋሱ ሳቀች፡፡

"በጣም ደስተኞች ነበርን፡፡ ምንም የማታውቅ የዋህ ነበርች፡፡ አሁን ግን ልብሷ ብቻ በእጄ ላይ ቀርቶ ይገኛል፡፡ ሰንደል ጫማዎቿም በመሬት ላይ ወድቀዋል፡፡ ከአሁን ወዲህ የለችም ማለት ነው? አ! አንድ ሰው እርዱኝ . . . ምንድነው የሆነው? ምንድነው የሆነው?

" እግዚአብሔር የሚባለው ካለና መኖሩም እውነት ከሆነ ፣ የኔ ትንሿ መላዕኬ፣ ትንሿ ልጄ ምን እንደሆነች ንገረኝ፡፡ የት ነው ያለችው?

"ይህ አይሆንም . . . ተነጥቃ ሊሆን አይችልም ሊሆን አይችልም፡፡ ያ ዝም ብሎ አፈታሪና የማይታመን ወሬ ነው፡፡ ያ ሊሆን አይችልም፡፡ ብልህ ሰው ያንን ነገር ያምናል፡፡ ነገር ግን . . . እርሷ ሄደች፡፡ ደግሞም በሁሉ ሥፍራ  . . .  ልጆቻችን ሄደዋል፡፡

ከሌላ አለም የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ? ሊሆን ይችላል? . . . ሁሉም ልጆች  ተነጥቀው ሊሆን ይችላል? . . . ለምን? ለምን? ለምን እግዚአብሔር?

## የመዝሙሩ መጨረሻ

ነገሮችን ለማስተካከል አሁንም አልረፈደም፡፡
ስለዚህ  መብራታችሁን በሚገባ አዘጋጁ፣
ብርሃናችሁን ጠብቁ.
ይኸው በአጠገባችሁ ቆሟል ስለዚህ እጁን ያዙት፣
በማንኛውም ሰዓት ሊመጣ ይችላል፤
መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና፡፡

# ክፍል አንድ
# የጌታ የራሱ ቃል ለእናንተ

The Lord's Own Words for You

---

## 1.1. ስለ ንጥቀት ከጌታ ከራሱ የተላከ ደብዳቤ ቁጥር 1

እ.አ.አ. ኦክቶበር 7 ቀን 2014 ዓ.ም

{Post Rapture Letter from God #1}

"ልባችሁን በማፅናናት እየጠራኋችሁ ነው፡፡ እኔ አልተውኳችሁም ደግሞም መቼም አልጥላችሁም፡፡ ምን ያህል ከባድ ሐዘንና ባዶነት እየተሰማችሁ ደግሞም አንዳንዴ የተከዳችሁ የሚመስላችሁ ወቅት እንዳለ አውቃለሁ፡፡ በአሁን ሰዓት ሁሉ ነገራችሁ ለምን? የት? ለምንድነው እስካሁን እዚህ ያለሁት? ለምንድነው የተተውኩት? አሁንስ ምንድነው የማደርገው? በሚሉ ጥያቄዎች ነው የተሞላው፡፡"

"ብዙዎች በዚህ ወቅት በኢንዱስትሪው፣ በንግዱና ገንዘብን በሚያስገኙ መስኮች ሁሉ የተፈጠሩትን ብዙ የከፍት ሥራዎች አዲስና የሚያጓጉ አጋጣሚና ሙያዊ እድል እንደሆነ ቆጥረውታል፡፡ እናንተም ግን ወደ አለም በጥልቅ ዘልቃችሁ በመግባት በሥራ ለመጠመድ ከሚፈታተናችሁ የልብ ምኞት ራሳችሁን መቆጣጠር አለባችሁ፡፡"

"በህመማችሁና ግራ በተጋባችሁ ጊዜ እንኳን ከእነዚህ ነገሮች በፍፁም መራቅ አለባችሁ፡፡ ካልተረጋጋ ከዚህ አለም እርቃችሁ በአሥር እጥፍ እኔን በሙሉ ልባችሁ መፈለግ አለባችሁ፡፡ በእውነተኛ ንስሐና የልብ ለውጥ ጠንክራችሁ ወደ እኔ ጩኹ እኔም እረዳችኋለሁ፡፡ እጆቼንም ዘርግቼ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት እቀበላችኋለሁ፣ ከፍርሃታችሁም አረጋጋችኋለሁ፡፡"

"የጠፋችሁ አይደላችሁም፡፡ በሚመጡት ቀናቶች ውስጥ አሁንም ምን ያህል እንደምወዳችሁ በይበልጥ እያያችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ እናት ልጇን ልትተው ትችላለች፡፡ እኔ ግን አልጥላችሁም፡፡ እኔ ላድናችሁ ሁልጊዜ እዚሁ ነኝ፡፡"

"አሁንም ለእኔ በጣም ተወዳጅና ከፍተኛ ዋጋ ያላችሁ ልጆቼ ናችሁ፡፡"

"አሁንም እናንተ ትልቅ ኃብቶቼ ናችሁ፡፡ ስለዚህ አሁንም እንኳን ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡"

## 1.2. ስለ ንጥቀት ከጌታ ከራሱ የተላከ ደብዳቤ ቁጥር 2

እ.አ.አ. ኦክቶበር 7 ቀን 2014 ዓ. ም.

{Post Rapture Letter from God #2}

"ግን ለምን ? የሚል ጥያቄ በአይምሯችሁ እየተመላለሰ አስቸግሯችሁ ይሆናል፡፡"

"ኦ! የኔ ጌታ ለምን?ለምን?ለምን እዚህ ተተውኩ ? የሚል፡፡"

"ልጆቼ ከንጥቀቱ ተለይታችሁ እዚህ እንድትቀሩ በፍፁም የታቀደ አይደለም፡፡ ይህ ለልጆቼ ሁሉ፣ በእውነትም ለአካሌ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሙሽራዬ የተዘጋጀ የኔ ምህረት የተሞላበት ስጦታ ነበር፡፡ እናንተም በንጥቀቱ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ከዚህ ታይቶ ከማይታወቅ ወደፊትም ሊከሰት ከማይችል አሰቃቂና ስቃይ የበዛበት ህይወት ታመልጡ ነበር፡፡"

"አጀማመራችሁ ጥሩ ነበር ነገር ግን ጊዜ በሄደ ቁጥር ከአለም ጋር ተቆራኛችሁ፡፡ በስም ብቻ ክርስቲያን ተብላችሁ የአንድ ቤተክርስቲያን አባል በመሆን ጊዜ ማሳለፊያ ብታደርጉትም ብዙ ጥፋትን ያስከተለ ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን እናንተ በየጊዜው እየራቃችሁ ሄዳችሁ፡፡"

"ከእኔም ጋር አብረን የምንሆንበት ጊዜ እያነሰ እያነሰ መጣ፡፡ በእምነታችሁ ጉዳይም ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአለም ጋር እየተስማማችሁ እንደመጣችሁ እናንተም ታውቁታላችሁ፡፡ ስለዚህም ስለ እኔ መናገሩን አቆማችሁ፡፡"

"ይህ፣ አዲስ የጀመራችሁት ግንኙነትና ነፃ የሆነ አመለካከታችሁ ተደምሮ በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ነፍሶች ዓይታችሁ በእነርሱ ላይ እንድትፈርዱ አስቻላችሁ፡፡ እነርሱንና ለእነርሱ ውድ አድርገው ያዙትን የበታች አድርጋችሁ ተመለከታችሁ፡፡ በእኔ መምጣት በመደሰታቸው እንኳን ደስታቸው ዋጋ እንደሌለው በመቁጠር በግልፅ በመተቸት ነቀፋችኋቸው፡፡"

"እኔ ስደርስ ሁላችሁም ማድረግ የምትችሉት በፍርሃትና በሃፍረት መቆምና ለማመን ያቃታችሁ ነገር በፊታችሁ ሲፈፀም ማየት ብቻ ነበር፡፡"

"ምክንያቱም እናንተ አላመናችሁም፣ ስላልጠበቃችሁ አልፀለያችሁም፡፡ ስለዚህም ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እኔም መጣሁ፡፡ እናንተ ግን አልተዘጋጃችሁም ነበር፡፡"

"ስለዚህም ልወስዳችሁ አልቻልኩም፡፡"

## 1.3. ስለንጥቀት ከጌታ ከራሱ የተላከ ደብዳቤ ቁጥር 3

እ.አ.አ. ኦክቶበር 7 ቀን 2014 ዓ.ም.

{Post Rapture Letter from God #3}

"አሁን ምን እናድርግ? ብላችሁ ጠይቁኝ፡፡"

"ከምንግዜውም በበለጠ ወደ እኔ ቅረቡ፡፡ ሁልጊዜ እኔን በልባችሁና በአይምሯችሁ ለማሰብ እንድትችሉ፣ ስሜን ሁልጊዜ በአንደበታችሁ ላይ እንዲሆን ፀጋ እንዲሰጣችሁ ፀልዩ፡፡"

"የልብሴን ጫፍ አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ ከአሁን ወዲያ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ከአጠገባችሁ እንድሄድ አትፍቀዱ፡፡ በየትኛውም ቦታ ሁልጊዜ እኔን የማሰብ ልማድ አዳብሩ፡፡ ሁልጊዜ በሐሳበ ህሊናችሁ እኔን ተመልከቱ፡፡ ስለዚህም ደግሞ ፀልዩና እኔ እንዲሆንላችሁ አደርጋለሁ፡፡ እንደ ተለመደው እኔ ቀደሜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ነገር ግን መኖሬ ሊሰማችሁ፣ አብልጦ ታማኝ እንደሆነ ጓደኛ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ግንኙነት መፍጠርና ከእኔ ጋር መነጋገር አለባችሁ፡፡

በእያንዳንዱ ሐሳባችሁና ስሜቶቻችሁ ላይ በብልሃት የምፈፅመው ፍላጎት አለኝ፡፡ ይህም ራሳችሁን ዝቅ፣ ትሁትና ትንሽ ለማድረግ ጥረት እስካደረጋችሁ ድረስ ነው፡፡"

"እኔ ምንጊዜም ቢሆን ከሁሉም በላይ ታማኝና ሚስጥረኛ ጓደኛ ነኝ፡፡ ደግሞም ራሱን እንደ ህፃን ታናሽ ከሚያደርግ የበለጠ ወደ እርሱ እንድቀርብ የሚያደርገኝ ነፍስ የለም፡፡ ከራሳቸው ቆዳ በበለጠ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ቅርብ እሆናለሁ፡፡ እናም ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡

" እስካሁን ድረስ ገና ግራ እንደተጋባችሁና በዙሪያችሁም ያለው አለም ሁሉ መጥፎ ትርምስ ውስጥ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ እናንተ ልትገልፁት የማትችሉት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሰላምና ፀጥታ በውስጣችሁ እየተሰማችሁ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ይህንንም ስጦታ በመስጠት እቀጥላለሁ፡፡ በዚህም በትክክል እንድታስቡና ግልፅ በሆነና በሚያስደንቅ ሁኔታ ማገናዘብ እንድትችሉ ያደርጋችኋል፡፡ "

"ስለሚያስፈልጋችሁ ነገር አትጨነቁ፡፡ እንዳያችሁት የሚያስፈልገውን ሁሉ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ ከአሁን ወዲያም የሚያስፈልጋችሁን በማይመስል ሁኔታ ከየት መጣ ሳትሉ ሰዎች ይሰጧችኋል፡፡ በዚህም እውነተኛውን የእምነት ህይወት ቶሎ በመለማመድ ከተለመደው ውጪ በሆነ ሁኔታ እንኳን ሆናችሁ እንዴት ውብ እንደሆነ በተግባር ታዩታላችሁ፡፡

«ምንም ነገር ከእኔ ቁጥጥር ውጪ አይደለም፡፡ ያለ እኔ ፈቃድ ምንም የሚሆን ነገር የለም፡፡ በሚያስፈልጋችሁ ጊዜ የሚያስፈልጋችሁን ነገር አዘጋጃለሁ፡፡ በምንም ነገር መስጋት የለባችሁም፡፡ ብቻ እናንተ ዓይኖቻችሁንና ልባችሁን በእኔ ላይ አድርጉ፡፡ በጣም የተወደዳችሁ ውድ ልጆቼ ናችሁ፡፡ ምንም መጥፎ ነገር እንዲነካችሁ አልፈቅድም፡፡ መላዕክቶቼን ቀንና ሌሊት እንዲጠብቋችሁ አዝዣቸዋለሁ፡፡ የምታገኙት አቅራቦት ብቻ ሳይሆን ፤ የእኔን ፍቅርና እንክብካቤ እናም ታማኝነቴን እንደሆነ ትገነዘባላችሁ፡፡ ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የሚሆን የተትረፈረፈ ነገር ይሰጣችኋል፡፡

«እንደናንተ ንስሐ የገቡትን ሌሎችን ታገኛላችሁ፡፡ በራሳችው ምክንያት ስብራት የደረሰባቸው፣ ነገር ግን ደግሞ ሙሉ ታህድሶ በማግኘታቸው ፍፁም ትሁት የሆኑትን ታገኛላችሁ፡፡ እነዚህም ልባቸው ሙሉ ለሙሉ ለእኔና ለእግዚአብሔር መንግስት የሰጡ ናቸው፡፡

«ህዝቦቼን እናት ህፃናት ልጆቿን እንደምትሰበስብ ይህንንም የፈተና ወቅት በአሸናፊነት እንዲወጡ አደርጋለሁ፡፡ ለሁለት ጊዜ እንዲጠሩ ስለተደረጉ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ እንደ ከዋክብት ያንፀባርቃሉ፡፡ የመከራውን ዘመን በፅናትና በክብር አሸንፈው ስለወጡ ከእኔ ጋር ነግሰው ይገዛሉ፡፡

## 1.4. አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?

{What do I do now?}

*በዚህ ወቅት ምናልባት እራሳችሁን እየጠየቃችሁ ያላችሁት " አሁን ምን ማድረግ አለብኝ " በማለት ነው፡፡*

*በዚህ ላይ የእኛ ምርጥ ሐሳብ፡ ኢየሱስን ልክ ሌሎች ጓደኞቻችሁን እንደምትጠይቋቸው እንድትጠይቁት ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ ከጓደኛ በላይና በጣም የቅርብ ጓደኛ የሚሆን ነው፡፡ እርሱ ምንም ጉዳያችሁንና ሁሉን ነገራችሁን ሊታጫውቱት የምትችሉት ጓደኛ ነው፡፡ እርሱ በምንም ነገር ላይ ፊቱን አያዞርባችሁም፡፡ ስለዚህም ለሁሉ ነገር አጠገባችሁ ይገኛል፡፡ አሁን እንኳን በዚች ሰዓት አጠገባችሁ ነው፡፡ እናንተ ብቻ ልባችሁን ለእርሱ በመክፈት የነበራችሁን ተስፋና ህልም እንዲሁም ፍርሃታችሁንና ተስፋ መቁረጣችሁን በግልፅ ንገሩት፡፡ ሌላው መረሳት የሌለበት ነገር ራሳችሁን ሳትቆጥቡ ሁለንተናችሁን ለእርሱ አስረክቡ፡፡ የፈጠራችሁ እርሱ ስለሆነ ከዛ በላይ ለእናንተ መልካም የሆነውን፣ ሁለንተናዊ ፍፃሜያችሁንና የማያልቀው ደስታችሁ ምን እንደሆነ ያውቃል፡፡*

*"እንዴት? እኔ በእውነት ይህንን ልፈፅመው እችላለሁ?" ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ፡፡*

*ዋናው ቁም ነገር እርሱን ለመጠየቅ የጣፈጠና የሚያምር ቋንቋ ወይም ትልልቅ ቃላቶችን መጠቀም አያስፈልግም፡፡ የሚያስፈልገው ነገር ከልብ የመነጨ እውነተኛ ጥያቄን ብቻ ነው፡፡*

*ኢየሱስ አሁን ባላችሁበት ደረጃ እንዲሁ ይወዳችኋል፡፡ ስለዚህ እራሳችሁን በመሆን ተዝናንታችሁ ምንም ተጨማሪ ነገር ሳትጨምሩ እንዲሁ ቅረቡት፡፡ ስለ ኃጢያታችሁ እንዳዘናችሁና ከአሁን ወዲያ ግን ህይወታችሁን ሁሉ ለእርሱ እንደምተሰጡ ንገሩት፡፡*

*የህይወታችሁ አዳኝና ጌታ አድርጋችሁ በእውነት ለመቀበል እንደምትፈልጉ ንገሩት፡፡ በዚህም እራሳችሁን ሳትቆጥቡ ሁለንተናችሁን ለፍቅሩና ለጥበቃው አሁንና ለዘላለም አሳልፋችሁ እንደሰጣችሁት ንገሩት፡፡*

*አሁን ከዚህ በኋላ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆናችኋል፡፡ አሮጌው ህይወት አሁን አልፏል፡፡ አሁን በሚያስደንቅ ሁኔታ በዚሁ ደቂቃ ዳግም ተወልዳችኋል፡፡ አዲስ እንደ ተወለደ ህፃን ልጅ ንፁህ፣ ነጥብ እንኳን ቆሻሻ እንደሌለበት፣እንዲሁም መጨማደድ እንደሌለበት ንፁህ ህፃን ልጅ ሆናችኋል፡፡ አዲስ ነፍስ አዲስ ህይወት ተሰጥቷችኋል፡፡ ቆንጆና የማያልቅ፣ በነፃነትና በደስታ፣ በወጣትነት ለዘላለም በህይወት የምትኖሩበት ሰማያዊ መኖሪያ እንዳላችሁ ቃል ተገብቶላችኋል፡፡*

# ክፍል ሦስት
# ከንጥቀት ወደኋላ ለቀሩት የተሰጠ መልዕክት

{Messages for the Left Behind}

---

## 3.1. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ሊሆን ስላሉ ክስተቶች የተናገረው፦ ክፍል 1
## የክንውኖች ቅደም ተከተል

እ.አ.አ ማርች 2 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Speaks On: What Is to Come After the Rapture,
Order of Events - Part 1}

መጨረሻው ከመድረሱ በፊት አጥፊው አይመጣም፡፡ ያየሸው የሚሆነው ከተመወሰዳችሁ በኋላ ነው (ቤተ ክርስቲያን ከመነጠቋ በኋላ)፡፡ ይህ ለሚቀሩት ተዘግቦ እንዲቀርና ከእኔ ውጪ የሚሆን ነገር እንደሌለ በግልፅ እንዲያውቁትና ተስፋ እንዳይቆርጡ ነው፡፡ ያሉበት ሁኔታ ተስፋ የሌለው እንዳልሆነ በቃሌ መታመን ይችላሉ፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ በእኔና በምህረቴ እንዲተማመን እፈልጋለሁ፡፡

ለዚህ ነው ይህ ክስተት እንደሚፈጠር ቢያንስ ከፊሉን በቅድሚያ ቢነገራቸው የወደፊቱን አቅጣጫ በመረዳት ደህንነት ሊሰማቸው ይችላል፡፡ ነገሮችን ቀድሜ በግልፅ የምነግራቸው ይህንን በመረዳት ሁሉም በእኔ ቁጥጥር ስር እንደሆነ እንዲያውቁት ነው፡፡ ይህንን ከዚህ ቀደም ብዬዋለሁ፣ ቢሆንም ይህ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ አሁንም እደግመዋለሁ፣ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ተስፋ ለመቁረጥ ሁኔታው እጅግ ስለሚያስገድዱ በዚህም የተስፋ መቁረጥ ወቅት ዲያቢሎስ ብዙዎችን ነጥቆ ይወስዳል፡፡

"በምድር የምትቀሩ ሁሉ ይህንን ልታውቁ ይገባል፣ ይህ ሁሉ አሳዛኝ መከራ አብቅቶ ሁሉም እንደገና ንፁህ ሆኖ የሚታደስበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በዚያን ጊዜ ክፉ ምንም ጉዳት ሊያመጣ አይችልም፡፡ በዚያ ወቅት ማንኛውም ክፋት የሚመነጨው ከሰው ልብ እንጂ ከአጋንንት አይሆንም፡፡ ምድርንና የሰውን ልብ ለማንፃት በእሳት መጠመቅ ይሆናል፡፡ ይህንንም ክስተት በህይወት ተገኝተው ተካፋይ የሚሆኑት በፍፁም ሊረሱት የማይችሉት ነገር ይሆናል፡፡ ውሎ ሲያድር ግን የመሪባን ውኃ ክስተት ሰዎች እንደረሱት ሁሉ ይህንንም ወደፊት ስለሚረሱት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ክፉን ከምድር በማስወገድ ምድርን ለማንፃት እገደዳለሁ፡፡"

"አጥፊው ፕላኔት ኒብሩ እናንተ ሙሽሮቼ ከምድር እስከምትወሰዱ ድረስ አይመጣም፡፡ እናንተ ልክ እንደተወሰዳችሁ በምድር ላይ ትርምስምስ ይሆናል፡፡ እናም አንዱ አገር ሌላውን ድል ያደርጋል፡፡ በዚህም ሰበብ በሸርያ መመሪያ መሰረት ማርሻል ህግ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ እኔን የማይክድ በሰይፍ ይገደላል፡፡ የአውሬውን ምልክት የሚቀበል ደግሞ ይጠፋል፡፡ ማወቅ ያለባችሁ የኔ ምህረት ገደብ የለውም በነዚህም ጊዚያት እንኳን ስሜን ጥሩ፡፡

"ህዝቤ አድንሃለሁ ተነስና ስሜን ጥራ፡፡ ህዝቤ እኔን እመነኝ፣ በጭንቀላትህ እንኳን እመነኝ፡፡ በምድር ላይ የምትሰቃየው ስቃይ ከምትቀበለው ምልክት ጋር ሲወዳደር ምንም አይደለም፡፡

ስለ አውሬው የጠየቅሽኝን ጥያቄ ለመመለስ እነርሱ የሚራቡት በምድር ውስጥ ሲሆን የክፋት ቁጭታቸውን ለመወጣትና ጥፋትን ለማምጣት በትክክለኛው ሰዓት ካሉበት ይወጣሉ፡፡"

"በዚያን ጊዜ በህይወት ያለው በሞተው ይቀናል፡፡ ይህ የሚሆነው ለሰው ዘር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ፍጥረታት ነው፡፡ እኔ እያንዳንዱን ፍጥረት በፍቅሬ አልወድምን? ደግሞስ በእያንዳንዱ ቀን ለሚዋኙበት ውኃ፣ ለሚበሉት ምግብና ለሙቀት ፀሐይን አልሰጠኋቸውምን? አቅርቦቴ የተትረፈረፈ ቢሆንም ነገሩ እየባሰ ሲመጣ ብዙዎች ከእኔጋ በገነት ተደስተው እንደሚኖሩ  ሁሉ እነርሱም ወደ እኔ መጥተው ይኖራሉ፡፡ ክሌር፣ እኔ ሁሉንም ፍጥረታት እወዳለሁ፡፡  ደግሞም እመኚኝ ስቃያቸውን እንዴት ማቅለል እንደምችል አውቃለሁ፡፡ ፍጥረታት ሁሉ በዚህ ኃጢያተኛ ትውልድ ምክንያት በመሰቃየት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ሁሉ ግን የተከሰተው ክፉ ከመጀመሪያውም ጀምሮ ባደረገው ከፍተኛ ጥምረት ምክንያት ነው፡፡"

"ፕላኔቷ/ኒብሩ/ ወደምድር እየቀረበች ስትሄድ ነገሮች እየተባባሱ ይሄዳሉ፡፡ ሰይጣንም የራሱን አጀንዳ በሰው ዘር ላይ በቶሎ ለመፈፀም በመሯሯጥ ላይ ይገኛል፡፡ የአውሬውንም ምልክት በሰዎች ላይ በግድ ቶሎ ለመጫን እየተሞከረ ሲሆን ይህ ደግሞ የቤተሰብን መከራ የሚያበዛ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ ሁኔታውንም ተቋቁመው እንዲያልፉ ጥንካሬን እሰጣቸዋለሁ፡፡ በመጨረሻውም የተዘጋጀላቸውን የአሸናፊነት አክሊል ይጭናሉ፡፡"

"ሰዎች ከአሁን ወዲያ ምንም ተስፋ የለም ብለው በቆረጡበት በዛን ጊዜ እኔ ያን ጊዜ እመጣለሁ፡፡ ያን ጊዜ ነው መጥቼ ሁሉን የማድሰው፡፡ ልክ በዚያን ጊዜ፣ ጨለማው በበረታ ጊዜ፣ ህዝቄኤል በህልሙ እንዳየው /የክሌር ባለቤት/ እመጣለሁ፡፡ አንዳንድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በስራ ላይ እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ፡፡ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች እንዳይበላሹ ያደረኩት ከህዝቤ ጋር ለመገናኘት ስለሚጠቅሙ ነው፡፡ ህዝቤን መልዕክት እንዲደርሰው ለማድረግ ኢንተርኔትን፣ ሬድዮንና ሌሎች የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን መጠቀሜን እቀጥላለሁ፡፡ ለዚህ ነው እነዚህ መገናኛ ብዙኃንን ሊያጠፉ የሚችለውን ኢ-ቦንብ እንዲያፈነዱ  የማልፈቅደው፡፡ የቴክኖሎጂው መጠበቅ ጉዳይ አፖካልፕስ 10.5 በሚለው ፊልም ላይ እንደተጠቀሰው ዓይነት ይሆናል፡፡"

"የቤተክርስቲያን መነጠቅ የመጨረሻው መጀመሪያ ይሆናል፡፡ ይህንን የሚጠብቁት ስለ መነጠቅ ጥያቄ የሚፈጥርባቸው ብቻ ሳይሆኑ ክፉ ራሱ እየጠበቀው ነው፡፡ በዚህም ክስተት ብዙ ሰዎች ስለሚጠፉ ይህንን ምክንያት በማድረግ ክፉ መዋቅሩን ለመዘርጋት ለራሱ ጥቅም ያውለዋል፡፡ ቢሆንም ይህንን ለማድረግ ጊዜ ይወስድባቸዋል፡፡ በዚህም ለትንሽ ጊዜ ሰላም ይሆናል፡፡"

"አሜሪካ ሙሉ ለሙሉ አትወድምም፡፡ የመሬት መሸራተት፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የግዙፍ መሬቶች ቦታ መልቀቅ፣ እንዲሁም የሃኑራት መከፈል የሚሆነው በመጨረሻው ነው፡፡ በዚህ መሃከል በአሜሪካ ምድር ላይ ጦርነት ይከሄዳል፡፡ ስለ ማያሚ/Miami/ ነግሬሻለሁ፡፡ የሌላውን ድምፅ አትስሚ እኔ የነገርኩሽ ትክክል ነው፡፡"

"ብታምኝም ባታምኝም ራሽያ አሁን እንኳን  አገራችሁን ለመምታት እቅድ እያወጣች ነው፡፡ በዚህ ወቅት እንኳን ዛሬ እናድርገው ወይስ ነገ እያሉ በትኩረት እያወጡ እያወረዱ ይገኛሉ፡፡ በአሜሪካ ውስጥ ለዚህ የሚያስፈልገውን ነገር በየቦታው አስቀምጠዋል፡፡ የጦር መሳሪያዎች በየጫካው ተደብቆ ይገኛል፡፡ ከባድና ሌሎች መሳሪያዎች እንዲወጡ የመሬት ውስጥ መግቢያዎች በአሜሪካ ምድር ይከፈታሉ፡፡ የሚካሄደው ጦርነት በአብዛኛው እንደተለመደው ዓይነት ነው፡፡

**ክሌር**፡ - ኒውዮርክ ከተማ ይመታል ወይስ በሱናሚ ነው የሚጥለቀለቀው?

" አዎን ይመታል"

**ከሌር**፡- ነገር ግን ስለ ሱናሚና ስለ መሬት መንቀጥቀጥ የሚነገረውስ?

"ከተማው በቦንብ ከተመታ በኋላ የተረፈው ደግሞ በውኃ ውስጥ ይሰምጣል፡፡ በእውነቱ ከሆነ ሁለቱም በአንድ ጊዜ የሚከሰት ነገር ነው፡፡ ሁለቱም በአንዴ"

**ከሌር**፡- አ! ኢየሱስ ምንም የማያውቁትም ሁሉ?

"አዎ የኔ ውድ ምንም የማያውቁት ሁሉ፡፡ ከሌር ይህንን አስታውሺ አንቺ ከምታስቢው በላይ እወዳቸዋለሁ፡፡ እናም ቶሎ በምህረቴ እወስዳቸዋለሁ፡፡ በምድር የሚቀሩት ናቸው ምድር እንደ ገሃነም በሆነችበት ሁኔታ ውስጥ የሚቆዩት፡፡"

"እንዳየሽው ኮርያኖችና ራሽያኖች በሁሉ ቦታ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም ምልምል አሜሪካን ሙስሊሞች ከዳተኞች ይሆናሉ፡፡ ሰዎች በሰው ልጅ ላይ እምነት ያጣሉ፡፡ ምክንያቱም የራሳቸው ዜጎች እንኳን ስለሚከዷቸው ነው፡፡"

"እነዚህ የተመለመሉት ሰዎች ሴቶችን፣ ወንዶችንና ህፃናትን በአላህ ሥም በመግደላቸው ጥሩ ሥራ እንደሰሩ እንዲያምኑ ተደርገዋል፡፡ እነዚህም በራስ ወዳድ ሰዎች ምክንያት ያሳለፉትን ከባድ ህይወትና የፈጠረባቸውን ንዴት ማብረጃ አድርገው በመቁጠር የሰው ልጆችን መበቀያ መንገድ አድርገው ይወስዱታል፡፡ በበታችነት መታየታቸው ስላደነዘዛቸው ይህንን የመግደል ጥማታቸውን በኃይል ካልሆነ በቀር ማንም ሊያስቆማቸው የሚችል የለም፡፡

"ይህም ቢሆን ለበአል ያልሰገዱና በህይወት የሚቀሩ እዚህም እዛም አሉኝ፡፡ እነዚህንም እኔ እጠብቃቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን መሰቃየታቸው አይቀሬ ነው፡፡ በእሳት ውስጥ በማለፍ ይፈተናሉ፡፡ እናም ስመጣ ዋጋ ያላቸው ሆነው አገኛቸዋለሁ፡፡ እነዚህ ቅሬታዎች ከሰው ልጆች በጥቂት መቶኛ(ፐርሰንት) የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የአንቺ ቤተሰቦችም አሉበት፡፡ አንቺ ያስተማርሻቸው ትምህርት ስለሚያሳድጋቸው ለዚህ ጊዜ ዝግጁ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡"

"ብዙ መሰበርና ብዙ ንስሐ መግባት ይሆናል፡፡ ትተሻላቸው የምትሄጅው የሚነበበውና የሚደመጠው ሁሉ ለእነርሱ እንደ ወርቅ ማዕድን መመሪያ ይሆናቸዋል፡፡ ነገር ግን መንፈሴም አብሯቸው ይሆናል፡፡ እናም ብዙ የሚያደርጉት ነገር ከአንቺ የተማሩትን ይሆናል፡፡ ስለሚያድጉም መራራና ፍርድ ሰጪ ከመሆን ይፈወሳሉ፡፡ ማመዛዘን ገና ሲጀምሩ የሁለታችሁንም እውነተኝነት ይረዳሉ፡፡

ብዙ ያወቅሻቸውና እኔ ለአንቺ የተናገርኳቸው ነገሮች ነገር ግን የራስሽ ሐሳብ የመሰለሹ አብዛኞዎቹ የአንቺ ሳይሆኑ የኔ ናቸው፡፡ እነዚህም ሐሳቦች ተመዝነውና ሚዛናቸውን ጠብቀው ከእውነት ጋር ይቆጠራሉ፡፡ እውነት የአንቺ መለኪያ በመሆኑ ይህንን አጥብቀሽ ከያዝሽ አትስችም/አትቃጠይም፡፡

**ከሌር**፡- ጌታ የቢጫው ድንጋይስ ጉዳይ ?/ Yellow stone/ አሜሪካን ለማጥፋት ችሎታ አለው፡፡

"ቢጫው ድንጋይ የሚሰራበት ንድፍ አለው፡፡ መፈንዳት ይፈነዳል፣ ፍንዳታው ግን እንደታሰበው በትልቅ መጠን አይሆንም፡፡ ይህም የኔ ሥራና የኔ ምህረት ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ከውስጡ የሚወጣው የቀለጠው ድንጋይ/magma/ ወደ

ውጪ የሚወጣበት ብዙ ቀዳዳዎች ስላሉት በእነዛ መውጫዎች ከመሬት ውስጥ እየወጣ ብዙ ማይሎች ይጓዛል (ልክ በውቅያኖስ ላይ እንዳየሽው)።"

"እኔ አሁንም ቢሆን ለአሜሪካ እቅድ አለኝ፡፡ እሰብራትና ትሁት አደርጋታለሁ፡፡ እናም እደገና አድሳታለሁ፡፡ አቆስላታለሁ ደግሞም እጠግናታለሁ፡፡ አዎ ይህ ምድር እጅግ የተበላሸ ነው፡፡ ብዙዎችን  በአሰቃቂ ወንጀል ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል፡፡ ቢሆንም ግን መልካም ቅሬታዎች ስላሉ ይህንን መልካምነት አበዛዋለሁ፡፡ በኃይል እሰብራትና አስተሳሰቧን እንደገና አስተካክለዋለሁ፡፡"

"ለነፃነት የሚዋጉ ሚሊሊሺያ ቡድኖች ይኖራሉ፡፡ እነሱ የጠላትን አካባቢ ወረው ድል ሲያደርጉ የኔን ህዝብ ነው የሚመስሉት፡፡ እኔም ለቆሙለት ዓላማ ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ አብሬያቸው እቆማለሁ፣ እዋጋላቸዋለሁ ደግሞም እጠብቃቸዋለሁ፡፡ እነሱ ለዚች አገር የጀርባ አጥንት ይሆናሉ፡፡ አገሪቷ በታደሰች ጊዜም ከእነዚህ ብዙዎቹ ጀግኖችና ቅዱሳን ይሆናሉ፡፡"

**ከሌር**፡- ጌታ ይህንን ሁሉ  የምትመለከተው ልክ "ሚሽን" በሚለው ፊልም ላይ እንዳለው ይመስለኛል፡፡ ይህም እጅን ለጠላት ከመስጠት ይልቅ መሞት ይሻላል የሚለውን ሐሳብ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

"እንደሱ እንኳን አይደለም፡፡ ለቆሙለት ዓላማ እኔ ኃይል እሰጣቸዋለሁ፣ ከእነርሱም ጋር እሆናለሁ፡፡ ዙሪያውን ሁሉ ቀላል ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ በውስጣቸው እጅግ ስጦታ ያላቸው ተዋጊዎች አሉኝ፡፡ በትክክለኛው ሰዓትም ሥራቸውን ይጀምራሉ፡፡ እነርሱም ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ጥበብ ይሰጣቸዋል፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሚተማመኑት እኔን እንጂ መሳሪያቸውን ስላልሆነ ነው፡፡ "

"በዚያን ጊዜም ከተሞች ለደህንነት አያስተማምኑም፡፡ ከከተሞች ይልቅ በረሃው ደህና ይሆናል፡፡ ይህም ቢሆን ግን በየጫካውና በየሸለቆው ሰውን የሚያድኑ አውሬዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ትልቅ ጥበብ የሚያስፈልገው፡፡ ብዙዎች የኔን ሥም በመጠቀም ከእነዚህ አውሬዎች ያመልጣሉ፡፡ እኔም ግዙፍና አድነው ለማጥፋት ከተፈጠሩት ፍጥረታት እጠብቃቸዋለሁ፡፡"

**ከሌር**፡- እኔ እዚህጋ አስደንጋጭ አውሬ ስለገጠማቸው ሁለት ወጣቶች እውነተኛ ታሪክ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ከእነዚህም ወጣቶች አነዱ ጌታን ገና የተቀበለው እንደ ትላንት ነው፡፡ ወቅቱ ፀደይ ወራት በመሆኑ እርሱና ወንድሙ ተራራ ለመውጣት ወደ ጫካው እየሄዱ እያሉ አንዲት ቡችላዋን የምትጠብቅ አውሬ (እነሱ እንደመሰላቸው) ጩኸት ይሰማሉ፡፡ እናም ይህቺ አውሬ 40 ጫማ ርቀት ላይ ብቻ በመቆም አካባቢውን ሁሉ ተቆጣጥረዋለች፡፡ በዚያን ጊዜ እነርሱ ሊያደርጉ የሚችሉት አንድ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስን ሥም መጥራት ብቻ ነበር!!!፡፡ ስለዚህም ሁለቱም በአንድ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም አቁሚ በማለት ተናገሩ፡፡ በዚያኑ ደቂቃ ጩኸቷን በማቆም በማጉረምረመረና አፏራውን በመበተን ቀስ ብላ በመጣችበት ተመልሳ ሄደች፡፡

"ስለዚህም እነዚህን ግዙፍ የሆኑ ፍጥረታትን በኢየሱስ ሥም አስቁሟቸው፡፡ ምናልባትም ዕርዳታ ለመጠየቅ ያላችሁ ይኸው ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡"

## 3.2. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ሊሆን ያሉ ክስተቶች የተናገረው፡- ክፍል 2 የቢጫው ድንጋይ ክስተት፣ ይቅርታዬና እቅዴ

እ.አ.አ. ማርች 4 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Speaks On: What Is to Come After the Rapture -2

Yellow Stone, My Mercy and Plans}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ "ስለ ቢጫው ድንጋይ/Yellowstone/ ጉዳይ መናገር አሁን ትክክለኛው ጊዜ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የዚህ ክስተት ጉዳይ ከባድ ይሆናል ብለው እየጠበቁ ነው፡፡ ሁኔታውም ይህንን ስለሚናገር ስለዚህ ነገር ማውራቱ ተገቢ ነው፡፡ ሰዎች ግን ያልተገነዘቡት ነገር ለአሜሪካ ያለኝን ፍቅርና የማሳያትን ምህረት ነው፡፡ አዎን ከሁሉም አገሮች የምወዳት አገር ነች፡፡ እናም ትሁት ከሆነችና ፍፁም ከታደሰች በኋላ ለእርሷ ትልቅ እቅድ አለኝ፡፡

"እርሷ ሙሽራዬን ስለምትመስል ከታደሰች በኋላ እጠቀምባታለሁ፡፡ ፡፡ ደግሞም ህዝቤን እስራኤልን ወደ ባቢሎን በግዞት እንዲሄዱ ባደርግም እስከመጨረሻው እንዳልጣልኳቸው ሁሉ ለአሜሪካም  የወደፊት የክብር ተስፋ ሳይኖራት ፍፁም ባዶ ላደርጋት እቅድ የለኝም፡፡ በእኔ ለሌላ ጥቅም ትውላለች፡፡ ሰዎች ሁሉ አንድ ያልገባቸው ነገር ቢኖር የአሜሪካ አጀማመር እንዴት እንደነበረ ነው፡፡ አሜሪካን የመሰረቷት ብዙ አባቶች ማሶኖች /Masons/ ሲሆኑ እነዚህም መንፈሳዊ ህይወታቸው የተበከለ ነው፡፡ ጠቅላላውን የዋሽንግተን እስቴት (የኮሎምቢያ ዲስትሪክት) የተመሰረተው በአረማዊ መመሪያ መሰረት ነው፡፡ ስለዚህም በዚያን ጊዜ የተመሰረተችበት መመሪያ ፍሬ እያፈራ ነው፡፡ የዘራችውን ነው እያጨደች ያለችው፡፡ ስለዚህም ይህንን የተበላሸና የተበከለ ነገሯን በማጥፋት የእውነተኛ አምልኮን ቅርስ በመገንባት ለዓለም የመልካም ነገር ኃይል እንድትሆን ጥቅም ላይ እንድትውል ትደረጋለች፡፡"

"ክሌር እኔ ለመግዛት ወደ ምድር ስመጣ በምድር ላይ እኩልነትንና ፍትህን አደርጋለሁ፡፡ መንግስት ሁለተኛ በዘር፣ በቀለምና በእምነትን የተነሳ የሰው ዘርን እንዲጨቁንና ዝቅ እንዲያደርግ በፍፁም አልፈቅድም፡፡ ምንም እንኳን ምድር እኔን በማወቅ ብትሞላና ክብሯ ቢሆንም የሰው ልጅ ከራስ ወዳድነትና ከስስት የተነሳ  የሌሎችን ሰዎች ነፃነት ለመንጠቅ ይነሳሳል፡፡ ይህ በፍፁም የማልፈቅደውና ሁለተኛ ሊመለስ የማይቻል ጉዳይ ነው፡፡ ስስት መልካም የሆነውን ነገር ወደ ክፉ የሚመልስ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን እስከዚያን ጊዜ ድረስ ብዙ ውበትና ሰላም የሚታይበት ይሆናል፡፡ ትውልዱ መልካምነትን በመፈለግ ያብባል፡፡ እኔ ለሰው ልጅ እንዲሆን የምፈልገው እውነተኛው እምነት ሁሉንም ወደ ብርሃን በማውጣት የኔን ክብር እንዲያመጣ ነው፡፡ ደግሞም ለእኔ መኖር እንደ መተንፈስ ያህል ቀላል ይሆናል፡፡ ደስታ በቤተሰብ፣ በሰፈርና በከተሞች መካከል ይትረፈረፋል፡፡ ምክንያቱም እኔን በማወቅ ለሰው ልጆች ያለኝ ፍቅር ግልፅ ሆኖ ስለሚታይና ስለሚታወጅ ነው፡፡"

"የአሜሪካ ምዕራቡ ክፍል ከሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች ሳይወድም ይቀራል፡፡ ከዚህም ሥፍራ አዲስ አስተዳደር ይነሳል፡፡ የአሜሪካ የምዕራቡና የደቡብ ምዕራቡ ክፍል በቢጫው ድንጋይ/Yellowstone/ ፍፁም እንዳይደመሰስ የማደርገው አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ግብርናና ቴክኖሎጂ የእግዚአብሔርን  መርህ በፍፁም መልኩ የተከተለና በመላዕክቶቼም ተግባርያዊ የሚሆን ይሆናል፡፡ እንዲሁም እንዲያስተዳድሩ አደራ የተሰጣቸው፣ ጠቃሚና ሁሉንም ከግል ፍላጎትና ጥቅም ውጪ በእኩልነት ለመንከባከብ ብቁ  መሆናቸውን ያስመሰከሩና በራስ ወዳድነት ውስጣዊ ፍላጎት ያልተጠመዱ ለዚህ ሥራ ብቁ

የሆኑ በሥራው ላይ ይሰማራሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን ሁኔታ የሮም መንግስት በመጀመሪያ ከአስማት በመነጨ የውስጥ ፍላጎት ምክንያት የመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለ ሮም በማወራ ወቅት ስለ መንግስት እያወራሁ እንጂ ስለ ቤተ ክርስቲያን እያወራሁ አይደለም፡፡"

"የቤተ ክርስቲያኔ መገንባት የሚጀምረው ከአካሉ ውስጥ እያንዳንዱን ሰፈርና ከተማ ለመምራት በተመረጡት ነው፡፡ ለልዩ መሰባሰብ ካልሆነ በቀር ቁጥራቸው ትንሽ ነው የሚሆነው፡፡ በዚህ ትልቅም ስብሰባ እኔ ራሴ በመገኘት አንዱ ከሌላው እንዴት በሰላምና በፍቅር እንደሚኖር አዳዲስ መረዳቶችንና መገለጦችን የማካፍልበት ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን ገና ከጅምሩ እኔ ካቋቋምኩት በመሸሽ ሌሎች አማራጮችን የሚፈልጉ አሉ፡፡ ይህም ጉልበት እንዳይበረከክ የሚያደርግ በምንም ያለመርካት ውጤት ወይም ፍሬ ነው፡፡ አመፃውንም የሚያነሳሱ የእነዚያ አባቶች ይገኛሉ፡፡ ክሌር ከሰው ውስጥ ክፉን እስካለወጣሁ ድረስ ስግብግብነትና ኩራት በሰዎች ውስጥ ይኖራል፡፡"

"እኔ ስላዘጋጀሁት ስለ ወደፊቱ ተስፋ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ እርግጥ ነው የኔ መንግስት ወደዚህ ምድር እስኪመጣ ድረስ ረዥም፣ ጨለማና ደም የበዛበት መንገድ አለ፡፡ ነገር ግን ሁሉ ሰው እንዲያውቀው የምፈልገው የኔ መንግስት ይመጣል፡፡ አዎ ይመጣል፡፡ ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ተስፋ አለ፡፡ ሰላም  የሁለቱን ፍላጎት ባማከለ ወንድማማች ፍቅር ይመሰረታል፡፡ ምንም እንኳን አገሮች የራሳቸው ልዩ መለያዎቻቸውን ይዘው ቢቆዩም ለሃብት ምንጭ እና ለኃይል አቅርቦት በመካከላቸው ጥልና ንትርክ አይኖርም፡፡ በቀላል አገላለፅ ይህ በፍፁም አይፈቀድም፡፡ ምንም እንኳን የሰው ተፈጥሮ በዚህ መንገድ ለመሄድ ቢያመዝንም እኔ ግን እውነተኛ ነፃነትና ፍትህን በሥራ ላይ እንዲውል አደርጋለሁ፡፡ ማንም አይናቅም፣ እንድም እንኳን፡፡ በጣም ታናናሾች እንኳን ቢሆኑም፡፡ ምክንያቱም መንፈሴ ምድርን ሁሉ ይፈትሻል፣ ያያል፣ ያልተስተካከለውን በማስተካከል ለድሆች፣ ለታናናሾችና ለተገፉት ፍትህን ያሰፍናል፡፡

የኔ አጋር በዚህ ጉዳይ ላይ አንቺም ተሳታፊ ነሽ፡፡ አንቺን የሚያስደስት ብዙ ሥራ አለኝ፡፡ ደስታሽ ከባህር እስከ ባህር ይዘረጋል፡፡ አገሮች ይከፋፈላሉ፣ ነገር ግን ርቀታቸው ግን በጣምም ብዙ አይደለም፡፡ ምናልባት አንድ ጀልባ የማትጠቀሚበት ርቀት ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም የአየር ንብረት፣ የባህልና የእንዱስትሪ ልዩነቶች ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም በሁለት በተከፈሉ ከተሞች መካከል የንግድ ልውውጦች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን በነዳጅ የተነሳ ሰዎች እንደገና መልሰው አይጣሉም፡፡ ምክንያቱም ምድር ከነፃች በኋላ ወዲያውኑ አዲስ የኃይል መዋቅር ይተከላል፡፡ የመገናኛ ዘዴ ከምንጊዜውም በበለጠ ቀላል ይሆናል፡፡ የአየር መበከል ጉዳይ የቀረና ያለፈ ታሪክ ይሆናል፡፡ ፍጥረታትን ወይም ሰውን የሚያጠፋ ነገር ማንም እንዲያከናውን አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሰዎች ከሞኝነታቸው የተነሳ ይህንን ውብና ቆንጆ ህይወታቸውን በመጣል ይጫወቱበታል፡፡ እኔም ይህንን እንዲያጠራቅሙት፣ አንድ ላይ እንዲያስሩትና ምናልባትም ሁለተኛ ተመልሰው በዚች ምድር ላይ እንዳይኖሩባት እፈቅድላቸዋለሁ፡፡

(ክሌር) ጌታዬ ስለ ወደቁ መላእክቶች/Aliens/ ጠቅላላ አጀንዳ ምን እንደሆነ በደንብ እንዲገባኝና አንተ ስለእነርሱ ምን ለማድረግ እንዳሰብክ ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡

"እነሱ የፈለሰፉትና በእጃቸው የሚገኘው ቴክኖሎጂ የተጣመመ፣ የመጨረሻውን ጭካኔ የያዘና አስቀያሚ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የተደረገው ከስስት፣ ከጥላቻ፣ ለስልጣን ከመስገብገብና ለመልካም ነገር ግድየለሽ ከመሆን ከውስጥ ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህን አንዳቸውም ሳይቀሩ በጠቅላላ ከምድረ ገፅ እጠርጋቸዋለሁ፡፡ እነዚህ አታላይ ኢጋንንቶችና የተጣመሙ

የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች ህይወትን መፍጠር እንደሚችሉ ራሳቸውን ከእኔ ጋር ለማወዳደር በመሞከር ዓለምን ለማሳመን የሚሞክሩት ነገር ከአሁን ወዲያ አይኖርም፡፡ የእነሱ ችሎታ ህይወትን ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡

በፈረንጆች አቆጣጠር በ2015 ዓ.ም መንግስታችሁ የተደራደረው ነገር የማይጠገን ዋጋ ያስከፍላቸዋል፡፡ ይህም ህይወታቸውን፣ ነፍሳቸውንና ዘራቸውን ነው፡፡ እንደገናም ተመልሰው ወደ ስልጣን መምጣት አይችሉም፡፡ ዓለም ሁሉ ወደታች ተገልብጦ ክፉ ሁሉ ከውስጧ ይደፋል፡፡ ይህንንም እኔ ስመጣ አየዋለሁ፡፡ እኔ ከመምጣቴ በፊት ግን የሶስት ቀን ጨለማ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ የሰው ልጆች ሁሉ ፍፁም ተስፋ የሚቆርጡበትና ከአሁን ወዲያ ምንም ተስፋ የለም የሚሉበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ነው መላዕክቶቼን በመላክ የክፉውን ሥራ የሚያስፈፅሙትን በሙሉ፣ የሽብርና የማጥፋት አጀንዳቸውን ሁሉ እንዲገቱና እንዲያጠፉ የማደርገው፡፡"

"ኤደን ገነት በምድር ሁሉ ላይ እንደገና ተመልሳ የመጣች እስኪመስል ድረስ ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው ህይወት አዲስ የሚሆነው፡፡ በነዚያም ቀናት የሚታየው የብርሃን ፀዳል የኔን ምህረትና ክብር ያውጃል፡፡ በዚያን ጊዜ በብዙ የምድር ክፍል ሁሉ ነገር በአንድ ጊዜ እንደ አዲስ መብቀል ይጀምራል፡፡ በእውነትም አዲስ የንጋት ቀን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ክፉ ከዚያን ወዲያ መግዛት የማይችልበት ስለሆነ ነው፡፡ ሰዎች ብጥብጥንና ክፋትን ቢፈልጉም እንኳን አያገኙትም፡፡

(ክሌር) ወደ ቅድስቲቱ ከተማ መግባት የማይችሉት - ዝሙትን የሚፈፅሙ፣ ውሸታሞች፣ ሌቦችና የመሳሰሉትስ?

"በተዛባ ህይወት ውስጥ የሚኖሩትን መልሶ ለማቋቋም ብዙ ሙከራዎች ይደረጋሉ፡፡ ለመስተካከል ለሚፈልጉት ፍቅሬ፣ ደግነቴና ምህረቴ ያነፃቸዋል ደግሞም ይፈወሳሉ፡፡ አዲስን ህይወት እንዲኖሩ የሚረዳቸውን ምንም ነገር አልሰጣቸውም፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን በዛን ጊዜ እንኳን ብዙዎች የዱሮ ነገራቸውን እንዳለ ይይዙታል፡፡ አንድን ነገር የሚያደርጉትም በዱሮው መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም በመጨረሻውም መቀጣታቸው አይቀርም፡፡ ክፉ ሰዎች ክፋታቸውን እንዲያበዙ በእኔ አስተዳደር አልፈቅድም፡፡ ስለዚህም ትክክልና መልካም የሆነውን የሚከተሉትን ከማበላሸታቸው በፊት እንዲያቆሙ ይደረጋሉ፡፡"

"መጓጓዣዎች ለኃብታሞች ብቻ መሆኑ ከዚያን ጊዜ በኋላ ያበቃለት ጉዳይ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሰው ያሰበውን ለማከናወን የሚበቃውን ያህል ለማግኘት የሚያስችል እኩል ሙብት ይኖረዋል፡፡ በቀደመው ጊዜ ውጤታማ የነበሩና ህጌን የጠበቁ፣ ከመወለዳቸው ጀምሮ እንዲሰሩ የተመደበላቸውን ሥራ ሊፈፅሙ የተነሱትን ሌሎችን ለማሳደግ ሥፍራ ይሰጣቸዋል፡፡"

"በእኔ መንግስት ውስጥ እንቅፋት፣ አድልኦ፣ ጉቦና የመሳሰሉት እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ ሁሉም የራሱ ድርሻና ደስተኛ ህይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን ያህል ይኖረዋል፡፡ ታያላችሁ ኮሚኒዝም ይህንን ተግባርያዊ ለማድረግ ሐሳብ ነበረው፡፡ ነገር ግን ከሰው ልጅ የተበላሸ ተፈጥሮ ምክንያት ሊሰራ አልቻለም፡፡ ከእኔ ህግና ስርዓት ውጪ እንደዚህ ዓይነቱ ሊያብብ፣ ሊያድግና ሊቀጥል አይችልም፡፡ የሰው ልጅ ምንጊዜም ራስ ወዳድነት ያጠቃዋል፡፡ ስለዚህም ኃይል ያላቸውና ሌላ የሰራውን ለመስረቅ የሚፈልጉ ውጤታማ የሆነውን ሰው ጎትተው ወደታች ይጥሉታል፡፡"

"እነዚህን ጠቃሚ  ጉዳዮች ለብዙዎችን በመንገር ነው ተስፋ እንዳለ በመንገር ልረዳቸው የምፈልገው፡፡ ምክንያቱም ለሰው ልጆች የመጣውን የጨለማ ጊዜ ወደኋላ ሳይመለሱ በፅናት ተቋቁመው እንዲያልፉት ነው፡፡ "

## 3.3. ወደፊት ምን እንደሚከሰትና በእግዚአብሔር ጥበቃ እንዴት መቆየት እንደሚቻል ክፍል 3 እና 4

እ.አ.አ. ማርች 5 ፣ 2015 ዓ.ም

Jesus Speaks On: What is to Come, How to Stay Under God - parts 3 & 4

ኢየሱስ ስለ ኤሊየንስ፣ ስለ ክሎንስ፣ ስለ ፕላኔት X እና ስለ መከራው ዘመን እንዲሁም የመከራውን ዘመን በእግዚአብሔር ጥበቃ እንዴት ማለፍ እንደሚቻል ይናገራል፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ.... " ልብሽን በቅርብ እያደመጥኩት ነበር፡፡ በልብሽ ከሌላ ዓለም መጡ ስለተባሉ ፍጥረታት ማለትም ስለ ኤልያንስ /ET'S/ ይህም በብዙ ዓይነት መልክ ስለተገለጡት የኢጋንንት ዓይነቶች እያሰብሽ ነበር፡፡ እናም ክሌር ስለዚህ ነገር ልነግርሽ ይገባል፡፡ አንዳቸውም መልካም አይደሉም፡፡ ሁሉም የወደቁ መላዕክቶች ናቸው፡፡ እየሰሩ ያሉትም እኔንና የሰው ልጆችን በመቃወም ነው፡፡አንዳንዶቹ መልካም ገፅታ እንዳላቸው ለማሳመን እየሞከሩ ነው፡፡ ነገር ግን አትሞኚ፡፡አጀንዳቸው በጣም ወደ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ከሰዎች ጋር በመግጠም ትጥቅ እያስፈቱ ናቸው፡፡ እነዚህኞዎቹ ግራጫ መልክ ካላቸው እጅግ አደገኞች ናቸው፡፡

ኦ!! ስለዚህ ነገር ማውራት እንዴት እጠላለሁ፡፡ ቢሆንም ግን ይህንን ነገር ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም፡፡ እያንዳንዳቸው እጅግ ክፉዎች ናቸው፡፡ ህዝቤን የበለጠ ቅዱስና ጠንካራ ለማድረግ ከምጠቀምባቸው በስተቀር አንድም መልካም ነገር ከእነርሱ አይገኝም፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ለእኔ ሎሌዎቼ ናቸው፡፡ በራሳቸው ለብቻቸው የሚሰሩ ቢመስሉም ነገር ግን መፈፀም የያዙት ከጥንት ጀምሮ እንዲያከናውኑ የታቀደባቸውን ነው፡፡

"የሚመጡት በተለያየ ዓይነት ቅርፅና መጠን ነው፡፡ እንዲሁም የሚጠቀሙበት መጓጓዣ አንዱ ከሌላው ይለያል፡፡እናንተ እንዳሰባችሁት በፎኒክስና/Phoenix/ በአሪዞና/Arizona/ ታይቶ ለብዙ ጊዜ የቆየው ይህ መጓጓዣ ኒብሩ ከሚባለው ፕላኔት/Niberu/ በመምጣት ምድሪቱን ለመመልከትና ለማጥናት ቆይታ ያደረገ አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህ የመንግስት እጅ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ነው በቦታው ላይ ብዙ ቢቆዩም እንኳን ወታደራዊ ኃይሉ ጣልቃ ያልገባው፡፡

"ህዝቡ ግን አሁንም ጉዳዩ ምን እንደሆነ ትክክለኛውን አያውቅም ፡፡ የተሰጠው መረጃ የተሳሳተ መረጃ ነው፡፡ እነርሱ (ET'S ተብለው የሚታወቁት) በጣም ተንኮለኞች በመሆናቸው የሰውን ደካማ ጎን በመጠቀም ለራሳቸው ጥቅም ያውሉታል፡፡ ሰዎች መታመን እንደሌለባቸው ባለማወቅና ባለማመዛዘን በነፃነትና በደስታ ይቀበሏቸዋል፡፡ እነሱም ገራጫ የሆኑትን በማጣጣል እነሱ የዋሆችና ምንም የማይተናኮሉ ለማስመሰል የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡"

"ከሁሉም በበለጠ ደግሞ በምድር ላይ ብዙዎችን ግራ ለማጋባት የተዘጋጀው ነገር በብዙ ዓይነት ዝርያ ሰው ያራባቸው ሰዎች ናቸው (Clones)፡፡ በቁጥርና በዓይነት ብዙ አድርጎ በማራባት በሰዎች ላይ ግራ መጋባትን ለመፍጠር ተጠቅመውበታል፡፡ እናም አዎ ምድርን ለማጥፋት አቅሙ አላቸው፡፡ ነገር ግን አሳታውሱ እነርሱ ካቴና የታሰረባቸው ውሾች ናቸው፡፡ ስለዚህም

ይህንን ለማድረግ ፍቃድ አልተሰጣቸውም፡፡ ክሌር እኔ ምድርን እወዳታለሁ፣ እርሷ በጣም ቆንጆ ነች፡፡ እርሷ ድንቅ የፈጠራ ሥራ ናት፣ እናም እንድትጠፋ አልፈቅድም፡፡

**ክሌር፡-** ነገር ግን አዲስ ሰማይኛ አዲስ ምድርስ?

**ኢየሱስ፡-** በልቤ እንዳለው ራዕይ ለውጥን ወዲያው አደርጋለሁ፡፡ ሁሉም ሰው የጌታን ክብር ያያል፡፡ የነበረ እንደነበረ አይቀጥልም፣ ሁሉ አዲስ ይሆናል፡፡

**ክሌር፡-** በባህር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትስ?

**ኢየሱስ፡-** "በሁሉም ሥፍራ ሐይቅ ይኖራል፡፡ ከዚህ በኋላ ሁከትና ብጥብጥ የለም ስለዚህም የሁከት አካባቢዎች /ሁኔታዎች/ አይኖሩም፡፡ ምክንያቱም ከአሁን ወዲያ አመፃ በሰው ልጆች መካከል አይሰራምና ነው፡፡ ሁሉ ነገር በደህና ሁኔታ በገነት የአትክልት ሥፍራ እንደሆነው ይሆናል፡፡"
ሰዎች ማዕድናትና ለማውጣት ይቆፍራሉ፡፡ ነገር ግን የምድር ከርስን በሚጎዳ መልኩ አይደለም፡፡ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው እያንዳንዱ ብረትና አስፈላጊ ነገር ሁሉ ይቀርብለታል፡፡ በልብ የታሰበና የተቀረፀ ፕሮጀክት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ የሚውል ይሆናል፡፡

ወራቶች እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር የምናገረውን ወደ ማመን እየመጣሽ ነው፡፡ ምን ያህል በግልፅ ትሰሚኝ እንደነበር ነገር ግን እኔ እንደምናገርሽ ምን ያህል እንዳላስተዋልሽ ብታውቂ በጣም ትደነግጪ ነበር፡፡ ነገር ግን የኔ ፍቅር በየጊዜው ንስሐ በመግባትሽና እንዲሁም በእኔ በመታመንሽ ብዙ ተጉዘሽ እዚህ ደርሰሻል፡፡

**ክሌር፡-** አመሰግናለሁ ጌታ!!!

**ኢየሱስ፡-** እሺ ስለ ቢጫው ድንጋይ/Yellw stone/ ጉዳይ ደግሞ የኔ አንዱ የምህረት ክፍል መሆኑን እገልፅልሻለሁ።፡፡ በተጨማሪም የክርስቲያኖች ፀሎት ሰይጣን ምድርን ድምጥማጧን ለማጥፋት እንዳሰበው እንዳይሆንና ጉዳቱ መጠነኛ እንዲሆን አስተዋፅዎ አድርጓል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፣ የክርስቲያኑ ፀሎት በሚድኑትና በሚነጠቁት ሰዎች ላይ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ዘመኑ ዝም የሚባልበት አይደለም፡፡ በአሁኑ ዘመን ዝም ማለት ሞትን ያስከትላል ፡፡ አሁን ዘመኑ ጣራ ላይ ወጥቶ ንጉሣችሁ ሊመጣ ነው!!! ንጉሣችሁ ሊመጣ ነው!!! በማለት የሚጮህበት ጊዜ ነው፡፡

ፕላኔት X የተባለችው ወደ ምድር ቀርባ በታየች ጊዜ ፣ በዚያን ጊዜ የሰው ልጆች ምንም ማድረግ የማይችሉበት ጊዜ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የመትረፋችሁ ጉዳይ በፍፁም አጋጣሚ ላይ ይወሰናል፡፡ በእርግጥ የኔ ምህረት እንዳለ ሆኖ፡፡ ነገር ግን የኔን ምህረት የሚያገኙት እጅግ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን በዓለቶች፣ በንቃቃትና በሸለቆ ውስጥ በመሆን ከዚያ ጥፋት የተረፉትን ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ ጥበቃ የማደርግላቸውና የሚያስፈልጋቸውን የማቀርብላቸው እኔ ነኝ፡፡

በዚያን ጊዜ መንፈሳዊ ህይወታቸው በእጥፍ ያብባል፡፡ ምክንያቱም የሚሆነው ነገር ሁሉ በእኔ አቅርቦት ላይ የተደገፈ ስለሆነ ነው፡፡ ወደ እኔ ፊታቸውን ፍፁም ለመለሱት ትንሹ ምግብ ይባዛላቸዋል፣ የውኃ አቅርቦት፣ ፈውስና ማንኛውንም ዓይነት ጥበቃ ከእኔ ያገኛሉ፡፡

የመከራው ዘመን አብቅቶ እኔ በምመለስበት ጊዜ እንደ ወርቅና እንደ ብር ነጥረው እንደ ቅዱሳን በመንግስቴ ውስጥ ያበራሉ፡፡ እኔ የመረጥኳቸው ለዚህ ጊዜ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ አሁን ካሉበት ህይወት የበለጠ ከፉ ነገር ይከሰታል ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ተዘጋጅተዋል፣ አንዳንዶቹ ግን ገና ክርስቲያን አልሆኑም፡፡ ምንም እንኳን በልባቸው ድምፄን ቢሰሙም በቤተክርቲያን ያለው ህጋዊነት እንዲሁም የእነሱ ነፃነትን መውደድ፣ ህግና ደንብን መጥላት ወደእኔ እንዳይቀርቡ አድርጓቸዋል፡፡

"ነገር ግን እኔ በመጣሁላችሁ ጊዜ ይህ ሁሉ ይቀየራል፡፡ በዚያን ጊዜ የተቀጣጠለ እምነት ይኖራል፡፡ በተለይም በጌታ ተነጠቀው ልጆቻቸውና የትዳር አጋሮቻቸው በዚህ የቀሩት እስከ ጥልቅ ልባቸው፣ እንዲሁም አጥንትና መቅኒው እስኪለያይ ድረስ ጥልቅ የሆነ እምነት ይሆናል፡፡ ከዚያም ምድር እየነፃችና እየጠራች ስትሄድ ብዙዎች ለእኔ ያላቸው ፍቅርና ቅድስና እየጨመረ ይሄዳል፡፡ይህም እንዲያብቡና እንዲፈኩ ያደርጋቸዋል፡፡

ብዙዎቹ ለራሳቸው መኖርን በማቆም ከእኔ ጋር ለመኖር በማሰብ ሞትን ይመርጣሉ፡፡ ተነጥቀው በሄዱትም ይቀናሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ፍላጎታቸው የመነጨው መከራንና ችግርን ከመሸሽ ሳይሆን ለእኔ ካላቸው ፍቅርና ከእኔ ጋር ለመኖር ካደረባቸው ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ባለመሰልቸትና ወደ ኋላ ባለማለት በተዘጋጀላቸው ይቀጥላሉ፡፡ በዚያ ወቅት ልጆቼ በእኔ ላይ በተደገፉ መጠን ታምራቶቼን ያያሉ፡፡ ነገር ግን በራሳቸው በተደገፉ መጠን ለአደጋ ይጋለጣሉ፡፡ የእኔ እጅ በደንብ የሚንቀሳቀሰው በፍፁም እምነት ውስጥ ነው፡፡ እኔ ጣልቃ በመግባት ክፍተትን መሙላት የምችለው ለሚፈልጉኝ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ለራሳቸው አቅርቦት ለሚፍጨረጨሩ የእኔ እጅ ጣልቃ ለመግባትና ለመንቀሳቀስ ታጥራለች፡፡ ስለዚህም በእኔ ላይ መደገፋቸው እየጨመረ መሄድ አለበት፡፡ በወቅቱ ብዙ ነገሮች ተስፋ እያስቆረጣቸው ስለሚሄድ ያላቸው ምርጫ ትንሽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን በእኔ ላይ መደገፋቸውን ባፋጠኑት ቁጥር የሚፈልጉትን ለማግኘት ይቀላቸዋል፡፡

ነገር ግን ለሽንፈት አሳልፌ አልሰጣችሁም፡፡ እንዳውም ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሲጋጠም አብሬው እንደነበርኩ ሁሉ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ ብትመለከቱ ህዝቤ እስራኤል አንድ ለአሥር በሆነ ቁጥር ጠላቶቻቸው ብልጫ ቢኖራቸውም በጦርነት ወቅት ግን ቀኝ እጄ ስለረዳቻቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንዴት እንደተቀዳጁ በጣም ብዙ ብዙ ምሳሌዎችን ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ እናም በእኔ ላይ እምነታችሁን እስከጣላችሁ ድረስ ሁሉን እንድታልፉት አደርጋለሁ፡፡

"ነገር ግን በወቅቱ ከዳተኞች ስለሚኖሩ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እርስ በእርስ ልትተዋወቁ ይገባል፡፡ ብዙዎች ከእናንተ ጋር ለመቀላቀል ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን አሁን የማስጠነቅቃችሁ ምንም እንኳን ጠያቂዎቹ ከእናንተ አስቸኳይ ምላሽ የሚፈልጉም ቢሆን እኔ ሳልፈቅድ አንድም ሰው ወደ ህብረታችሁ እንዳትቀላቅሉ፡፡ አያችሁ በበጎ ፈቃዳችሁ ወይም በመልካምነታችሁ ላይ በመነሳት በቡድኑ ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ፡፡ ከዚያም ከእናንተ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ ስለሌላቸው እናንተ የምታደርጉትን ነገር ሁሉ ቦታ አይሰጡትም፡፡ እኔ ካልፈቀድኩ በቀር ማንንም ወደ ቡድኑ አታስገቡ፡፡ የሎጥን ምሳሌ

በመውሰድ መንፈስ ቅዱስ እንዲመርጥላችሁ ፀልዩ (ሎጥ ወደ ቤቱ ያስገባው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩትን መላዕክቶችን ነበር)፡፡ በራሳችሁ ሐሳብ መደገፋችሁን ፍፁም ጣሉት፡፡ እምነታችሁን በእኔ ላይ ብቻ አድርጉ፡፡ እኔ ብቻ ነኝ የወንዶችንና የሴቶችን እንዲሁም የህፃናትን ልብና የውስጥ ፍላጎት ምን እንደሆነ የማውቅ፡፡"

ዲያቢሎስ በተንኮልና በድብቅ የሚሰራ በመሆኑ በመልካምነታችሁ ላይ በተቃራኒው ይነሳባችኋል፡፡ ስለዚህም በእኔ ላይ ብቻ ተደገፉ፡፡ በሰው ምክኒያታዊነት ላይ አትደገፉ፡፡ በእነዚህ ወቅቶች ውስጥ አንዳንድ ጊዜ "እርስ በእርሳችሁ በመተያየት ጠፋን አለቀልን መሞታችን ነው" ባላችሁ ጊዜ ነገር ግን ተስፋችሁንና እምነታችሁን በእኔ ላይ ስለጣላችሁ እኔ አስመልጣችኋለሁ፡፡ ለጠላቶቻችሁ እንዳትታዩ በማድረግና በአውሬዎቹ ላይ ማስፈራትን በማምጣት እናንተን ሊያጠፉ የመጣውን እመልሳለሁ፡፡ ሁልጊዜ የኔን ስም /ኢየሱስ ክህርስቶስ/ ለመጠቀም አትርሱ፡፡ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ጠላቶቻችሁ እናንተን ለመፈለግ ወደ ጫካው ሲመጡ እኔ ግን ለጠላቶቻችሁ እንዳትታዩ በማድረግ በአጠገባችሁ ያልፋሉ፡፡ ፡፡ አንዳንድ ጊዜም እናንተን ሊፈልጉ በመጡት ላይ ፍርሃትን በመፍጠር እናንተ ካላችሁበት ሥፍራ እንዲርቁ አደርጋለሁ፡፡ ልጆቼ እናንተን ለማዳን የምጠቀምበት ብዙ ብዙ መንገዶች አሉኝ፡፡ እናንተን ለማዳን መሬት እንኳን አፈዋን ከፍታ እናንተን የምትደብቅበት ጊዜ ይኖራል፡፡

ስለዚህም በፍፁም ተስፋ እንዳትቆርጡ፡፡ በእኔ ላይ እምነት፣ እንዲሁም እኔ ድግሞ እናንተን እንደማፈቅራችሁ እምነት ይኑራችሁ፡፡ በእናንተ ላይ ካለኝ ፍቅሬ የተነሳ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እንደምሆን እመኑ፡፡ የደሙን ኃይል ይኸውም የኔን የደም ኃይል ጥሩ፡፡ እንዲህም ብላችሁ አውጁ "የኢየሱስ ደም ሸፍነን፣ ጠብቀን፣ ለጠላቶቻችን እንዳንታይ አድርገን፣ ከልለን፡፡"

"ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን በደንብ ካዘጋጁትና በእኔ ላይ ታምነው ምንም ካላዘጋጁት መካከል ምንም ብልጫ አይኖርም፡፡ ክሌር ለወደፊቱ ምንም ቅድመ ዝግጅት እንዳታደርጊ የከለከልኩሽ አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ እኔ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አቀርባለሁ፡፡ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ ድምፄን በትክክል መስማትና መመሪያዬን መከተል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አድርጉ የምላችሁ ነገር የማይመስልና ከተለመደው ውጪ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እኔ የማዛችሁ ያ ድርጊት ለእናንተ አማራጭ የሌለው የመዳን መንገድ ሊሆን ስለሚችል የአልኳችሁን አድርጉት፡፡ ፀሎት ማንም ምንም ሊያሸንፈው የማይችል የእናንተ መሳሪያ ነው፡፡ ስትፀልዩም በልሳን ፀልዩ፡፡ በልሳን ስትፀልዩ ዓለም በራሱ ካሰለጠናችሁ አስተሳሰብና አመለካከት በላይ በጥበብ አይምሮአችሁን እንዲያነቃቃ ያደርጋል፡፡ የኔ መንገድ እንደ ዓለም መንገድ አይደለም፡፡"

"ፀሎት የእናንተ ትልቅ መሳሪያ ነው፡፡ ከፀለያችሁም በኋላ የምናገረውን በደንብ አዳምጡ፡፡ መመሪያ ፤ራዕይ፣ የፀሎት መልስና በውስጣችሁ መረዳትን እሰጣችኋለሁና ስለዚህም ከእኔ ጠብቁ፡፡ የምናገራችሁን ነገር በጊዜውና በወቅቱ ለመረዳት ተለማመዱ፡፡ ምክንያቱም እኔ የምሰጣችሁን ጥበብ በጊዜ መቀበል ከአደጋ ያድናል፡፡ እኔ እንዴት እንደምትከናወኑ፣ እንደምትሄዱ፣ አስተምራችኋለሁ ደግሞም እመራችኋለሁ፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን በማንበብ በቃሉ መገለጥና/ሬማ/፣ ወደ አይምሯችሁ በሚመጣው ቃል ተጠቀሙ፡፡ እኔ የማስታውቃችሁን ነገር ምንም ሳያመልጣችሁ ተጠንቅቃችሁ አድምጡ፡፡ እኔ በተለያየ ዓይነት መንገድ እናገራለሁ እናንተ ብቻ በትጋት ነቅታችሁ ጠብቁ፡፡ ደግሞም ከፊታችሁ አደጋ እንዳለ ለማስጠንቀቅ ምልክቶችንና ስዕሎችን እልክላችኋለሁ፡፡

"የኔ ልጆች በፍቅር እወዳችኋለሁ፡፡ ከምትወዷቸው ጋር እናንተንም አብሬ ለመውሰድ ብችል በወሰድኳችሁ ነበር፣ አዎ እችል ነበር፡፡ ነገር ግን በራሳችሁ ምክንያት እንቢተኛ ሆናችሁ፡፡ አሁን ግን ልባችሁንና አይምሯችሁን በመክፈት፣ እንቢ ሳትሉ፣ ሳትጠራጠሩና በሙሉ እምነት እኔን ለመቀበል መማር አለባችሁ፡፡ ምንም ነገር መስራት ያቆመ በመሰላችሁ ጊዜ በመደጋገም እንዲህ በሉ .... ኢየሱስ አምንሃለሁ፡፡ ይህንንም የምትሉት እኔ አጠገባችሁ እንዳለሁና እንደምሰማችሁ በዓይነ ህሊናችሁ በማሰብ ይሁን፡፡ በዚህ ጊዜ የውስጥ ሰውነታችሁ በእርግጠኝነት ይሞላል፡፡ ይህ እርግጠኝነታችሁ በእኔ ላይ ያላችሁን እምነት የሚገልጥ ስለሆነ በጉዳያችሁ ላይ ለመንቀሳቀስ ይገፋፋኛል፡፡"

ይህንን አስታውሱ በምንም ነገር ላይ እርዳታ የሚሰጣችሁ ብታጡ እኔ አለሁላችሁ፡፡ ደግሞ ይህንን አስታውሱ እናንተ፣ ከአብ፣ ከእኔና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ላይ ሆነን ከየትኛውም በምድር ላይ ካለ ኃይል የኛ ድምር ኃይል የላቀ ነው፡፡ እናንተና እኔ ሆነን ብልጫ ያለን ነን፡፡ አንዳንድ ጊዜም እንዲረዷችሁ መላዕክቶቼን ልኬ ሲረዷችሁ ትመለከታላችሁ፡፡ ለዚህም አይናችሁን እከፍታለሁ እመኑ፡፡

## 3.4. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው ክስተት የተናገረው፡ - ክፍል 5 ለማን ጥበቃ እንደሚያደርግና እንደማያደርግ የሰጠው መግለጫ

እ.አ.አ. ማርች 6, 2015 ዓ.ም.

{Jesus Speaks on: after the Rapture, Who I can protect and who not-part}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ.... "ከእናንተ ጋር አብሬ እንድሆን የምትፈልጉ ከሆነ ትህትና፣ እራስን መግዛት፣ ታማኝነትና የበጎ ፈቃድ ሥራ እጅግ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ በፊት በራሳችሁ መንገድ ሌሎችን ስትመሩ ከነበራችሁ አሁን በዛ መንገድ መቀጠል አትችሉም፡፡ ነገር ግን በራሳችሁ እርግጠኖች ካልሆናችሁና በአሁኑነጊዜ ከማንኛውም በበለጠ እኔ እንደማስፈልጋችሁ ካወቃችሁ እናንተ በመምራት ትልቃላችሁ፡፡ ልጆቼ በዓለም የተማራችሁት የመምራት መንገድ በዚህ በፍፁም ተስማሚ አይደለም፡፡ እኔ ጥበቃ ላደርግላችሁ የምችለው ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉትን ነው፡፡ ነገር ግን ለሁሉም መልስ ለማግኘት ወዲያና ወዲህ የሚፈነጨው እርሱ ለጥፋት የተጋለጠ ነው፡፡ እኔ በእናንተ እምነቴን ልጥል የምችለው ከጓደኛም ሆነ ከቤተሰብ እስካሁን የተማራችሁት ምንም ዋጋ እንደሌለው ስታውቁና ከዚህ አስተሳሰብ ሰብራችሁ ስትወጡ ነው፡፡ በእናንተ እምነት የሚኖረኝ ያላችሁን ኩራትና ዕብሪት በመጣል መቴት ላይ ተደፍታችሁ እኔን ይቅርታ ስትጠይቁኝ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው በበራችሁ ላይ የመጣውን ፈተና እንድትወጡና በሥጋና በነፍስ በህይወት እንድትኖሩ ለማድረግ ሥራ የምጀምረው፡፡"

"በእኔ ፊት ራሳችሁን ብታዋርዱ በእርግጠኝነት ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ ምንም እንኳን ኩራትና ዕብሪታችሁ ከእናንተ ጋር ለብዙ ጊዜ የቆየ ቢሆንም ነገር ግን ይህ ኃጢያት መሆኑን አውቃችሁ ከዚህ ነፃ ለመሆን ከፈለጋችሁ ከእናንተ ጋር በመሆን እሰራለሁ፡፡ ነገር ግን አሁንም በራሳችሁ ጥበብ ለመቀጠል ብትፈልጉ እኔ ልረዳችሁ የምችለው ጥቂት ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ከራሳችሁ በበለጠ በተቻለ መጠን ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡"

"እኔ ወደ ምድር በመጣሁት ጊዜ እራሴን በሌሎች ላይ ጌታ ለማድረግ አልመጣሁም፡፡ ነገር ግን ራሴን ዝቅ አድርጌ የደቀመዛሙርቶቼን እግር አጠብኩ፡፡ መሪ ለመሆን የሚገባው እንደዚህ ዓይነቱ ነው፡፡ መሪ የሆነ ወይም የሆነች የሌሎቹን ፍላጎት ማስቀደም አለበት/አለባት፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ የመጣችሁት ትሁት ከሆነ ቤተሰብ ስለሆነ ስለዚህ ነገር ሰውናገር በደንብ ይገባችኋል፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቻችሁ ለዚህ ምሳሌ የሚሆናችሁ ሰው ስላላገኛችሁ ትሁት ለመሆን ትግል ይገጥማችኋል፡፡ ይህ ግን እንናተን ተስፋ ሊያስቆርጣችሁ አይገባም፡፡ እኔ እናንተን እንደገና ለመሥራት በትጋት እሰራለሁ፡፡ ለዕብሪታችሁ አሳልፌ አልሰጣችሁም፡፡ እናንተ በእውነት መለወጥ ከፈለጋችሁ እኔ አስተምራችኋለሁ፣ እመራችኋለሁ፡፡ እናንተና የእናንተ የሆኑት ሆኑት ህወታችሁ የሚተርፈው በእኔና እኔ በማሳያችሁ መንገድ ላይ ፍፁም ስትደገፉ ብቻ ነው፡፡ ራሳቸውን በፊቴ ባዋረዱትና በእኔ ላይ በተደገፉት እኔ ሁልጊዜ መውጫ መንገድ አዘጋጃለሁ፡፡"

"ተራሮች ቢንቀጠቀጡ፣ ባህር ቢናወጥ እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፣ በፍፁም አልተዋችሁም፡፡ ሐቀኛ የሆኑትን በእውነት ራሳቸውን ዝቅ ባያደርጉም ባያደርጉም ታውቋቸዋላችሁ፡፡ ንዴት፣ ሐሜት፣ ሁከትን የሚፈጥሩና በመንገዳችሁ ላይ የሚቆሙ እነዚህ ለመውደቅ መንገድ ከፋቾች ናቸው፡፡"

"ከሁሉ በላይ ህይወታችሁን ለእኔ በመስጠት ነፍሳችሁን ጠብቋት፡፡ ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያስገባው ራስን ዝቅ የማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ በራሳችሁ ህይወትን መምራት አለመቻላችሁን ማወቅ ነው፡፡ ይህም ኃጢያት መሥራታችሁን፣ ሌሎችን መጉዳታችሁን፣ በህይወታችሁ ትክክለኛና ያልበሰለ ውሳኔ መወሰናችሁንና ማክበርና መደገፍ ያለባችሁን ችላ ማለታችሁን ማወቃችሁ ነው፡፡ እንዲሁመ መስማት ያለባችሁን በተለይም ሽማግሌዎችን ያለመስማታችሁ ነው፡፡"

"ስለዚህም ይህንን የተመሰቃቀለ ህይወታችሁን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲህ በማለት ለእኔ አሳልፋችሁ መስጠት አለባችሁ፡፡ ‹ ጌታ ሆይ እኔ ደጋግሜ ኃጢያትን ሰርቻለሁ፣ እኔ ለአንተ የምገባ አይደለሁም፣ነገር ግን ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ፡፡ ራስ ወዳድነትና ዕብሪት ስለተሞላው ህይወቴ ንስሐ እገባለሁ፣ ይቅር በለኝ፣ በደምህ አጥበህ አንፃኝ፡፡ውስጤ ካለው ክፉ ነፃ አውጣኝ፡፡ እኔ ትኩስና አዲስ የሆነውን ማንነት ይኸውም የአንተን መልክ የሚመስለውን ለመሆን እንደገና መወለድ እፈልጋለሁ፡፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ህይወቴን አሳልፌ ለአንተ እሰጣለሁ፡፡ ተቀበለኝ፣ ምራኝ ደግሞም አድነኝ፡፡" ከዚህ ፀሎት በተጨማሪ እኔ ያስተማርኩትን የአባታችን ሆይ ፀሎት ፀልዩ፡፡ ከዚያም በእናንተ ፀባይ ላይ ቅፅበታዊ ማስተካከያ ወይም ለውጥ እንደማመጣ ተጠባበቁ፡፡"

"እኔ በልቤ የዋህና ትሁት ስለሆንኩ ከእኔ ተማሩ፡፡ እኔ እጅግ ብዙ የፍቅር ደብዳቤዎችን ትቼላችኋለሁ፡፡ እነርሱን አንብቡ፣ የተናገርኩትንም እመኑ፣ በልባችሁ ውስትም ሥር እንደሰድ ፍቀዱ፡፡ እኔን ከማወቅና ከመውደድ ከሚመጣ ደስታ ጋር የሚወዳደር ምንም ሌላ ደስታ የለም፡፡ አሁን ባላችሁበት ደረጃ ባይገባችሁም፣ እኔ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር ማወቅ ብቻ የሚያጋጠማችሁን ፈተና ሁሉ ጥሳችሁ እንድታልፉ ይረዳችኋል፡፡ በምንም ሁኔታ ብታልፉ እኔ በቀኛችሁ እጃችሁን ይዤ፣ እያነጋገረኳችሁና እያፅናናኋችሁ ነው፡፡

"ከእኔ ፍቅር ሊለያችሁ የሚችል ምንም ነገር የለም፣ ምንም፡፡ በምድር ቢሆን፣ ከምድር በላይ ፣ ኤሊየን ቢሆኑ፣ ሞት ቢሆን፣ ብትወድቁ እንኳን ከእኔ ምንም ሊለያችሁ አይችልመ፡፡እኔ ላነሳችሁ በአጠገባችሁ ቆሜያለሁ፡፡ ከእኔ ፍቅር ምንም ሊለያችሁ የሚችል የለም፡፡ ስለዚህም በምትወድቁ ጊዜ አትፍሩ፡፡ በመንገዳችሁ ስህተት ልትሰሩ እንደምትችሉ እወቁ፡፡ ልትወድቁ እንደምትችሉና እኔ ደግሞ እናንተን አንስቼ እንደገና እንደማቆማችሁ እወቁ፡፡ በምትወድቁ ጊዜ ከእኔ አትሸሹ፣ ወደ እኔ ተመለሱ እንጂ ከእኔ አትሸሹ፡፡ እንዲያውም ወደእኔ ሩጡ፡፡ እኔ ወደእቅፌ አስገባችኋለሁ፣ እንባችሁን አብሳለሁ፡፡ እኔ አልወቅሳችሁም፣ እኔ የምፈርድባችሁ ሰው አይደለሁም፡፡ በፍፁም፣ እኔ እወዳችኋለሁ፡፡ እኔ ገና ሳትወድቁ እንደምትወድቁ ስለማውቅ እናንተን ለማንሳት ተዘጋጅቻለሁ፡፡"

"እኔ መቼም ቢሆን እንደማልጥላችሁ እወቁ፡፡ ይህንን በሙሉ እውቀት ተረዱ፡፡ የእኔ መገኘት በማይሰማችሁ ጊዜ እንኳን እናንተን ለመርዳትና ለማገዝ እንዲሁም ይቅር ልላችና ላድሳችሁ እዚያው አጠገባችሁ ነኝ፡፡ በዚህ እውቀት በመመርኮዝ በእኔ ላይ ፍፁም ተደግፋችሁ ወደፊት ቀጥሉ፡፡"

"ከዚህ ቀን በኋላ እናንተ የራሳችሁ አይደላችሁም፡፡ ነገር ግን ልንከባከባችሁ፣ ልመራችሁና ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ ወደ ክብር ላመጣችሁ የኔ ናችሁ፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር ስለሆንኩ ምንም አትፍሩ፡፡ እኔ ባለሁበት በዛ እንድትሆኑ እኔ ሥፍራ ላዘጋጅላችሁ ከእናንተ ቀድሜ ወደእዛ ሄጃለሁና፡፡ እኔና እናንተ ለዘላለም አብረን የምንሆንበትና የእናንተ ብቻ የሆነ ልዩ ሥፍራ ተዘጋጅቶላችኋል፡፡ እኔ እንደ ሰው ብቻ የምወዳችሁ ሰው አይደለሁም፡፤ እኔ አምላካችሁ ነኝ፡፡ እናም ፍቅሬ መጨረሻ የማይገኝለት ነው፡፡ ምክንያቱም ለፍቅሬ በመጨረሻ የለውም፡፡ ለዘላለም የእናንተው ነኝ፡፤ አሁን ደግሞ እናንተም የኔ ናችሁ፡፡"

## 3.5. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው የተናገረው- ክፍል 6
## የፍርዱ መዶሻ፣ ኢጋንንቶች፣ የወደቁ መላዕክቶች አጀንዳ፣ የእሳተ ጎሞራና የሰው መስዋዕት

ማርች 7/ 8 ቀን 2015

{Jesus Speaks On: After the Rapture - part 6}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ "እስቲ ስለ እሳተ ጎሞራ እናውራ"

*እሺ*

"ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቢጫው ድንጋይ እሳተ ጎሞራ የበለጠ እየተነቃቃ ነው፡፡ በዚህም የአሜሪካን አብዛኛውን ክፍል ለማጥፋት የሚችል ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን የእሳተ ጎሞራው አወጣጥ መካከለኛ እንዲሆን እንደማደርገውና ጥፋቱም የተወሰነ ብቻ እንደሚሆን ነግሬሻለሁ፡፡ነገር ግን ይህንን ብዙዎች አያምኑም፡፡ አብዛኛው አለም የሚጠብቀው ስሜት የሚቀሰቅስና አሳተ ጎሞራው በከፍተኛ ደረጃ ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ቀላል ነው፡፡ በእግዚአብሔር ስለማያምኑ ወይም አገራችሁን ለማዳን የማደርገውን ባለማመን ነው፡፡ ይህ አገር ደግሞ ታውቂያለሽ የእናንተ ብቻ ሳይሆን የኔም አገር ነው፡፡"

*ጌታ አንተን ለመቀበል እንቢ ቢሉም ?*

"ሞኞች ብቻ ናቸው እንቢ የሚሉት፡፡ ነገር ግን በአሜሪካ ብዙ ብዙ ክርስቲያኖች ምንም እንኳን ከድሮው ከፍሪመሶንስ /Freemason/ የአምልኮ ቤተ መቅደሳቸው ፍፁም በሆነ መልኩ ትተው ባይወጡም መንፈሴ ግን በልባቸው ከእነርሱ ጋር አለ፡፡ በተለይም ነገሮች እየተጋጋሉ በሄዱ ቁጥር ብዙዎች ከልባቸው ወደእኔ ይመለሳሉ፡፡"

*በዚህ ጊዜ ብዙ ነቢያቶች ከንጥቀት በፊት ትልቅ የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት ይኖራሉ ያሉትን አሰብኩና ቶሎ ብዬ ጌታን ተመለከትኩት፡፡ እሱም በአሉታ መልክ እራሱን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ነቀነቀ፡፡ እኔም ባልተረጋጋ ሁኔታ ነገር ግን እኮ ሁሉም ጥሩ ነቢያቶች መነቃቃት እንዳለ ተናግረዋል . . .*

"ክሌር ይህ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ እያገራገርሽ ያለሽው ድንገት ልክ ባትሆኚ የሚያመጣውን ኃፍረት እያሰብሽ ነው፡፡ ይህንን ልበል እኔን በትክክል ካልሰማሽኝ የእንቅስቃሴው መኖር የአንቺን የለም የሚለውን ትንቢት ፍፁም ይጋርደዋል፡፡ ይህም ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት በአሜሪካ የለም፡፡"

*እርሱ ኢያለ ያለው እስከ ንጥቀት ድረስ የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት የለም ነው፡፡*

"አዝናለሁ፡፡ የሚሆነው እንደዛ ነው፡፡ የኔ አጀንዳ እንደዚያ ነው፡፡"

*ከእግዚአብሔር ጋር ማን ይከራከራል?*

በቀልድ ዓይነት "በእውነቱ ከሆነ የኔ ፍቅር ሁልጊዜ አንቺ ነሻ፡፡"

*እኔም ሳቅሁና፣ አዎን ይመስለኛል፣ እራሴን እኮንናለሁ፡፡*

"አንገተ ደንዳናዋ ነሽ፣ አዎ እንደዛ ነሽ"

*"ጌታ ለዛ ነው አንገቴን የሚያመኝ"*

"ያለጥርጥር"

*"እሺ፣ ይህ ግን የሚሳቅበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ብዙ ነቢያቶች ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት አለ ብለዋል፡፡ ነገር ግን እኔ ሁልጊዜ መንፈሴን እመረምራለሁ፡፡ እናም አሁን እየደነቀኝ ነው . . . "*

"ንስሐ ቢገቡ መጨረሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ነው?"

*ለዎ*

"ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲመለሱ በዚህ አገር ነዋሪ ለሆኑ (ለአሜሪካ)ብዙ እድሎችን ሰጥቻለሁ፣ ብዙ እድሎች፡፡ ስለዚህ ነው ሌላ የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት /Revival/ በአገሪቱ ውስጥ በማድረግ እንደ ወራዳ ነገር እንዲቆጠርና እንዲናቅ ማድረግ የማልፈልገው፡፡ እነዚህ አምላካቸውን ቁሳዊ ነገርን ያደረጉና ልባቸውን ያጠነከሩ በመሆኑ ልባቸውን የሚያለሰልስ አንድ ነገር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህ ነው የምጠብቀው፡፡"

(ክሌር) የኢኮኖሚውስ ውድቀት?

"እሱም ቢሆን የሚከሰተው ከንጥቀት በኋላ ነው፡፡"

"ወደር የሌለው የጭንቅ ጊዜ፡፡ ይህ ለታናናሾች ውረደትና ንቀት እንጂ ሌላ ምንም የሌላቸውን ጀርባ ይሰብራል፡፡ ቀላልና ተራ የሆኑት ግን አምላካቸው ለእነርሱ ሁሉ ነገራቸው የሆኑት ናቸው፡፡ የሚኖሩት ለሚያገኙት ነገር ሳይሆን፣ የሚኖሩት ለእኔ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔን ማግኘት ማለት ለእነርሱ ሁሉ ነገራቸው ነው፡፡"

"ስለዚህም ለእነርሱ ከዚህ በላይ ህይወታቸውን አሰቃቂ ማድረግ አልፈልግም፡፡ በዚህም ምክንያት እነርሱ ከዚህ ወደላይ እስኪሄዱ ድረስ እጠብቃለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ መዶሻው ይወድቃል!"

(ክሌር) መዶሻ?

"አዎ የፍርዱ መዶሻ በዚህ አገር ላይ ይወድቃል፡፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ ነው የሚወድቀው፡፡ ይህ በነገራችን ላይ በእውቀት ከላቁት መሪዎች/Ruling Elites/ አጀንዳ ጋር ይስማማል፡፡ እነርሱም መንግስት ከሚያቀርበው ሌላ የሚበላ ምግብ ሲጠፋ ሁሉን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡"

"ወደ እሳተ ጎሞራው ጉዳይ ስመለስ፣ በምድሪቱ ላይ የሰው ዝውውር የሚደረግበትን፣ አደንዛዝ ዕፆች የሚዘዋወሩበትን ቦታዎች እንዲሁም የከፋ የፍትህ መጓደል በሰው ልጆች ላይ የሚከናወኑባቸውን ቦታዎች ሁሉ ኢላማ አድርጌያለሁ፡፡ የመሬት መንቀትቀጥና የእሳተ ጎሞራ ክስተቶች የብዙ ሰዎች ህይወትን መቅጠፍና ብዙ ጥፋትን ያመጣል፡፡ የሰው ልጆችን ስቃይ ማየት የኔ ፈቃድ አይደለም፡፡ ነገር ግን በሰዎች ላይ የሚፈፀመውን ግፍ ምንም ልታውቁ አትችሉም፡፡ እነዚህ ቦታዎች የተገደሉ ሰዎች ደም ከምድር ወደ እኔ ከሚጮኸው ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም አልዘገይም፣ ፍትህን አመጣለሁ፡፡

"እንዲሁም እነዚህ እሳተ ጎሞራዎች ከምድር በታች ወዳለው ዓለም መግቢያ መስመሮች ሲሆኑ ከገሃነም ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም ገሃነም እየሞላ ሲሄድ ምድር እየተለጠጠች ትሄዳለች፡፡ ይህ አንቺ በራስሽ ያሰብሽው የመሰለሽ ሐሳብ ከአንቺ የመጣ ሳይሆን እኔ ራሴ እንደትረጂ ያደረግሁት ነው፡፡ ይህ ከእኔ የመጣ ሐሳብ ነው፡፡"

"በተጨማሪም የኢጋንንቶች እንቅስቃሴ መጨመርና የወደቁ መላዕክቶች/Aliens/ ወደ ምድር በግልፅ የሚወጡበት መሆኑ ነው፡፡ ዓለምን ሁሉ ሊገዛ በምድር ላይ ሊመጣ ያለውን የመጨረሻውን መንግስት ለማምጣት ሁሉ ነገር እንደሚገባው ተስተካክሎ ተቀነባብሯል፡፡"

" እነርሱን ማለትም ኢጋንንቶቹን (በነገራችን ላይ ህ የሰጣችኋቸው ስም ማን እንደሆኑ የሚገልፃቸው ስለሆነ ወድጄዋለሁ) የሚመጣው መንግስት በመመልመልና በየቦታው ፈጥረው ካስቀመጧቸውና በኋላ ከየቦታው ከሚያወጧቸው ክሎኖች ጋር አንድ ላይ በማሰማራት የመንግስቱ ተቃዋሚ የሆኑትን ህብረተሰብ አድነው እንዲያጠፉ አዘጋጅተዋል፡፡ አሁን እንኳን እነዚህ ፍጥረቶች እጅግ ገጠር የሆኑ አካባቢዎች ሳይቀር ይገኛሉ፡፡ የሚጠብቁትም ወጥታችሁ ፈልጉና አጥፉ የሚላቸውን አንድ ትዕዛዝ ነው፡፡ ይህ የሚቋቋመው አዲስ የዓለም መንግሰት ከእነዚህ ክሎኖች እርዳታ ውጪ ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት በፍፁም አይችልም፡፡

"አየሩ ሁሉ በወደቁ በእነዚህ መላዕክቶች ስለሚሞላ በሰዎች መካከል ይገኛሉ፡፡ ሰዎችም ከአጠገባቸው ስለሚሆኑ ደንግጠው ወዮ በማለት ይጮሃሉ፡፡ በመጀመሪያው ጊዜያቶች ምንም የማያደርጉ መስለው ይቀርባሉ፡፡ በኋላም ያለምንም ማስጠንቀቂያ 'ክፉ' የሚባሉት ምድሩን ይወሩና ጦርነት በሰማይ ይጀመራል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት አንዱን የአለም መንግስት ለማምጣት አገሮችን ሁሉ ለማቀጣጠል የሚደርጉት ዘዴ ነው"

"እሳተ ጎሞራና ኃጢያት የበዛባቸው ስፍራዎች ቅርብ ለቅርብ መገኘታቸው የአጋጣሚ አይደለም፡፡ የእሳተ ጎሞራ መገኘት ከአጋንንት እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ይህም በዚያ አካባቢ ክፍት የገሃነም በር እንዳለ ያመለክታል፡፡ በሃዋይም የሆነው ሁኔታ በትክክል ይኸው ነው፡፡ ኦ! የኔ ፍቅር ብዙ የማታውቂው ነገር አለ፡፡ በራስሽ ግንዛቤ እንዲገባሽ ለማድረግ መሞከሩን ተይና የሰማሽውን ዝም ብለሽ ፃፊ፡፡ እሺ?"

"ስለዚህም የእሳተ ጎሞራ፣ ኢጋንታዊ እንቅስቃሴና ኃጢያት ቀጥታ ግንኙነት አላቸው፡፡ እንዲሁም ጥንቆላ፣ እንግዳ የሆነ የአምልኮ ስርዓት ማካሄድ፣ ይህም በአብዛኛው ሰዎችን መስዋዕት አድርጎ ማቅረብን ይጨምራል፡፡ በልጅነትሽ ያየሻቸው እነዚያ ፊልሞች ዝም ብለው ፊልሞች አይደሉም፡፡ እውነትን በመመርኮዝ የተሰሩ ናቸው፡፡ እናም ሰው መስዋዕት ሆኖ

በሚቀርብበት ቦታ ሁሉ ከአካባቢው ካለው መንፈሳዊ መሪ /ጠንቋይ/ ጋር ሰይጣን አብሮ እንዳለ እርግጠኛ መሆን ትችያለሽ፡፡"

(ክሌር) አዎ አስታውሳለሁ በፊልሙ ውስጥ የነበሩትን ኢንካዎችና ፖሊንሺያኖች

"አዎ እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆኑ ሰይጣንን የማምለኪያ መንገድ አለው፡፡ ነገር ግን የትኛውም ቢሆን የሚወስደው ያው ወደ እርሱ ነው፡፡"

"በእኔ የተነገረው ቃል ሁሉ ሊፈፀም ግድ ነው፡፡ ምድር በጌታ ክብር ትሞላለች፡፡ ከአሁን ወዲያ ክፉ በምድር ላይ ሊኖር የሚችልበት ምንም ቦታ የለውም፡፡ ሁሉም ነገር እኔ ባቀድኩት በዘላለም እቅዴ መሰረት አዲስ ሆኖ እንደገና ይበቅላል፡፡"

"ይህንን ለአንቺ እየገለጥኩልሽ መልዕክት ገብቷቸው ለሚቀበሉት እና በመጨረሻም መልካም እንደሚያሸንፍና ወደፊትም ብዙ ተስፋ እንዳለ መመልከት እንዲችሉ ነው፡፡ በራሳቸው ጊዜ አይኖቻቸው ይከፈታሉ፡፡ ይህ መልዕክት የተሰጠሽ ሌሎች ሰዎች በፍፁም ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን በአግባቡ አከናውና ቢሆን ኖሮ ይህ ምንም አያስፈልግም ነበር፡ ነገር ግን በፖለቲካ ግፊት ምክንያት እንዳይገለጥ ሆኖ ነበር፡፡ አሁን ግን ሊገለጥ ጊዜው ነው፡፡

## 3.6. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ሊሆን ስላሉ ክስተቶች የተናገረው፡- ክፍል 7
## አለም በኃዘን ይመታል

እ.አ.አ. ማርች 11 ቀን 2015 ዓ.ም
{Jesus Speaks On: After the Rapture - part 7}

*የተወደዳችሁ ቤተሰቦች ይህ መልዕክት በብዙ ግርምት የተሞላ ነው፡፡ ለእኔ ዛሬ ማታ በእውነት የሚገርም ነው፡፡ በአምልኮ ላይ እያለሁ ነገሮች እንደቀድሞው ጀመሩ፡፡ ከጌታ ጋር እየደነስኩ ነበር፡፡ ያአስተዋልኩት ነገር  የለበስኩት ልብስ ጥቁር ነው፡፡ በምሽት የሚለበስ ሆኖ በብርሃን በሚያንፀባርቁ ነገሮች የተሸለመ ልብስ ነበር፡፡ እርሱም የለበሰው እንደዛው ጥቁር ነው፡፡ እየደነስን እያለ እኔ ግን እራሴን እንዲህ እያልኩ እጠይቅ ነበር ሃዘንተኛ ይመስል ለምን ጥቁር ልብስ ለበስኩ ነገር ግን ሃዘን ነው እንዳልል እየደነስን ነው፡፡በዚያን ጊዜ ትንሽ ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡ ስለዚህም ጌታን እንዲህ በማለት ጠየኩት፡-*

*ጌታዬ እኔ የሚያንፀባርቅ ጥቁር ልብስ ምንም እንደለበስኩ አልገባኝም፡፡ እንዲህም ሆኖ ደግሞ አንድ ትልቅ ክብረ በዓል እንደምናከብር እየደነስን ነው፡፡*

"ጥቁር የለበሽበት ምክንያት አለም ሁሉ ስለሚያዝን አንቺም አብረሽ ስለምታዝኚ ነው፡፡ ነገር ግን ደግሞ ትልቅ ደስታ በውስጥሽ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በውስጥሽ ያለውን ደስታ አለም ከአንቺ ነጥቆ ሊወስድ ስለማይችል ነው፡፡"

"የኔ ፍርድ በዚህ አገርና /በአሜሪካ/ በምድር ሁሉ ላይ በሚመጣበት ጊዜ እኛ ግን በዛ ወቅት ውስጥ እንደንሳለን፡፡ ይህም አንድ አይናችንን አለምን እያየን በአንድ አይናችን ደግሞ መንግስተ ሰማይን አሻግረን እናያለን፡፡ ነገሮች ወደዚህ ምድርና ወደ አለም ሁሉ እየቀረቡ ሲሄዱ እናንተ ደግሞ ወደ ሰማዩ አገራችሁ እየተጠጋችሁ ትሄዳላችሁ፡፡"

ክሌር አውቃለሁ በመንፈስሽ ነገሮች እየቀረቡ እንደሆነ እየተረዳሽ እንደሆነ፡፡ ደግሞም በእርግጥም እየቀረበ ነው፡፡የኔ ፍቅር ይህ በቅርብ ይሆናል፡፡ ከእኔ ጋር እወስድሽና ለዘለአለም ከእኔ ጋር ትሆኛለሽ፡፡ የፍቅሬን ስጦታ ሁሉ አትረፍርፌ በመስጠት ከዚያ በኋላ ለሁልጊዜ ለዘላለም አብረን በደስታ እንኖራለን፡፡

*በዚያን ጊዜ እኔ ለራሴ "በዚህ አለም ደግሞ ማንም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በደስታ አይኖርም" ብዬ አሰብኩ . . . ፡፡*

*አ! ጌታ  ይህ በጣም ውድና በጣም የሚያስደስት ነገር ነው፡፡ የውስጥ ማንነቴ በዚህ ተስፋ እጅግ ዘለለ፡፡ ይህ በእርግጥ አንተ የተናገርከውና በቅርብም የሚፈፀም ነገር ነው፡፡*

"ስለጥርጣሬና ስለ ማመን ምን ብዬሽ ነበር?"

*እንደሚመስለኝ ይህንን ነገር ከምንም ጋር ላወዳድረው የምችለው ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ እኔ ካለሁበት እውነታ ሩቅና እጅግ መልካም ከመሆኑ የተነሳ ለማመን አስቸጋሪ የሆነ ነገር ነው፡፡*

*በዚህ ጊዜ ሳቀና* "አዎ የኔ ፍቅር ምን እንደሚሰማሽ በደንብ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እውነት ነው፡፡ እኔ እርግጥ እንደሆንኩ ሁሉ ይህም እርግጥ ነው፡፡ ይህ ከምትገምቺው በላይ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ይህ ደግሞ እኔን የበለጠ ያስደስተኛል፡፡ ምክንያቱም አንቺ ባልጠበቅሽው መንገድ የፍቅር ስጦታዬ ሲያስደስትሽና ሲያስደንቅሽ በማየቴ ነው፡፡"

*ስለዚህም አለም ያዝናል፣ እኛ ግን አንድ አይናችንን አለምን እያየ አንድ አይናችን ደግሞ መንግስተ ሰማይን ያያል ማለት ነው?*

"በትክክል "

*ጌታ! የሰው ልጅ በምድር ስቃይ ላይ መሆኑን እንዲሁም አንተ ከእነርሱ ጋር እየተሰቃየህ መሆኑን እያወቅሁ እንዴት ደስተኛ ልሆን እችላለሁ? ይህንንና ደግሞም . . . በእርግጥ እየጠየኩ ነው፡፡*

"ተመልሶ መጥቶ መርዳትን?"

*አዎ! ማለቴ ስለ እኛ ብዙ የሚባሉ ነገሮች አሉ፡፡ ይህም ሰልጥነን በመከራው ዘመን ወደ ምድር በመምጣት እንደምንረዳ ፡፡*

"ወደ እረፍቴ ትገብያለሽ፡፡ እስካሁን ለፍተሻል አሁን ደግሞ ታርፊያለሽ፡፡ በየትኛውም መልኩ ቢሆን የሚመጣውን ፍርድ ተካፋይ እንድትሆን ሙሽራዬን አልጠራኋትም፡፡ እኔ ከዚህ ወስጄሽ በሰማይ ሆነሽ የምድርን ስቃይ እንድትጋሪ አይደለም፡፡ አሁን ግልፅ ሆነልሽ?

*አ!*

"አላደርገውም፡፡ የአንቺ ሥራ እኔ ለመግዛት ወደ ምድር እስከመለስ ድረስ አልቋል፡፡ ላፅናናሽ እመጣለሁ እንጂ ለምድራዊ ስቃይ አላጋልጥሽም፡፡ ማድረግ አልችልም ደግሞም አላደርገውም፡፡"

*ጌታ በዚህ ላይ አንድ ጥበብ ልጠይቅህ እችላለሁ?*

ለምን አትችይም?ሁልጊዜ ትጠይቂኛለሽ የዛሬው ለምን ልዩ ይሆናል? እምም?

*ይህ የሚያስቅ ነገር አይደለም! ግን እንድስቅ እያደረግሽኝ ነው፡፡*

"አንዳንድ ጊዜ አብረን የጨዋታ ጊዜ ሊኖረን ይችላል፡፡ ከባድ በሆነና የሁለታችንም ልብ በተሰበረ ጊዜ እንኳን፡፡ በእኔ አምላካዊ እቅድ መሰረት የእያንዳንዳችን አካሄድ ልክ አለው፡፡ ዓላማ አለኝ ደግሞም ልክ አለኝ፡፡ የኔ ፍቅር አትጠይቂ፣ ያልኩሽን እንዲሁ ተቀበይ፡፡ ከዚህ አለም ስቃይ ባይተዋር እንድትሆኚ የሰጠሁሽን ነፃነት እንዲሁ ተቀበይ፡፡"

*ጌታ ውስጤን ሳቅ ሳቅ እያለኝ ነው፡፡*

"ክሌር ያ እምነት ከማጣት የተነሳ ነው፡፡"

*ስለዚህ ሳቄን ተቃወምኩት፡፡ ያንጊዜ በሚደንቅ ሁኔታ ለቆኝ ሄደ፡፡*

"የኔ ፍቅር ብዙ ሰዎች የቅጣቱ ዘመን የጀብዱ ሥራ ስለሚመስላቸው ተመልሰው መጥተው መገኘት ይፈልጋሉ፡፡ስለምን እንደሚያወሩ እንኳን አያውቁም፡፡ ስለሚመጣው ነገር መላዕክቶቼ ተዘጋጅተዋል፡፡ ሊሆን ባለው ነገር ላይ እነሱ ብቻ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

*በመንግስተ ሰማይ የምናደርገውስ ፀሎት? አንተ እዛ ሆነህ ስትፀልይ ስናይህ . . . እኛም አብረንህ በእርግጥ እንፀልያለን? ልጆቻችንስ! ለዛስ እንዴት ምላሽ እንሰጥም?*

"የምትፀልዩላቸው ጊዜ ይኖራል፡፡ነገር ግን እውቀታችሁ አሁን ካለው አጅግ የላቀና በዚያን ጊዜ የምትፀልዩት ለእነሱ የሚበጃቸውን ነው፡፡ አሁን እንዳላችሁ ዓይነት መተሳሰር ከእነሱ ጋር አይኖራችሁም፡፡ እንዳውም የምታዩአቸው እኔ እንደማያቸውና ከኃጢያት መንፃት እንዳለባቸው የሰው ዘር አድርጋችሁ ነው፡፡ ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅር አይቀንሰውም ነገር ግን አመለካከታችሁ ከመንግስተ ሰማይ አንፃር ይሆናል፡፡"

*ስለዚህ አሁን እነሱ በሚሆኑት ነገር እያየሁ በስሜት አውሎ ንፋስ እንደምነዳ አልነዳም ማለት ነው?*

"በትክክል፡፡ እሩቅ ብትሆኚም እንደ እናት ትወጃቸዋለሽ፡፡ ነገር ግን በዚያን ጊዜ እኔ ለእነሱ ያለኝ የፍቅር ፈቃድ ምን እንደሆነ በደንብ ይገባሻል፡፡"

*ስለዚህ በመከራው ወቅት ወደ ምድር አንመለስም ወይም ደግሞ በምድር ምን እየተከናወነ እንዳለ የማየት እድል የለንም ማለት ነው?*

"የለም አትችሉም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለማበረታታ ታገኟቸው ይሆናል እንጂ የነገሩ ተሳታፊ አትሆኑም፡፡ እንዳውም በድንገት በመገኘት የማበረታቻ ቃል ለመስጠት እንጂ የሚያመውን እውነታ ተካፋይ አትሆኑም፡፡"

"አየሽ የአንቺ እውነታ በብዙ መልኩ ልዩ ነው የሚሆነው፡፡ ማለትም አሁን በሥጋ በምድር ላይ እንደ ሆነሽው ያህል ስሜታዊ በመሆን በነገሩ ላይ ተሳታፊ መሆን የማትችይበት ነው፡፡ ምክንያቱም አንቺ ወደፊት የምትኖሪበት እውነታና ዓለም ልዩ ስለሚሆን ነው፡፡"

"ምንም እንኳን ብርሃን ትንሽ ሲሰብር እያየሁ ቢሆንም፣ አውቃለሁ ለአንቺ ይህንን ፅንሰ ሐሳብ ለመረዳት ከባድ እንደሚሆን፡፡"

*ሳቅ አለና፣* "አየሽ በመንገስተ ሰማይ ነገሮች ሁሉ ልዩ ናቸው፡፡ አሁን እዚህ ሆነሽ እንኳን እንኳን በሰማይ ስትሆኚ እንዴት ምላሽ እንደምትሰጪ ወይም እንዴት ምድርን እንደምታዪ ማሰብና መገንዘብ አትችይም፡፡እውነታው ይህ ነው፡፡ አሁን ያለሽበት ግን ጭጋግ ብቻ ነው፡፡ ከዛ ነገር ርቀሽ እያለሽ በምንም ዓይነት መልኩ ማስረዳት አልችልም፡፡ የኔ ፍቅር አንቺው እራስሽ ተገኝተሽ በተግባር ማየት አለብሽ፡፡ነገር ግን ስለዚህ ነገር የነገርኩሽን ቃል እንዳለ ውሰጂው፡፡ ይህንን ታደርጊያለሽ?

*አዎ አደርጋለሁ፡፡ ቅድም ያለማመንን ከተቃወምኩ በኋላ ስለነገርከኝ ነገር ሰላም ተሰምቶኛል፡፡ ኢየሱስ ትልቅ ውስጣዊ ሰላም አግኝቻለሁ፣ የምትነግረኝ ሁሉ እውነት ነው፡፡ ደግሞም እንደተናገርከው እንደዛው ይሆናል፡፡*

" እያወራሁ ያለሁትን ጉዳይ ለመቀጠል ብዙዎች ሊፈፀም ያለውን ታሪክ ተመልሰው ባለማየታቸውና ተሳታፊ ባለመሆናቸው በጣም ነው ቅር የሚሰኙት፡፡ ለእናንተ እንደዚህ እላለሁ፡፡ ይህንን ቃሌን ስሙ፡፡ ወደ መከራ እኮ ነው የምትገቡት፡፡ ለእናንተ ወዳልተዘጋጀውና በስርዓት ላልኖሩት ለተዘጋጀላቸው ስቃይ ነው የምትገቡት፡፡ እናንተ ለእኔ ያላችሁን ፍቅር አሳይታችኋል፡፡ ስለዚህም እኔን ንቀው ያልታዘዙት በሚያልፉበት በእነዚህ ነገሮች ውስጥ እንድታልፉ አልፈልግም፡፡"

"ነገር ግን አብረን ወደዚህ በምንመለስ ጊዜ ያን ጊዜ እድሉን ታገኛላችሁ፡፡ በዚያን ጊዜ ሁሉ ነገር አዲስ ይሆናል፡፡ ያን ጊዜ የሚሰጣችሁ ምድብ ሥራ ስለሚኖር እንዲሁም ብዙ አጋጣሚዎችና አዲስ ነገሮች በመኖራቸው ምክንያት ያን ጊዜ የተሰጣችሁን ስጦታ ትጠቀሙበታላችሁ፡፡ አ! የኔ ሙሽሮች ለእናንተ ያለኝ እቅድ በጣም የሚስደስቱና በጣም ድንቅ

ናቸው፡፡ ደግሞም በልባችሁ ለመስራት ትመኙ የነበረውን ሁሉ ለመፈፀም የሚያስችል አስፈላጊ ነገር ሁሉ በሙላት ይሰጣችኋል፡፡"

"አዎን ፍፁም በሆነ መልኩ ነው የሚሟላላችሁ፡፡ ሙዚቃችሁ ያብባል፣ የሞዚቃው ጨዋታ ፍፁም ከመሆን አንድም አይጎድልም፡፡ ቅባቱ ደግሞ ልቦችን ወደ እኔ በማምጣት እንድፈውሳቸውና መልሼ እንድገነባቸው ያደርጋል፡፡ አያችሁ ሁላችሁም የምትጠብቁት ይህንን ነው፡፡ ከእኔ ቀድማችሁ በመሄድ የምታስቡት ይህ በቅጣት ዘመኑ የሚካሄድ መስሏችሁ ነው፡፡"

"ሁላችሁም በልባችሁ ውስጥ የተቀመጠውን፣ እንዲሁም እኔ በበለጠ ለእናንተ ያቀድኩትን ብዙ ብዙ ነገር እንድትሰሩ ብዙ አጋጣሚዎች ይኖራችኋል፡፡ ከአሁን ወዲያ ብዙ ደክማችሁ ከልበ ደንዳናነት የተነሳ ምንም ውጤት የማታዩበት አይሆንም፡፡ እንደዛ አይሆንም መስጠት ያለባችሁን ሁሉ ለመቀበል ልብ ሁሉ በደንብ ይከፈታል፡፡"

" ኦ! የኔ ሙሽሮች ሐሴት አድርጉ፡፡ ሐሴት አድርጉ ዋጋችሁ ትልቅ ነውና ደግሞም የሚሰጣችሁ ሥራ ትልቅ ነውና፡፡ ሐሴት አድርጉ፡፡ በፊታችሁ ይህንን ተመልከቱ፡፡ አዎ እውነት ነው በጥቁር ልብስ ትደንሳላችሁ፡፡ አንድ አይናችሁ መንግስተ ሰማይን አንድ አይናችሁ ደግሞ ምድርን ይቃኛል፡፡ እውነታው መሆን ያለበት ግን አመድ የተነሰነሰበት ማቅ ልብስ ሳይሆን በክንዴ ላይ መሆናችሁ ነው፡፡"

"ጥሩ! የኔ ፍቅር አሁን ረካሽ?"

*"ኦ! አዎ ጌታ፣ እኔ አምኛለሁ፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፡፡ አንተ የምትናገረው እውነቱን ብቻ እንደሆነና ቶሎ ሊሆን ስላለው ነገር ኢያዘጋጀኸኝ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡"*

"የኔ ፍቅር የተናገርኩትን ስለተቀበልሽ አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻው በልብሽ የነበረውን ጥያቄ ምላሽ ተቀብለሽ ስለተረጋጋሽ በደስታ ልቤ ዘለለ፡፡ደግሞም የእረኛሽን ድምፅ በእውነት ሰምተሻል፡፡"

"ደግሞም ታማኝ ድምፄን በእውነት እስከታውቂው ድረስ በአንቺ ላይ መስራቴን እንደማላቆም ነግሬሽ ነበር፡፡ እነዚህን ነገሮች የምሰራው እኔ ነኝ፡፡ ከአንቺ የምፈልገው አሁን እንዳደረግሺው እንድታደርጊ ብቻ ነው፡፡"

"አመሰግናለሁ የኔ ፍቅር፡፡ እምነትሽን በእኔ ላይ ስለታልሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ ከሌር አፈቅርሻለሁ፡፡ቃሌን በአንቺ መናገር እንደጀመርኩት ከእኔ ጋር ወደ ቤት እስከትመጪ ድረስ እንዲሁ እቀጥላለሁ፡፡"

ማራናታ! ጌታ ቶሎ ና!

## 3.7. ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡ ማያሚ በኒኩላር ሲመታና ሲወድም ንጥቀት እንደሚሆን እወቁ - ክፍል 8

እ.አ.አ ማርች 12 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Speaks on: The Day of the Rapture - part 8}

*እኔ ዛሬ ለእናንተ ያለኝ መልዕክት ትንሽ ከበድ ያለ ነው፡፡ እኔ በአሁኑ ሰዓት ትንሽ ደነግጫለሁ . . . . ዛሬ ምሽት ጌታ ከእኔ ጋር የተወያየውን ነገር ላካፍላችሁ ነው፡፡*

*ነገሮች ስለሚፈፀሙበት ጊዚያት ትንሽ ጥያቄ ነበረኝ፡፡ ምን አዲስ ነገር አለ - ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው . . . ነገር ግን የእኔ ግን ጥያቄ ነገሮች የሚፈፀሙበት ጊዜያት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታ በልቤ ውስጥ ያስቀመጠውን ሁሉ አከናውኜ እንድምጨርስ ለዚያም በውስጤ ሰላም እንደሚኖረኝ ተናግሮኛል፡፡ ነገር ግን ጊዜው መቼና መቼ እንደሚሆን ግን አልነገረኝም፡፡ ስለዚህም እኔ አስቤ የነበረው ከንጥቀት በፊት አከናውኜ እጨርሳለሁ የሚል ግምት ነበረኝ፡፡ በዚህ ምሽት ግን ለእርሱ ይህንን ጥያቄ ባቀረብኩለት ጊዜ ትንሽ ተደንቄያለሁ፡፡*

*ጌታ ይህ ነው እኔን ያሳሰበኝ ጉዳይ፡፡*

"ስለ ጉዳዩ እንነጋገር ?"

*አዎ ያ እኔን በጣም ይረዳኛል*

"ይህንን በዚህ ጊዜ ስርተሽ መጨረስ አለብሽ ብዬ የሰጠሁሽ የጊዜ ገደብ የለም፡፡ እኔ ያልኩሽ የሰጠሁሽን ሁሉ ሰርተሽ ትጨርሻለሽ ነው እንጂ መቼ እንደሆነ ግን አልተናገርኩም፡፡"

*ጌታ አንተ ያመለከትከኝ ከንጥቀት በፊት እንደሚሆን ነው፡፡ ደግሞም ከሙሽራዬ ፊት የተቀመጠውን ደንቃራ ነገር ያነሳሁት የበለጠ ጊዜ እንዲኖራት ነው ብለህ ነበር፡፡ አሁን እኔ በጣም በጣም ግራ ገብቶኛል፡፡ ምክንያቱም አሁን ነገሮች ሁሉ የተመሰቃቀሉ እየመሰለኝ ነው፡፡*

"የተመሰቃቀለውን እኔ ግልፅ ላድርግልሽ፡፡ በመጀመሪያ ሁሉም ነገር ተሰርቶ እንደሚልቅ ቃል ገብቼልሻለሁ፡፡ አውቃለሁ አንቺ ያሰብሽው ከንጥቀት በፊት ሁሉም እንደሚያልቅ ነው፡፡ ነገር ግን ምንም የጊዜ ገደብ አልሰተሁሽም፡፡"

*ኦ ጌታ እባክህ እርዳኝ፡፡ ያለማመን ወጥመድ ውስጥ እየገባሁ ነው፡፡*

"የኔ ፍቅር እንደ ዘወትሩ ፀንተሽ ቁሚ፡፡ ትዕግስተኛ መሆን አለብሽ፡፡ አንቺ ለመስራት የሰብሽውን፣ ያም እኔ በልብሽ ያስቀመጥኩትን ሁሉ አከናውነሽ የምትጨርሽበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ይህም ከንጥቀት በኋላ ይሆናል፡፡"

*ከንጥቀት በኋላ?*

"አዎ ከንጥቀት በኋላ?"

*ነገር ግን ለሙሽራህ ተጨማሪ ጊዜ እንደምትሰጣት ተናግረሃል፡፡*

"አዎ ተጨማሪ ጊዜ ሰጥቼያታለሁ፡፡"

*ነገር ግን እኔ የመሰለኝ ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ነበር፡፡*

"እርሱን በግልፅ ስንት ዓመት እንደሆነ አልነገርኩሽም፡፡ ስለ እርሱ አሁንም አባቴን የሚለውን እየጠበኩ ነው፡፡ መቼ መሆን እንዳለበት ጊዜውን የመምረጥ ነገር አለ፡፡ መቼ መሆን እንዳለበት ትክክለኛው ጊዜ የመምረጥ፡፡"

*እሺ . . . እኔ ትንሽ ነገሮች ተቆርጠውብኝ ነው፡፡*

"*ያለማመን ደግሞ እንደገና መጣ*"

*ጥፋተኛ ሆኜ ተገኝቻለሁና ኢየሱስ እርዳኝ*

*በዚህ ሰዓት እሳት ለማቀጣጠልና ለህዝቅኤል እራቱን ለማሞቅ ፈለኩኝ፡፡ ደግሞም ይህ ጊዜ እርሱን እንኳን ደህና መጣህ የምልበት የዕረፍት ጊዜዬ ነው፡፡ እናም አውቃለሁ ወደ ህዝቅኤል ብሄድ ግራ ከገባኝ ነገር ይገላግለኛል፡፡ መጫወቻ ሆኛለሁ ወይንስ በእውነት የሚናገረኝ ኢየሱስ ነው?*

*(ህዝቅኤል) ተመልሻለሁ፡፡ አብሮሽ ያለው ኢየሱስ ነው፡፡*

"አሁን ረክተሽ ሰላምን አገኘሽ?"

*አዎን ጌታ*

"እንድረዳሽ ጠይቀሽን ነበር፡፡ የኔ ጣፋጭ ሙሽራ እርሱ የኔ አፍና የአንቺ ደግሞ ተከላካይ ነው፡፡"

*ኦ ኢየሱስ እንደዚህ ብዙ ጥያቄ እየጠየኩህ እንዴት ጣፋጭ ትለኛለህ?*

"ቅር አልተሰኘሁም እንዳውም የአንቺ ግልፍተኝነት የእኔን የዋህነትና ትህትና ለልጆቼ እንዳሳይ እድል ይሰጠኛል፡፡ በሌላ አነጋገር እኔ ለክሌር ትሁትና የዋህ ስሆን እናንተ ደግሞ አንዱ ለሌላው የዋህና ትሁት በእርግጠኝነት ትሆናላችሁ፡፡"

"አየሽ የአንቺን ግትር ባህርይ ለመልካም ነገር እጠቀምበታለሁ፡፡"

*ጌታ በእውነት አንተ ለስላሳ፣ደግና ይቅር ባይ ነህ፡፡ ከእኔ ጋር ባለህ ግንኙነት ትዕግስተኛ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ፡፡*

ስለማፈቅርሽና ትግልሽ ስለሚገባኝ አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ በነገራችን ላይ ይህ በአለም አቀፍ ላሉ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሰራ ነው፡፡ አሁን ግን ያንን እኮ ፈትተነዋል አሁን የምፈልገው ልነግርሽ ነው፡፡

*ይኸው ጌታ እዚህ ነኝ*

*በዚህ ጊዜ ግንባሬን ሳመኝ*

"እሺ ደህና ጊዜው አጭር ስለሆነ ሁለታችሁም እያላችሁ ይህንን መልዕክት ቶሎ ቶሎ ብዬ ላጠቃለውና ለዛ ቀን ራሳችሁን እንድታዘጋጁ ይሁን፡፡ በአሜሪካና በዓለም ሁሉ ሊመጣ ያለውን ማዕበል ማፈረካከስ የምትችሉት በፀሎትና ፀንቶ በመቆም

"ሁለታችሁም በእያንዳንዱ ቀን በማንኛውም ሰዓት ጠንካራና የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡"

*መዘጋጀታችንን እንዴት እናውቃለን?*

"እጅግ ውስጣዊ የሆነ ሰላም ይሰማችኋል፡፡ በሁለታችሁም ውስጥ የሚሰማችሁ የጥድፊያ ስሜት ነበር፡፡ የምታጠፉት ምንም ጊዜ እንደሌላችሁ በመረዳት በትኩረት ቀጥሉ፡፡ እባካችሁ ወገባችሁን ታጥቃችሁ የሰጠኋችሁን መልዕክት ጠንክራችሁ በመሥራት አቀናብሩትና እዚህ ለሚቀሩት ተዉላቸው፡፡"

"ክሌር እየሰማሽ ነው?"

*ጌታ እኔ ድብዝዝ ብሎብኛል*

"ያ የበላሽው ስኳር ነው፡፡"

*አ!*

"ከእኔ ጋር ለመቆየት ሞክሪ፡፡"

"በመጠኑ የሆነ የኒውክላር ልውውጥ ይኖራል፡፡ ይህም በዓለም ላይ ሽብርን ለመንዛት በቂ ሲሆን ኦባማ ሰላምን እንዲያመጣ በማለት ስልጣን ላይ እንዲወጣና ጀግና ሆኖ እንዲቆጠር ያደርገዋል፡፡"

አሜሪካ በከፍተኛ ጩኸትና ሁካታ ትታወካለች፣ መገናኛ ዘዴዎች በጊዜያዊነት ይቋረጣሉ፡፡ ነገር ግን ማርሻል ሎው ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ መገናኛ ብዙሃን አስፈላጊ ናቸው፡፡ ደግሞስ አሸናፊው በመገናኛ ብዙሃን አሸናፊነቱን በዓለም ሁሉ ሳይነገር እንዴት ደስታውን ያጣጥማል፡፡ አሜሪካ ከዚህ አስደንጋጭ ሁኔታ ማንም ከሚጠብቀው በላይ ቶሎ ታገግማለች፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ነገር ወደፊት ምን እንደሚሆን በሙሉ እውቀት የተዘጋጀ ነው፡፡

አሜሪካ ከአሁን ወዲያ የዓለም ታላቋ ኃያል አገር አትሆንም፡፡ ይህች አገር ብዙ መልሳ የምትገነባውና የተመረዘውን የምታስተካክልበት ብዙ ስራዎች አሉባት፡፡ እንዳትሳሳቱ በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው ሲሻኮትና ሲታገል በምድር ሥር ያሉ ከተማዎች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ይሸሽጋሉ፡፡ በዛን ጊዜ ህግና ስርዓት ይጠፋል፡፡ ወንጀለኞች ለመድፈርና ለመዝረፍ ዕድሉን ይጠቀሙበታል፣ ህይወት እጅግ የተዘበራረቀ ይሆናል፡፡

ያን ቀን፣ ቦንቡ በወደቀ ዕለት በዛው ቀን ነው እኔ ለእናንተ የምመጣላችሁ፡፡ ራሳችሁን ቀና አድርጉና ሰማዩን ተመልከቱ፡፡ በዛኑ ቀን እኔ ለእናንተ እመጣላችኋለሁ፡፡

እንደገና ልድገመው ራሳችሁን ቀና አድርጉ፡፡ በዛኑ ቀን እኔ ለእናንተ እመጣላችኋለሁ፡፡ ተስፋ አትቁረጡ ደግሞም አትደንግጡ፡፡ ደግሜ ደግሜ ነግሬያችኋለሁ፣ የመዳን ቀናችሁ ቀርቧል፡፡ ይህ ነው ስትጠብቁት የነበረው ዘላለማዊ ዕለት፡፡"

*ጌታዬ እኔ መናገር ተስኖኛል፡፡*

" እየመጣ ነው፡፡ እኔ አርግጥ እንደሆንኩ ያም እየመጣ ነው፡፡"

"አትፍሩ፣ የቆማችሁበትን አጠንክራችሁ ያዙ፣ አይናችሁን ደግሞ ወደ ሰማይ አቅንታችሁ ተመልከቱ፣ እኔ እመጣለሁ፡፡

*ጌታ እርዳን ፡፡*

"እንዲረዱአችሁ እኔ መላዕክቶቼን ቀድሜ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ሁሉም የተዘጋጀ ስለሆነ አትገዳገዱም ወይም አትወድቁም፡፡"

*ጌታ ተመስገን፡፡ እጅግ እናመሰግንሃለን፡፡*

"ኢያችሁ ይህንን ለእናንተ ላረጋግጥላችሁ ፈልጌ ነበር፡፡ ነገር ግን የእኔና የእናንተ ግንኙነት የተጠበቀ መሆኑን እርግጠኛ እስክትሆኑ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ፡፡"

*ኢየሱስ እኔ በእውነት ደንዝዣለሁ*

"አውቃለሁ፡፡ አውቃለሁ ይህንን ለመቀበል ከባድ እንደሆነ ፡፡ ነገር ግን በደንብ አዘጋጅቻችኋለሁ፡፡ ስለዚህም ፈተናውን በደመቀ ሁኔታ ነው የምታልፉት፡፡"

*ኢየሱስ በቃ ይኸው ነው?*

"ለአሁን ይኸው ነው"

የዛሬው *መልዕክት እዚህ ላይ ያበቃል፡፡*

## 3.8. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው የተናገረው - ክፍል 9
## ከንጥቀት ለሚቀሩት የተስፋ ጥቅል አዘጋጁ

እ.አ.አ. ማርች 13 ቀን 2015 ዓ.ም
{Jesus Speaks On: After the Rapture - part 9}

ዛሬ በጣም የሚገርም ነገር ገጥሞን ነበር፡፡ ይህም በምን ምክንያት እንደሆነ አናውቅም ነገር ግን ኢንተርኔት የለም ነበር፡፡ ምናልባት ገመዱ ተበጥሶ ይሁን አላወቅንም፡፡ ብዙ ጊዜ ግን የህንፃ ግንባታ ሲካሄድ ገመዶች የበጠሳሉ፡፡ ቀኑን ሁሉ የለም ነበር፡፡ ስልኩ ግን በእርግጠኝነት ከኢንተርኔቱ ጋር ተያይዟል፡፡ በዚህም ምክንያት ስልክም የለም ነበር፡፡

በደህናው ጊዜ ከምገናኛቸው ሰዎች ጋር ባለመገናኘቴ  ምክንበት ብቸንነት ተሰምቶኝ መደናገጥ ፈጠረብኝ፡፡ እናም ሌሎችስ ኢንተርኔት ባለመኖሩ ምን ተሰምቷቸው ይሆን ብዬ አሰብኩ፡፡ ከሌሎች ጋር ባለመገናኘታቸው እነርሱም እንዴት መገለል፣ ፍርሃትና ግራ መጋባት ተሰምቷቸው ይሆን? ወደ ጌታ ፊት ለፀሎት ስቀርብ በልቤ ውስጥ እጅግ ከበደብኝ፡፡

ጌታ እንዲህ አለኝ . . . "ከንጥቀት ወደኋላ ለሚቀሩት ለምትወጃቸው የተዘጋጀ ጥቅል መተው አለብሽ፡፡ ክሌር ይህ ኃሳብ የአንቺ ሳይሆን የኔ ነው፡፡ ቀኑን ሙሉ በእኔ ልብ ውስጥ ነበር፡፡ እናም የመገናኛ መስመሮች መቋረጣቸው በትክክል ገልፆታል፡፡

"ውድ ልጆቼ እነዚህ መልዕክቶች ጠቃሚዋችሁ ከሆነ ከሄዳችሁ በኋላ ምትወዷቸው እንዲያገኟቸው ኮፒ በማድረግ እነርሱ ሊያገኙአቸው የሚችሉበት ሥፍራ አስቀምጧቸው፡፡ ይህ ጥንቃቄ ብቻ ነው፡፡ ከንጥቀት በኋላ እናንተ መልዕክቱን የምታገኙበት ድህረ ገፅ ላይኖር ይችላል፡፡

"በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ለእነርሱ አጀንዳ ማን አደገኛ እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ አንድ ነገር አግኝታችሁ የሚነካችሁ ከሆነና የእናንተን ዕይታ የሚያሰፋና ሰላም የሚሰጣችሁ ከሆነ ዳውን ሎድ በማድረግ ሊገኝ በሚችል ሥፍራ አስቀምጡት፡፡

ሲዲና ዲቪዲም ማዘጋጀት አለብን?

"ማንኛውንም ለማስቀመጥ የሚመችና ሲፈለግ የበለጠ ሊገኝ የሚችል ሁሉ ይሆናል፡፡ ምናልባት አንዱ ኮፒ አንድ ነገር ቢሆን እንኳን ሁለት ኮፒ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡ ዲያቢሎሶች ማንኛውንም ቅዱስ ሆነ ነገር ለማጥፋት እጅግ ይቸኩላሉ፡፡ ይህም በትዕዛዝ የሚሆንና ወደኋላ የሚቀሩት ተገልለው እንዲቀሩ ለማድረግ ነው፡፡"

መታተም የሚችሉ በፒዲኤፍ የተዘጋጁ ፅሑፎች አሉን፡፡

አዎን የሚታተመው ምርጥ  ነው፡፡ ምክንያቱም ለማንበብ ቀላል ሲሆን እንዲሁም በዛ ወቅት ኤሌክትሪክና ኢንተርኔት ስለሚቋረጥ እስከሚጠገን ድረስ ትንሽ ስለሚቆይ ነው፡፡ ይህም ጥቅል መቀመጥ ያለበት እጅግ ፍቅርን ከሚገልፅ ደብዳቤ ጋር ነው፡፡ ሰዎችን ከመክሰስ ተጠበቁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር እብድ ያደርጋቸዋል ወይም ተስፋ ያስቆርጣቸዋል፡፡ ንግግራችሁ የሚገነባ፣ ጨለምተኛ ያልሆነና ተስፋን የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ በዋናነት ግን ፍቅርን የሚገልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

እንዳመለጣቸው በደንብ እያወቁ ቁስላቸውን መንካት አያስፈልግም፡፡ ይልቅስ ማድረግ ያለባችሁ በጉልበታቸው እንኳን መቆም ስለማይችሉ ማበረታታት ነው፡፡

"ኑዛዜ የሚመስል ነገር ወይም ነገሮች እንዴት እንደሚከፋፈሉ ዝርዝር ነገሮች ተዉላቸው፡፡ ይህም እርስ በርሳቸው እንዳይጨቃጨቁ ይረዳቸዋል፡፡ስታከፋፍሉ አታዳሉ፡፡ እንዳውም ለማይገባቸው በልዩ መልክ ደግ ሁኑላቸው፡፡

"አሁን ትኩረታችሁ ሁሉ መሆን ያለበት በነፍሳቸው መዳን ላይ ነው፡፡ እኔ አፍቃሪ አምላክ ነኝ፡፡ ነገር ግን በሰው ልጆች ላይ ቁጣዬ በተነሳ ጊዜ እነዚህን ሁሉ ማሳመን ከባድ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህንን አስታውሱ አስቀድሜ የወሰንኳቸውን አስቀድሜ አውቃቸዋለሁ፡፡

"ይቅርታ እንደምታደርጉላቸው በንግግራችሁ ግለፁላቸው፡፡ እናንተም በእነርሱ ላይ የሰራችሁትን ኃጢያት ምን ምን እንደሆነ ዘርዝራችሁ ይቅርታ በመጠይቅ እንዲተዋቸው አድርጉ፡፡ ይቅርታ ጠይቋቸው፡፡ ያለፈውን ለመተውና ወደፊት ለመዘርጋት ይህ ቅባት ያስፈልጋቸዋል፡፡ እመኑኝ ይህ ዘሎ መውጣት ይሆንላቸዋል፡፡ ማንም ሊያስበው የማይችለው አስቸጋሪው ሽግግር ከዚህ ወጥቶ መለወጥ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡

"የጌታ ማደሪያዎች ፀሎት የሚለውን እንዲፀልዩና እጇን እንዲዩዙ አበረታቻቸው፡፡ በችሎታዬ እመራቸዋለሁ ደግሞ በፍቅር አፅናናቸዋለሁ፡፡ነገር ግን ለእኔ እንደሚገኙ ሆነው መፀለይ አለባቸው፡፡ አዎ በጉልበታቸው ተንበርክከው የሚፀልዩትና በትህትና የሚያቀርቡት ልመና እጅግ ተደማጭነት ያለው ነው፡፡ ከዚህ በበለጠ መልኩ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የግል፣ ቅርበት ያለውና እጁን ይዞ የመሄድ ግንኙነት እጅግ መልካም ሲሆን ሌላው የቀረው እንዲሁ በራሱ ይቀጥላል፡፡

"እነርሱ ማወቅ ያለባቸው እንደምወዳቸው ነው፡፡ ሁልጊዘ ከእነርሱ ጋር ነኝ፡፡ ደግሞም ሊቀርቡኝ ይችላሉ፡፡ ለወደፊቱም ተስፋ ያላቸው ናቸው፡፡ አሁን ቢሞቱም ወይንም በመከራውን ዘመን ውስጥ ቢያልፉ ወደፊት ገና መልካም የሆነ ጊዜ ይጠብቃቸዋል፡፡ እንዲያውቁ የምፈልገው ሁሉም ነገር ያለቀና የተበላሸ አይደለም፡፡ እንዲህ አይደለም፣ እንዳውም ህይወታቸው ገና መጀመሩ ነው፡፡ አዎ እርግጥ ነው መንገዳቸው በአደጋ የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ እኔ በጣም በተጠጉ ቁጥር ታምራቶችን እንዲሁም የፍቅሬ ጥልቀት ምን ያህል እንደሆነ በመለማመድ ምላሹ እጅግ የጠለቀ ይሆናል፡፡

"ህይወታቸውን ሙሉ ለማግኘት ሲሸከረከሩ የነበሩት ነገር ደግሞ ግን ሲሸሹ የነበሩት ነገር ይህ ነበር፡፡ አሁን ግን እኔ እውነት እንደሆንኩ፣ እንደምወዳቸውና ከእነርሱ ጋር እንደሆንኩ የሚያውቁበት ጊዜ ነው፡፡

"ባለፉት አመታት ሁሉ ሊሰሯቸው የሚገቡ ነገሮች ነገር ግን ያልሰሯቸው ሁሉ የሚሰሩት አሁን በዚህ ወቅት ነው፡፡ ነፍሳቸውን የሚያጧት ያገኟታል፣ ነፍሳቸውን ግን አጥብቀው የሚይዟት ያጧታል፡፡ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስል ነገር ግን በእምነትና በመተማመን ላይ የሚሽከረከር ነገር ነው፡፡ በቃሉ ውስጥ የተፃፉት ምልክቶችና ተስፋዎች በመፈፀማቸው ምክንያት መፅሐፍ ቅዱስ በ180 ዲግሪ እንደሚመልሳቸው ተስፋ አለ፡፡

"ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንዶች ምን እንደሚያስከትል ሙሉ እውቀት እያላቸው በራሳቸው መንገድ መጓዛቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በዚህም የሚማሩት ትምህርት አለ፡፡ አንድ ቀን ታዲያ የአመፃቸውን ጥልቀት ምን ያህል እንደሆነና ውጤቱም ለምን አደገኛ እንደሚሆን በሙላት ታውቃላችሁ፡፡

*ጌታ በታላቁ መከራ ወቅት ምን እንደሚፈፀም ማየት የምንችልበት ሊጋጣሚ አለ?*

"ነገሮችን የምንከልስበት ወይም መልሰን የምናይበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር እናንተ ለማወቅ አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድታዩ ይደረጋል፡፡ ወደ መጨረሻው አካባቢና ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ወደ ምድር ከመመለሳችን በፊት ብዙ እንድታዩና

ከእኔ ጋር ተመልሳችሁ ለመግዛት እንድትዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ከዛ ሁሉ በፊት ግን በምድር በተመደባችሁበት ሥፍራ ለመስራት የሚያስችል ትልቅ የግንዛቤ ማስጨበት፣ የስልጠና፣ የመታጠቅና የዝግጅት ጊዜ ይኖራል፡፡

"አሁን እዚህ ሆናሽ የማይቻል የሚመስል ነገር በመንግስተ ሰማይ አገባብ መሰረት ሲታይ የተሌ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ዳሩ ግን የጫጉላ ጊዜ ስለሚኖር በምድር ያለውን የሰው ልጆች መከራ በማምጣት ይህንን ጊዜ አላበላሽም፡፡

በዚህ ጊዜ ሁልጊዜ እንደማደርገው ሁሉ ብዙ ጥያቄዎች ይመጡብኝ ጀመር፡፡ እናም እንዲህ አልኩት . . . ጌታ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ምክንያቱም ሐሳቤን ማንበብ እንደሚችል ስለማውቅ ነው. . .

እርሱም ቀጥዪ. . . "በእያንዳንዱ ምሽት ሌላ ነገር ነው. . . ነገር ግን ይገባኛል፡፡"

*ቤተሰቦቻችንን ማየትና መርዳት አለመቻላችንን ሳስበው በጣም ከባድ ስለሆነብኝ ነው፡፡ ይህ በእውነት እኔን የማይለቅ ነገር ሆኖብኛል፡፡*

"ምክንያቱም ከዛ ጋር በጣም ከመጣበቅሽ የተነሳ እያንዳንዱ ነፍስ ለመቀደስ መጓዝ ያለባትን መንገድ ስላልገባሽ ነው፡፡ለዚህ ነው ትላንትና በመንገዳቸው ላይ ነው የምትቆሚው ያልኩሽ፡፡ በህይወታቸው ውስጥ ከእኔ መኖር ይልቅ የአንቺ መኖር የበለጠ የሚጠቅም ይመስልሻል?"

*ኦ በፍፁም! ነገር ግን እንደማስበው የሁለታችንም . . . ጥሩ ይመስለኛል. . .*

"አየሽ ያንን ለምን እንደማልፈቅድ?"

*ዝም ብዬ ስገምተው አብሬያቸው ብሆን ምናልባት ትልቅ ችግር እሆንባቸዋለሁ፡፡*

"ከሌር አንዳንድ ጊዜ እንድታበረቻቻቸው ይፈቀድልሽ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ይህንን የምሰራው በራሴ መንገድ ነው፡፡"

ጌታ ያንተን መንገድ ተቀብያለሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ ሐሳብ ላይ የመጨረሻዬ እንዲሆን እባክህ እርዳኝ፡፡

"እርዳታሽ ዱሮ እየመጣ ነው፡፡ በመንግስተ ሰማይ ደግሞ በእውነት ሥራ የሚበዛብሽ ሴት ስለሆንሽ ፍርሃትሽን ለማጥፋት ይህ ይረዳሻል፡፡"

*ይህ ምናልባት የማይረባ ጥያቄ ሊሆን ይችላል ግን በመንግስተ ሰማይ ጠላት የምናስበውን ነገር ሊያቃውስ ይችላል?*

"አይ ይህንን ለማድረግ አልተፈቀደለትም፡፡ እንዲህም በመሆኑ በመንግስተ ሰማያት የማሰብ ነፃነት ስለሚኖርሽ በምድር በነበርሽ ጊዜ ከጨለማ ኃይላት የሚሰነዝርብሽን ጭቆና ምን ያህል ከባድ እንደነበር ትረጃለሽ፡፡"

ስለዚህም የትኛውም ስርዓት የሌለው አስተሳሰብ በመንግስተ ሰማይ ቢመጣ ሁሉም ከእኛ ነው ማለት ነው?

"ከሌር በመንግስተ ሰማይ ምንም ስርዓት የሌለው አስተሳሰብ የለም፡፡ እውነትና ግልፅነት ብቻ ነው ያለው፡፡ ካላየሽው በስተቀር ልታውቂው ስለማትችዪ ምን ዓይነት ይሆን ብለሽ ለማሰብ እንኳን እንዳትሞክሪ፡፡

*እሺ፡፡*

"እንድትበሳጩ ወይም እንድትሰጉ አልፈልግም፡፡ ሁሉም ነገር ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ የሚካሄድ ነገር ነው፡፡ ለዘላለም ህይወት የሚያስፈልጋችሁ ነገር ሁሉ ተዘጋጅቶ ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡

ጌታ ሌላ የምትለን ነገር አለ?

"አድማጮችሽን ብዙ የቀረ ጊዜ እንደሌለ ንገሪያቸው፡፡ ለሚወዷቸው ትተውላቸው የሚሄዱትን ጥቅል ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሚወዱት የሌላቸው ደግሞ በአካባቢያቸው ላሉት ጥቅሉን ያዘጋጁና ይተዉ፡፡ ለሌሎች በማሰብ ለሚመጣው መከራ እንዲዘጋጁ ማድረግ ብዙ ቅባት ይጨመራል፡፡ በዚህ ዓይነት ደግነት ብዙዎችን ተስፋ ከመቁረጥ ትታደጋላችሁ፡፡ በኋላም ከግራ መጋባት ስላወጣችኋቸው ያመሰግኗችኋል፡፡

"እባካችሁ ታማኝ በመሆን አዘጋጁ፡፡"

"ነገ የበለጠ እወዳችኋለሁ"

*እኔም እወድሃለሁ፡፡ ጌታ በቅርቤ ሁን*

"ቅርብሽ ነኝ"

**መዝሙር**
**እርሱ እውነት ነው ይመጣል፣ እባካችሁ ስሙ**
**በህዝቅኤል ዱ ቦስ**

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ

ታውቃላችሁ በእያንዳንዱ ቀን እርሱ ለእናንተ አለ፣

በእያንዳንዱ የሌሊት ወቅት እርሱ ለእናነተ አለ፡፡

ታውቃላችሁ እርሱ ለእናንተ ያስባል፣

ይህ እውነት እንደሆነ ልታውቁ ይገባል፡፡

በህይወት ዘመናችሁ ሁሉ ይህንን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ

ይህ ከባድ አይደለም ልባችሁን ክፈቱ

የእርሱ ፍቅር ወደ ውስጥ ዘልቆ ይግባ፡፡

ስሙን ብቻ ጥሩ፣ ሁሉም እንደነበረ አይቀጥልም

የምናሸንፈው የዘላለም ህይወት አለ፡፡

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ

እውነት እንደሆነ አታውቁም፣እርሱ ሊመጣ ነው፣ እባካችሁ ስሙ፡፡

## 3.9. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው የተናገረው፡ ክፍል 10
## የአሜሪካ የውቅያኖስ ማዕበሎች

እ.አ.አ. ማርች 15 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Speaks On: After the Rapture - part 10}

*ጌታ የዛሬውን መልዕክት "የውቅያኖስ ማዕበሎች " በማለት ጀመረ፡፡*

እንደተናገርነው አገራችሁ አሜሪካ የውቅያኖስ ማዕበል ውስጥ እየገባች ነው፡፡ ሁሉ ነገር ተስተካክሎ ተቀምጧል፡፡ የሚቀረበው ምድሪቷን በድንገት አጥቅቶ ተግባርያዊ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ቀጠሮ ተይዞለታል፡፡ ይህችን ምድር ለማንበርከክ ብዙ ክስተቶችን በአንድ ጊዜ ለመፈፀም ሁሉ ነገር በደንብ ተቀነባብሯል፡፡ ለዚህም ጉዳይ የሰለጠኑት እስኪጠሩ ድረስ በየጥጋ ጥጉ እየጠበቁ ናቸው፡፡

"ምንም መጥፎ ወሬ መስማት ያልፈለጉ ብዙዎች ማየት ባልቻሉትና ባልጠበቁት ነገር ተይዘው ሊጠመዱ ነው፡፡ ብዙዎች መሪዎቻቸው ምን ያህል የተባላሹ እንደሆኑ ምንም እውቀቱ የላቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ በኒውዩርክ ገበያ መአከል የደረሰው ድንገተኛ አደጋ በአሜሪካ መንግስት በተደረገ ሴራ እንደሆነ የሚያምኑትን እንዴት የራሳችሁን መንግስት እንዲህ ትላላችሁ በማለት እንደ እብድና ያለተለመደ አስተሳሰብ ያላቸው አድርገው ይቆጥሯቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ህይወታቸው የሚያጠነጥነው በዙሪያቸው ባለው ምቾትና የኑሮ ደረጃ በመሆኑ ምን እየመጣ እንደሆነ ማየት ተስኗቸዋል፡፡ ስለዚህም በሚመጣው ነገር እጅግ ግራ የሚጋቡት እነሱ ናቸው፡፡ በእነርሱ ላይ እየተፈፀመ ያለው በሚሊዮን ዓመት ውስጥ እንኳን ይደረጋል ብለው በፍፁም አያምኑም ፡፡ በዛው አንፃር ግን ይፈፀማል ብለው ያላሰቡት በሚያሳስብ ደረጃ በእርግጥ እየተከናወነ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን እነሱ ምንም ትኩረት አልሰጡትም፡፡"

"ቦንቡ በወደቀ ጊዜ በህዝብ ላይ ግራ መጋባትና ድንጋጤ ይሆናል፡፡ የብዙ ሰዎች የቤተሰብ አባላት መጥፋት ድንገተኛ የልብ ድካም ሞትንና እራስን በራስ ማጥፋት ያስከትላል፡፡"

"እንዲህም ሆኖ ግን ከአደጋው የሚተርፉና አጥሩን ጥሰው በመውጣት ለነፃነታቸው ተነስተው የሚዋጉ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ እጅግ ዘግይተዋል፡፡ ነፃነታቸው ቀድም ብሎ ተወስዷል፡፡ አሁን ማድረግ ያለባቸው የወደፊቱን ይህም የመንግስተ ሰማይ ህይወታቸውን ማረጋገጥ ነው ፡፡ ይህም ስለ መዳናቸው፣ ንስሐ ስለ መግባታቸውና በሁሉ ነገር በእኔ ላይ መደገፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ነገር ግን በእኔ እርዳታ ሳይሆን በራሳቸው አይምሮ በመመራት መሳሪያ አንስተው ለመዋጋት የሚያስቡ ይወድቃሉ፡፡ በዚህ ምድር ላይ የመጣውን ማንኛውንም ነገር ሊያሸንፉ የሚችሉት እኔን የሚያውቁኝና የእኔ የሆኑ፣ በዚህ ምድር ለትክክለኛው ነገር እንዲዋጉ በእኔ የተጠሩ ወንዶችና ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ብቻ ናቸው ማንኛውንም እንግዳ የሆነ ነገርን ሁሉ ሊያሸንፉ የሚችሉት፡፡"

"ስለዚህም ለብቻችሁ ይህንን ለመፈፀም ያሰባችሁ በሚያሳዝን ሁኔታ ተሳስታችኋል፡፡ እስካሁን ከተዘጋጁት ጋር በመሆን በሥልጣን ሥር ሆናችሁ ሥሩ፡፡"

*"ጌታ አገሪቷን ለመመከት እነዚህ የተመረጡት የአንተ ከሆኑ ለምን ሳይነጠቁ ይቀራሉ?"*

"ይህ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ የኔን ሙሽራ ባህርይ ታውቂያለሽ?"

*የማውቅ ይመስለኛል፡፡*

"ጦረኛ ነች?"

*እንዳውም አይደለችም፡፡ እርሷ በፊልሙ እንዳየኋት አይነት ቁስ ነች፡፡ ሲገድል የተቀጠረው ወታደር በፊቱ ያገኘውን ሰው ሁሉ እየተኮሰ ሲገድል ቀጥ ብሎ ወደ ጎዳዩ እንደሄደው፣ ከዚያም በጥይቱ ተበሳስቶ እንደተገደለው ሚሽነሪ ዓይነት ናት፡፡*

"ትክክል ነው፡፡ እነዚህ ዓይነት ሙሽሮች ናቸው እኔን ሊገናኙኝ የሚመጡት፡፡ የኔ ሙሽራ ባህር ይህ ነው፡፡ እርሷ አፍቃሪ ነች እንጂ ተዋጊ አይደለችም፡፡ እርሷ የምትዋጋው ከራሱ ኃጢያት ጋር ብቻ ነው፡፡"

*ነገር ግን ቀደም ባለው መልዕክትህ ለውጊያ የተመረጡ እንዳሉ ተናግረሃል፡፡*

ይህ የአንዳንድ ነፍሶች ባህርይ ነው፡፡ እነዚህ ነፍሶች አፍቃሪ ለመሆን ተዋጊ ይሆናሉ፡፡ እነዚንህም እወስዳቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ነፍሶች ተፈጥሮአቸው በጣም በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ባህርያቸው መዋጋት ነው፡፡ እነዚህም በመንግስቴ ውስጥ *ሥራና ሥፍራ* አላቸው፡፡ በመጨረሻውም የፍቅር መንገድ ይገባቸዋል፡፡ መላዕክቶቼ የፍቅር መንገድ በደንብ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ክብሬንና መንግስቴን መጠበቅ ግዴታ ስለሆነባቸው ለመዋጋት ተነስተዋል፡፡ ጦርነቱ ሲያበቃ ግን ማለቴ ሁሉም ጦርነት ሲያበቃ መዋጋት ያቆማሉ፡፡ ምክንያቱም የሚዋጉት ምንም ስለማይኖር መዋጋት አያስፈልጋቸውም፡፡ ነገር ግን ያ ጊዜ ገና አልደረሰም፡፡

ጌታ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ፡፡ በመጨረሻው የጥፋት ወቅት ጊዜ አትላንቲስን፣ ዳይናሶርንና ሌላውን ሁሉ ስታጠፋ አብረህ ሁሉን ለምን አላጠፋኸውም?

"የኔ ፍቅር ይህ ለአንቺ አሁን አስፈላጊ መረጃ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመንግስተ ሰማይ ሁሉም ነገር ግልፅ ሆኖ ይገባሻል፡፡እሺ፡፡"

*ጌታዬ አንተ በጣም የምትወደድ ነህ፡፡ጥያቄ እንድጠይቅ ሁልጊዜ ትፈቅድልኛለህ፡፡*

አንቺ እኮ የኔ ትንሿ ልጄ ነሽ፡፡ ደግሞም እያደግሽ ስለሆነ በምንም ዓይነት መልኩ ጥያቄሽን እንዳትጠይቂ በማድረግ ተስፋ አላስቆርጥሽም፡፡ እሺ አሁን ወደ እቅዳችን እንመለስ፡፡

*ወደ እቅዱ ?*

"አዎ፡፡ ለመጉዳትና የራሳቸው የግል ፍላጎት ለማርካት ወደ ሰለጠኑት፣ አይምሮአቸው በስስት ተበልቶና ተደፍኖ ስለ ተበላሸው፣ ወደ ከፉና ወደ ጎዳዮቹ እቅድ፡፡ የሚፈሩት ነገር እነሱ ላይ ይደርሳል፡፡ በምንም ዓይነት መልኩ ቢሆን ከሚመጣው የእሳት ቃጠሎ አያመልጡም፡፡"

"እውቀት በማጣታትና በራሳቸው ላይ በመታመን ሁኔታዎች ሁሉ እነሱ እንዳሰቡት የሚሆን መስሏቸዋል፡፡ ከእውነቱ ምን ያህል ርቀው እንዳሉ ምንም ፅንሰ ሐሳቡም የላቸውም፡፡ ከአንዱ እቅድ ወደሌላው እቅድ በተላለፉ ቁጥር ስግብግብ እቅዳቸው የሚያስከትለውን ከባድ አሉታዊ ውጤት ለማወቅ ምንም ፍንጭ የላቸውም፡፡ እነሱ የሚመለከቱት በአጭር የሚያገኙትን ነገር ነው፡፡ ነገር ግን በሰው ልጆች ላይ ያውም በራሴ ሐምሳል በፈጠርኩት ፍጥረት ላይ የሚፈፅሙትን አሰቃቂ ኃጢያት አልተገነዘቡም፡፡ ቀኑም እጅግ ሐዘን ይሆንባቸዋል፡፡"

"የኔ ፍቅር በተለይም የማስጠነቅቀው በመከራው ዘመን በዚህ የሚቀሩትና በራሳቸው መሳሪያን በማንሳት ሊዋጉ የሚፈልጉትን ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ከባድና አስቀያሚ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ለአሁኑ ግን መሆን ያለበት እርስ በርስ መያያዝ፣ መፀለይና በሁሉም ፊት ሊመጣ ስላለው ነገር አንዱ ሌላውን ማፅናናት ነው፡፡"

"ለተስፋ፣ ለፍቅርና ለደህንነት እርስ በርስ የመያያዝ ጊዜ ቢኖርም በመካከላቸው ግን ከዳተኞች ይኖራሉ፡፡በመንፈስ ብቻ ነው አንዱ ሌላውን ነፍስ ሊያውቅ የሚገባው፡፡ ሥጋ ይዋሻል ደግሞም ያታልላል፡፡ ነገር ግን መንፈስ እውነት ለሆነው ምስክርነት ይሰጣል፡፡ ለዚህ ነው መፀለይና ከእኔ ጋር ህብረት ማድረግ ፍፁም አስፈላጊ የሚሆንባቸው፡፡"

<u>እኔን መጀመሪያ ሳታማክሩ ምንም ነገር እንዳታደርጉ!</u>

በመጀመሪያ እኔን ሳታማክሩ ማንንም ሰው እንዳትቀበሉ፡፡ ምክንያቱም በሰው ልብ ውስጥ የተደበቀውን የክፉ አጀንዳ እኔ አጋልጣለሁ፡፡

*እዚህጋ ትንሽ ጊዜ ወስጄ መናገር የምፈልገው ለአንዳንድ ነገሮች ዕጣን እንዴት አድርገን እንደምንጠቀም ነው፡፡ ዕጣን መጠቀም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ለምሳሌ ጌታን የሸጠውን ይሁዳን ማን እንደሚተካው ለማወቅ ደቀመዛሙርት ዕጣ ተጠቅመዋል፡፡ እንዲሁም ዮናስ የነበረችበት መርከብ ስትናወጥ ችግሩ ማን ላይ እንደሆነ ለማወቅ ዕጣ በማውጣት ዕጣው ዮናስ ላይ ወድቀቋል፡፡ እኛም ይህንን ተከትለን በመፅሐፍ ቅዱስ ተስፋ የተገቡልንን ቃሎች በመፃፍ በመፀለይና መንፈስ ቅዱስን በመጠየቅ የትኛውን የቃሉን ክፍል እንደምናነብ ምሪትን እንጠይቃለን፡፡ ደግሞም ጌታን ጥያቄዎችን እንጠይቅና የመፅሐፉ ቅዱስ ቃሎችን ለምሳሌ ውሸት፣ የሥጋ ምኞት፣ቅናት፣ ደስታ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ስናገኝ ይህም ያለንበትን ሁኔታ ወይም የእቅድን ተግባር ሊያሳየን ይችላል፡፡ በዚህም አሰራር ዕጣን አንድን ነገር ለመለየትም መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ለምሳሌ በምትሰሩት ሥራ ላይ ማን ተሳታፊ እንደሚሆን ማን ደግሞ ተሳታፊ እንደማይሆን ለማወቅ ስሞችን በቁራጭ ወረቀት በመፃፍና ዕጣውን በማውጣት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡*

*ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . .* "ይህንን መልዕክት ለማጠቃለል እርስበርስ ተያያዙ፣ ለፀሎት ከፍተኛ ሥፍራ ስጡት፡፡ ምክንያቱም ከፀሎት ውጪ በጨለማ ውስጥ ያሉ ቡድኖች ብቻ ትሆናላችሁ፡፡ በሰው ጥበብ ላይ አትደገፉ፡፡ በእኔ ላይ ብቻ ተደገፉ፡፡ ደግሞም መንፈሴ መመሪያ ይሰጣችኋል፡፡ ይህም በትልቅ ንፋስ ሳይሆን በለሰለሰ ትንሽ ድምፅ፣ ረጋ ባለ ግፊት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ይመራችኋል፡፡

"ይህንን አስታውሱ፡፡ ሰውነታችሁን ብታጡ ጊዜያዊና የብልጭታ ክስተት ስለሆነ የሚያሳስብ አይደለም፡፡ነገር ግን ወሳኝና ዘላለማዊ የሚሆነው የነፍሳችሁ ጉዳይ ነው፡፡ ከልጆቻችሁ ወይም ከወላጆቻችሁ ጋር እንደገና መገናኘታችሁ፣ የእናንተን እንስሳቶችና ምንም የማያውቁትን እንደገና ታገኙአቸው ይሆን የሚለው ነው፡፡ ዋናው ወሳኙ ነገር እኔ ለወደቁትና ለአመፀኞች መላዕክት ባዘጋጀሁት እሳት ውስጥ መጣል ወይስ ማርና ወተት ወደምታፈልቀው፣ የዘላለም ደስታ ተገባላችሁን ወደተገባላችሁ የተስፋ ምድር ለዘላለም መውረስ? ነገር ግን በፍፁም እንዳትሳሳቱ፡፡ በምድር የኖራችሁት ኑሮ ለዘላለም ከምትኖሩበት የዘለለም መኖሪያችሁ ጋር በምንም ነገር ሊወዳደር የሚችል አይደለም፡፡

"ምንም ነገር ቢሆን ፣ፍፁም ምንም ነገር ነፍሳችሁን ለዘላለም ገሃነም አሳልፋችሁ እንድትሰጡ የሚያደርግ ነገር ሊኖር አይገባም፡፡

## 3.10. ኢየሱስ ከንጥቀት በኋላ፡ የራዕይ መፅሐፍ ለምን መፈፀም እንዳለበት የተናገረው - ክፍል 11

እ.አ.አ. ማርች 16 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Speaks On: After the Rapture Part 11}

*የዩቲዩብ ቤተሰቦች ዛሬ ከጌታ ዘንድ የራዕይ መፅሐፍ ለምን ተፈፃሚነት ማግኘት እንዳለበት የሚገልፅ መልዕክት አለኝ፡፡ በጣም ከባድና ልብን የሚሰብር ነው፡፡*

*ከጌታ ጋር በነበረኝ የቆይታ ጊዜ በጣም ድንቅ የሆነ መዝሙር ባለማቋረጥ እየሰማሁና ከጌታዬ ጋር እየደነስኩ ነበር፡፡ ጌታ በጣም በቅርቤ በመገኘት ድንቅና ጣፋጭ ጊዜ ነበረኝ፡፡ ዛሬ ጌታ በሚገርም ሁኔታ በእርግጥ በአጠገቤ ተገኝቶ ነበር፡፡ መዝሙሩም "ኢየሱስ ቅዱሱ ኢየሱስ" የሚለው የቴሪ ማክልሞን መዝሙር ነው፡፡ የመዝሙሩም አዝማች ኢየሱስ፣ ኢየሱስ፣ ኢየሱስ፣ኢየሱስ፣ ኢየሱስ የኔ ጌታ የሚል ነው፡፡*

*ከጌታ ጋር እንዲህ እንድትቀጥሉ አበረታታችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም እርሱ ከሁላችሁም ጋር በዚህ ዓይነት መልኩ እንድትቀርቡት ነው የሚፈልገው፡፡ የኛም ቻናል ዓላማ ይኸው ነው፡፡ ከመጀመሪያው ጀምራችሁ የዚህን ቻናል ትምህርቶች ብትመለከቱ ከጌታ ጋር እንዴት እንደምንቀርብና ህብረት እንደምናደርግ የሚያስተምር ነው፡፡ በውስጣችን ከሚኖረው ጌታ ጋር የምናደርገው ፀሎት/Dwelling prayer/ ከጌታ ጋር በቅርበት የምንገናኝበት ፀሎት ነው፡፡ ለምን መሰላችሁ ይህ ለእያንዳንዳችሁ ያለኝ ከልቤ የመነጨ መሻት ነው፡፡ ሁላችሁም ከጌታ ጋር በቅርበት ተገናኝታችሁ በሰማይ እንዳለው እንዲሆን ነው፡፡ እስቲ በሰማይ እንዳለው እንደዛው በምድርም አሁን ይሁን!*

*ለማንኛውም ወደ መልዕክቱ ልመለስና ዛሬ ጌታ በእውነት ተገኝቶ ነበር፡፡ ከጥቂትም ጊዜ በኋላም ሙዚቃውን እንዳጠፋው ጠየቀኝ፡፡ ይህንን ሰሞን መቼም እንዴ ወደላይ አንዴ ወደታች የስሜት መዋዠቅ ውስጥ ነበረኩ፡፡ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ ንጥቀቱ እጅግ እጅግ ቅርብ እንደሆነ በማሰብ ነበር፡፡ እናም በድንገት ያንን ለንጥቀት የነበረኝን የመጣደፍ ስሜት አጣሁትና በቅርብ እንደማይሆን ተሰማኝ፡፡ ስለዚህም ነገሮች ሁሉ እንደነበሩ ሊቀጥሉ ነው የሚል ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆንኩ፡፡*

*ታውቃላችሁ ይህ እንግዳ ነገር ነው፡፡ ቶሎ እንደሚመጣ በመናገር እያሟሟቀን በዚያ ሁኔታ እንድንቀጥል ለማድረግ ይሆን እኔ አላውቅም፡፡ ከዚያ ደግሞ በዚያ ሁኔታ ትንሽ እንድንቆይ በማድረግ ነገሮች እስኪያድጉ ይጠብቃል፡፡ ወይም ደግሞ ንጥቀቱ እጅግ በጣም ቅርብ ስለሆነ በዚያ ሁኔታ እያሟሟቀና እያበረታታን ሊያቆየን እንደሆነ፡፡ እኔ በልቤ የሚሰማኝ ይህንን ዓይነት ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ለሁሉም መልስ የለኝም፡፡*

*ስለዚህም ዛሬ ማታ ጠየቁትና መለሰልኝ፡-*

*ኦ ጌታዬ ምንድነው ነገሩ? አንዳንድ ቀን ቶሎ እንደምትመጣ በከባዱ ይሰማኝና በማንኛውም ደቂቃ የምትመጣ ይመስለኛል፡፡ አንዳንድቀን ቀን ደግሞ የመምጣትህ ነገር ከውስጤ ይጠፋና ነገሮች እንደነበሩ የሚቀጥሉ ይመስለኛል፡፡*

"ይህ የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡"

*ነገር ግን እኔ አልወደድኩትም፡፡ መቼ እንደሆነ ያለማወቅ በጣም ያማል፡፡*

"ምን መስራት እንዳለብኝ ማወቁ ለእኔም ህመም ነው፡፡ የራዕይ መፅሐፍ እንዲፈፀም አልፈልግም፡፡ ነገር ግን እኔ መጥቼ በምድር ለመግዛት ደግሞ በግዴታ መጀመሪያ መፈፀም ያለበት መፈፀም አለበት፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም መፈፀሙ አስፈላጊ ቢሆንም መፈፀም ያለበት ግን የኔ ፈቃድ ሳይሆን የአባቴ ፈቃድ ነው፡፡

እንዲህም ቢሆን ግን ይህ ነገር መሆኑ በጣም በጥልቀት ያማል፡፡ነገር ግን የኔ ፍቅር ይህንን አንቺ እንድታዩው አልተፈቀደልሽም፡፡ አንቺ እንደሌላው አለም ይህንን በማየት ራስሽን መለወጥ አያስፈልግሽም፡፡ ሙሽሮቼ በእኔ ጎን ተሰባስበው መጥቼ እንድወስዳቸው የኔን መምጣት እየተጠባበቁ ነው፡፡ ነገር ግን ራዕዩ መፈፀም ያለበት ለማይበገሩት፣ በኩራት ለተሞሉት፣ ለዕብሪተኞች፣ በራሳቸው ለሚተማመኑና በራሳቸው ለረኩ፣ በተለያየ ምኞትና በከፍተኛ ፍላጎት አይናቸው ለታወሩ ነው፡፡ በእነዚህ ላይ ነው ራዕዩ መፈፀም ያለበት፡፡

*እዚህጋ ትንሽ ጊዜ ልውሰድና አንድ ነገር ልበል፡፡ እኔ በግማሽ ጎኔ ከልጆቼ ጋር ባለ ጉዳይ ያለብኝን የአለም ነገር ላጫውታችሁ፡፡ ከመጀመሪያው ባሌ የወለድኳቸውን ልጆቼን እኔ ሳልሆን ያሳደጋቸው አባታቸው ነው፡፡ ጋብቻችን የተቀደሰ ጋብቻ አልነበረም፡፡ ትዳራችን ለሁለታችንም ቀንበር የሆነብን ነበር፡፡ በቀድሞ ባለቤቴና በልጆቼ ላይ ምናልባት ከአንዱ በስተቀር ኑሮ እጅግ ከባድ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ አሰቃቂ የሚባሉ ነገሮችን ለምሳሌ በአንድ ህብረተሰብ የሚገኙትን ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት መግደል ለምን ይፈቅዳል ? ለሚለው ጥያቄያቸው ማስረዳት ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ ሰዎች ኃጢያት ለመስራት ሰበብ ይሆንላቸዋል፡፡ 'እግዚአብሔር ይህንን አድርጓል፣ ያንን አድርጓል ስለዚህም በእርሱ አላምንም ፡፡ እርሱ ፍቅር ቢሆን ኖሮ፣ መልካም ቢሆን ኖሮ እንደዚህ አያደርግም ነበር' ይላሉ፡፡*

*ይህንን ነገር ስንት ጊዜ እሰማ እንደነበረ ልነግራችሁ አልችልም፡፡ ስመልስላቸው የነበረው ታዲያ ዛሬ ማታ ጌታ የተናገረውን የሚመስል ዓይነት መልስ ነበር፡፡ እስካሁን ጌታ ጨካኝ የሚመስላችሁና ወይም ደግሞ እርሱ ምድርን የማይቆጣጠር የሚመስላችሁ፣ አዎ ምናልባት በአንድ ነገር ልክ ናችሁ፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር 'አይቆጣጠርም'፡፡ እርሱ የሚፈቅደውና የማይፈቅደው ነገር አለ፡፡ በዚህ በኩል ልክ ነው፡፡ ነገር ግን ሰይጣንና የሰው ፈቃድ ነው ነገሮች እንዲከናወኑ የሚያደርጉት፡፡ ቁልፉን ለመጫን ወይም ላለመጫን የሰው ፈቃድ ነው የሚሰራው፡፡ ቦንብ ለመስራት ወይም ላለመስራት እንኳን ፈቃድ የሰው ልጅ ነው፡፡*

*ጌታ በእኛ ነገር ጣልቃ ገብቶ ስንት ጊዜ ከአደጋ እንዳስመለጠን አውቃለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜም የሰውን ፈቃድ እንኳን በመጣስ ይህንን ያደርጋል፡፡ አሁን ግን የራዕይ መፅሐፍ ተፈፃሚ መሆን አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህም ጌታ ወደ ምድር መጥቶ መግዛት እንዲችል ነው፡፡ ዛሬ ስለዚህ ነገር ነው ትንሽ ሊነግረን የሚፈልገው፡፡*

*ስለዚህ እግዚአብሔር ጨካኝ ነው ለምትሉና የእርሱ አካሄድ ላልገባችሁ ለእናንተ ምናልባት ይህ መረዳትን ይፈጥርላችሁ ይሆናል፡፡ ጌታ እዚህጋ የሚለው ሙሽሮቹ የራዕይ መፅሐፍ ተፈጻሚ ሲሆን በማየት ትኩረታቸውን ለመሳብ አያስፈልገውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በእርሱ ዘንድ በመገኘት ለመታዘዝ ተዘጋጅተዋል፡፡ ነገር ግን ቀሪው አለም፣ አለምን የሚቆጣጠሩ፣ ገዢ ምሁሮች፣ የማይበገሩ፣ኩራት በውስጣችሁ የሞላና በራሳችሁ የሚተማመኑ የራስ ወዳድነትና ራሳቸውን አስተሳሰብ ውጤት ማየት አለባቸው፡፡ ከዚህም መቀጠል እችላለሁ፡፡*

*ዋው ጌታ በጣም ጠንካራ ሆነውብህ መሆን አለበት እነርሱን ለማሳመንና ለመቀየር ይህንን መንገድ የመረጥከው፡፡(ይህ የሚያወራው የመከራውን ዘመን ነው)፡፡*

ማንም ገዳይ የሆኑ እንስሳትን ከምድር በታች የሚያራባ፣ ወረርሽኝና ቸነፈርን በማምጣት አለምን ለመቆጣጠር የሚያስብ ሁሉ ጠንካራ የአመለካከት ማስተካከያ ያስፈልገዋል ! ይህም እኔ ካቀድኩት ያነሰ የትኛውም ነገር አይመልሰውም፡፡

"አባቴና እኔ የተለያዩ አማራጮችን በማውጣት በማውረድ የመጨረሻ ትንሽ ጥፋት  የሚያመጣውን የመረጥን አይመስላችሁም? ትንሽ የሚያስቆጣ? ትንሽ የሚጎዳ?"

*አዎ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ይህ የአንተ ተፈጥሮ ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመሆንህ ነገሮችን ማውጣት ማውረድ ባይጠበቅብህም . . .*

"አዎ እኛ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ተነጋግረንበታል፡፡ በእውነት ተነጋግረናል፡፡ ብዙ ነገሮችን በመውሰድ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡አንዱን እንኳን ወስደን ብናይ እኔ ከአስርታት ዓመታት በፊት ንፁህ የሆነ የቴክኖሎጂ ሰጥቻቸው ነበር፡፡ ነገር ግን እነሱ እኔ ከሰጠኋቸው ይልቅ የሚጣሉበትን ቴክኖሎጂ መረጡ፡፡"

"በእነሱ ውስጥ ያለው የግል ፍላጎት እጅግ የላቀ ነው፡፡ አይናቸው በፍፁም ስለታወረ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው የሚበጀውን መልካም ነገር እንኳን መለየት አይችሉም፡፡ በአለም ሁሉ ላይ የሚነሳው ችግር የኃይል አቅርቦት/ምንጭ/ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ነፃ ስጦታ የሆነውን የኃይል አቅርቦት ለመቀበል አልቻሉም፡፡ ነገር ግን እነሱ ያንን በመጨቆን የኃይሉን ምንጭ ለጦርነትና ለሰው ልጅ ጥፋት የሚውል የጦር መሳሪያ ግንባታ እንዲውል በማድረግ ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲውል የሰጠሁትን የኃይል ምንጭ አግደዋል፡፡ እንዴት የተጣመሙ እንደሆኑ ታያለሽ?"

*አዎ ጌታዬ ተረድቻለሁ፡፡ ነገር ግን ምንም የማያውቁ ንፁህ የሰው ልጆች መሰቃየታቸው የሚያሳፍር ነው፡፡*

"ነገር ግን የሰው ልጅ ሲባል ከላይ ጀምሮ እስከታች እስከዚህ ንፁህ የሚባል የለም፡፡ የወሲብ ድርጊቶችን ማየት፣ የባርያ ጉልበት፣የወሲብ ሽያጭ፣ ከድሆች ላይ ከዚያችው ካለቻቸው መስረቅ፣ እንዲሁም ድሆች እርስ በርሳቸው መሰራረቅ፡፡ ከታች እስከላይ ያለው ሁሉም አንድ ላይ የተበላሸና የሸተተ ነው፡፡ ራስን የመውደድ የሰው ተፈጥሮ ነው በእግዚአብሔር ሊጠበቅ የሚያስፈልገው፡፡ ሰው ሰውን ሊጠብቀው ወይም ሊቆጣጠረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሰው ለመበላሸት ቅርብ፣ ደካማና ለራሱ ጥቅም ሲል ትክክል ያልሆነን ነገር ለመስራት ቀድሞ የሚስማማ ነው፡፡

"አየሽ ወደዚህ ደረጃ ዝቅ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም እኔ ተመልሼ ሰው ለራሱ የፈጠረውን የተበላሸ፣ የተበከለ፣ ዝቅ ያለውን ሁሉ በማጥፋት ምድርን እንደገና መሙላት አለብኝ፡፡ አሁን ጊዜው ሩቅ አይደለም፣ የኔ ትንሽዬ እባክሽ ጠብቂኝ፡፡ ሩቅ አይደለም፣ጠብቂኝ፡፡ሩቅ አይሆንም፡፡

*ዛሬስ ማታ የእርሱን መምጣትና ከእርሱ ጋር መሆንን እጅግ ፈልጌያለሁ፡፡ ይህንን መቀበል አለብኝ፡፡ ስለዚህም በትንሽ መሰዋዬ ሥፍራ ሆኜ አነባሁ፡፡ ምክንያቱም እጅግ ስለናፈቀኝና ከእርሱ ጋር መሆን በጣም ስለምፈልግ ነው፡፡ ይህም አለም በጣም የተመሰቃቀለ ነው፡፡ ነገር ግን የመምጣቱ ነገር ሩቅ አለመሆኑን መናገሩ ትንሽ የሚያበረታታ ቃል ነው፡፡*

*ኦ፣ ኢየሱስ ለዘላለም ይመስላል፡፡ ደግሞም በየቀኑ እያረጀሁና በየቦታው እያቆጠቆጠ ባለው ብክለት የበለጠ ከተሳሳተ ሐሳቤ እየተመለስኩ ነው፡፡*

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ብርታት ሰጥቼሻለሁ፡፡ ስለዚህም እስካሁን ማለፍ እንደቻልሽው ሁሉ አሁንም እነዚህን ነገሮች ተቋቁመሽ ማለፍ ትችያለሽ፡፡ እንድትወድቂ ወይም ዝልፍልፍ እንድትዪ አልፈቅድም፡፡ የኔ ፍቅር ወደላይ አነሳሻለሁ፡፡ "

*ዛሬ ታዲያ ስለምንድነው መናገር የፈለከው ?"*

"የሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊነት ነው ለማውራት የምፈልገው፡፡"

"በሰውና በሰይጣንና የሚከናወኑ ድርጊቶች የኔንም ሥራዎች ወደ ፍፃሜ ያደርሳሉ፡፡"

*ይህ አግባብ አይደለም!*

"ያንን አውቃለሁ፣ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ብቻ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሊመጣ ያለው ነገር የእያንዳንዱ ሰው አስተዋፅዎ እንዳለበት ማየት አቅቷቸዋል፡፡ አንድ የመጠጥ ሱሰኛ ለእሱ መጠጣት ማንም ተጠያቂ መሆን ባይችልም እርሱ ግን ሁልጊዜ ምክንያቶችን እየፈጠረ ሌሎችን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሚከሰው ዓይነት ማለት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ወንጀለኛውን ከመጠቆም ይልቅ እኔን መውቀስ ይቀላል፡፡

*ጌታ እነሱ ሁልጊዜ የሚያነሱት ለእስራኤሎች ቃል የገባህላቸውን ምድር ስታወርሳቸው እስራኤሎች ወንዶችን ፣ ሴቶችንና ልጆችን ሁሉ እንዲገድሉ ያደረከውን ነው፡፡*

"አዎ ምክንያቱም አጋንንቶች ከሴቶቹ ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ አልነበሩም፣ ለአምላካቸው ለሞሎክ ወይም ለሰይጣን መስዋዕት ለማቅረብ ልጆች ኃይለኛ ለሆነ እሳት ሲሰጡ አልነበሩም፣ እነዚህ ትንንሽ ህፃናት ከህመሙ የተነሳ አምርረው ሲያለቅሱ አልነበሩም፡፡ የነበራቸው ሁሉ ለሰይጣን ስለት ሲሰጡ እነሱ በዛን ጊዜ አልነበሩም፡፡ ካንሰርን የሚመጣ፤ በመንፈሳዊ አሰራር የሚመጣ በሽታ በወንዶች በሴቶች፣ በህፃናትና በእንሰሳ ላይ ሲቀበር እነሱ አላዩም፡፡ ቢያንስ ህፃናቶቹ ከእኔ ጋር በሰማይ ናቸው፡፡ ቢያድጉ ኖሮ በእርግጠኝነት ሌሎች ምንም የማያውቁ ህፃናትን በማሰቃየትና በጭካኔ በመግደል በገሃነም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በተጣሉ ነበር፡፡"

"አለም የማያውቀውና የማያየው ብዙ ነገር አለ"

"ለሰዎች የሚቀለው ግን በሆነባቸው ነገር እግዚአብሔርን መውቀስና በለመዱት የኃጥያት የኑሮ ዘይቤ በመቀጠል ምርጫቸው ተገቢ እንደሆነ ለማሳመን እግዚአብሔርስ መቼ ትክክል ነው? ወይም እርሱን ሰምቶ መታዘዝ ዋጋ የለውም በማለት ምክንያት ያቀርባሉ፡፡"

" ሁሉም እንደዚህ ዓይነት አመለካከት የላቸውም ፡፡ አንዳንዶቹ በፅድቅ የሚኖሩና ነገር ግን በሃይማኖት ጦርነትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እኔን የሚወቅሱ ናቸው፡፡ ነገሩ በእውነት በማን እንደሚሰራ በትክክል ማየት አይችሉም፡፡

"ነገር ግን በእውነት የሚወዱኝ ያውቃሉ፡፡ እነሱ መልካም ይሁን ክፉ ለይተው ያውቃሉ፡፡ በሚገባ ያውቁኛል፣ በተወሰኑ ቡድኖች ላይ እንኳን ሰይፌን ብመዝ በእኔ ላይ እምነት አላቸው፣ እነዛ ሰዎች የአይምሮአቸው ዝንባሌ የገሃነም እንደሆነና ለሰይጣን እንደሚኖሩ፣ ደግሞም የሰይጣን የህይወት ዘይቤ እንደሚሰብኩ ያውቃሉ፡፡"

"በዚያን ጊዜ እንኳን እስራኤሎች የማያምኑትን የአኗኗር ዘይቤ ስለተከተሉና እንዲሁም እነዚህን ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ ስላስገቡ መውደቂያቸው ሆነ፡፡"

*(ክሌር) ከዚህ ጋር የሚሄድ አንድ ነገር ብናገር፡፡ በሰለሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ ብዙ ሚስጥራዊ የሆኑ ክፍሎች ተገኝተዋል፡፡ አስከፊ ነገር እየተካሄደ እንደነበርም ነቢያቶች ተናግረዋል፡፡ ይህም አስከፊ የሆነ አምልኮ በእነዚህ ሚስጥራዊ ክፍሎቹ ውስጥ ይካሄድ እንደነበረ ነው፡፡*

"መልካምንና ክፉን በአንድ ላይ ማስኬድ አይቻልም፡፡ አንዱ ሌላውን ይሰርዘዋል፡፡ ፈሪሳውያኖቹ አጭበርባሪዎች ሆነዋል፡፡ ምክንያቱም በገንዘብና በመግባባት ምክንያት ሰለሞንና ሌሎቹ በቤተ መቅደስ ውስጥ "አምላካቸውን" ያስከበረ ሚስጥራዊ የሆነ ክፍሎችን እንዲገነቡ ፈቅደዋል፡፡ ይህም ሰለሞን ባገባት በመጀመሪያ አረማዊ ሴት ምክንያት ለጥፋት ምክንያት ሆነ፡፡"

"አንድ የተበላሸ አፕል በርሜል ውስጥ ያለውን ሁሉ እንደሚያበላሸው ይህ ለእናንተ ትምህርት ይሁናችሁ፡፡ እንደ አንድ ሴት ውበትና ማፅናናት የመሰለ ነገር የለም፡፡ ይህም ታሪክን በብዙ መልኩ የቀረፀና ለብዙ ስልጣኔ ውድቀት የሆነ ነው፡፡"

"ስለዚህ በአለም ለሚገኘው ክፉ እኔን መውቀስ ካለማወቅና ከኩራት የተነሳ ነው፡፡ ሰው አያውቅም ወይም በራሱ ላይ ምን እያደረገ እንደሆነ እየገባው ነው ማለት ነው፡፡ በእርግጥም እቅዱም እንዲበላሽ አይፈልግም ወይም መስተካከል አይፈልግም፡፡ ስለዚህም ዘንጉን በተቃራኒው ይገፋል፡፡ ይኸውም የእርሱ የኃጢያት ህይወት ቀጣይነት እንዲኖረውና ትክክል እንደሆነ ለማሳመን እኔን ይወቅሳል፡፡ የኔ ፍቅር ለዚህ ነው በራዕይ መፅሐፍ የተነገሩ ትንቢቶች መፈፀም ያለባቸው፡፡ ሰው በራሱ ላይ ምን እንዳደረገና በመጨረሻም የት እንዳደረሰው ማየት አለበት፡፡"

"የማደርገው ነገር ሁሉ ከቁጣ አይደለም፡፡ ማለትም ሰው ቁጣዬን ያየዋል፡፡ ሰው እንደሚለው እኔ ይህንን የማደርገው ከበቀል የተነሳ ሳይሆን ለማስተማር ነው፡፡በሚያም መንገድ ማስተማር፡፡ ነገር ግን እራሳቸው ባዘጋጁት አልጋ ላይ መተኛት አለባቸው፡፡ በዚያ ሁኔታ እንኳን ከምህረቴ የተነሳ ጣልቃ ገብቼ ብዙ ነገሮችን ባልከለክልላቸው ብዙ ዘግናኝ የሆኑ ነገሮች ይከሰቱ ነበር፡፡ በሰማይ ስትሆኚ ብዙ ነገር ግልፅ ይሆንልሻል፡፡ በዛ ብዙ ነገር እየገባሽ ይሄዳል፡፡"

"ስለዚህም ወደፊት ምን ሊመጣ እንዳለ ብቻ ተረጂ፡፡ ይህ የኔ ምርጫ ሳይሆን የእነርሱ ምርጫ ነው፡፡ ይህ የኔ በቀል ሳይሆን የእነሱ የሥራ ውጤት ነው፡፡ የሚሆነው ሁሉ ሰውን ከመጥላት የተነሳ ሳይሆን ሰውን ከማፍቀር የመጣና ስሜቱን ቀስቅሶ ለመመለስ ነው፡፡ እኔ የማደርገው እያንዳንዱ ነገር ምንጩ ፍቅር እንጂ ከሌላ ከምንም የመነጨ አይደለም፡፡

"ወደ ገሃነም የሚገቡትን ነፍሳት እንኳን ቢሆን፡፡ እነሱ የፈለጉትና የመረጡት ነው፡፡ ነፃ ፈቃዳቸውን የምሰርዝ እኔ ማነኝ? እነዚህ ሰዎች በምንም ዓይነት መንግስተ ሰማይ ቢሆኑ አይደሰቱም ነበር፡፡ ይህንን ነፃ ፈቃድ ለሰው የሰጠሁት በራሱ ምርጫ እንዲያደርግ ነው፡፡ መልካምን ወይም ክፉን መምረጥ ይችላል፡፡ ከዚህ የበለጠ ምን ማድረግ እችላለሁ?"

*ምንም፣ ፍፁም ምንም ልታደርግ አትችልም፡፡ ሰዎች ኢይነሰውሮች ስለሆኑና ስለማያዩ የሚያሳዝን ነው፡፡ ችግራቸውን የፈጠርከው አንተ አይደለህም ፡፡ እነሱ በራሳቸውና በሰይጣንም እርዳታ ነው፡፡*

"ስለዚህ አሁን ዋነኛውና ወሳኝ ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህም አዲስ ምዕራፍ ሁሉም ነገር እንደገና ትክክል የሚሆንበት፣ ኩራትና ዕብሪት የሚጋለጥበት፣ ብክለት የሚወገድበትና ሰው መልካሙን ከክፉ መምረጥ የሚችልበት ሌላ ዕድል የሚፈጥርለት ነው፡፡" "እኔ እየመጣሁ ነው፡፡ ይህ ጊዜው ነው"

## 3.11. ከንጥቀት በኋላ የሚከሰት ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት

እ.አ.አ. ኤፕሪል 6 ቀን 2015 ዓ.ም

{The Great Revival after the Rapture}

*ዩ-ቲዩብ ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ፡፡ እዚህጋ ቀለል እናድርገውና ኢቃዬን አዘጋጅቼ አለሮጥኩም ስለዚህም አሁንም አለሁ፡፡ በዚህ ምሽት ጌታን እየሰማሁ እያለሁ ሳለሁ በልቤ ከንጥቀት በፊት ይሆናል የሚባለውን ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ጌታ ግን ለእኔ ከንጥቀት በፊት አይሆንም ያለኝን እያሰላሰልኩ ነበርኩ፡፡ ትክክል ባልሆንስ? ዩ-ቲዩብ ቤተሰቦችንስ አሳስቼያቸው ቢሆንስ? እያልኩ ሳስብ ነበር፡፡ በዚህም ሐሳብ ልቤ እጅግ ከብዶብኝ ነበር፡፡*

"ጌታም እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ፡- እንደፈራሽ አውቃለሁ፡፡ እንዴት እንደሚሰማሽም አውቃለሁ፡፡"

*ጌታ አዝናለሁ*

ለምኑ ነው የምታዝኚው? ምናልባት ስለ ታላቁ መንፈሳዊ መነቃቃት እኔ ያልተናገርኩሽ መስሎሽ ጥያቄ ፈጥሮብሽ ነው ያዘንሽው? የከበደው ልብሽን እስቲ ቀለል ላድርገው፡፡ እናንተ ከምድር ካልተነጠቃችሁ በስተቀር ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት የለም፡፡ ያን ጊዜ መቼም ሆኖ የማያውቅ መነቃቃት ይሆናል፡፡ እኔም መንፈሴን አፈሳለሁ፡፡

*"ያን ጊዜ ግን እኛን ከዚህ ስትወስደን መንፈስህን ከምድር ትወስድ የለም?"*

"ህዝቤ ታዲያ ካለ እርሱ እንዴት ሊለወጥ ይችላል? ስለ ኃጢያት እንደሚወቅስ አልተፃፈም? "

"እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው"(ዮሐንስ 16፡8-11)፡፡

*ታዲያ ቃልህ "ከመንገድ ይወሰዳል" ለምን ይላል? ብዙዎቹ ይህንን የመፅሐፍ ክፍል የሚተረጉሙት እንደዚህ ነው፡፡*

*በዚህ ጊዜ በጣም በሚደንቅ ሁኔታ መዝሙረ ዳዊት 85 ወደ እኔ አመጣ፡፡*

"<u>አቤቱ፥ ለምድርህ ሞገስን አደረግህ፥ የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ። የሕዝብህን ኃጢአት አስቀረህ፥ አበሳቸውንም ሁሉ ከደንህ። መዓትህንም ሁሉ አስወገድህ ከቍጣህ መቅሠፍት ተመለስህ። የመድኃኒታችን አምላክ ሆይ፥ መልሰን፥ ቍጣህንም ከእኛ መልስ። በውኑ ለዘላለም ትቈጣናለህን? ቍጣህንስ ለልጅ ልጅ ታስረዝማለህን? አቤቱ፥ ትመለሳለህ ታድነንማለህ ሕዝቡም በአንተ ደስ ይላቸዋል። አቤቱ፥ ምሕረትህን አሳየን፥ አቤቱ፥ መድኃኒትህንም ስጠን</u>።"(መዝሙር 85፡1-7)

*"ስለ መዳናቸው" የሚለው ውስጤን ነካው፡፡ ዋናው ነጥብ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢያታቸው ሲወቅሳቸው ነው ወደ መዳን የሚመጡት፡፡"*

"ስለዚህ አየሽ እርሱ በታላቁ መነቃቃት ጊዜ በዚህ በመገኘት ሥራ ላይ ነው፡፡"

*ጌታ ከንጥቀት በኋላ በህዝቡ ላይ የሚመጣውን መነቃቃት ታላቁ መነቃቃት ብሎታል፡፡*

"አየሽ የኔ ፍቅር መነቃቃት በእርግጥ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ሰዎች የሚሄዱበት መንገድ የሞት መንገድ መሆኑን እራሳቸው እንዲረዱ ካልተገደዱ በስተቀር መነቃቃቱ እጅግ ጠባብ ይሆናል፡፡ በተለይም የኔ ህዝብና የአንቺ ህዝብ ይህም በእናትሽ በኩል የተላለፈ የአይሁድ ደም ስላለብሽ ነው፡፡ በወቅቱ ስደት ስለነበረ አይሁድ መሆንሽ ተደብቆ እንጂ አይሁድ ነሽ፡፡"

*በእውነት?*

"አዎ፣ በእውነት፡፡"

"ይህንን እናገራለሁ ብዙዎች የአይሁድ ደም አለባቸው ነገር ግን አያውቁትም፡፡ እንደነገርኩሽ በደመና ስመጣ ሁሉ ሰው ያየኛል፡፡ ሁሉም ሰው ማለት ሁሉም ሰው ነው፡፡ አመጣጤ በድብቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ያልተቀበሉኝ ህዝቦቼ አይተው ስላልተቀበሉኝ ያለቅሳሉ፡፡ የምድር ነገድ ሁሉ ያዝናሉ አይልም?"

<u>"በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፡፡"</u> ማቴዎስ 24፡30

*"ጌታ ይህንን ብዙዎች የሚሉት ግን ስለ ዳግም ምፅአትህ እንደሚያወራ ነው፡፡"*

"በራዕይ መፅሐፍ ላይ ከተወሰነ ምዕራፍ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ያለመነሳቷ እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን በራዕይ 1፡6 ላይ ዮሐንስ ለቤተ ክርስቲያንን ሰላምታ አቅርቧል፡፡"

*<u>"መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን። እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ። አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።"</u> ራዕይ 1፡6-8*

"ይህ መፅሐፍ ደግሞ የተፃፈው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ነው፡፡"

"ይህንን ያደረግሁት ሆን ብዬ ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝቤ ማን እንደሆንኩ እንዲያውቁ ነው፡፡ ማን እንደሆንኩ ካላወቁማ እንዴት ንስሐ መግባት ይችላሉ? እኔን ከሰማይ ስመጣ ባዩ ጊዜ ግን ሳይቀበሉኝ በመቅረታቸው ምክንያት እስከ አጥንት መቅኒያቸው ድረስ ዘልቆ በሚገባ ፀፀት ይመታሉ፡፡"

*"ጌታዬ እኔ የማቴዎስ ወንጌልን ቅደም ተከተል ለማወቅ እንዴት እንደምቸገር ታውቃለህ"*

"የነገሮችን ቅደም ተከተል ግር እንደሚልሽ አውቃለሁ፡፡ ቤተ መቅደሱ እናንተ ከዚህ ሳትሄዱ አይሰራም፡፡"

"ስለዚህ አንተ የተናገርከው ቅደም ተከተሉን ሳይዝ ነው ማለት ነው? አንዱ በአንዱ ላይ እንደሚገነባ ግልፅ ይመስል ነበር፡፡ ነገር ግን ያ የሚሆነው ከንጥቀት በፊት ነው፡፡ ወይስ ያልገባኝ ነገር አለ፡፡

ክሌር በዚህ ላይ ተደላድለሽ እንድትቆሚ እፈልጋለሁ፡፡ በንጥቀት ጊዜ እታያለሁ፡፡ነገር ግን እግሬ ምድርን አይረግጥም፡፡ነገር ግን እታያለሁ፡፡ ህዝቤም ስላልተቀበሉን ያዝናሉ ያለቅሳሉ፡፡ አህዛብ ከእኔ ጋር ወደ ሰማይ ሲወሰዱ እነርሱ ግን በምድር ይተዋሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ገሃነም ተሰብሮ ሁሉም ወደ ምድር ይለቀቃሉ፡፡ ይህም ጊዜ የመከራው ዘመን ጅማሬ ይሆናል፡፡ይህንን ሳረጋግጥላችሁና ሰይጣን የከፋቱን አጀንዳ በምድር ላይ ለመፈፀምና የክርስቶስ ተቃዋሚውን በስልጣን ላይ ለማውጣት ምንም ጊዜ አያጠፋም፡፡

"ምድር እንደ ሰከረ ይዞርባታል፡፡ አክስለሬተሩ የሚያዛባው የመሬትን የዋልታ ማግኔቲክ አደረጃጀት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ፕላኖቶችን ጭምር በእርግጠነት ያቃውሳቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ኒብሩ የምትባለው ፕላኔትና የአስተሮይዶች ወደ መሬት መቅረብ ነገሩን ያባብሰዋል፡፡ሁሉም ገሃነምን ሰብረው ይወጣሉ አላልኩም? ይህ በአንድ ላይ የሚፈፀመው ሆን ተብሎ ነው፡፡ የምድር ፍርድ የሚፈፀመው በተፋፋመ ሁኔታ ነው፡፡"

"የምወዳቸውን ያህል አይሁዶች በምንም ዓይነት መልኩ ስግብግብነትንና ለጥቅም ሲሉ ሰውን ማምታት አላቆሙም፡፡ ስለዚህም በእነሱ ላይ የሚመጣው ፍርድ በሁለት እጥፍ ነው፡፡ የመጀመሪያው እኔን ስላልተቀበሉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በንግድ ስምምነት ወቅት እኔ ከእነርሱ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን በቸልተኝነት በመተዋቸው ምክንያት በአለም ፍጥረት ላይ ስለሚፈሰው ደም ሁሉ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተወቃሽ ናቸው፡፡ እጅግ ተወቃሽ ናቸው፡፡ ስለዚህም በፍርዱ ወቅት እዚህ የሚገኙት ሌላው ምክንያት ይህ ነው፡፡ ባዘጋጁት አልጋ ላይ መተኛት አለባቸው፡፡ እሺ አሁን ግልፅ ነው? "

*"እምም ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም እንደገና ማንበብ አለብኝ፡፡ ወዲያው እንደማይገባኝ ታውቃለህ፡፡*

"በትንሹም ቢሆን ይገባሻል የኔ ፍቅር"

ጌታ ስለ ንጥቀቱ ከማያሚ ሌላ ምንም ልዩ የሰጠኸኝ ምልክት የለም፡፡ ያ የአንተ ኃላፊነት ነው ብዬ ትቼዋለሁ፡፡

"ማያሚ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወይም የጦርን ወሬ ከመስማት አይለይም፡፡ ከእውቀት መጨመር የተነሳ የደረሰውን ጉዳት መቀበል እጅግ አዳጋችና ግራ የሚያጋባ፣ የሚያደናግርና ከምንጊዜውም የበለጠ የሚያስደነግጥ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት እኔ የምመጣው ማንም በማይጠብቀኝ ጊዜ ይሆናል፡፡ አየሽ ይመጣል በተባለው በሁሉም የጨረቃ ወቅት ወይም በፊስት ቀናት ይመጣል ተብዬ ስጠበቅ ነበር፡፡ በፊስት ቀን እንደማልመጣ ወዲያው ልትረዱ ይገባችኋል፡፡ ምክንያቱም እየጠበቃችሁን ስለሆነ ነው፡፡ በማልጠበቅ ቀን እንደምመጣ አይናገርም? ያ ለእናንተ ትንሽ ፍንጭ ሊሰጣችሁ ይገባል፡፡"

*እሺ ጥሩ ይህ ሰዎች የሚመጣበትን ጊዜ አውቀናል ብለው ከሚናገሩት ተቃራኒ ነው፡፡*

"አዝናለሁ"

*ኦ ጌታ አንተ በእውነት ሉአላዊ ነህ*

"አንዳንድ ነገሮችን በተቀጠረው ሰዓት ማድረጌ እርግጥ ነው ፡፡ ነገር ግን ይህ ንጥቀትን እንደማይጨምር ተናግሬያለሁ፡፡ ታዲያ ለምንድነው የተቀጠረውን የንጥቀትን ቀን ለማወቅ የምትፈልጉት?"

እምም. . . ምክንያቱም ይመስለኛል ስሜት ስለሚሰጥ?

"በትክክል፡፡ እኔ ደግሞ ይህ ስሜት የሚሰጥ መሆን እንደሌለበት አመልክቻለሁ፡፡ ስለዚህ ተዝናኑ፡፡ እኔ የምለውን ለመገመት መሞከራችሁን አቁሙ፡፡ ክሌር እኔ አስተማማኝ የሆነ ምልክቶችን ቀደም ብሎ ሰጥቼሻለሁ በዛ ላይ እረፊ፡፡ እባካሽ ግራ መጋባትን አትዝሪ፡፡ ከአመታት በፊት የሰጠሁሽን አጥብቀሽ ያዢ፡፡ በዚህም ላይ እረፊ፡፡ ከሁሉም ስሜት በሚሰጠው ላይ ግምት መስጠትሽን አቁሚ፡፡ ለዚህ ጉዳይ መልስ ለመስጠት ከዋክብትንና ጨረቃን በመጠቀም በምታደርጉት ሙከራ ሁላችሁም እራሳችሁን እያደከማችሁ ነው፡፡"

## 3.12. የሚመጣውን የመከራ ዘመን እንዴት ማለፍ እንደሚቻል

እ.ኢ.አ. ኖቬምበር 7 ቀን 2015 ዓ.ም

{Surviving the Coming Tribulation}

*በጌታ ውስጥ የምትኖሩ ውዶች! ጌታ ይባርካችሁ*

*ዛሬ ማታ ጌታ መልዕክቱን ለማተኮር የፈለገው ስለሚመጣው የመከራ ዘመን ነው፡፡*

"በየትኛውም ታሪክ ውስጥ ሆኖ የማያውቅ ወደፊትም ሊሆን የማይችል ወቅት ሊመጣ ነው፡፡ አሁን ምን ላደርግ ነው ብሎ ሰው ሁሉ የመጨረሻ ሊያስብ የሚችለውን ሐሳብ የሚያስብበት ነው፡፡ ለእነሱ ምንም ነገር ስሜት የማይሰጥና ሁሉም ነገር መላ ቅጡ የጠፋ ነው የሚሆንባቸው፡፡ ነገር ግን እኔ በዛን ጊዜ በምድር ለሚቀሩት አሁን እያዘጋጀኋቸው ነው፡፡"

"ኃብት ማካበት፣ በስልጣን ላይ መሆን ወይም በትልቅ የክብር ስፍራ መቀመጥ ምንም ዋጋ የለውም፡፡ ምክንያቱም በዛን ጊዜ ሁሉም ነገር ፍርስርሱ ስለሚወጣና የሚሆነው ነገር ሁሉ የሚታየው ለአዲሱ አለም አቀፍ ስርዓት ታዛዥ ከመሆናችሁ ላይ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ትልቅ ስልጣንን የሚፈልግ ማንኛውም ክርስቲያን ከንጥቀት በኋላ በንዴት ግድግዳውን ይመታል፡፡ በዚህም መደንገጥ አያስፈልግም የሚያስፈልገው ግንዛቤ መጨበጥ ብቻ ነው፡፡ በመከራው ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ገንዘብ ማካበት ሳይሆን ለመኖር ነው ገንዘብ ለማግኘት የሚያስፈልጋቸው፡፡ ይህንን ስናገር በአካል ለመኖር ብቻ ማለቴ አይደለም፡፡ ነገር ግን መኖር በመንፈሳዊ ህይወታቸው መኖርንም ያጠቃልላል፡፡ ለዚህም የመንፈሴን እንቅስቃሴ መረዳትና ንቁ መሆንን ይመለከታል፡፡"

"በመከራው ውስጥ ለሚያልፉት ጥበቃ የሚያገኙት ከመንፈሴ ብቻ ነው፡፡ በየትኛውም አይምሮ የሚደረግ እቅድ ለቤተሰብ ሰላምን አያመጣም፡፡ የኔ ችሎታና ጥበቃ ብቻ ነው በብቃት ሊያድናችሁ የሚችል፡፡ ለዚህም ምስክር የሚሆን ራቢ ራዲጅ ነው፡፡ በመከራው ዘመን ለማለፍ ወደኋላ የቀራችሁ የኔ ውዶች የትኛውም የጦር መሳሪያ ያድነናል ብላችሁ አታስቡ፡፡ በሙሉ ልባችሁ ወደ እኔ ተመልሳችሁ እኔን ለጥበቃ ጠይቁኝ፡፡ በእኔን ብቻ የምትደገፉ ከሆነ ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ ጥበቃ እጠብቃችኋለሁ፡፡ ሰይፍን የሚያነሱ ግን በሰይፍ ይጠፋሉ፡፡"

*እዚህጋ ጣልቃ ገብቼ "ሚሽን" የሚለውን ፊልም ያያችሁትን ሰዎች ላስታውሳችሁ ፈልግሁ፡፡ ፊልሙን ላላያችሁት ደግሞ ቆንጆ ፊልም እንደሆነ እነግራችኋለሁ፡፡ የመጨረሻው የፊልሙ ክፍል የሚያሳየው ቅጥረኛ ወታደሮቹ / the mercenaries/ የአገሪቱን ተወላጆች ሁሉ ለመግደል ወደ ጫካው ሲመጡ ነው፡፡ ከአገሪቱ ተወላጆች ውስጥ ሁለት ቡድኖች የተለያየ አመለካከት ነበራቸው፡፡ አንዱ ቡድን ጀስዊት ተብለው በሚታወቁት አንድ ሰው የሚመራ ቡድን ሲሆን ይህ ቡድን የሚፈልገው መዋጋት ነው፡፡ ሌላኛው ቡድን ደግሞ የሚፈልገው መፀለይ ነው፡፡ ታዲያ ልነግራችሁ የምፈልገው በመጨረሻው በውጊያ ብቻ ለማሸነፍ ከፈለጉት ቡድኖች ይልቅ የፀለዩት ጥሩ ውጤት እንዳገኙ ነው፡፡*

"ይህች አገር/አሜሪካ/ ከጠላት እጅ ለመታደግ የሚዋጉ ወንዶችና ሴቶች ወታደሮችን አዘጋጅቻለሁ፡፡ እነዚህም ወደ ተግባር በመግባት ከሚመጣው ስርዓት ምድሪቱን ለመንጠቅ የነቃ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡ የሚመጣው ጊዜ ክስተት ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ ያልታየ ሲሆን የኔም ጥበቃ በሰው ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ጠንካራው ጥበቃ ይሆናል፡፡"

"ይህም ቢሆን ግን መከተል ያለባችሁ የተወሰኑ ህጎች አሉ፡፡ ታማኝነት ከሁሉም የላቀና አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላው መቆጣጠር ያለባችሁ ለሌላው መጥፎ ምሳሌ ላለመሆን የራሳችሁን ኃጢያት ነው፡፡ ሰይጣን እጅግ ብልጥ ስለሆነ አንድን ነፍስ እንዴት አድርጎ ኃጢያት እንደሚያሰራው ያውቃል፡፡ ሌላው የኔን ጥበቃ ለማግኘት ከፍተኛ ነጥብ የሚያስጡት የበጎ አድራጎት ሥራ፣ ትህትናና ትዕግስት ናቸው፡፡"

"በኃጢያት በወደቃችሁ ጊዜ ምንም ጊዜ አታጥፉ ወዲያውኑ ወደእኔ ቅርቡ፡፡ በእውነት ንስሐ በመግባት ያንን ኃጢያት ተቃወሙት፡፡እኔም ወዲያውኑ እሸፍናችኋለሁ ጥበቃዬንም አጠናክራሉ፡፡ ያንንም ኃጢያት ደግማችሁ እንዳትሰሩት ፀጋዬን አሰጣችኋለሁ፡፡ በሌሎች ላይ እንዳትፈርዱ አስተምሬያችኋለሁ፡፡ የኔን ሽፋን ወዲያው የሚያሳጣችሁ ኃጢያቶች ኃሜት፣ አሉባልታ፣ ስም ማጥፋትና ወሬ ናቸው፡፡ ጠላት ይህንን በመካከላችሁ የሚፈጥረው ከፋፍሎ ለማሸንፍ ብቻ ሳይሆን ለጥቃት ተጋላጭ እንድትሆኑ መንገድን ይከፍታል፡፡ የበለጠ ቁልፍ ስፍራ እየተሰጣችሁ በሄደ ቁጥር የልባችሁም ዝንባሌ የተስተካከለ እንዲሆን መጣር አለባችሁ፡፡"

"የታመሙ ወይም የደከሙ ሰዎችን አታንኳሱ፡፡ የእነሱ ፀሎት አስፈላጊና እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡"

*ይህ በእኛም ተልዕኮ ውስጥ እውነት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሽማግሌዎችና የደካሞች ፀሎት የሚደንቅ ውጤት ሲያመጣ ተመልክተናል፡፡*

"ስሜቶቻችሁ የእናንተ የመጨረሻ ጠላቶቻችሁ ይሆናሉ፡፡ በቂ እንቅልፍ ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የምታሳልፉት የጭንቀት ጊዜ የማሰብ ችሎታችሁንና ጉልበታችሁን ያደክማል፡፡ ይህ የዕረፍት ጊዜ የመትረፍ ስልት ይሆንላችኋል፡፡ በተለይም መንፈሳዊ የመትረፍ ስልት፡፡ ፀሎትና የበጎ አድራጎት ተግባር የመትረፍ አጋጣሚያችሁን ይጨምራል፡፡ ፀሎት ግን ከሁሉም ኃይል ያለው አንደኛ መሳሪያችሁ ይሆናል፡፡"

"ጠላት እጅግ ተንኮለኛ ስለሆነ በስሜታችሁ ላይ የተለያዩ ጫናዎችን በመፍጠር አንዱ በአንዱ ላይ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡ ይህ ወንድሙን በሌላው ወንድሙ ላይ የሚያስነሳውን የጠላት ሙከራ ማክሸፍ የሚቻለው ቁጭ ብሎ ሁሉን ነገር በግልፅና በእውነት መነጋገር ነው፡፡"

*እዚህ ላይ ንስሐ ስለ መግባት አስፈላጊነት መጨመር እፈልጋለሁ፡፡አንድ ጊዜ የማን አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑን ካወቃችሁ፣ ትክክለኛ ምርጫ ያላደረገው፣ ወይም ትክክል ባልሆነ መንገድ የከሰሰው ሰው ንስሐ መግባትና ሌላኛውን ሰው ይቅርታ መጠየቅ አለበት፡፡*

"እጅግ በጣም የሚያስፈልገው ትዕግስትና ንዴትን ማሳለፍ ነው፡፡ ውድቀት ከበስተኋላው ሁልጊዜ ምክንያት አለው፡፡ እናም ይህንን ለመወጣት በጎ በማድረግና በወንድማማች ፍቅር ለማሳለፍ ለእናንተ የሚቀርብ የሁልጊዜ ፈተና ነው፡፡ "

"አስታውሱ አንዱ ሌላውን በፈረደበት ፍርድ ይፈረድበታል፡፡ ስለዚህ ይቅርታ እንዲደረግላችሁ ከፈለጋችሁ እናንተ መጀመሪያ ይቅርታ ማድረግ አለባችሁ፡፡ እራሳችሁን ከሌላው አስበልጣችሁ ታዩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህንን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፣ ይህ የእናንተ መውደቂያ ነው፡፡"

የተወደዳችሁ እርስ በርሳችሁ በከፍተኛ ደረጃ ለመከባበር እራሳችሁን ማስለመድ አለባችሁ፡፡ ምናልባት ሌላው በእናንተ ፊት የተነቀ መስሎ ሊታያችሁ ይችላል፡፡ እኔ ግን የማየው ልብን ነው፡፡ ስለዚህም በኔ ዕይታ ብዙ ፍቅር ያለው ነው የበላይ፡፡

እናንተ በብዙ ነገር ልትበልጡ ትችላላችሁ ነገር ግን በበጎ ተግባር ላ ካልተሰማራችሁ ይህ የሚዳርጋችሁ ለማያስፈልግ ኩራትና ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በውስጣቸው ቅን ለመሆን ፈቃደኛ ከመሆናቸው የተነሳ በጣም ጎበዝ፣ ብልህና ስኬታማ የሆኑ ሰዎች እንኳን ከእነርሱ በትልቅ ልዩነት ዝቅ ይላሉ፡፡

"አሁን የእናንተ ጉዳይ የአለም ጉዳይ ሳይሆን መንፈሳዊና መለኪያውም ሰማያዊ ሚዛን ነው፡፡ ስለዚህም በአለም ሲለካ ትክክክል ቢሆንም በሰማያዊ ልኬት ግን ተቀባይነት የለውም፡፡ የሪክ ጆይነር መፅሐፍ በጎ ተግባርና መንፈሳዊ ዕይታ ግንባር ቀደም እንደሆነ ገልፆታል፡፡ ይህንን አስታውሱ ማንኛችሁም ብትሆኑ ፍፁም የሆነ መፅሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ መረዳት የላችሁም፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለውህዱ /Mix/ የሚጨምረው ስጦታ አለው፡፡ ለዚህም የእናንተ ኃላፊነት የተሰጣችሁን ማወቅና ኮትኮት በማሳደግ ለውህዱ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህም እውነተኛው የቡድን ተግባራዊ ሙከራና እያንዳንዱ በልዩነቱ በማፍራት ለሌላው ማስተላለፍን ያመለክታል፡፡ በዚህም ስኬታችሁ ወይም ውድቀታችሁ የሚለካው ለደካማው ባደረጋችሁት ጥንቃቄ መጠን ነው፡፡"

"ስጋት ወይም ፍርሃት ባደረባችሁ በየትኛውም ጊዜ መሆን ያለበት የመጀመሪያው እርምጃች መፀለይ ነው፡፡ ፀሎት ነው የመጀመሪያ ምላሻችሁ መሆን ያለበት፡፡ በማንኛውም የጦርነት ወቅት እንደሚደረገው በእውነት በጣም አስፈላጊና ዋና ከሆነው ነገር የሰውን ትኩረት ለመስረቅ ብዙ ሐሰተኛ የወሬ ዘመቻዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ መረጃ ለማግኘት በእኔ ላይ ብቻ የምትተማመኑ ከሆነ በእንደዚህ ዓይነቱ ወጥመድ አትወድቁም፡፡"

"በተጨማሪም አማኞችን ጠራርጎ ለማውጣት የሚደረግ ሙከራ አለ፡፡ ስለዚህም ከእናንተ ጋር ህብረት እናደርጋለን የሚሉትን አትመኑ፡፡ ተልዕኳቸው ምን እንደምታደርጉ አጀንዳችሁን ለማወቅና ሪፖርት ለማድረግ ነው፡፡"

"በእናንተ ውስጥ እያንዳንዱ ልዩ የሆነ ዓላማ አለው፡፡ ስለዚህም በእያንዳንዱ ውስጥ ያለውን ልዩ ነገር በማወቅ አዳብሩት ደግሞም አክብሩት፡፡ ከመካከላችሁ አንድ ሰው ለማገልገል ቢፈልግ በምንም ዓይነት ሁኔታ አትከልክሉት፡፡ እነዚህን የሚሰሩት ስራ ስጧቸው እንጂ ስራፈት አታድርጓቸው፡፡ ይህ በኋላ በእናንተ ላይ መጥፎ ምላሽ ያስከትላል፡፡ ሰላምን በቡድኑ ውስጥ ለመጠበቅ የቡድኑ እያንዳንዱ አባል ተፈላጊ፣ ዋጋ ያለውና ጠቃሚ መሆኑ እንዲሰማው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም በቅንጅት ሲሰራ ሁሉም እርካታ ያገኛል፡፡ በቡድኑ ውስጥ የመከፋፈል አዝማሚያ ሲታይ የሚከፋፍል መንፈስን በመቃወም ፀልዩ፡፡ ይህ ሁልጊዜ ጠላት የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡"

*በዚህ ጉዳይ ላይ የምናገረው ነገር አለ፡፡ ቡድኑን ለመከፋፈል አብሮ የሚሰራ መንፈስ የውሸት መንፈስ፣ ሐታላይ መንፈስ፣ ያለመግባባትን የሚፈጥር መንፈስ፣ እንዲሁም ንግግርን የሚያጣምም መንፈስ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ በቡድን ውስጥ መከፋፈልን የሚያመጡ መናፍስቶች ናቸው፡፡*

"ይህ ጠላት ያለማቋረጥ የሚፈፅመው ተግባር ነው፡፡ ይህም ከፋፍሎ ማሸነፍ ወይም አንዱን ከውስጣቸው ለውድቀት ማስነሳትና ማሸነፍ በሚለው መርህ መሰረት ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ በወደቀ ጊዜ አግዙት፡፡ የወደቀውን ሰው ሞቅ ባለ ሁኔታ፣ ዋስትና በተላበሰ መልክና በሙሉ ይቅርታ አንሱት፡፡ በመናደድ ምላሽ መስጠት መናፍስቶችን ኃይል በመስጠት አለመስማማትንና እርካታ ማጣትን ያመጣል፡፡ ይህ ደግሞ በአንዳንዶች ልብ ውስጥ መከንከንን በመፍጠር ቆይቶ ከባድ አመፅንና መከፋፈልን የሚያመጣ ይሆናል፡፡"

"ምንም ነገር ቢሆን ጥሩ ነው ወይም ጥሩ ኢጋጣሚ ነው አትበሉ፡፡ የምታደርጉት ምንም ነገር ቢኖር መጀመሪያ ፀልዩና ከእኔ መልሱን አግኙ፡፡ የትሮጃኑን ፈረስ ታሪክ ሁልጊዜ አስታውሱ፡፡ በዘን ጊዜ ሁሉም የመሰላቸው ከጠላቶቻቸው በጣም የሚገርም ምርኮ ያገኙ መስሏቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በሳቡትና በውስጡ የመሸገው የጦር ኃይል ከውስጡ ወጥቶ ከተማውን ሲቆጣጠር ነው እውነቱ የተገለጠው፡፡"

"ሁሉም በአንድ ላይ ሲጠቃለል በዚህም አስቸጋሪ ወቅት ስኬት ይኖራል፡፡ ነገር ግን እንዲገባችሁ የምፈልገው ስኬትን የምለካው በህይወት መኖራችሁ ወይም በውጊያ ችሎታችሁ አይደለም፡፡ የከፍታ መለኪያዬ ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህም ለእኔ መሞት ማትረፍ ነው፡፡"

"ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ።ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።"(ማቴዎስ 10፡28-29)

# ክፍል አራት
# ስለ ንጥቀት ለካሮል ጄንጊስ የተሰጠ መልዕክት

Rapture Messages given to Carol Jennings

---

### 4.1.በክርስቶስ የሚገኘውን ህይወት ፈልጉ

እ.አ.አ. ሜይ 8 ቀን 2015

{Seek Life in Jesus}

*ካሮል፦ የኔ ኢየሱስ በዚህ ማለዳ ትናገረኛለህ ?*

"አዎ የኔ ፍቅር"

አሁን ይህንን ቃል እተውልሻለሁ፡፡ ኃበዝ ሁኚ ደግሞም እምነት ይኑርሽ፡፡ እኔ ሁልጊዜ ከአንቺ ጎን ሆኜ ነው የምጓዘው፡፡ ስለዚህ ዛሬ በኔ ጠንካራ ሁኚ፡፡ ዛሬ ወይም በማንኛውም በፊትሽ ባሉ ቀናቶች በምድር ላይ ስለሚሆነው ነገር አትፍሪ፡፡ ይህንን እንደማታውቂ አውቃለሁ፡፡ ይህ የሚፃፈው ወደፊት መጥተው ለሚያነቡት ሰዎች ነው፡፡"

"የኔ አገልጋይ የሆነችው ካሮል ትግሉን ለብዙ ዘመን በከባድ ሁኔታ ታግላለች ደግሞም በእኔ ድልን አግኝታለች፡፡ እናንተም እንደሷ እንድታደርጉ ከልብ ትመኛለች፡፡ እርሷ ከዚህ እስከትሄድ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን ለእሷ የምናገረውን በደንብ አድምጡ፡፡ ለእናንተ ብርታት፣ጥንካሬና ጥበብ የሚሰጣችሁ ማቴሪያል አለላችሁ፡፡ እርሷ በራሷ አይምሮ በጣም ትንሽ ናት፡፡ ነገር ግን በእርሷ የሚያልፈው የኔ ኃይል የሰው ልብን ለመንግስቱ ለመቀየር ኃይል አለው፡፡"

"ይህንን መፅሔት የምታነቡ ፈልጉኝ፡፡( እነዚህ ቃላቶች ከእኔ የግል መፅሔት ተወስደው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ እንዲካተቱ ተረድገው ነው)፡፡ ፈልጉኝ እናም እገኝላችኋለሁ፡፡ ለክሴር የሰጠዋትን ደብዳቤዎች አንብቡ፡፡ እነዚያ ደብዳቤዎች ለእናንተ የህይወት መመሪያዎችና የቅድስና መንገዶች ናቸው፡፡ የሰጠኋችሁን ቃሎች ተከተሏቸው፡፡ ትዕዛዛቶቹን ፈፅሟቸው፡፡ እኔ እነዚህን የሰጠኋችሁ በህይወት እንድትኖሩባቸው ነው!

"በዚህ ጊዜ የጠራኋችሁ ለመንግስቴ ነው፡፡ በእናንተም አማካኝነት ሌሎችን ብዙዎችን እደርሳለሁ፡፡ ለሌሎች ለብዙዎች ሲባል በዚህ ወቅት እንድትገኙና የእኔ ጥሪ እንዲደርሳችሁ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለዚህ የተመረጣችሁ ናችሁ፡፡"

"ኑ የኔ ጓደኞች ፣ ለእኔ ታማኝ ሁኑ፡፡ እናም የመንግስተ ሰማይን ቁልፍ እሰጣችኋለሁ፡፡ አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፡፡"

"ንጉሱ ኢየሱስ"

## 4.2. ሁሉን ነገር ለመተው አሁን ጊዜው ነው

እ.አ.አ. ሜይ 8 ቀን 2015 ዓ.ም
{It is Time to Let Go}

"በሚመጡት ቀናቶች ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ለእናንተ እጅግ አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት ነው፡፡ ይህም መቼ እንደምትበሉ፣የት እንደምትሄዱና እንዴት እንደምትኖሩ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ነገሮች እጅግ እየፈጠኑ ስለሚሄዱ ጊዜያቶችን እንደተለመደው መጠቀም አይቻልም፡፡ብዙ ነገሮችን ወደኋላ እየተዋችሁ ወደፊት ብቻ መሄድ አለባችሁ፡፡ ለእናንተ የሚጠቅም ወይም መያዝ ያለባችሁ የሚመስላችሁን ነገር ሁሉ እየተዋችሁ መሄድ ያለባችሁ ጊዜ ነው፡፡"

"አሁን ሁሉን ነገር ትታችሁ መሄድ ያለባችሁ ጊዜ ነው፡፡ አሁን ያላችሁ ኃብት ወይም ንብረት በምርጫ ወቅት ከህይወታችሁ ወይም ከቤተሰቦቻችሁ ህይወት ጋር ሲነፃፀር እጅግ ትንሽ ወይም ምንም ነው፡፡ ስለዚህም በማንኛውም ጊዜ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፣  ከአንዱ አገር ወደ ሌላ አገር ወይም ከአንዱ ከተማ ወደሚቀጥለው ከተማ ለመንቀሳቀስ የተዘጋጃችሁ እንድትሆኑ አሁን እያስጠነቀቅኋችሁ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በአስተሳሰባችሁ ብልጥ ሁኑ፣ ለእናንተና ከእናንተ ጋር ላሉት በህይወት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ብቻ አዘጋጁ፡፡ ይህም መፅሐፍ ቅዱስ፣ ጥቂት ቅያሪ ልብሶች፣ የሚጠጣ ውኃ፣ደረቅ ምግቦች ወይም የጣሳ ምግቦች እንዲሁም አንድ ወይም ሁለት ብርድ ልብሶችን አዘጋጁ በጀርባ በሚታዘል ሻንጣ በማዘጋጀት ደቂቃ ባልሞላው የማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ አንስታችሁ እንድትሄዱ በቅርባችሁ አስቀምጡ፡፡"

"በጥቂቱ የሚያስፈልጓችሁ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ለምሳሌ እንደ ኮፕዩተር/ከተቻለ/ ፣ ባትሪዎች፣ የባትሪ ድንጋዮችና ጥቂት ፍላሾች  ቅርብ በሆነ ቦታ በሚቀመጥ ሻንጣ ውስጥ አስቀምጧቸው፡፡ ለመጓዝ እራሳችሁን በሸክም ማስጨነቅ የለባችሁም፡፡ የምትይዟቸው ነገሮች ቀላል መሆን አለባቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ደግሞ ህይወታችሁን ቀላል ያደርጉላችኋል፡፡"

"በምድር ላይ በቅርቡ ሊከናወኑ ያሉ ክስተቶች እጅግ አስደንጋጭና ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ነው፡፡ በዛ ውስጥ ለማለፍና በጠላት ተይዞ ላለመገደል በእኔ ላይ ትልቅ እምነት መጣልን ይጠይቃል፡፡"

"የኔ ፍላጎት በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎች እንዲከተሉኝ፣ እንዲሰሙኝ፣እንዲታዘዙኝና በህይወት እንዲኖሩ ነው፡፡ በዚህም ወደ ሚሊንየሙ መንግስት ተሻግረው እኔ መልሼ አዲስና ንፁህ ባደረኩት ምድር ተዋልደውና ተባዝተው ምድርን እንዲሞሏት ነው፡፡"

"እርግጥ ነው በሰባቱ ዓመታት ውስጥ ብዙዎች ይሞታሉ፡፡ ነገር ግን ለእኔ ታማኞችና በፍጥነት የምትታዘዙ ከሆነ ከእነሱ መካከል አትሆኑም፡፡ እኔ እጠብቃችኋለሁ፣ ደግሞም በራሴ ጊዜና ቦታ እመራችኋለሁ፡፡ እኔ እረዳችኋለሁ፡፡ ነገር ግን እናንተ ደግሞ ሁል ጊዜ እኔን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች መሆን አለባችሁ፡፡ እናንተን ለመርዳት እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ መላዕክቶቼም በዙሪያችሁ ይሆናሉ፡፡ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ጥያቄ ሲገጥማችሁ፣ ከፈራችሁ፣ ግራ ከተጋባችሁ እኔ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡"

"በዚህ ጊዜ ቅዱሱን መንፈሴን በጆሯችሁ በግልፅ መስማት ግዴታ ነው የሚሆነው፡፡ ለነፍሳችሁ መዳን እንደጠየቃችሁን ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ጠይቁኝ፡፡ እነዚህም በመንፈስ ቅዱስ እሳት መጠመቅ፣ በመንፈስ ለመፀለይ የልሳን ስጦታ፣ የፈውስ ፀጋ፣ እንዲሁም የእወቀትና የትንቢት ስጦታዎች ናቸው፡፡"

"በዚህ ወቅት ላይ ሆናችሁ ስለ ኢንተርኔት አታስቡ፡፡ በደንብ መጠበቅ ያለብኝን እጠብቃለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን በዚህ ደረጃ ኢንተርኔት ብታጡም እኔ እራሴ ላስተምራችሁና እነዚህን ስጦታዎች ላካፍላችሁ በአጠገባችሁ እሆናለሁ፡፡"

"የተወደዳችሁ ይህንን ከልባችሁ ውሰዱት፡፡ እምነት ይኑራችሁ፡፡ በቅርብ ጊዜ የሰማይ አባት ይህንን አለም ታይቶ በማይታወቅ አይነት በፍርድ ትርምስምስ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን ለእናንተ ቀድሞ የተዘረጋ እንከን የለሽ እቅድ አለኝ "

"ዛሬ ምሽት በእምነትና  እኔን በማመን በረከት እየባረኳችሁ በፍቅር እሰናበታችኋለሁ፡፡

"የእናንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡"

## 4.3. ኢየሱስን ተከተሉ እንጂ የአውሬውን ምልክት አትቀበሉ!

እ.አ.አ ሜይ 9 ቀን 2015 ዓ.ም

{Follow JESUS – Do not take the mark of the beast!}

ካሮል፡- ጌታ እውደሃለሁ፡፡ አሁን በጣም እየቀረብን መምጣታችንን ባሰብኩ ቁጥር አይምሮዬ ባዶ እየሆነና እያዞረኝ ነው፡፡ ታውቃለህ ስንጠብቅ በጣም ብዙ ጊዜ ነው፡፡ ህይወቴን ሙሉ ስጠብቅ ነበር! እንዲህም ሆኖ ወደ ኋላ መለስ ብዬ አመታቶቼን ስቃኛቸው እንደ ጥቂት ደቂቃዎች ነው የምቆጥራቸው፡፡

"ዋናው ነጥብ ይህ ነው፡፡ ፍቅር ዛሬ ምሽት በአይምሮሽ ላይ ያስቀመጥኩት ሐሳብ ይህንን ነው፡፡ ህይወት እጅግ አጭር ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ዘላለም በጣም በጣም በጣም ረዥም ነው፡፡ በዚህ ምድር ወደኋላ ለሚቀሩት ግልፅ ሊሆንላቸው የሚገባው ዋናው ሐሳብ ይህ ነው፡፡ የቀረው ህይወት የመጨረሻውንና አስፈላጊውን ውሳኔ የምትወስኑበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም በሚመጡት ቀናቶች እኔን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የምትወስኑበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

"መንግስት፣ ጓደኞቻችሁ፣ አለቆቻችሁ፣ ቤተሰቦቻችሁ ወይም ሌላ ማንም ሰው ምንም ይበል ምን ሊያሳምናችሁ ቢሞክር በፊታችሁ ያለው ምርጫ ሁለትና ሁለት ብቻ ነው፡፡ እኔን ወይም ሰይጣንን መምረጥ፡፡"

"ከእኔ ጋር ህይወት መቆሚያ የሌለው ነው፡፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም በክብርና በህይወት መኖር፣ እንዲሁም ልትገምቱት ከምትችሉት በላይ ንፁህ ፍቅር የሚገኝበት ህይወት ነው፡፡"

"ከሰይጣን የምታገኙት ግን ህመም፣ ሞት፣ መከራ፣ የማያልቅ ስቃይና በእሳት ውስጥ መጣል ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሞት በሥጋ መሞት ሲሆን ሁለተኛው ሞት ደግሞ በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ ከፈጠርኳችሁ፣ እስትንፋስ ለነፍሳችሁ ከሰጠኋችሁና እናንተ ሊገባችሁ ከሚችለው በላይ ከምወዳችሁ ከእኔ መለየታችሁ ነው፡፡"*(ይህም ሁለተኛ ሞት ለዘላለም ወደ እሳት ባህር መጣል ነው)*

"ዛሬ ማታ ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ፡፡ የቱን ትመርጣላችሁ? የነፍሳችሁን ጠላት የሆነውንና አለምን ሁሉ በሚችለው ዘዴና ውሸት በመጠቀም እናንተንና የሰውን ዘር ለመስረቅ፣ ለመግደልና ለማጥፋት የተዘጋጀውን? እናንተን ሊያሳምናችሁ በፈጠረው ደስታን በሚመስል ጊዚያው እርካታ የዘላለምን ህይወት መሸጥ ዋጋ ያለው ነገር አይደለም፡፡"

"ይህ ከያዕቆብና ከኤሳው ታሪክ ጋር አንድ ነው፡፡ ባርኮትንና ኃብትን በጥቂት ሥጋዊ ደስታ ለመለወጥ አንዴ ውሳኔ ከወሰኑ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ ያጡትን ማግኘት የማይቻል ነው፡፡"

ዛሬ ምሽት እነግራችኋለሁ፣ የአውሬውን ምልክት ተጠንቀቁ፡፡

"ሰው በነገሩ ይስቃል፣ መንግስት ስለነገሩ ይዋሻል፡፡ እኔ ግን እውነቱን እነግራችኋለሁ፡፡ ከተቀበላችሁት የዘረ መለመልን /DNA/ በመቀየር የሰይጣን ልጅ እንድትሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ነፃ ለማውጣትና ለማዳን የሚቻልበት መንገድ የለም፡፡ ልጆቼ ብልህ ሁኑ፡፡ አሁን በጣም ብልህ ሁኑ፡፡ እኔን ስሙኝ፡፡ እንድረዳችሁና በፊታችሁ የመጡባችሁን ቀናቶች እንድታመልጡ ድምፄን ስሙ፡፡ ድምፄን በመስማት ብቻ ነው በህይወት የምትኖሩት፡፡ድምፄን በመስማት ብቻ ነው ሰይጣን ያቀደባችሁን ሞት የምታመልጡት፡፡ምንም እንኳን ጊዜው ከባድና የስቃይ ጊዜ ቢሆንም የሚቆው ግን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አድናችኋለሁ፡፡ እዛው ከእናንተ አጠገብ እሆናለሁ፡፡ መጀመሪያ ለደህንነት እኔን ጥሩኝ /ንስሐ ገብታችሁ ነፍሳችሁ እንዲድን/ ፡፡ ከዚም ጠላት እንዳይገድላችሁና የመከራውን ዘመን በህይወት እንድትኖሩ እኔን ጥሩኝ፡፡"

የሚወዳችሁ አባታችሁ፣ አባ ኢየሱስ፡፡

## 4.4. የቀረው እጅግ ጥቂት ጊዜ ስለሆነ ወደእኔ ኑ

እ.አ.አ. ሜይ 11 ቀን 2015 ዓ.ም.
{There is very little time – Come to Me}

"ዛሬ በዚህ ማለዳ በተለመደው አጠራራ ጓንደኞቻችን ብለን ለምንጠራቸው የማስተላልፈው መልዕክት አለኝ፡፡ የምናገረውም ስለ ጊዜ ነው፡፡ ስጊዜ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ብሎ ተናግረንበታል፡፡ ነገር ግን ስለ ጊዜ ስናነሳ ብዙ ገፅታዎች አሉት፡፡ ዛሬ ግን የማነሳው የጊዜ ገፅታ ነፍሳችሁ የሚመለከት የጊዜ ሁኔታ ይመለከታል፡፡"

"አሁን የቀራችሁን ቀሪ ጊዜ መቁጠር ያለባችሁ ከእኔ በቀጥታ ለእናንተ የተሰጠ እጅግ ውድ ዕቃ ነገር ግን ለትንሽ ጊዜ ብልጭ ብሎ የሚጠፋ አድርጋችሁ ነው፡፡ ይህ የተሰጣችሁም ጊዜ እናንተ እንደፈለጋችሁ ልትጠቀሙበት፣ ለመደሰቻ ጊዜ ወይም ደግሞ ሸቀጦችን ከገበያ ቦታዎች ያለአግባብ እንድታግበሰብሱበት አይደለም፡፡ ይህ ያለፈ ታሪካችሁ መሆን አለበት፡፡ አሁን ሁላችሁንም የምላችሁ ሙሽሮቼ ወደቤታቸው ከመምጣታቸው በፊት ቅድስናን እና ፅድቅን ጨምሩ እንዳልኳቸው አሁን ደግሞ እናንተን ለዛ ህይወት እጠራችኋለሁ፡፡"

"እኔን በህወታችሁ ላይ በመሽም ታዘዙኝ፡፡ እንዲሁም በመፀሐፍ ቅዱስ ላይ ያስቀመጥኩላችሁን እውነት ታዘዙ፡፡ በምድር ላይ ለመጨራሻ ጊዜ ያመጣሁትን የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት አይታችኋል፡፡ እናንተ ለዛ ምስክሮች ናችሁ፡፡ በዛ ወቅት የተላለፈውንና ከውስጡ ለውጪ አገራት እንኳን ሳይቀር የተሰራጨውን ይህንን ትምህርት ሳትቀበሉ እንዳትቀሩ፡፡ የሰማችሁትን የእውነትንና የመዳንን ቃል በቀላሉ አትመልከቱት፡፡ እነዚህ የሰማችኋቸው ቃሎችና እውነቶች ህይወታችሁን ከአደጋ ለመታደግ ወሳኝ ናቸው፡፡"

"ይህ አሁን ያላችሁበት ወቅት ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሲቆጠር ለሰባት ዓመታት ብቻ የሚቆይ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ምናልባት ይህንን ፅሑፍ ያገኛችሁት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከሆነ ነው፡፡ ይህንን መልዕክት ስታገኙ ለህይወታችሁ ትልቅና እጅግ አስፈላጊ ነገር አግኝታችኋል፡፡ ምናልባት ይህንን ስታገኙ ይህም ወዲያው ከንጥቀት በኋላ መሆኑ ነው እኔን ለመስማት የመጀመሪያዎቹ ዕድለኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ምናልባትም በምድር የቀሩትንና የኔ የሆኑትን ለመሰብሰብ በሚደረገው የመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በመንፈሴ ከምትሞሉት መካከል የመጀመሪያዎቹ ከሆናችሁ በእርግጥም የተባረካችሁ ናችሁ፡፡ "

"ነገር ግን ይህንን እውነት እነግራችኋለሁ፡፡ ይህንን መልዕክት የምታገኙት የቅጣቱ ዘመን ከጀመረ 1ኛ ወይም 2ኛ ወይም 3ኛ ዓመት ካለፈ በኋላ ከሆነ ይህንን የሰማችሁትን ቃል ለመቀበል ወቅቱ ነው፡፡ አሁን እኔን ለመፈለግና በእኔ ለመገኘት ጊዜው ነው፡፡ ምክንያቱም እዚህ ደረጃ ከደረሳችሁ በኋላ ጊዜ ማጥፋት ውሳኔ ለመስጠት ጊዜው እያለፈባችሁ ነው፡፡

"በሰባተኛው ዓመት አጋማሽ ላይ በህይወታችሁ ላይ እንደገና ሌላ መነዋወጥ ይሆናል፡፡ ይህም ነውጥ በሚታየው አለም ላይ ብቻ ሳይሆን በማይታየውም አለም ትልቅ መናወጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የክፉ ኃይላት በከባድ ሁኔታ ለጦርነት ይሰለፋሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ በምንም አይነት መልኩ ቢሆን የተለመደውን ዓይነት ህይወት መኖር እጅግ የማይቻልበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆነው እስካሁን ድረስ ለገዢው አባማና ከበታቹ ለሚያስተዳድሩት ክፉዎች ካልተንበረከካችሁ ነው፡፡"

"አዎን ለእናንተ የክርስቶስ ተቃዋሚው ማን እንደሆነ እየጠቆምኳችሁ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ (ከ3 1/2 ዓመት በኋላ ማለት ነው) ይህ ሰው ለመቃወም ለሚሞክሩት ሁሉ እንዴት የከፉዎች ተምሳሌት እንደሆነ ሳታውቁ አልቀራችሁም፡፡ በሚቃወሙት ላይ ብዙ ሞትን፣ ብዙ ጥፋትን፣ ብዙ በሽታዎችንና ጉዳቶችን በማምጣት በብዙ ሚሊዮኖች ላይ ከባድ ጥፋትን አድርሷል፡፡ ብዙዎችም እርሱን በመቃወም ህይወታቸው አልፏል፡፡"

"ይህንን መልእክቴን ያገኛችሁት ካሮልና ከሌር ከሚባሉ አገልጋዮቼ ሲሆን እነርሱም እኔ መጥቼ ወደ መንግስተ ሰማይ ከእኔ ጋር እንዲኖሩ ከመውሰዴ በፊት ይህንን መልዕክት በአለም ላይ ተበትነው ያሰራጩ ከነበሩት ከብዙዎቹ መካከል ናቸው፡፡ ነገር ግን እናንተ የመጨረሻችሁን ውሳኔ ለማስተላለፍ የቀራችሁ በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፡፡ እናንተን በዛ ጊዜ ጠላት ሁሉ ነገር ደህና እንደሆነ እንዲያሳምናችሁ በመፍቀድ ከእውነተኛ ሰዎች እውነቱን እንዳትረዱ ወደ ጎን ዞር ብላችሁ ነበር፡፡"

"አሁን ግን እነግራችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ውሸትና የነፍሳችሁ አጥፊ ሴራ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ይህንን ውሸት መቀበል የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም ጊዜው በጥድፊያ እያመለጣችሁ ነው፡፡ የኔ የሆኑትን ህዝብ በአስተማማኝ ሥፍራዎች ፣በህይወት እንዲኖሩ አሰባስቤ፣ በጤንነትና በምግብ አበልፅጌና የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ አድርጌ በአለም ዙሪያ ሁሉ በየቦታው አስቀምጫለሁ፡፡ አሁን አጄን ያዙና ወደ እነርሱ እንድመራችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ ልባችሁን በሙሉ ለእኔ አሳልፋችሁ ስጡኝና ወደ እነርሱ ልምራችሁ፡፡ በመራኋችሁም በዛ ቦታ አስከፊውን ጊዜ በሰላም፣ በእውነትና አይታችሁ በማታውቁት ወይም እጅግ በረሳችሁት በእውነተኛ ፍቅር ትጨርሱት ይሆናል፡፡ "

"ልጆቼ አሁን የእናንተ ጠላት ጊዜ ነው፡፡ አሁን ይህ ለእናንተ በደንብ ላይገባችሁ ይችላል፡፡ ነገር ግን ወደፊት ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባችኋል፡፡ አሁን በዚህ መልዕክት ላይ የተፃፈውን የእኔ ቃል ብቻ ተቀበሉኝ፡፡ እንደዚህ ግልፅ የሆነ ብዙ የማስጠንቀቂያ መልእክቶች አታገኙም፡፡ አሁን እንኳን በነፍሳችሁና በመንፈሳችሁ ላይ እነዚህ ቃሎች እውነትና ታማኝ እንደሆኑ እንድታምኑ እየሰራሁ ነው ምክንያቱም እነዚህ ቃሎች የተነገሩት በእውነተኛውና በታማኙ ነው፡፡ "

"እባካችሁ ወደ ልባችሁ አስገቡኝና ላግኛችሁ፣ ላድናችሁና ደህንነታችሁና መዳናችሁ አስተማማኝ ወደሆነው ወደ በረሃ ተሸከሜ ልውሰዳችሁ፡፡ ምክንያቱም በመንግስቴ ከእኔ ጋር እንድትገናኙ ልቤ እጅግ ይናፍቃል፡፡"

"ኑ! የኔ ውድ ጓደኞች ኑ! እናንተን እየጠበኩ ነው፣ ኑ!

ኢየሱስ - ክርስቶስ፡፡ ለነፍሳችሁ መዳን በመስቀል ላይ የሞተው፣ አሁንም በማያልቀው ፍቅሩ ወደእኔ እንድትመጡ እየጠበኳችሁ ነው፡፡

## 4.5. ለእናንተ ያለኝ ፍቅር እጅግ ትልቅ ነው

ሜይ 12 ቀን 2015 ዓ.ም

{How great is My Love for you}

"የተወደዳችሁ ዛሬ ማለዳ ለመናገር የምፈልገው ስለ ፍቅር ነው፡፡"

"ስለ እኔ ፍቅር"

"አ! የኛ ውድ ጓደኞች በካርሎስ መፅሔት ላይ የተላለፈውን እስካሁን ስታነቡ ነበር፡፡ እርግጠኛ ነኝ እስካሁን ለእኔ ያላትን ፍቅር በመፅሔቷ በሁሉም ስፍራ በፃፈችው ፅሑፍ በማየት ተረድታችኋል፡፡ ይህንን ፍቅር ልዩ ሆኖ አግኝታችሁታል? የእርሷ ፍቅር እንዴት ጥልቅና ጠንካራ እንደሆነ በትንሹ እንኳን ብልጭ ብሎ ታይቷችኋል? በከፍተኛ ደረጃ እንኳን ከእርሱ ጋር ብትጓዝ በደበዘዘ ሁኔታ እንጂ ማየት ያልቻለችውን፣ እንዲሁም በጣም በጥቂቱ ቆንጠር አድርጋ ያገኘችውን አምላክ ማፍቀሯ ለምን እንደሆነ ገብታችኋል? በዚህ ምድር ላይ የኖረችው ለ61 ዓመታት ሲሆን ስለ እኔ የተረዳችውና እንደምወዳት ያወቀችው ለ58 ዓመታት ነው፡፡ ተገረማችሁ? ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?" እናንተ እንደምታስቡት የማይታየውን፣ እጅግ በርቀት የሚገኘውን መውደድ ?

አ! የኔ ውድ፣ ውድ ጓደኞች ይህንን እወቁ፡፡ ከመወለዳችሁ በፊት፣ አለምን እንደምታዩት አድርጌ ከመፍጠሬ በፊት፣ እናንተ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ እንደ ጭላንጭል የተቀመጣችሁ ፍጥረት ነበራችሁ፡፡ እግዚአብሔር አብ ፀነሳችሁ - እናንተን፣ አይምሯችሁን፣ ልባችሁን፣ ነፍሳችሁን፣ ሰውነታችሁን፣ ሁለንተናችሁን፣ መንገዳችሁን ሁሉ፡፡ እንዲሁም እንደዚህ ባለ ጊዜ እንድትወለዱ ተደርጋችሁ፡፡ እናንተ በአጋጣሚ በተደረገ ወሲባዊ ግንኙነት ወደዚህ አለም የመጣችሁ አይደላችሁም፣ በፍፁም፡፡

"ስለ እናንተ እያንዳንዱን የወሰነው እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ ይህም የት አገር ፣ ከየትኛው ቤተሰብ፣መቼ እንደምትወለዱ ሁሉ በእርሱ የተወሰነ ነው፡፡ የት መማር እንዳለባችሁ ትዕዛዝን የሰጠሁ፣ አብራችሁ የተጫወታችሁትንና የተደባደባችሁትን ሁሉ የወሰነው፣ ጥሩ የምትሉት ወይም የማትሉት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያለውን እያንዳንዱን የህይወታችሁን ታሪክ የወሰነው እርሱ ነው፡፡"

"ኃጢያት ብዙ ሙከራዎችን፣ ፈተናዎችንና ከባድ ነገሮችን ወደ ህይወታችሁ ይዞ መጣ፡፡ ከእነዚህም አብዛኛዎቹ ምናልባት የመጡት በጠላታችሁ በሰይጣን ነው፡፡ ከተወለዳችሁ ጀምሮ ስለ እኔ መጥፎ እንድታስቡ ያደረገው እርሱ ነው፡፡ እኔ ግን እዛው ከእናንተ ጋር ነበርኩ፡፡ ከዛች ጊዜ ጀምሮ መላዕክቶቼ እየጠበቋችሁ ነበር፡፡"

"እናንተ ብቻዬን ነኝ ብላችሁ ባሰባችሁት ወቅት፣ ህይወት እጅግ ከብዷችሁ ከዚያ በኋላ መቀጠል የማትችሉ በመሰላችሁ ጊዜና ከዚያ የበለጠ ከባድ ነገር ሊመጣ እንደማይችል በመገመታችሁ ጊዜ ሁሉ ወደ እኔ እየሳብኳችሁ፣ በነፍሳችሁ ውስጥ ፍቅሬን እያፈሰስኩና እኔን ቀና ብላችሁ ተመልክታችሁ የኔን ልብና የኔን መንገድ እንድትመለከቱ በመፈለግ ከእናንተ ጋር ነበርኩ፡፡ "

"ቆንጆ ቢራቢሮ ባያችሁ ቁጥር፣ ወይም ህፃን ድመት አይታችሁ በህይወታችሁ ደስታን ስታመጣ እኔ ነኝ ይህንን ሁሉ ወደ እናንተ የላኩላችሁ፡፡ እውነተኛ የፍቅር ቃል ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከህፃቶቻችሁ ወይም ከወንድሞቻችሁ፣ ከአስተማሪዎቻችሁ፣ ወይም ከጓደኞቻችሁ የሰማችሁት እነሱ አወቁትም አላወቁትም እኔ ነበርኩ በእነርሱ ውስጥ አልፌ ስናገራችሁ የነበረው፡፡ እጄን ይዛችሁ እንድትከተሉኝ በመፈለግ፡፡ አያችሁ? እኔ በመልካሙም በመጥፎውም ነገር ሁሉ አብሬያችሁ ነበርኩ፡፡

'ታዲያ ይህንን ያህል ከወደደኝ ለምን ይህ ወይም ያ ነገር ደረሰብኝ' ለምን ይህ ያ ሆነ? "በማለት ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ 'ደግሞስ ፍቅር ሲል ምን ማለቱ ነው? እስቲ በአካባቢያችንን ያለውን ተመልከቱ' እስቲ አሁን ያለሁበትን እንኳን ተመልከቱ ??? ልትሉ ትችላላችሁ፡፡' አዎ እነዚህ ነገሮች ሊገቡን አይችሉም፡፡ ነገር ግን እስቲ እራሳችሁን ለደቂቃ ያህል ከዚህ ውስጥ አውጡ፣ ንዴታችሁንና መራራነታችሁን ወደ ጎን አድርጉና ለጥቂት ጊዜ ከእኔ ጋር በመሆን ስለ ምክንያት እንነጋገር፡፡

“ለመሆኑ አንድ አፕል የሚበቅለው አጠገቡ ካሉት ዛፎች በተመሳሳይ ሁኔታ ነውን? በእያንዳንዱ ላይ የተበላሸና ያልተበላሸ ፍሬ አይኖረውምን?ፍሬዎቹ አጠገብ ለአጠገብ ተንጠልጥለው እያሉ አንዱ የሚያብረቀርቅ ቀይ ሌላው ደግሞ ደብዘዝ ያለና በትንሹ የሚምር አይሆንምን? እንዲሁም አንዱ ፍሬ በነፍሳት ተወግቶ እዛው በዛፉ ላይ እያለ መበስበስ ይጀምር የለምን? ሌላውስ ደግሞ ተቀጥፎ በመበላት ደስታን ይሰጥ የለምን? ቀጥፎ ለወሰደው ደስታን ይሰጥ የለምን? ሌላው ደግሞ እዛው በዛፉ ላይ በመቆየት ሲበስል መሬት ወድቆ በእግር ይረገጥ የለምን?

“እወነቱን ልንገራችሁ እነዚህ ሁሉ እኔ የፈጠርኳቸው ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው እኔ ማን እንደሆንኩ ክብሬን፣ ግርማዊነቴንና በመፍጠር ኃይሌ ለምድር የሰጠሁትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለሌሎች ፍጥረታቶቼ ግድ እንደሚለኝ ሁሉ ለእነዚህም ግድ ይለኛል፡፡

"ሁለት አዲስ የተወለዱ ቡችሎችን እንውሰድ፡፡ አንዱ ቡችላ አሰልጥነው በቤት ውስጥ ክብካቤ ወደሚያደርጉለትና ደስተኛ ህይወት ወደሚሰጡት ቤት ተወሰደ፡፡ አንዱ ደግሞ ልቡ ክፉና ጨለምተኛ ወደሆነ ቤት፣ ሁልጊዜ ወደሚመታው፣ ወደ ሚያሰቃየውና መጨረሻም ወደ ገደለው ሰው ቤት ተወስደ፡፡ ሁለቱም የተወደዱ አይደሉምን? ሁለቱስ የኔ ፍጥረታት አይደሉምን? ሁለቱስ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አይደሉምን? በመጨረሻስ መላዕክቶቼን ልኬ እኔ ወዳለሁበት አቅፈው እንዲያመጡትና በደስታ እንዲኖር አላደርግምን?

"አሃ! አያችሁ ሰዎች አይኖቼ ድንቢጦችን እንኳን እንደሚያይና አንዷ እንኳን እኔ ሳላውቅ እንደማትወድቅ ስነግራቸው አያምኑኝም፡፡ ደግሞም እያንዳንዱ በፍጥረቴ ውስጥ ያለ ነገር እንዴት የልቤ ክፍል እንደሆነ አይገባቸውም፡፡

"አሁን ምናልባት ታሾፉብኝ ይሆናል፡፡ ካሮል እንኳን በዚህ ጊዜ ተነስታ ማሰብ ጀመረች፡፡ ስለዚህም አሁን እየተናገርኩት ያለ ሐሳብ በእውነት ከእኔ የወጡ ቃሎች ወይስ ከእርሷ የመነጩ እንደሆኑ ጠየቀችኝ፡፡ ነገር ግን ምን እንዲገባችሁ እየሞከርኩ እንዳለ ልብ ብላችሁ አድምጡኝ፡፡"

*ጌታ መናገር እችላለሁ?*

"አዎ ትችያለሽ"

ስለ አፐሉ ፍሬ ሲያስረዳ ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝም ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ እውነት ይህንን ነገር እተናገረኝ ያለው ኢየሱስ ነው በማለት እየተደነቅሁ ነበር፡፡ እርሱ መሆኑን ሳረጋግጥ ግን የተናገረው እንዲገባኝ ትንሽ አይምሮዬን ከፈተልኝ፡፡ እኔ ራሴ ሰዓሊ ስለሆንኩ በእያንዳንዱ የስዕል ፈጠራዬ ውስጥ የኔ የሆነ ነገር ይኖራል፡፡ እናም በእነዚህ ስዕሎቼ ውስጥ የእናትነት ስሜት አለበት፡፡ ሳላውቀውም እነዚህ የስዕል ፈጠራዎቼ ሁሉ ይህ እንዲሰማቸው እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህ የገባኝ ነገር የምናያቸው ነገሮች ሁሉ የእርሱ "ድንቅ የፈጠራ ሥራዎች"ናቸው፡፡ በዚህም መንገድ እርሱ የእያንዳንዱ ክፍል ነው፡፡ ይህም አንድ በአንድ በአይናችን በአለም የምናየው አንድም ሳይቀር አፐልን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ ይህ በደንብ እንዲገባን ትላንትና ማታ ጌታ ስለ ሰማያዊ ቤታችን ለክሌር የነገራትን እጠቅሳለሁ፡፡

"ፍቅር የሰራውን ለውጥ ታያላችሁ፡፡ አንበሳና ኢጋዘን ጎን ለጎን ተኝተው በመተቃቀፍ አብረው ያንቀላፋሉ፡፡ ኦተሮች በውኃ ላይ በመንሳፈፍና ቆንጆ የሆኑ ሼሎችን በእግራችሁ ሥር በመጣል እንድታሻሿቸው ይጋብዟችኋል፡፡ ንቦች የልብ ቅርፅን በመፍጠር ወደላይ እየበረሩ ማራቸውን እንድትካፈሉ ይጋብዟችኋል፡፡

"በስራችሁ የሚገኘው አሸዋ እናንተ እንዲመቻችሁ ለማድረግ በመስተካከል ቅርፁን ይቀይራል፡፡ ገደላማ ሸለቆው እግር መርገጫና እጅ መያዣ ስላለው በቀላሉ ለመውጣትና ለመውረድ ያመቻል፡፡ ወደላይም ስትወጡ በጣም የሚያስደስት በእምነበረድና በክርስታል ያጌጡ ትንንሽ ዋሻ የሚመስሉ ታገኛላችሁ፡፡ ንስር አሞራ ወደ ጎጇቸው ገባታችሁ ጫጩታቸውን እንድትዳስሱ ይጋብዟችኋል፡፡ የዛፍ ቅጠሎች በአጠገባችሁ ስታልፉ በደስታ ይዘላሉ፡፡ በላዩ ላይ ስትሄዱ ሳሩም በፍቅር እየኮረኮራችሁ፣ ቅርፅ ባለው መልክ እያነፀባረቀ ሰላምታ ይሰጣችኋል፡፡

"ኦ! በመንግስተ ሰማይ የሚገኙ ድንቅ ነገሮች ማለቂያ የላቸውም፡፡ ይህ ሁሉ ለእናንተ የተቀመጠ ነው፡፡ ምክንያቱም እናንተ በምድር የኖራችሁት ለእኔ ነው፡፡ ስለዚህም አሁን በዘላለሙ መኖሪያችን መገመት በማትችሉት ነገሮች ነገር ግን በምድር ሲመስጣችሁ በነበረው ነገር አስደስታችኋለሁ፡፡

*እዚህ ላይ ጌታ የነገረን ነገር አሸዋው፣ ዛፎቹና ሳሩ ሳይቀር ለእርሱ ፍቅር ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ ለእኛ ነው፡፡ እኛ እንዲገባንና በውስጡ እንድንጠቃለል ነው፡፡*

"አመሰግናለሁ የኔ ፍቅር፡፡ በደንብ አድርገሽ ነው የገለፅሽው፡፡

"ጓደኞቼ ምንም የማይታሰበውን አፐልን እንኳን ቦታ ሰጭቼው በእኔ ንድፍ የተሰራና ክብሬን የሚገልጥ ከሆነ፣ እንዲሁም አጠገባችሁ የሚገኘውን ውሻ ክብካቤ የማደርግለት ከሆነ ስለ እናንተስ ምን ያህል ግድ የሚለኝ ይመስላችኋል? ለእናንተስ ያለን ፍቅር ምን ያህል የበለጠ ይመስላችኋል?

"አ! የተወደዳችሁ ውድ ጓደኞቼ! ስለእያንዳንዳችሁ በልቤ ያለው ፍቅር ልትገምቱት ከምትችሉት በላይና የሰው ልጅ ከሚረዳው በላይ ነው፡፡ እናንተ እኮ ከፈጠርኳቸው ፍጥረታት ከፍተኛውን ደረጃ የያዛችሁ ፍጥረታቶቼ ናችሁ፡፡ አዳምን ከምድር አፈር ከማበጀቴና ህይወቴን በእርሱ ውስጥ እፍ ከማለቴ በፊት በአይምሮዬ ውስጥ የተፀነሳችሁ ናችሁ፡፡
አያችሁ? አሁን እንኳን ምን ያህል ነፍሳችሁ ወደ እኔና ወደ መንግስቴ መጥታ ከእኔ ጋር ለዘላለም እንድትኖሩ እንደምጓጓ ትንሽ ገባችሁ?

" እንድታስቡበት እለምናችኋለሁ፡፡ አለም በአሁን ሰዓት ምን ያህል ውበት እንዳላት ዙሪያችሁን ተመልከቱ፡፡ ውልብ የሚል ማብለጭለጭ ይታይባታል፡፡ ከአሁን ጀምሮ ትንሿን ትንኝ፣ ቢራቢሮና እያንዳንዱን እንሰሳት ተመልከቱ፡፡ እንዲሁም ገና በማደግ ላይ ያለውን እያንዳንዱን ዕፅዋት በማየት አስተውሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የእኔን ማንነት የሚገልፁና ለእናንተ የፈጠርኩት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

" የዚህ ሁሉ ፈጣሪ የሆንኩት እኔ እወዳችኋለሁ፡፡

"ጓደኞቼ ወደ እኔ ኑ! አለም ለእናንተ እጅግ አስቀያሚ፣ ሸካራና አደገኛ ናት፡፡ ነገር ግን እንዲህም ቢሆን ለሚያስፈልጋችሁ ነገር፣ ለመፅናናትና ለእርዳታ ብላችሁ ወደ ጠላት እቅፍ ውስጥ እንዳትገቡ፡፡ እውነቱን ልንገራችሁ እዛ የምታገኙት በሽታ፣ሞት፣ ጥላቻና ጥፋት ብቻ ነው፡፡

"ጓደኞቼ ወደ እኔ ኑ፡፡ እኔ በክብር የተሞላ፣ መሰረታዊና ድንቅ የሆነ ህይወት አሰጣችኋለሁ፡፡

ወደ እኔ ኑ ጓደኞቼ! ወደእኔ ኑ!

የሁሉም ምንጭ የሆነው !!

## 4.6. አሁን ምረጡ ገንዘብንና በራስ መተማመን ወይስ እኔን

እ.አ.አ. ሜይ 12 ቀን 2015 ዓ.ም

{Money, Self -Reliance or ME. You Must Decide}

*ጌታ ዛሬ ምሽት ለጓደኞቻችን መልዕክት አለህ?*

"አዎ አለን መፃፍ ጀምሪ፡፡"

"የዛሬው ምሽት ርዕሳችን ገንዘብ የሚል ነው፡፡"

"አሁን ያላችሁ ብር ብዙ ቢሆን ትንሽ በመከራው ጊዜ ገንዘብ በፍጥነት ነው ያለፈ ታሪክ የሚሆነው፡፡ አንድ ደረጃ ላይ ስትደርሱ ውሳኔ ልታስተላልፉ ግድ ይሆናል፡፡ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚውን የኦባማንና የአስተዳደሩን ምልክት ለመብላት፣ ለመትረፍና ለመኖር ልወሰድ? በሚለው ላይ ይሆናል፡፡ "

"ወይስ ሌላ ጥሩ አማራጨን?"

"ከእነዚህ ሁለት አማራጮች አንዱን መምረጥ ምን እንደሚያስከትል እንመልከት፡፡ የአለም ኢኮኖሚ ሲወድቅ፣ ሁሉም የገንዘብ መዋቅሮች ሲፈራርሱ፣ በአለም ላይ ያሉ ሳንቲሞች፣ የገንዘብ ምንዛሬዎች ሲተረማመሱ፣ ምልክቱን መወስድ ተገቢ የሚመስልበት፣ ትልቅ ነገር ማይመስልበት፣ እንዳውም አርቆ ማሰብና ብልህነት የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ደግሞም እስካሁንም ሲሰራበት የነበረና ሐሳቡ አዲስ ያልሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ትንሽ የኮምፒዩተር ቺፕ እጃችሁ ወይም ግንባራችሁ ላይ ብታደርጉ ምናለበት? በቃ ይኸው ነው፡፡ ነገሩን አታካብዱ፣ የምትፈልጉትን ገዝታችሁ እጃችሁን ጅህን በማወዛወዝ ክፍያውን መፈፀም ብቻ ነው በቃ ሌላ ጣጣ የለውም የሚባልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ አጋንንት በሰዎች ውስጥ አንዴ ከተደበቁና የወደቁ መላዕክቶች ከመጡ፣ ያን ጊዜ ለበላይ አለቆቻቸው የመታዘዝ ግዴታ ይመጣል፡፡ ስለዚህም አነዚህ ሰዎች እነሱ ትክክል ሌሎቹ ሰዎች ግን የተሳሳቱ አድርገው በአይምሯቸው እንዲቀበሉ በዚህም ውሸትን እውነት እውነትን ውሸት አድርገው እንዲቀበሉ ይደረጋሉ፡፡"

"ነገሩ በዚያም አለ በዚህ፣ በምንም መልኩ ተቀነባብሮ ይቅረብ የመጨረሻው ውጤት እኔን መከተል ወይም ሰይጣንን መከተል ነው፡፡"

ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት ቺፑን በሰውነታችሁ ውስጥ ማስገባት የወደፊት ህይወታችሁ ላይ የማይፈታ ማህተም ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ነው፡፡ ቺፑ የአጋንንት "ዘር" አለበት፡፡ አንዴ በሰውነታችሁ ውስጥ ከተቀበረ ሌላ ዘረ መለመል /DNA/ ወደ ደማችሁ ውስጥ ይልካል፡፡ ይህም ዘረ መለመልን /DNA/ ለዘለቄታው በማጥፋት በድሮው ዘመን ኔፍሊም የሚባሉትን /ዘፍጥረት 6፡1/ ዘረመለመል እንዲኖራችሁ ያደርጋል፡፡ ይህም ከሆነ ወዲያ ወደ ነበረበት እንደገና መመለስ አይቻልም፡፡ ደግሞም ይቅር አይባልም፡፡

"ለዚህ ነው አሁን ከመርፈዱ በፊት ወደ እኔ እንድትመለሱና ህይወታችሁን ለእኔ አሳልፋችሁ እንድትሰጡ የምጮኸው፡፡ በቺፑ ትንሽ ድርቆሽ ገዝታችሁ ለጥቂት ቀናት ከምትቆዩ ይልቅ ራሳችሁን ለሞት አሳልፋችሁ በመስጠት ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ ብትገናኙና ለዘላለም ብትኖሩ ይሻለችኋል፡፡ በወቅቱ ስልጣን የሚይዙት እንደሆነ ብትኖሩ ወይም ብትሞቱ ትንሽም ግድ የላቸውም፡፡ በዚያም ቢሆን በዚያ መሞታችሁ እንደሆነ የማይቀር ነው፡፡"

"እነሱ ሁሉንም ነገር የሚያደርጉት አንድ ግባቸውን ወይም አንድ ፍላጎታቸውን ለመፈፀም ብቻ ነው፡፡ ይህም የሰውን ልጅ ሁሉ በመስረቅ፣ በመዝረፍ፣ በመግደልና በማጥፋት ሁሉንም በቋሚነት የገሃነም ዜጎች ማድረግ ነው፡፡ የፈለገውን ያህል ታማኝነታችሁን ለእነርሱ ብትገልፁ የእናንተ ህይወት ለእነሱ ምንም ዋጋ የለውም፡፡"

"በሌላው አንፃሩ ግን የእናንተ ህይወት ለእኔ ከሁሉ ነገር እጅግ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ወደ ምድር የመጣሁት ለእናንተ ብዬ ነው፡፡ በመስቀል ላይ ህይወቴን የሰጠሁት ትንሹን እርምጃ እንድትራመዱ ነው፡፡ "

# ክፍል አምስት
# ከጌታ ተጨማሪ ትምህርቶች

{More Lessons from the LORD}

---

## 5.1. ሰርን /CERN/ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ የለም"

እ.አ.አ. ኤፕሪል 5 ቀን 2015 ዓ.ም

{I AM GOD Alone, There Is Non Other}

"እኔ ትልቅና መጥፎ ንጉሥ ሆኜ በመገኘቴ ፍርድ የሚፈረድባችሁ አይደለም፡፡ ነገሩ እንደዚህ አይደለም ፡፡ እኔ ለትሁቱ ትሁት ፣ ለተሰባሪው በሁሉ ነገር የለሰለስኩ ፣ ለሚፈራው እጆቼን ዘርግቼ የማቅፍ ነኝ፡፡ ነገር ግን ለሚናደዱና ለከፉዎች ኃይለኛና ተከላካይ፤ አታላዮችን በራሳቸው ወጥመድ የማጠምድና ለጠማሞች የብረት በትሬን የማወዛውዝ ነኝ፡፡"

"በዚህም ዓይነት መልክ ሙሽራዬን በመጠበቅ ለእያንዳንዱ የሚገባውን ተገቢ ዋጋ እሰጣለሁ፡፡ ይህ ትውልድ ወደ ንስሐ እንዲመጣ ብዙ ለፍቻለሁ፣ ደግሞም ብዙ ጠብቄያለሁ፡፡ በዚህ ሰዓት እንኳን የፍጥረቴን የፍጥረቴን አወቃቀርና ባህርይ / the science of My Creation/ እንዲረዱት ለእነርሱ አቅርቤያለሁ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን አልበገር ካለው እምነት ማጣታቸውና የተመራማሪውን ህብረተሰብ ሙያዊ ፍላጎት ለማርካት፣ እንዲሁም ስሜን ቢያውጁ ተከትሎት የሚመጣውን መሳቂያና መሳለቂያ መሆንን ባለመፈለግ ትተውታል፡፡"

"ከዚህም የተነሳ በዚህ ወሳኝ በሆነ ታሪካዊ ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡ እናም እየተቋቋምኩ የለሁት እራሳቸውን እግዚአብሔር አድርገው ከቆጠሩ ጋር ነው፡፡ ሰይጣን በዙፋኑ ላይ ለመሆን እንደተመኘ ያህል፣ እነርሱም ከእኔ በልጠው ለመገኘት፣ ይህ ባይሆን እንኳን በትንሹ ከእኔ እኩል ለመሆን ተመኝተዋል፡፡ "

"ታዲያ ፍጥረት የተገነባበትን ብሎኬት መጫዋቻ ያደረገውን ይህንን ጠማማ ትውልድ ምን ልበል? ቀጥሉ! የፈጠርኩትን ሁሉ እስክታጠፉ ድረስ ሙከራችሁን ቀጥሉ ልበል? የለም ይህ አይሆንም፡፡ ጥፋቱን ወደራሳቸው እመልሳለሁ፡፡ ለእነሱም እንደዚህ እላለሁ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ የለም፡፡" እስትንፋሳችሁን መልሼ መውሰድና ወደ አፈር መመለስ አልችልምን? የለም ይህ በእነሱ ላይ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም እነሱ ለአለም እግዚአብሔር እንደሆኑ ለማሳት ባላቸው ትልቅ መሻት የተነሳ ታውረዋልና ነው፡፡"

"በሌላ ሳይሆን በሰይጣን በራሱ የተነሳሳ ይህንን ውስት ውስጡን በተንኮል የሚንቀሳቀስ ባህርይ ልታገስ አልችልም፡፡ የቆሙበትን የሚያጠፉትን እንደዚህ ዓይነቶቹን ለማስቆም እቀጣለሁ ደግሞም እገስፃለሁ፡፡ እኔ የሚሾፍብኝ ሰው አይደለሁም፡፡ ደግሞም እነርሱ እንዲሚያመልኩት ጣዖት የማልሰማ፣ የማላይና የማልናገር አይደለሁም፡፡ እንዲህ አይደለም፡፡ እነርሱ ወደዱም ጠሉም አመኑም፣ አላመኑም እኔ ፈጣሪያቸው ነኝ፡፡ ለማድረግ እየሞከሩ ያሉት ነገር ውጤቱ አለም ከተፈጠረች ጀምሮ አይታ የማይታውቀውን ጥፋት በምድር ላይ የሚያመጣን ነገር ነው፡፡ እያንዳንዱ ለራሱ ወዳዘጋጀው ጥልቅ መኖሪያ ይሮጣል፣ ነገር ግን እንዲሁ በከንቱ ይሮጣል፡፡ ውኃው ካሉበት እየጎተተ ያወጣቸዋል፣ የትም ማምለጥ አይችሉም፡፡"

## 5.2. ሁሉ ነገር እንደነበረ የሚቀጥል ይመስላል

እ. አ.አ. ኤፕሪል 7 ቀን 2016 ዓ.ም

{Everything seems business as usual}

እንደምን አደራችሁ! ከጌታ ዘንድ የሚያበረታታ ዓይነት መልዕክት አለኝ፡፡ በቅዳሜና እሁድ መነጠቅ ይሆናል ብለን በማሰብ ብዙ ነገር ካደረግና በኋላ ጌታ ያሰበንው ሐሳብ ትክክል እንዳልሆነ እንዲህ በማለት እርምት ሰጠን፡፡ ይህ ነገር እናንተ ባሰባችሁት ጊዜ የሚሆን አይደለም፡፡ ዛሬ ደግሞ እንዲህ እያልኩ ሳስብ ነበር፡፡ የሚገርም ነው! በዛ በውጪ ነገሩ ሁሉ እንደነበረ ቀጥሏል፡፡ፀሐያማ ቀን፣ ዛፎች እንቡጥ ማብቀል ጀምረዋል፣ ብዙ አጋጣሚዎች እየመጡ ነው፡፡ ስለዚህም ህይወት ቀጥሏል፡፡ እናም እንዲህ በማለት አሰብኩ፣ ጌታ ትንሽ ተጨማሪ ጊዜ አይኖረንም? ወይንስ ትንሽ አብደናል? ለመነጠቅ የፈለጉ እብድ ክርስቲያኖች? ወይም ሌላ፡፡ ጌታ ትንሽ ተጨማሪ ጊዜ ይኖረናል? እናም በዛን ጊዜ ህይወታቸውን ላልቀየሩና ወደ ጌታ ላልመጡ ነፍሳት፣ ለክርስቲያኖች ነፍስ እንኳን እውነተኛ ሸክም ተሰማኝ፡፡ በእኛ ቻናል እንኳን ብዙ ሰዎች ከጌታ ጋር ጥሩ ተሞክሮ እያደረጉና ከእርሱ ጋር የጠለቀ ግንኙነት እየፈጠሩ ናቸው፡፡ ለብዙ ጊዜ ከጌታ የራቁ የነበሩ አሁን ግን ብዙ ተስፋ እየታየ ነው፡፡ 'እናም ትንሽ ተጨማሪ ጊዜ ቢኖረን!' ይህንን በማለቴ ግን የበሰበሰ ቲማቲም እንዳትወረውሩብኝ! ምክንያቱም አውቃለሁ ማናችንም ብንሆን እዚህ የምንቆይበት ጊዜ እንዲራዘም አንፈልግም፡፡ በምንም መልኩ ሁላችንም ከዚህ መሄድ ነው የምንፈልገው፡፡ ነገር ግን ሳስብ የነበረው ሰዎች በእውነት በህይወት ለመኖር ምልክት እያሳዩ ነው፡፡ ንስሐ እየገቡና ወደ ጌታ መቅረብ እየፈለጉ ነው፡፡ይህም መልዕክት የሚያመለክተው ይህንን ነው፡፡

እንዲህ በማለት ጀመርኩ፡፡ "አ ጌታዬ ተጨማሪ ጊዜ ቢኖር እንዴት ተመኘሁ፡፡ ብዙ የጠፉና ግራ የተጋቡ ነፍሳት አሉ፡፡ ስለዚህም ብዙ ሰዎችን ለመንካትና ብዙ ሰዎችን እንድንደርስ ፈለግሁ፡፡"

"አውቃለሁ"

"ተጨማሪ ጊዜ እንድኖረን ተመኘሁ"

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የለንም"

"ነገር ግን ታውቃለህ . . . ሁሉ ነገር እንደተለመደው ይመስላል"

"መግዛትና መሸጥ፣ ማግባትና ለጋብቻ መስጠት?"

"አዎ አለም የተረጋጋና እስከ መጨረሻው እንዲሁ የሚቀጥል ይመስላል፡፡"

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን አይቀጥልም፡፡ ያታልላል፡፡ ያለው ሁኔታ እስካልተናጋ ድረስ ከበስተጀርባ ብዙ ነገር እየተከናወነ ቢሆንም ለማውቅ ግድ የሚላቸው ጥቂቶች ናቸው፡፡"

"ሰዎች ምላሽ እየሰጡ ነው፡፡"

"ስለፈሩ ነው ምላሽ እየሰጡ ያሉት"

ቢሆንም ምላሽ እየሰጡ ነው፡፡ ተጨማሪ ጊዜ አይኖረንም?"

"እኔ የማውቀውን ብታውቂ ኖሮ፣ ይህንን ጥያቄ አትጠይቂም ነበር፡፡"

"ጌታ ስለዚህ ጉዳይ በየቀኑ ነው ከራሴ ጋር የምታገለው፡፡ አለም እጅግ የተረጋጋና አስከመጨረሻው በተለመደው መልኩ የሚቀጥል ይመስላል፡፡ አንተ ባትሆንና መገለጥ ባይኖር ኖሮ እንዲሁ ይቀጥላል ብዬ እስብ ነበር፡፡

"ታዲያ እኔን በማግኘትሽ ደስ አይልሽም?"

"ጌታ ምን ጥርጥር አለው! ህይወት ከአንተ ውጪ ህልም እንጂ ህይወት አይሆንም ነበር፡፡"

"አውቃለሁ እንዴት እንደሚሰማሽ፡፡ እንዴት እንደሚሰማሽ አውቃለሁ ምክንያቱም እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ እኔም ሸክምሽ ስለሚሰማኝ ነው፡፡ ነገር ግን ምን እየተከናወነ እንዳለ እኛ ስለምናውቅና አንቺ ግን ስለማታውቂ ነው፡፡ ነገሩ የነበረው እንዳለ እንዲቀጥል የመፈለግ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም 'የኔ የሆነ ነገር ምንም አይነካ፣ ሥራዬን አሰራለሁ፣ ትርፍ አገኛለሁ፣ የምፈልገውን እገዛለሁ፣ ስለዚህም ኑሮዬን በሰላም ልኑርበት የሚል ነው፡፡'

" ብዙዎች ያሉት በዚህ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ሌሎች ደግሞ በስውር እቅድ በማውጣት ለማጥቃት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ እቅዳቸው እንደሚሰራም ተማምነዋል፡፡ ምክንያቱም ሌላው የተለመደውን ማትረፉንና ሸቀጥ መሰብሰቡን ተያይዞታል፡፡ ደግሞ ይህ በሰላም እስከቀጠለ ድረስ ደስተኞች ናቸው፡፡"

"ሌሎች ደግሞ ስለ ሃይማኖትን ነፃነት፣ ስለ መናገር ነፃነት፣ ስለ ትክክለኛ ፍርድና ስለ ደህንነት እሴት ያላቸው ሰዎች የሚመጣውን ነገር የማስጠንቀቂያ ደውል በመስማት፣ ነገር በድንጋጤ በመሞላት በጨረፍታ ካዩት ነገር ለማምለጥ እቅድ እያወጡ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ወደላይ አሻቅበው እየተመለከቱ ከዚህ እንዳድናቸው የኔን መምጣት እየተጠባበቁ ናቸው፡፡"

ከሌር ሁሉ ነገር በአይናችሁ ፊት እየሆነ ነው ያለው፡፡ ነገር ግን በፊታችሁ እየታየ ያለው ህይወት በሁሉም ዓይነት መልኩ የቀረበው ነው፡፡ በአንድ መልኩ የተለመደውን ሸቀጡን የሚሞላው ሲሆን በሌላው ወገን ደግሞ የበላይነትን፣ ተቀጣጣሪነትን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በሌላው የህይወት ክፍል ነፃነት ሲሆን በሌላኛው ደግሞ መንግስተ ሰማይ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የህይወት ነፀብራቅ ክፍሎች በፊታችሁ ይገኛል፡፡ ስለዚህም በእያንዳንዱ ቀን የትኛውን የህይወት ዓይነት እንደምትመርጡ መወሰን አለባችሁ፡፡ የትኛው የህይወት አቅጣጫ ነው የእናንተ ትክክለኛው ህይወት? እናም የትኛው ነው የእናንተ ጌታ? ማንን ነው የምታገለግሉት? አንደኛው የህይወት ክፍል ፈንድቶ በማሸነፍ የሌላውን ነፃነት ሁሉ እስኪጨፈልቅና ምድር ከውስጥ ወደ ውጪ ከላይ ወደታች እስከትገለበጥ ድረስ፣ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሰዎች ወደኋላቸው መለስ ብለው ይመለከቱና ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ይላሉ፡፡"

"ይህማ የሆነባችሁ ምክንያት የሚያስፈልጋችሁን ብቻ የምታገኙበትን የህይወት አቅጣጫ መርጣችሁና ከሌላው ሁሉ ባይተዋር በመሆን ተለይታችሁ መኖር ስለመረጣችሁ ነው፡፡ ከዚህ የህይወት አቅጣጫ ሌላ ምንም የሚታያችሁ ነገር አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በመረጣችሁት የህይወት አቅጣጫ ስኬታማ ለመሆን ለሌላው ጊዜ ስለሌላችሁ ነው፡፡ እናም አንድ ቀን . . . ሁሉም አበቃ፡፡ ስለዚህም ግራ በመጋባት ቆማችኋል፡፡ እድለኞች ሆናችሁ እስካሁን ቆማችሁ ከሆነ ይህ ነው ነገሩ፡፡"

"የመሬት መራድ በተከሰተ ጊዜ የመሬቱ ውፍረት ምን ያህል እንደነበረ የሚያስታውሰው አይኖርም፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ የሚታወሰው በተከሰተው ርደት የደረሰው መራራ ችግርና እጦት ነው፡፡ ይህም በሆነ ጊዜ በፍርስራሹ ላይ ሆነው

ይፈልጉኛል፡፡ አለምን ማፍቀር እንዴት ራቁታቸውንና ምስኪን እንዳደረጋቸው ይገባቸዋል፡፡ ሲያገኙኝም አቅፋቸዋለሁ፣ በቁስላቸውም ላይ ዘይትን አፈስለሁ፣ ለቅድስናም አነሳቸዋለሁ፡፡"

"እያልኩ ያለሁት ነገር ሳይነጠቁ ለቀሩ ሰዎች አትዘኑ ነው፡፡ ይህ የእነሱ እጣ ፋንታ ነው፡፡ ምክንቱም እነሱ የመረጡት በዛ የህይወት መንገድ ብቻቸውን ተለይተው፣ በራሳቸው እጅ የሚያስፈልጋቸውን በማግኘትና ህይወታቸውን በሙሉ ትኩረታቸውን ስኬትን ለማግኘት ነበር፡፡አዎን ይህንን መርጠዋል፡፡ አለምም እንዲህ በመሆኑ በፊቴ የማያዩና ራቁታቸውን አድርጎ አስቀርቷቸዋል፡፡ ይህም እኔ ነፍሳቸውን እንዳድናቸው አድርጓል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ገሃነም በእነሱ በተሞላ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የሌላቸውና የማያስፈልጋቸው ሰዎች ስለሆኑ እንጂ ሁሉም መጥፎ ሰዎች ሆነው አይደለም፡፡ የኔ ምህረት ነው የእነሱ አለም እንዲደቅና እነዲያበቃ ያደረገው፡፡ ለእነሱ ያለኝ ፍቅር ነው ይህንን መቅሰፍት እንዲመጣ ያደረገው፡፡ ራቁትነታቸው ብቻ ነው ወደ እኔ ሊያመጣቸው የሚችለው፣ እውነትን የማወቅ ረሃብ ምኞት፡፡"

"አያችሁ ሰው ቤቱን አንድ ጊዜ በአሸዋ ላይ ከሰራና ዝናብ መጥቶ ጎርፍ ቤቱን ጠራርጎ ከወሰደው፣ ያን ጊዜ ነው ያ ሰው ቤቱን በአለት ላይ መገንባት አስፈላጊ መሆኑን የሚረዳው፡፡ በወቅቱ ታዲያ በአጠገቡ በመገኘት እንዴት እንደሚገነባው አስተምረዋለሁ፡፡ እናም አያችሁ በይደር ላይ የሚገኘውና የማይቀረው አቅርቦቴ ልጆቼን በመንፈስና በእውነት ወደ እኔ ለመመለስ ነው፡፡"

አዎን አስጨናቂ ነው፣ አዎን ጭካኔ ያለበት ነው፡፡ አዎን ለአይን ሲታይ ሚዛኑን ያልጠበቀ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ለታዳጊ ልጁ መኪና ለመግዛትና የቅንጦት ቤት ለመስራት በጣም ደሃ የሆኑትን የሦስተኛ አለም አገሮችን ሲበዘብዝ የነበረ ሰው ግን ምንም አልተባለም፡፡ በእንደዚህ ዓይንት አመለካከት የተጠመዱ ሰዎች እነሱ የሚፈልጉት ነገር በምንም ዓይነት መልኩ ይሁን ብቻ የሚፈልጉትን ማግኘት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዓለም እጅግ የበታች የሆኑ አገሮች ኑሮ እንዲቀምሱት ይደረጋል፡፡ እነዚህም አገሮች በእናንተ ፊት የአኗኗራቸው ዘይቤ የሚመስላችሁ እነርሱ ግን ተስፋ በመቁረጥ በመቅለስለስ ባህል ውስጥና በወደቀ ኢኮኖሚ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ እናንተ ግን በተትረፈረፈ ሁኔታ ውስጥ ትገኛላችሁ፡፡

"ክሌር ይህ በጣም በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ እናንተ የማታዩት ነገር እነዚህ ሰዎች እንዴት እንደሚበዘበዙ ነው፡፡ እኔ ለዘሪ ዘርን አልሰሰጠሁምን? ነገር ግን አሁን ስግብግብና ክፉ ሰዎች ዶለተው ደሃው የእነርሱን ዘር እንዲገዛ ለማስገደድ ዘዴ ፈጥረዋል፡፡ ይህንን ለስንት ጊዜ ነው የምፈቅደው? የደሃው ጩኸት በየዕለቱ ወደ ጆሮዬ ይደርሳል፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ጥቂት የህክምና አገልግሎት እንኳን ለማግኘት ይቸገራሉ፡፡ በአንፃሩ እናንተ አገር መካከለኛ ገቢ ያላቸው እንኳን ተጠቃሚ የሚያደርግ የህክምና መዋቅር እያለም ሌላውን ለመቆጣጠርና ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት በየጊዜው አዲስና የተሸሻለ መንገድን በመቀየስና ምንም በማያውቁት ላይ በመረማመድ እናንተ ታብባላችሁ፡፡"

"ኦ በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን እጅግ የተበላሸ ነው፡፡ ይህ ነገር ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዲቀጥል አባቴ ለምን ይፍቀድ?" እኛ የሰዎችን ልብ ለመቀየር ብዙ ጥረናል፡፡ ነገር ግን እነሱ ቀዳሚነት ባለው ኑሮ፣ ለምቾትና ለመደላቀቅ ካላቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ትክክለኛ ባልሆነ የአኗኗር ዘዴ አይናቸው ታውሯል፡፡

"እነዚህን ነገሮች ለእናንተ መናገር ለእኔ የተለመደ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንዲገባችሁ የምፈልገው በየቀኑ የምመለከታቸው የብልሹነት ገፅታዎች እንዴት የሚገርም እንደሆነና በአንፃሩም ለፍትህ የሚጮኸውን ጩኸት ነው፡፡ በጣም የባሰው ደግሞ

ይህ ድሆችን እስከ መጨረሻው ጠብታ ገንዘባቸውን ለመጭመቅ የተለመደ ወንጀላቸውን የሚያቀነባብሩ ሰዎች የራሳቸውን ህይወት አደጋ ላይ መጣላቸውን ያለማወቃቸው ነው።።"

"አዎ ይህ አንዱ ገፅታ ብቻ ነው። ነገር ግን ይህ ጥላቻን ያለመረጋጋትንና ተስፋ መቁረጥን ያነሳሳል። ሙስሊሞች ለእምነታቸው እራሳቸውን መስዋዕት ሲያደርጉ በደስታ ነው። ምክንያቱም በዚህ ተስፋ በሌለው፣ በተበላሸና ውስብስብ በሆነ አለም ውስጥ ደስታን የሚሰጣቸው አንድ እድል ይኸው ስለሆነ ነው። ሰው ለመኖር ምክንያት ሲኖረው የነበረውን ህመም በመሸፈን ወደ ክብር ለመመለስ ስሜት ይኖረዋል። ነገር ግን የመኖሩ ሚስጢር ከጠፋበት በክብር መሞትን ይመርጣል። ስለዚህም ሰይጣን በዚህ ፍትህ በሌለበት ምድር ላይ ሰው ሊያገኝ የማይችለውን ነገር ራሱን ነፃ በማውጣት 'በገነት' እንዲኖር እድልን ፈጠረለት። ታዲያ እነዚያን ድሆችን የሚያድኑትን፣ በአብዛኛው አይሁድ የሆኑትን የባንክ ባለቤቶችና /Bankers/ የአለም መሪዎችን እነሱ መጥላት የለባቸውም?"

"ደግሞ ሌላ ጥሩ ውጤት የማግኘት ስሜት አለ። 'ሴተኛ አዳሪን ማጥፋት'። ይህ ራሱ አስከፊ ነው። ስለዚህ አያችሁ? ይህ ችግር ተስፋ የሌለው የተወሳሰበ ነገር ነው። እኔ ግን ለመንገስና ለመግዛት ተመልሼ ስመጣ የብረት ዘንጉ የሚሰርቀውንና ዝቅ የሚያደርገውን ጀርባ ይሰበራል። ከሰው ሁሉ በታች የተናቀውን እንኳን።"

"ፍትህና አክብሮት ለሚፈልጉት ሁሉ ሊሰጥ ይገባል። በሚያስከብር እውነተኛ ሥራና አስፈላጊ ትምህርት ሁሉም እንዲያገኙ እድል ሊሰጠው ይገባል። እንዲህም ቢሆን ግን ከእግዚአብሔር ውጪ አንድም ሰው አይበለፅግም። ገና ከመጀመሪያው አንድም ሰው ከእግዚአብሔር ውጪ፣ ራሱን ለእኔ ፍፁም በመስጠት እንዲሁም እኔን ለማገልገል ፍላጎት ከሌለው ህይወት ሊኖረው አይችልም። ህሊናቸው መረዳት ከማይችሉት በቀር እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ውስጥ መኖር አስፈላጊነቱን ያያል።"

"አየሽ ክሌር ከታች ወደላይ እንደገና መጀመር አለብን። ሌላ አማራጭ ስለሌለ ተስፋ አትቁረጪ። ሁሉንም ነገር ለማቃናት እመጣለሁ። ቃል እገባልሻለሁ፣ ሁሉንም ነገር እናቃናዋለን። ይህ እስኪሆን ድረስ ግን በሰማይ የዕረፍት ጊዜ እንዲኖርሽ ለማሰብ ሞክሪ። ይህንን የምልሽ ግማሽ ማንነትሽ ሰዎችን ለመርዳት ተጨማሪ ጊዜ እንደምትፈልጊ ስለማውቅ ነው።"

"ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ። ይህም ፍቅር አምላካችሁ ብቻ ያለውና ራስን አሳልፎ የሚያሰጥ ፍቅር፣ ይህም ፍቅር አንድ ነፍስን ወደ እኔ ለማምጣት የሚናፍቅ ፍቅር ነው። እባርካችኋለሁ ደግሞም የምጠይቃችሁ በህይወታችሁ ለእኔ ቦታ እንዲኖር ለማድረግ የምታደርጉትን ጥረት እየጨመራችሁ እንድትሄዱ ነው። እናም አንድ ቀን ለስቃያችሁ፣ ለፀሎታችሁና ለልፋታችሁ ዋጋ ይከፈላችኋል።"

## 5. 3. የአሜሪካ ሞት

እ.አ.አ. ኤፕሪል 9 ቀን 2015 ዓ.ም

{The Death of America}

ዛሬ ምሽት ወደ ፀሎት በጣም አርፍጄ ነው የገባሁት፡፡ ምክንያቱም ለእናንተን አስቸኳይ መልዕክቶች መልስ ለመስጠት እየሞከርኩ ነበር፡፡ የተወደዳችሁ ቤተሰቦች ጌታን እያመለኩም እያለሁ ሃያ ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለታችንም ጥቁር ልብስ ለብሰን አየሁ፡፡ እኔ የለበስኩት አንድ ሴት ባሏ ሲሞትባት እንደምትለብሰው ልብስ ዓይነት ሲሆን ጌታም አንድ ሰው ሚስቱ ስትሞት እንደሚለብሰው ዓይነት ነበር የለበሰው፡፡፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "በመንፈስም በአካልም የአሜሪካ ሞት"

በሰሜን ንፍቅ ክበብ ላይ ላዩን የተካሄደውን የሰይፍ ልምምድ በደንብ ታውቁታላችሁ፡፡ ይህ የተደረገው ለሰው ዕይታ ብቻ ነው፡፡

ሰዎች የእናንተ ፕሬዜዳንት የሚሉት፣ በስውር ነገሮችን የሚሰራ፣ ሰዎችን የማረከና ምርጫውን በማታለል ያገኘ ይህ ሰው ሰፊውን ህዝብ እየተጫወተበት ነው፡፡ ይህም ጥፋት በመጣ ጊዜ እውነተኛ መስሎ ለመታየት ሲሆን እውነታው ግን የሚመጣውን ጥፋት በመደበቅ ላይ ላዩን ብቻ የሚያሳይ ነገር ግን የሁሉንም አገራት ሉአላዊነትን በማጥፋት አለምን በአንድ የበላይ ገዢ እንዲተዳደር ለማድረግ ነው፡፡ ይህ ሰው እናንተ አሜሪካኖችን ለማጥፋት ብዙ የተዋናይነት ሚና የተጫወተ ሰው ነው፡፡ አሜሪካ ልታውቁ የሚገባው ይህ እንዲሆን እኔ ፈቅጄ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ጋለሞታ ከሚያልፈው ከሚያገድመው ሁሉ ተጋደማችሁ፡፡ እኔ ባላችሁ ቆሜ እያለሁ በአልጋችን ላይ ሁሉም በተራው ተኛበት፡፡

"እናም አሁን ምን ልበል?" . . . ' <u>ያየሃቸውም አስር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፥ ሥጋዋንም ይበላሉ፥ በእሳትም ያቃጥሉአታል። እኔ ሐሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም ሐሳብ እንዲያደርጉ ቃሌም እስኪፈጸም ድረስ መንግሥታቸውን ለአውሬው እንዲሰጡ በልባቸው አድርጌያለሁ።'</u>

"በእውነትም የምለው ይህንኑ ነው፡፡"

"እንዲህም ቢሆን ግን አሁንም ከእናንተው ጋር ነኝ፡፡ ሆሴህ ጎሜር የግልሙትና ሥራዋን ጨርሳና የምስጥር ፍቅረኞቿ አድክመዋት እስክትመጣ ድረስ እንደጠበቃት እኔም እዚሁ ነኝ ያለሁት፡፡ አዎ በእርግጥም እዚሁ ነኝ ያለሁት አሜሪካ፡፡ በሙሉ ልባችሁ ስትፈልጉኝ በእርግጥም ታገኙኛላችሁ፡፡ ከእኔ ጋር እንደገና እንድትስማሙ ዝግጁ ነኝ ይላል ጌታ የሆነው የእናንተ አምላክ፡፡

"ስለዚህ ጉዳታችሁ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ ወደ እኔ ተመለሱና እኔ መፅናናትን እሰጣችኋለሁ፡፡ ቁስላችሁን አጥቤ መድኃኒት በላዩ ላይ እቀባለሁ፡፡ በንፁህ ጨርቅም እሸፍነዋለሁ፡፡ በትክክለኛው መንገድ እመራችኋለሁ፡፡ የተበላሸውንም ቤታችሁን ጠግኜ ለእናንተ እመልሳለሁ፡፡ አዎን ትጠገናላችሁ፣ እነደገናም ለእኔ ታማኝ ትሆናላችሁ፡፡

"እኔ እያወራሁ ያለሁት ዋና ከተማችሁን ለሰራችሁለት ለአስቀያሚው በአል አምላኪዎች አይደለም፡፡ አይደለም እኔ መናገር የያዝኩት ለእናንተ አይደለም፡፡ እናንተማ ፈፅሞ ትጠፋላችሁ፡፡ ከምድር በታች ባለው አገራችሁ እንኳን ቢሆን ትጠፋላችሁ፡፡ እናንተ በሬሳ ሳጥናችሁ ውስጥ ሆናችሁ ደህንነት የሚሰማችሁ ናችሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ በመንገዴ ላይ ስላልሆናችሁ እንዳላችሁ አልቆጥራችሁም፡፡

"መናገር የያስኩት እኔ ያነሳሳሁትን ራዕይ እስካሁን ይዘው ላሉ ለአሜሪካን ልቦች ነው፡፡ ከውጪ ጋር አንተኛም ላሉ፣ ከፍታውን ይዘው ወደያና ወዲህ  የሚሉትን፣ በጥልቀት ማሰብ ያልቻሉትን፣ ለራሳቸው ምቾት በቀላሉ የሚጣመሙትን ስግብግቦችን ማሸነፍ ያልቻሉትን ነው እያናገርኩ ያለሁት፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡

"በብርታት ወደፊት ሂዱ፡፡ እኔ ራሴ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ በመጨረሻውም ለእናንተ የታቀደ ሁሉ ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡ እናንተም አለምን ሁሉ ለመርዳት እንደገና ከአመድ ትነሳላችሁ፡፡ ይህም ከእኔ መንግስት ጋር በተጣጣመ መልኩ ሰዎችን ሁሉ ከጨቋኙ ነፃ ለማውጣት ነው፡፡

"የፅድቅን ራዕይ የሰነቃችሁ የአሜሪካ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሰላሜ ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ ሽባ የሚያደርግ ምት ቢያገኛችሁም አገራችሁ ወደ እኔ ስትመለስ ግን መልሼ እገነባችሁና በእናንተ ዳግመኛ ደስታን አገኛለሁ፡፡ በአምላኳ ሥር ያላች፣ አምላኳ አብሯት የሚሰቃይ አንድ አገር ትሆናለች፡፡ የሚወዳችሁ አምላካችሁ ምድራችሁን በትልቅ ውበት ያለብሳታል፡፡ በእርግጥም እንደገና መልሶ ይገነባታል፡፡

"እነዚህን ቃሎች እውነትና የታመኑ ስለሆነ አጥብቃችሁ ያዟቸው፡፡"

## 5. 4. ከንጥቀት ወደ ኋላ ለቀሩት አቅርቦትና መመሪያ

እ.ኢ.አ. ኤፕሪል 22 ቀን 2015 ዓ.ም

{Provision and Instruction for those lefet behind}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . .

"ዛሬ ምሽት ለእናንተ መናገር የምፈልገው ስለ መንፈሳዊ እድገት ነው፡፡ እስካሁን ከእናንተ ጋር አብዛኛውን ጊዜዬን ሳደርግ የነበረው ስለ መንፈሳዊ እድገት ጉዳይ ነበር፡፡ ይህም በቁመት መጨመር፣ መሞላት፣ የተረጋጋ ህይወት፣ በጥሩ መሰረት ላይ መመመስረትና ለሁሉም ነገር ዝግጁ መሆንን ያጠቃልላል፡፡ ምክንያቱም የእናንተ ጭብጥ ህይወት ያለው በመንፈሳዊው አለም ከእኔ ጋር እንጂ በቅርብ ሊተረማመስ ካለው ከምድራዊ ህይወት ልክ አይደለም፡፡

"ሰዎች ምን ሊመጣ እንዳለ ካለማወቃቸው የተነሳ ህይወት በዚሁ መልኩ ለሁልጊዜው እንደሚቀጥል በመቁጠር ገና ብዙ እያቀዱ ናቸው፡፡ ለዛ ነው ስለሚመጣው ነገር አይናቸው የታወረው፡፡ ክሌር እኔ ከአንቺ የምፈልገው የምትችይውን ያህል ሰዎችን ከዚህ ከትርምስ ሁኔታ ሊያነሳቸው የሚችል ነገር ትተሽ እንድትሄጂ ነው፡፡ ለነፍሶች ላደርግ የምችለው ያንን ነው፡፡

" አያችሁ! ሰርን፣ ክሎኖችና ምሁራን መደበቂያ ሥፍራቸውን በድንጋዮች ውስጥ ለማድረግ እጅግ ከባድና አደገኛ ስህተት እየፈፀሙ ነው፡፡ በዚህም ድርጊታቸው ኃይለኛ የውኃ ነውጥና እሳተ ጎሞራ በእነርሱ ላይ ይከፈትባቸዋል፡፡ ይህም ትልቅ ጥፋትን ያስከትላል፡፡ በዛን ጊዜ ይህንን እንዲሰሩ ላቀናበሩት ጩኸታቸውን ያሰማሉ፡፡

(ክሌር) ይህ በፍፁም አይሆንም ያልከኝ መስሎኝ ነበር!!!

"ነገር ግን ሁሉም ዋጋ ቢስና በጥልቁ የሚዋጥ ይሆናል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ለእነሱ የሚገባና ትክክለኛ ነገር ይሆናል፡፡ እናም ለሁሉም ይህ ከምድር በታች የሚሰሩት ሰፈር ለእነርሱ አስተማማኝ እንዳልሆነ ምክር ሰጥቼያቸዋለሁ፡፡

"እንዲህም ሆኖ ግን በበረሃው ውስጥ አስተማማኝ ስፍራን አዘጋጅቻለሁ፡፡ የተፈጥሮ ዋሻ፣ ውኃ እንደልብ ያለበትና በቂ ምግብ የሚያገኙበት፡፡ ልክ መላዕክቶች ለእስራኤላውያን በበረሃ መና እንዳቀረቡላቸው ለመኖር የሚያበቃቸው በቂ ነገር ይለቀቅላቸዋል፡፡

(ክሌር) እዚህጋ ትንሽ እረፍት ልውሰድና፣ ይህ ለእኔ በጣም የሚደንቅ ነገር ነው!!! መላዕክቶች ነበሩ ማለት ነው በበረሃ ለህዝቡ መናውን ሲያከፋፍሉ የነበሩት፡፡ ይህ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው፡፡

"ብዙዎቹ የምግብ ማከማቻዎች ባዶ አይሆኑም፡፡ የህክምና አቅርቦትና ፈውስ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሁኔታ እስከ መጨረሻው በእኔ ይቀጥላል፡፡ ብዙዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ለፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የታመሙትን ክብካቤ በማድረግ፣ በፍርሃት ላይ የወደቁትንና  በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙትን ደግሞ በማበረታታትና በማፅናናት ይሰማራሉ፡፡ አንዳንዶች ህይወታቸው በምድር ሊያበቃ ሲል ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገቡ ይረዷቸዋል፡፡

"በዚህ ዘግናኝ ወቅት ግን እኔ አጅግ የሚደንቅ እቅድ አለኝ፡፡ በፀሎት ምክንያት ብዙ የጠላት ግድግዳዎች ይፈራርሳሉ፡፡ ቅዱሳንን ለመጠበቅ ከተፈጥሮ በላይና ቃል በቃል ሰማይና ምድርን አነቃንቃለሁ፡፡ አንዳንዶች መስዋዕት ይሆናሉ፣

አንዳንዶች በህይወት ይኖራሉ፡፡ ለሁሉም ግን የሚያስፈልገው ሁሉ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለጠላቶቻቸው ፈቃድ አሳልፌ አልሰጣቸውም፡፡ አዎን በጣም ትልቅ ስቃይ የሚይታበት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአንፃሩ ትልቅ ክብርና የእምነት አሸናፊነት የሚታይበት ነው፡፡ ከመንግስተ ሰማይ ብዙዎች ለማፅናናትና የሚያስፈልገውን ለማቅረብ ጉብኝት ለማድረግ ይላካሉ፡፡ መላእክቶቼ ወደኋላ ለቀሩትና ከኃይለኛው ቁጣዬ ለምሸፍናቸው ለደህንነታቸው ዋና ተጨናቂዎች ናቸው፡፡

"የማካፍላችሁን መመሪያ በትክክል ስሙኝ፡፡ ትልቁ መሳሪያችሁ ፀሎት ነው፡፡ እንዴት እንደምትፀልዩም አስተምራችኋለሁ፡፡ ምንም ሳትደክሙ ከውስጣችሁ ወደ ውጪ እንዲሁ ይፈሳል፡፡ ስለዚህም ፀጋዬ በእናንተ መካከል ጠንካራ ይሆናል፡፡ በፍርሃትና በአደጋ ጊዜ ፀሎት ከውስጣችሁ ይመነጭና በደቂቃዎች ውስጥ ሁለንተናችሁን ይወርሳል፡፡ እናም በአስተማማኝ ቦታ ውስጥ ትደበቃላችሁ፣ ሰላሜም ይበዛላችኋል፡፡

"ብዙዎች ይከዳዳሉ፡፡ ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስ መለየት ብቻ ነው ጥንቃቄ መውሰድና ከማይታመኑ ሰዎች ጋር ህብረት እንዳታደርጉ የሚያደርጋችሁ፡፡ በውጫዊ ሁኔታ ለምሳሌ በሚናገሩት፣ በሚመስሉት፣ በሚያደርጉት ድርጊትና በተለመደው በሰው ደረጃ ዓይነት ፍርድ የምትሰጡ ከሆነ ትሞኛላችሁ፡፡ በእኔ ላይ በመደገፍ ብቻ ነው ደካማ  ወይም እናንተን እንዲያገኙ የላኳቸውን ነፍሶች መለየት ያለባችሁ፡፡

"ይህንን በድጋሚ እናገራለሁ፡፡ ይህ የምሰጠው መመሪያ ወደ ኋላ ለሚቀሩት እነጂ ለሚነጠቁት አይደለም፡፡ እነዚህን መመሪያዎች በወረቀት አትሞ በቀላሉ ሊገኝ በሚችል ሥፍራ መቀመጥ አለበት፡፡

"በብሉይ ኪዳን ዘመን ህዝቤን እስራኤልን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ጥበቃ እንደጠበኩት እንደዚሁ ከንጥቀት ወደ ኋላ መቅረት ላለባቸው ጥበቃ አደርጋለሁ፡፡ ከእነሱ ውስጥ አንዱ መሪ ሆኖ ይሾማል፡፡ ለተሾመው ለእርሱ ወይም ለእርሷ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እውቀትና ጥበብን አሰጣለሁ፡፡ ከመካከላችሁ የተሾመውን ወይም የተሾመችውን ለተልዕኳችሁ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ በደንብ ጠብቋቸው፡፡ በእናንተ መካከል ዳያቢሎስ መከፋፈልን፣ አለመግባባትን፣ ማጉረምረምንና ቅናትን እንዳያመጣ ተጠንቀቁ፡፡ ይህ መርዝ በመካከላችሁ እንዳይሰራ ጠብቁ፡፡ እናንተን ለመከፋፈልና ለመበታተን ይህንን ይጠቀማሉ፡፡ አንድ ላይ በመሆን ሁኔታውን ማለፍ ትችላላችሁ፡፡ ከተለያይችሁ ግን ደጀን የሚሆን ድጋፌ ስለምታጡ ብዙ አደጋ ይገጥማችኋል፡፡ ስለዚህም ለያይተው እንዳያሸንፏችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ከጠላት በልጣችሁ ብልህ ሁኑ፡፡ በመልካምነትና በትህትና ከተመላለሳችሁ ችግር አይገጥማችሁም፡፡ በራስ ፍላጎት መንቀሳቀስ፣ ራስን መውደድ፣ ተጠራጣሪነትና መራራነት ገዳዮቻችሁ ናቸው፡፡

"በቡድን ውስጥ ብዙ ፈተናዎች ሊገጥማችሁ ይችላል፡፡ አዎ ብዙ ፈተናዎች፡፡ የሚያሙ ውሳኔዎችን መወሰን፣ የሞትና የህይወት ውሳኔዎች ማድረግ ሊኖርባችሁ ይችላል፡፡ የምትወስኑት ውሳኔ እጅግ ከባድ በሚሆን ጊዜ ሰላሜን አሰጣችኋለሁ፡፡ ውሳኔን ለመወሰን እንዲያስችላችሁ ዕጣ በማውጣት ልትጠቀሙ ትችላላችሁ፡፡

(ክሌር) እዚህጋ ጣልቃ ለመግባት፣ ዕጣ ለማውጣት ማንኛውንም ነገር መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ለምሳሌ ልምጭ፣ በጫካ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ፍሬዎችን ድንጋዮችን . . . ወዘተ፡፡ ዕጣ ማውጣትን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲጠቀሙ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ዮናስ ከታዘዘበት በመሸሽ በመርከብ ሲኮበልልና መርከቢቷ ስትናወጥ ይህ በማን ምክንያት እንደሆነ የሆነባቸው በመርከቢቱ ውስጥ ያሉት ዕጣ በማውጣት ነው የተጠቀሙት፡፡ እንዲሁም ጌታን የከዳው ይሁዳን ለመተካት የጌታ ሐዋርያት የተጠቀሙት ዕጣ ነበር፡፡

"በበርሃ ጉዟቸው ከእስኤላውያን ጋር እንደነበርኩ ከእናንተም ጋር እሆናለሁ፡፡ የፍቅሬን ምልክት፣ የአደጋን ምልክት፣ የምትሄዱበት መንገድ ትክክል አለመሆኑን ምልክት፣ በትክክለኛ መንገድ እየሄዳችሁ እንዳላችሁ ምልክት አሰጣችኋለሁ፡፡ እናንተ ግን ሁልጊዜ የምሰጣችሁን ምልክት በቅርበት ተከታተሉ፣ በጥንቃቄና በማስተዋል ተንቀሳቀሱ፡፡

(ክሌር) ታውቃላችሁ ሁልጊዜ ስለ ምልክቶች ሳስብ የልብ ቅርስ ያለው ድንጋይ፣ የኢየሱስ ፊት በዛፎች ግንድ ላይ ይታየኛል፡፡ እኔ አላውቅም ነገሩ ልዩ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በደንብ ከተከታተለ ምልክቶቹን ልታዩ ትችላላችሁ፡፡

"ምናልባት ትክክለኛ ውሳኔ ማድረጋችሁን ከተጠራጠራችሁ፣ ቆም በሉና ፀልዩ፡፡ እየተጠራጠራችሁ ጉዞ ከመቀጠልና ወጥመድ ውስጥ ከመግባት እኔን ብትጠብቁ ይሻላል፡፡ ውሳኔን ተግባርያዊ ለማድረግም ሆነ ለመጠበቅ ጊዜ አለው፡፡ ፈተናው እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው በጥበቃ ወቅት ላይ ነው፡፡ ሁልጊዜ ፀልዩ፣ አምልኩ፡፡ ጠላቶችቻሁን በከበባችሁ ጊዜ ሁሉ እስከዚያ ድረስ በእያንዳንዱ ጉዟችሁ ስለተደረገላችሁ ጥበቃና አቅርቦት አመስግኑ፡፡ የኔን ሥም እንደ ጦር መሳሪያ ተጠቀሙበት፡፡ ምክንያቱም እየተዋጋችሁ ያላችሁት ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም፡፡ ነገር ግን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።(ኤፈሶን 6፡ 12)

"አሁን ሁላችሁም እንድታስታውሱ የምፈልገው፣ እምነት በማጣት ወጥመድ ውስጥ መውደቅ እንዴት ቀላል እንደሆነ ነው፡፡ ያለማመን፣ ጥርጣሬና ፍርሃት እናንተን ለማጥቃት ጠላት የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ቀድሞ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ለሚመጣ አደጋ ቀድሞ ጥንቃቄ ይወስዳል፡፡

" የኔ ውዶች የሰጠኋችሁን መመሪያዎች አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ ምክንያቱም መመሪያዎቹ የህይወትና የሞት ጉዳይ ስለሆኑ ነው፡፡ ሰው በእናንተ ሰውነት ላይ ለሚያደርገው ነገር አትፍሩ፡፡ ግድ ሊላችሁ የሚገባው የዘላለም ነፍሳችሁ ጉዳይ ነው፡፡ ለሰውነታችሁ፣ ለልጆቻችሁ፣ለሚስታችሁ ወይም ለማንኛውም ምክንያት ብላችሁ አታመቻምቹ፡፡ ከክፉ ነፃ ላወጣችሁ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ ከክፉ አድነን ብላችሁ ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ ይህ አጅግ ኃይል ያለው ፀሎት ነው፡፡

## 5. 5. በሥጋ ላይ አትደገፉ

እ.አ.አ. ሜይ 9 ቀን 2015 ዓ.ም

{Put No Confidence in the Flesh}

ጌታ ዛሬ መልዕክት ይዞ ወደ እኔ በመምጣት የተናገረኝ መሰረታዊው ነገር በንጥቀቱ ተካፋይ ሳይሆኑ የቀሩና ስራ ስላላቸው ሰዎች ነው፡፡

"በማንኛው ምክንያት ይሁን የንጥቀቱ ተካፋይ ያልሆናችሁና እዚህ የቀራችሁ ሁሉ እባካችሁ በሥጋ አትደገፉ፡፡ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን እኔ ጣልቃ ሳልገባ እንዳውም በትክክለኛው አገላለፅ ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ለራሳችሁ የሚያስፈልጋችሁን ለማግኘትና እራሳችሁን ለመጠበቅ አታስቡ፡፡ በሥጋችሁ በታመናችሁ ቁጥር፣ ራሳችሁን ለማሸነፍ ችሎታችሁን በተጠቀማችሁ ቁጥር፣ ለሚያስፈልጋችሁ ነገር ለራሳችሁ ብቁ ለመሆን በጣራችሁ ቁጥር ለውድቀት እራሳችሁን እያዘጋጃችሁት እንደሆነ እወቁ፡፡ አሉ ደግሞ ባዶ ኪሳቸውን፣ የሚሄዱበት የሌላቸው፣ የሚበላ የሌላቸውና ምንም ዝግጅት ሳያደርጉ ወደ ታላቁ መከራ የሚገቡ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን በየደረጃውና በየመንገዳቸው የሚያስፈልጋቸው ይቀርብላቸዋል፡፡

"አንድ ነፍስ እምነቱን በእኔ ላይ ሲጥል የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ ነፃ ነኝ፡፡ ለመኖር የሚያስፈልገውን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ጉዳያችሁ ሁሉ የእኔ ሲሆን ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ደህንነት ያለመስማትና መርበትበት ቶሎ ውሳኔ እንድትሰጡና ያለጊዜው ወደ ዲያቢሎስ ገስግሳችሁ በእጁ እንድትወድቁ ከማድረግ በቀር ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ ነገር ግን ነፍሳትን ወደ እኔ በማምጣት ላይ ብታተኩሩ እኔ የሚያስፈልጋችሁን ለማድረግ ነፃ ነኝ፡፡ የኔ ታማኝነት ይሸፍናችኋል ደግሞም ደጀናችሁ ይሆናችኋል፡፡ እኔን የማያውቁ ሰዎች ናቸው ለራሳቸው የሚስፈልጋቸውን ነገር ለማሟላት የሚሯሯጡት፡፡ ካወቃችሁኝ ግን ለዚህ ሁሉ እኔ መውጫ መንገድ እንዳለኝ ትገነዘባላችሁ፡፡ ሙሉ የምግብና የመድኃኒት አቅርቦት፣ እንዲሁም ጠላት እንዳያያችሁ መሸፈንን ያጠቃልላል፡፡

"ከሌር ይህ የሚጠቅመው ሳይነጠቁ እዚህ ለሚቀሩት ነው፡፡ ከአሁን ወዲያ አብረን በምናሳልፋቸው አብዛኛዎቹን ጊዜያት እነሱን የማዘጋጅበት ይሆናል፡፡

በዚህ ጊዜ በአይምሮዬ ዛሬ ከመሬት መንቀጥቀጥ ጋር ተያይዞ ስለቀረበው ስለ የሎው እስቶን ቻርት ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እጅግ በጣም ትልልቅ፣ ጠንካራና ጠፍጣፋ ከለር ያላቸው ዘንጎች ሲሆኑ፣ ከተለመደው ወጣ ያሉ ናቸው፡፡ እናም እንዲህ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ 'ኒብሩ የምትባለው ፕላኔት ናት ማለት ነው ይህንን ሁሉ ለውጥ በምድር ላይ የምታመጣው፡፡ ደግሞ ይህንን ሁልጌዜ ያውቁ ነበር፡፡ ይህም እንደሚሆን ያውቁ ነበር፡፡'

"አዎ ሁሉንም ያውቃሉ፡፡ ይህንንም ለህዝቡ መናገር ሲገባቸው እነርሱ ግን ግማሹን የሰው ልጅ ሊጠርግ የሚችለውን ይህንን ትልቅ ጉዳት ምን ምን ሊሆን እነደሚችል ይቆጥራሉ፡፡

"የኔ ፍቅር አስፈላጊ ወደሆነው ዋና ጭብጥ ነገር እንመለስ፡፡ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነገር እኔ መልካምነትና ደግነት እንደማደርግ ማመንና መተማመን ላይ ነው፡፡ ከእነዚህ አመለካከቶች ውጪ አሸናፊ መሆን አይቻልም፡፡ የኔ ጥበቃ ለሚፈልጓቸው እንዳይታዩ ያደርጋል፡፡ የኔ ጥበቃ የዱር አውሬዎችን ያባርርላቸዋል፡፡ የኔ ጥበቃ ምድር ከፍታ እንድትውጣችሁና ከጠላቶቻችሁ እንድታመልጡ ያደርጋል፡፡ የኔ ጥበቃ በሌለበት ውኃና ምግብን ያቀርባል፡፡ እኔ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው አጀንዳቸውን ለመንግስቴ ነፍስን ለመሰብሰብ በተሰማሩ ላይ ነው፡፡ ይህንን

የማደርገው ከራስ ወዳድነት አልፈው ለሚሰጡና ለሚመሩ ነው፡፡ ይህንን የማደርገው ሌሎችን ለመንከባከብ ታማኝ ለሆኑት ነው፡፡ ለእነዚህ ነው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥበቃና አቅርቦት የማደርገው፡፡

"ድነት የሚያስፈልጋቸውን ብዙዎችን ወደ እናንተ እጨምራለሁ፡፡ ዘላለማቸው በእናንተ ላይ ተንጠልጥሏል፡፡ ስለዚህም ስለእነርሱ የዘላለም ጉዳይ ቅድሚያ የምትሰጡ ከሆነ እኔ ደግሞ እናንተን እሸፍናለሁ፡፡ በምድር ላይ ከሚመጣው ፈተና የተነሳ ነፍሳት ግራ ይጋባሉ፣ በፍርሃት ይዋጣሉ፣ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ወደላይና ወደታች ይራወጣሉ፡፡ ስለሁኔታው ግራ ከመጋባታቸውና ግንዘቤ ከማጣታቸው የተነሳ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ፀጋ በስተቀር ሊያረጋጋቸው የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የሚፈውሳቸው ፀጋ፣ ይህም እጃችሁን ራሳቸው ላይ በመጫን፣ ፍፁም ሰላም የሚሰጣቸውን የኔን ፀጋ ካልተቀበሉ በቀር፡፡

"እናንተ ለመፈወስ የተጠራችሁ፣ እኔ በእናንተ ውስጥ እኖራለሁ፡፡ የኔ እጅ ከልባችሁ ውስጥ ወጥቶ በእጃችሁ በኩል እንደሚቀሳቀስ በማሰብ እጃችሁን በታመሙትና በስቃይ ባሉት ነፍሶች ላይ እጃችሁን ጫኑ፡፡ ሌላውን እኔ እጨርሰዋለሁ፡፡ ማመን ያለባችሁ እኔ በእናንተ ውስጥ እንደምኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ ብቻ ነው ለየትኛውም ከባድ ለሚባል በሽታ መፈወስ ምክንያት የሚሆነው፡፡

"በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፣ በልሳን ተናገሩ፣ በልሳናችሁም ለሰዎች ዘምሩ፡፡ መናገር የያዛችሁት የኔን ቋንቋ ነው፡፡እኔም በእናንተ ውስጥ አልፌ ፍፁም የሆነውን ፀሎት እፀልያለሁ፡፡ በልሳን ለመፀለይ ማንም ተስፋ እንዲያስቆርጣችሁ አትፍቀዱ፡፡ ዲያቢሎስ የሚያፍሩ፣ በራሳቸው የማይተማመኑና ምንም ያልገባቸውን ነፍሶች በመጠቀም ይህንን ኃይል ያለውን ስጦታችሁን ሊያስቆማችሁ ይሞክራል፡፡ እናንተ ግን አትፍቀዱ፡፡ እንዳውም ከምንግዜውም የበለጠ በልሳን መፀለይ ያለባችሁ አሁን ነው፡፡ በምትፀልዩበት ጊዜ ለአንዳንዶቻችሁ የልሳኑን ትርጉም እሰጣችኋለሁ፡፡ ይህም የሚቃወማችሁ ሰው ፣ አውሬ ወይም ራሳችሁ እንደሆናችሁ ግልፅ እንዲሆንላችሁ ነው፡፡

"ብዙ የተለያዩ ተቃዋሚዎች ወደፊት ስለሚኖራችሁ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥበብ ያስፈልጋችኋል፡፡ ፀሎትን ከሁሉ ነገራችሁ ፍፁም ቀዳሚ ተግባራችሁ ካደረጋችሁ በቅድሚያ አስጠነቅቃችኋለሁ፡፡ ከራሳችሁ ህይወት እንኳን በበለጠ ከእኔ ጋር በፀሎት ለማሳለፍ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከህብረታችሁ አንድም ሰው ቢሆን ካለ ፀሎት መንቀሳቀስ የለበትም፡፡ ሳይፀልይ ከእናንተ ጋር የሚንቀሳቀሰው ያ ሰው ህብረታችሁን ለማዳከም ዋናው ሰው ነው፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ከዳተኛ ይሆኑና ጫናን በመፍጠር ህብረቱ ያልተገባ ምርጫ እንዲያደርግ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ የሚሻለውም እያንዳንዳችሁ በፀሎት መቆየትና የማይፀልዩት ግን ወደሌላ ሥፍራ እንዲሄዱ መፍቀድ ነው፡፡ ይህም ወደ እኔ ለማምጣትና እኔ በምፈልገው ደረጃ እንዲኖሩ ለማድረግ በራሳችሁ የምትችሉትን ሁሉ አድርጋችሁ መሻሻል ካላሳዩ ነው፡፡

"በመጨረሻውም ነገሮች እየተባባሱ ሲመጡ ከእኔ ጋር በሙሉ ልባችሁ መጣበቅና በራሳችሁ እውቀትና አካሄድ ያለመደገፍ ግድ ይላችኋል፡፡ በትክክለኛው አካሄድ መሄድ እንድትችሉ አነሳሳችኋለሁ፡፡ በህልማችሁ እንኳን እየመጣሁ መመሪያ አሰጣችኋለሁ፡፡ ወደ ክስተቶች መጨረሻ በሄዳችሁ ቁጥር ነገሮች የበለጠ እየተደበላለቁና የእናንተም ነፃ መውጣት እየቀረበ መምጣቱን በደንብ ተረዱ፡፡

"ለጥንካሬ፣ ለብርታት፣ ለጥበብ፣ ለርህራሄና ለሰላም ፀልዩ፡፡ በእምነታችሁ ነው የምትድኑት፡፡ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፡፡ ሁሉም ነገር የሚሆነው በእኔ ላይ ባላችሁ እምነትና መተማመን ብቻ ነው፡፡

"ሰዎች ሁኔታዎችን ማለፍ አቅቷቸው ፍፁም ሲሰበሩና መቀጠል ሳይችሉ  በአይናችሁ ትመለከታላችሁ፡፡ ያስጥለናል  ብለው የገመቱት እንደማያስጥላቸው ሲያውቁ ውስጣቸው ተስፋ ሲቆርጥ ትመለከታላችሁ፡፡ ያን ጊዜ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ መፀለይና ርህራሄን ማሳየት ነው፡፡ የኔ ፀጋ ይሸከማቸዋል፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዳንዶች እንደ ታመመና እንደ አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ፡፡ ለእነዚህም በሚቻላችሁ ሁሉ የሚያስፈልገውን አድርጉላቸው፡፡ በእነሱ ምክንያት ትዕግስታችሁን አትጣሉ ወይም አታባሯቸው፡፡ ምናልባት እነዚህ ሰዎች ለእናንተ ከእኔ ፀጋን ለመቀበል ምክንያት ይሆኑላችኋል፡፡ እናንተ እነርሱን ስለተከበከባችሁ እኔ ደግሞ እናንተን እከባከባችኋለሁ፡፡

"ቢሆንም ግን አንድን ሰው ወደ ኋላ ትታችሁ መሄድ ካለባችሁ ምግብና መጠጥ አብራችሁ በመተው ፀልያችሁ ለእኔ የምህረት እጆች አሳልፋችሁ ሰጥታችሁ ሂዱ እንጂ እራሳችሁን በመከሰስ አትጨነቁ፡፡ እናንተ ማድረግ ያለባችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ አሁን ደግሞ ተራው የኔ ነው፡፡ በምትችሉት ልክ ብቻ ነው የምትፈተኑት፡፡ በዛ ደረጃ በደረሳችሁ ስትደርሱ ወደ እኔ ፊታችሁን መልሱና እንዲህ በሉ፡፡ 'ጌታ እኛ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል ከአሁን ወዲያ ያለውን አንተ ተረከበን፡፡ በዚያን ጊዜ እኔ ደግሞ የምትቀጥሉበትን ብርታት እሰጣችኋለሁ፡፡

"ይህንን አስታውሱ የኔ ኃይል ፍፁም የሚሆነው በእናንተ ድካም ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ነው እናንተ ለእኔ ምን ያህል ውድ እንደሆናችሁና በእውነትም ደግሞ እኔ በእናንተ  ውስጥ ማን እንደሆንኩ የማሳየው፡፡ አሁን መረዳትን ሁሉ በሚያልፍ ሰላም፣ ብርታት፣ ፅናት እባርካችኋለሁ፡፡ ሩጫውን ፈጽሙ፡፡ እናም ይህንን አስታውሱ በሁኔታዎች ሁሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ምንም ነገር ቢያጋጥማችሁ አልተዋችሁም፡፡ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡

## 5.6. የገሃነም መንጎች ወደ ምድር ተለቀዋል

እ.አ.አ. ጁን 20 ቀን 2015ዓ.ም

{The Hordes of Hell Have Been Released}

"የገሃነም መንጎች ወደ ምድር ተለቀዋል"

"አመፅን ለመቀስቀስ ካሉበት ወጥተዋል፡፡ ሰው በእግዚአብሔር ላ በማመፅ ይህንን አድርጓል፡፡ በዚህም ሥራ የሰርን እጅ አለበት፡፡ እነዚህ ሰዎች ፍፁም እውሮች ናቸው፡፡ ይህ ነገር በእነሱ ላይ ምን ረብሻ እንደሚያመጣ አልገባቸውም፡፡ ምን እንዳደረጉ ባወቁ ጊዜ ግን ነገሩን ለማቆም የማይችሉበት ደረጃ ደርሷል፡፡ እነሱ በነቁ ጊዜ ያደረጉት ምድር ደርሶ የምድርን ግማሽ አጥፍቷል፡፡"

እዚህጋ አንድ ነገር ለመጨመር እፈልጋለሁ፡፡ በሰርን ግቢ ውስጥ የሺቫን ሃውልት በመትከል ማታ ማታ መብራቱ እንዲበራ ይደረጋል፡፡ ሺቫ የምትባለው ጣኦት የምትወክለው የጥፋትንና የትርምስን ህይወት ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ የሚለው ከመሰረቱም እነዚህ ሳይንቲስቶች ዕውር ከመሆናቸው የተነሳ ምን ዓይነት ትርምስን እንደሚፈጥሩና በእነሱ ላይ ምን ነገር እንደሚያመጣባቸው አያውቁም፡፡

ጌታዬ እኔ እኮ የመሰለኝ ሰርን በብዛት እየጎዳ ያለው የመሬትን የላይኛውን ክፍል፣ እንደገናም ፍጥረታቶቹም የሚመጡት ከሆነ ከአጋንንቶች ፕላኔት ነበር፡፡

"ገሃነም የሚገኘው ከምድር ታችኛው ክፍል ነው፡፡ በአጋንንት የተለከፉ ፍጥረታት ወደ ምድር በመውጣት ምድርን እንዳይበክሉ መከላከያ የተደርገበትን የተለየ ዳይናሚክ ስበት ሽፋኑን ወደ ጎን በማድረግ አንስቶታል፡፡"

ጌታ እያወራ እያለ አንድ ነገር ተመለከትኩ፤ ብርሃን የሚያስተላልፍ ትልቅ የአሳ መለኪያ ሳህን የሚመስል በመሬት ዙሪያ ያለና በአክስለሬተሩ የተነሳ አየሁ፡፡

"ክሌር በእውነት ከሆነ በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ እነዚህን ልጆች የማይገባቸውን ነገር እያዘበራረቁና በሆነ መልኩ ከእኔ በልጠው ለመገኘት ወይም እኔ የፈጠርኩትን በማባዝትና ከእኔ ጋር ለመስተካከል የሚፈልጉ አድርጌ ነው የማያቸው፡፡ ይህ በአብዛኛው የምሁርነት ኩራት ሲሆን ይህም የወንዶችና የሴቶች ቡድን ከፍ ወዳለው የፕሮፌሽን ጣራ ላይ ወጥቶ ቁጢጥ በማለት ጎብዝናቸውን ለአለም በማወጅ ብሎም ከእኔ ጋር እኩል እንደሆኑ ለማሳይት እየፈለጉ ነው፡፡"

"ነገር ግን አንድ ጉልህ የሆነ የጎደላቸው ነገር አለ፡፡ እና እኔንስ ማን ፈጠረኝ? አያችሁ እኔ በሰጠኋችሁ ህንፃ ብሎኬት ላይ መጫወት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን እርሱም እርስ በርሳቸው የተያያዙት በእኔ ፍቅርና ኃይል ነው፡፡ አዎ እነሱን በማንቀሳቀስ የተለያዩ ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችል ህግ አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የተፈጠሩት በእኔ ነው፡፡"

"የተሰራበትን ብሎኬት ባነሳው እነርሱ እዛው ውስጥ ሆነው አለም ያበቃለታል ነበር፡፡ እነርሱ በባዶ ሥፍራ ከሚንሳፈፍ የሉልሎች ኃይል /globs of energy/ውጪ ምንም አይደሉም፡፡ በነገራችን ላይ ይህ የሰይጣን ግብና ምክር ነው፡፡ የእነርሱን ከፍተኛ ፍላጎት በመጠቀም ሊያጠፋቸው ነው፡፡ አሁን ግን ዓይናቸው ማየት ስለማይችል ተሰውሮባቸዋል፡፡

እንደተናገርኩት ግን ምን እየሆነ እንዳለ መረዳት ሲጀምሩ ያን ጊዜ ደግሞ ወደኋላ ለመመለስ ጊዜው ያልፍበታል፡፡ ነገር ግን አለም የባህር ኃይል እንደተባበረባት ፊኛ ሳትነፋፋ እኔ ጣልቃ እገባለሁ፡፡"

"ለስንት ጊዜ ነው ከፈጠርኳቸውና የህይወትን እስትንፋስን እፍ ካልኩባቸውና ትልልቅ ጭንቅላት ካላቸው ከአንዳንዶቹ ጋር የመማሪያ እርዳታ አድራጊ የምሆነው? አይሆንም ይህ የስራ ህይወታቸውን ያበላሻል፡፡ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ በውስጣቸው ለእውነተኛው የሳይንስ አለም የተጠሩ መሆናቸውን ቢያውቁም እንደ ጲላጦስ ጥሪያቸውን በመከተል ስራቸውን ማበላሸት የለባቸውም፡፡ ጲላጦስ እኔን መስቀል እንደሌለበት ቢያውቅም በተነሳው ተቋውሞ ምክንያት ቄሳር ከስልጣኔ ያባርረኛል ብሎ በመፍራት ብቻ አደረገው፡፡ እናም አሁን ተመልከቱ የማያጓጓውን የገሃነም ህይወቱን፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር፡፡ እነዚህም ማስጠንቀቂ ተሰጥቷቸዋል፣ ነገር ግን ለሥልጣንና ታዋቂ ለመሆን ያላቸው ከፍተኛ ጉጉት ስለበለጠባቸው ታምራት ካልመጣ በስተቀር የሚያስቆማቸው ነገር የለም፡፡"

"ስለዚህም ይህውና የጥፋት አፋፍ ላይ ደርሰናል፡፡ የገሃነም መንጋዎች ወደ ምድር ክልል ወጥተዋል፡፡ እነዚህም የሚያውቁት የሰው ዘርንና እኔ የፈጠርኩትን ፍጥረት ሁሉ መጥላትና ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ እናም አሁን ማንም ሊገምተው ከሚችለው በላይ ሊገለጡ ነው፡፡ ይህም በሰዎች በኩል ምድሪቱን ማጥፋት ነው፡፡ ከሌር እነሱ የራሳቸው መንገድ አላቸው፣ እኔም በእጃቸው ሰጥቻቸዋለሁ፡፡"

"ነገር ግን፣ ጌታ ሆይ መጨረሻ የሌለው አለም የሚለውስ ፀሎትስ?"

"አ! ምድር ትወድማለች፣ ነገር ግን አትጠፋም፡፡ ከእኔ ጋር አዲስ የፀደይ ጊዜን ይዤ እመጣለሁ፡፡ በአዲስ የተፈጠረች ውብ ምድር፣ ሁሉንም መልሼ አስተካክላለሁ፡፡ በአክስለሬተሩ ፕሮጀክት ላይ የሚሰሩት አብዛኛዎቹ ክፉ አይደሉም፡፡ እንዲሁ ትልቅ ምኞት ያላቸውና መሰረታዊ የማሰብ ችሎታ የጎደላቸው ናቸው፡፡ እጅግ መሰረታዊ የሆነውን ህይወት መከተል ሲገባቸው ባለማስተዋል ዝናንና ክብርን የሚያስገኝላቸውን የምሁርነት ግባቸውን/Academic goal/ መርጠዋል፡፡ ብልህ የሆነ ድክ ድክ የሚል ህፃን ልጅ ሊቆጣጠሩት ከማይችሉት እሳት ጋር እየተጫወጡ እንደሆነ ሊያረጋግጥላቸው ይችላል፡፡"

"የዚህም መሰረታዊ ጉዳይ እነዚህ የገሃነም መንጋዎች ወንድና ሴቶችን በሁሉም አቅጣጫ በማነሳሳት ለመጨረሻው ጥፋት ይዳርጓቸዋል፡፡ በሰዎች ትከሻ ላይ በመቀመጥ ንፁህ የሚመስል ሐሳብ ነገር ግን ማዕበላዊ ጥፋት በምድር ላይ የሚያመጣ ፣ በስነ ምህዳሩ በኩል፣ በብዙዎች አይምሮ በኩል፣ አስተሳሰባቸውንና ስነልቦናቸውን በመቆጣጠር ለማይረባ መጨረሻ ህይወት ይዳርጓቸዋል፡፡ እነዚህም መሰረታዊ ጥበብና የማሰብ ችሎታ የጎደላቸው ናቸው፡፡"

"እግዚአብሔርን ያለማወቅና ሞራል ማጣት፣ ለጤናማ ህይወት መሰረታዊ የሆነውን ህይወት ባለመማራቸው እግዚአብሔርን መፍራት እንዲሁም ነገሮች እንዴት ተጠብቀው መቆየት እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ እነሱ ባጠቃላይ ስለ እምነትና ስለ ሃይማኖት፣ስለ ሞራል አስፈላጊነት እንዲሁም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን የህይወት ዘይቤ ከውስጣቸው ፍፁም አሽቀንጥረውታል፡፡ እውነትን ፣ እውነትን ብቻ ቢከተሉ ኖሮ መሰረታዊ የሆነውን የቱ እንደሆነ በመረዳት ቅዱስ ከሆነ ፍርሃት የተነሳ እኔ በስርዓት የፈጠርኳቸውን ነገሮች ባላተረማመሱት ነበር፡፡"

"የኔ ውድ እንዲገባሽ እፈልጋለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ክፉ ሥራው እየጨመረ ይሄዳል፡፡ አዎን ክፉ የሰው ልጆችን ለመንከስ፣ ለመበከልና ለማጥፋት እየተቃረበ ነው፡፡ ቀስ ብሎ ይጀምርና እየጨመረ በመሄድ በሚመጡት ጊዜያት ድልን ይቀዳጃል፡፡"

## 5. 7. ክብርን ለመጠበቅ የሰርን ክፋት መጨመር

እ.አ.አ. ጁላይ 22 ቀን 2015 ዓ.ም

{CEREN Wickdeness increase, pride protection}

ጌታ ዛሬ ማታ ለእኛ ድንቅ መልዕክት ነው ያለው፡፡ ከመልዕክቱ በፊት የነበረውን ሁኔታ ለማስታወስ ያህል ወደ ፀሎት ስመጣ ባልተረጋጋ ሁኔታ ላይ ሆኜ ነበር የመጣሁት፡፡ ምክንያቱም እዚህ ያለውን ነገር ማፅዳትና ማስተካከል የነበረብኝን በአግባቡ ማስተካከልና ስርዓት ማስያዝ ነበረብኝ፡፡ ያው ታውቃላችሁ በአይምሯችሁ የሚመላለሰውን መስራትና መጨረስ ያለባችሁን ካልጨረሳችሁ ድረስ አታቆሙም፡፡ ለማቆም እጅግ ከባድ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ፀሎት ስገባ አይምሮዬ ትንሽ ተናውጦ በትክክል በትኩረት መሆን አልቻልኩም ነበር፡፡ ኦ! ይህንን ጉዳይ ቶሎ ወዲያ ጨርሼ በሙሉ ልቤ ትኩረቴን በጌታ ላይ ብቻ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡

ጌታ ግን ባለ ብዙ ምህረት ነው፡፡ በግልፅ ነበር ራሱን የገለጠልኝ፡፡ ምክንያቱም ከምን ጋር እየታገልኩ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመጨረስ በማደርገው ግብግብ ራሴን እንዴት እየኮነንኩ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስበው እነዚህን ነገሮቹ መቸረስ ነበረብኝ፡፡ ስለዚህም የእኔ ደጋፊ ነበር፡፡

እንዲህ በማለት መልዕክቱን ጀመረ፡ "አንቺ እኔን ለማግኘት ካልመጣሽ እኔ አንቺን አላገኘሽም ማለት አይደለም፡፡ አዎ የሁለትዮሽ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን እንደማንኛውም ሰው ግማሹ ችግርሽ ራስን መውቀስ ነው፡፡ አሁን እርሱን ሁሉ ወደ ጎን እንተወው፡፡ የምንሰራው ሥራ አለ፡፡"

እርሱ እያለ ያለው በውሸት ራስን መኮነን እንጂ ትክክለኛውን መውቀስ አይደለም፡፡ ታውቃላችሁ ክፉ ደግሞ ያንን እድል ይጠቀምበታል፡፡ ታውቃላችሁ እንደዚህ ዓይነት የውሸት ሐሳብ ይልኩባችኋል፡፡ እና ደግሞ ያገኑታል፡፡ ታዲያ በዛ ከቀጠላችሁ ወደ ጌታ መቅረብ ሳይሆን ከእርሱ ሽሽታችሁ እንድትሮጡ ያደርጓችኋል፡፡ ወይም ከእርሱ ጋር ባላችሁ የፀሎት ጊዜ አያናግረኝም ወይም ከእኔ ጋር አይሆንም ብላችሁ እንድትፈሩ ያደርጓችኋል፡፡ ምክንያቱም አንድ መጥፎ ነገር ሰርታችኋል፡፡ እውነቱ ግን ውሸት ተነግሯችኋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ እንጠንቀቅ፡፡ ክፉ በሁሉም ላይ እንዲህ ያደርጋል፡፡

"ከሰርን ጋር ያለው ነገር በመንግስቴ መምጣት ላይ ክልከላን እያደረገ ነው፡፡ የኔ ፈቃድ ይፈፀማል፡፡ ቢሆንም ግን መቼም ቢሆን ተሞርዶ የማያውቀውን የሙሽራዬን የውጊያ ብቃት መሞረጃ ስልት ይሆነኛል፡፡ በእያንዳንዱ የሰይጣን እንቅስቃሴ እኔም በተቃራኒው እንቅሳቀሳለሁ፡፡ በእያንዳንዱ የመከልከል እንቅስቃሴው እኔ ደግሞ አስታጥቃለሁ፡፡ እንደተናገርኩት በምልከው ቅባት አለም እስካሁን አይቶት የማያውቀውን ነገር ተዋጊ ሙሽራዬ ታደርጋለች፡፡

"ከእርሷ የምፈልገው ኮስተር ያለ  ዓላማና ድርጊት ነው፡፡ ከባድ የሆነ ፆም ሳይሆን መካከለኛ ካሎሪ መውሰድ፣ መካከለኛ ራስን መካድና በፀሎት መቀጠል ነው፡፡

*ኢየሱስ መድኃኒቴን እንዳለወሰድ እደረጋለሁ?*

"በትንሹ፣ ነገር ግን የተረጋጋሽና ጠቃሚ እንድትሆኚ እፈልጋለሁ፡፡"

*ነገር ግን ከእነዚህ ኪኒኖች ውጪ መስራት ትችላለህ፡፡*

"ክሌር የራሴ ምክንያት አለኝ፡፡ በመድኃኒት ላይ ተደግፎ መኖር አንዳንድ ሃፍረት አለው፡፡ በእርግጥም በራሴ በቂ ነኝ ብሎ ማሰብን ይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ ትምክህትና ከሌሎች ጋር ራስን ማወዳደር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡"

"ይህ እውነት መሆኑን መቀበል አለብኝ፡፡ ወጣትና ምንም የሰውነት ችግር በሌለብኝ ጊዜ፣ የነበረብኝ ትዕቢት እጅግ ጠንካራና በእውነትም ከፍተኛ ነበር፡፡ ስለዚህም እርሱ የተናገረው እርግጥ በመሆኑ ልቀበለው እገደዳለሁ፡፡ ይህንን እየተነጋገርን እያለ ግን በውስጤ ደግሞ የመጎዳት ስሜት እየተሰማኝ ነበር፡፡ ከዚያም ጌታን ግን ይህ አሁን በልቤ ውስጥ እየተሰማኝ ያለው ምንድነው? ብዬ ጠየኩት፡፡

"ስለሚመጣው ነገር ኃዘን እየተሰማሽ ነው፡፡ ምንም የማያውቁት ናቸው እጅግ የሚጎዱት፡፡ ይህ ደግሞ ማናም ሊገባው በማይችል መንገድ ክፉን ያስደስተዋል፡፡ ቢሆንም ግን የእኔ አሽናፊነት አለ፡፡ የኔ ልጅ አንቺ የተጨነቅጪው እራስሽን ስለመውደድሽ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ የማየውን ማየት አትችልም፡፡ በሙሉ ልብሽ ነው ለእኔ ራስሽን አሳልፈሽ የሰጠሽው፡፡ ድካምሽን አውቃለሁ ስለዚህም ያንን በአሉታዊ ጎን አላየውም፡፡ ምክንያቱም ፍቅርሽ በእውነት ብዙ ነው፡፡ ይህንንም ያለመረዳትሽ ጥሩ ነው ምክንያቱም በትዕቢት ከፍ እንዳትዪ ስለሚረዳሽ ነው፡፡

"በተግባር ግን እንዳውም ከማሳየት በላይ ለእኔ በጥልቅ እንደምትቆረቆሪ አረጋግጠሻል፡፡ ለእኔ የሚያስፈልገው ደግሞ ይህ ብቻ ነው፡፡ ለብዙ አገልጋዮቼ ነገሮችን ሚስጥር አድርጌ አስቀምጫለሁ፡፡ ይኸውም ለእኔ ያላቸውን ስሜት፣ ለእኔ መሰጠታቸውን፣ የፍቅራቸውን ምልክቶችና የአገልግሎት ፍሬዎቻቸውን ሁሉ ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች ደብቄ የያስኩት አውቄ ነው፡፡ ምክንያቱም ለትህትና ደካማ ስለሆኑ እኔ ልጠብቃቸው ስለሚገባ ነው፡፡

"የአንድ ነፍስ ችግሩ የሚጀምረው ምን እንደሰራ ያወቀ ጊዜ ነው፡፡ የሰሩትን ሳያውቁ ሲቀሩና እየረሱት ሲሄዱ ግን በደህና ሁኔታ ላይ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን የተሠራው ሥራ ከእነርሱ የተነሳ እንደሆነ መቁጠር ሲጀምሩና ራሳቸውን እንደ አንድ ተፈላጊ ሰው አድርገው ሲቆጥሩ ይህ ቶሎ ካልተቀየረ ይህ የመጨረሻው ጅማሬ ይሆናል፡፡ ቶሎ ቢሆን ቆይቶ ሰይጣን የመውደቂያ መንገዳቸውን ማቀነባበር ይጀምራል፡፡ እናም በደንብ ስለማይሰሙ ለውድቀታቸው ይመቻቻሉ፡፡

"ከዚህም በመነሳት ለሙሽሮቼ ሁሉ ይህንን እናገራለሁ፡፡ ሰይጣን ያቀደውን ለማስወገድ ለእናንተ ስጦታዎችን ልለቅ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ባህርዮች የእናንተ እንዳይሆኑ እጅግ ትልቅ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ በኢጋንንት ትዕቢት የምትበከሉት ቀስ በቀስ ነው፡፡ ለራሳችሁና ለሰራችሁት ሥራ የሰጣችሁት ሥፍራ የሚሰማችሁና የምታስቡ ጥሩ እየሆነ እንዳይመጣ በደንብ በማጤን መርምሩ፡፡ ይህ በቅርበት ጥናት የሚያስፈልገው ጥንቃቄና ለእኔ ፍፁም መታዘዝን ይጠይቃል፡፡ እንዲህ ሲሆን ጠላት ሥራውን እንዲሰራና በነፍሳችሁ ውስጥ ስር እንዲሰድ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፡፡

"እስካሁን ያደረግሁት ይህንኑ ሲሆን በክሌርም ህይወት እርሷ እስፈቀደች ድረስ እያደረግሁ ያለሁት ይህንኑ ነው፡፡ እርሷም ለእናንተ  በግልፅ አካፍላለች፡፡ ይህም በአንድ አገልጋይ ህይወት ውስጥ እንዴት እንደምሰራ ለማየት ረድቷችኋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ መንገዳችሁን ቢያስቀይር ካልሆነም ደግሞ በሌላ በኩል ወይም በመካከል በማቆም እርሷን በመራሁበት ብቻ ሳይሆን በሌላ መንገድ ለራሳችሁና ለሌሎች ራሳችሁን ግልፅ እንድታደርጉ አደርጋለሁ፡፡ በዚህም እናንተንና ከእናንተ ጋር ያሉትን አበለፅጋችኋለሁ፡፡ በዚህም በቅባቴና በስጦታዬ አሳድጋችኋለሁ፡፡ ከእነዚህ ውጪ ግን ጠላት ከእናንተ ይሰርቃቸዋል፡፡

"ትህትና፣ ቸርነትና ግልፅነት በእናንተ ላይ የተነሳውን የጠላትን እንቅስቃሴ ለመግታት ትልቁ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህም ብዙ ጊዜ የቸርነት በሮችና የትህትና መሻፈኛዎች ናቸው ደካሞችና በቶሎ የሚጠቁ፡፡ እነዚህን ነገሮች ብታውቁና ተግባርያዊ ብታደርጓቸው ደስተኞች ትሆናላችሁ፡፡ ከፈተና መውጫ ሳይዘጋጅለት አንድም ፈተና በእናንተ ላይ አይመጣም፡፡

"ይህ የሚሆነው ግን በትዕቢት እየሰራችሁ ካልሆነ ነው፡፡ ትዕቢት የሚሰራው በደረጃ ነው፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ትዕቢት አለ፡፡ ሁልጊዜም፡፡ ነገር ግን መወጣት የሚቻለው በደረጃ ነው፡፡ ቅባትን በመልቀቅ የእናንተን ምላሽ አያለሁ፡፡ እንዲሁም የጠላትን እንቅስቃሴ አያለሁ እንደገናም የእናንተን ምላሽ እመለከታለሁ፡፡ እናንተ ተሰብራችሁና ተፀፅታችሁ ወደ እኔ ስትመጡ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ መቀጠል እንችላለን፡፡ የትዕቢት ኃጢያት ሰርታችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ወደዛ እያመራችሁ እንደሆነ ሊሰማችሁ ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ነው በትልቅ ፀፀት ወደ እኔ እንድትመጡና በእንጭጩ እንድትቀጩት የምፈልገው፡፡ ይህም መርዙ አድጎ በጠቅላላ ህይወታችሁ ውስጥ ከመሰራጨቱ በፊት ነው፡፡ ትንሽ እርሾ ሁሉንም ሊጥ ታቦካለች፡፡ አንዴ ሥር ከያዘ እንደ ሰደድ እሳት ነው የሚባዛው፡፡ ይህም በእናንተ ላይ ብቻ ሳይሆን በዙሪያችሁ ባሉትና  ነገሩን አስተውለው በማይመለከቱት ሁሉ ላይ ነው፡፡

*እዚህጋ ጌታ  የተናገረውን ግልፅ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡* "ወደ እኔ ተሰብራችሁና በፀፀት ከመጣችሁ . . . የጠላትን እንቅስቃሴ እመለከታለሁ፣ ደግሞም የእናተን ምላሽ አያለሁ" ነው ያለው፡፡

*ይህ ማለት ትዕቢት ሐሳባችሁንና ውስጣችሁን ሊወር ሲመጣ ታውቃላችሁ ማለት ነው፡፡*

*ደግሞም* "ተሰብራችሁና ተፀፅታችሁ ከመጣችሁ ወደሚቀጥለው ደረጃ እንሄዳለን" *ነው ያለው፡፡*

*በተጨማሪም ያለው* "የትዕቢት ኃጢያት ሰርታችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ወደዛ እያመራችሁ እንደሆነ ሊሰማችሁ ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ነው በትልቅ ፀፀት ወደ እኔ እንድትመጡና በእንጭጩ እንድትቀጩት የምፈልገው ይህም መርዙ አድጎ በጠቅላላ ህይወታችሁ ውስጥ ከመሰራጨቱ በፊት ነው፡፡" *ነው ያለው*

*ይህ ማለት በሌላ  አነጋገር* በትዕቢት ተንቀሳቅሳችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ ወይም የትዕቢት ኃጢያት ሰርታችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እናንተ በውስጣችሁ ወደዛ እየሄዳችሁ እንደሆነ ስሜቱ ይሰማችኋል፡፡ ይህም ስለ ራሳችሁ በውስጣችሁ ጥሩ ስሜት እየተሰማችሁ ሲመጣ እንደማለት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ነው እርሱ የኩራትን እንቡጥ እንድትቀነጥሱት የሚፈልገው፡፡ ስለዚህም ከዚያ ከማለፉ በፊት በዚያ ወቅት ላይ በመፀፀት ወደ እርሱ እንድትመጡ ነው የሚፈልገው፡፡

"ለዚህ ነው ክሌርን በተመለከተ ይህ ኃጢያት ነገሮችን ሊቆጣጠር ሲፈልግ በሚያም ሁኔታ ነገሮችን የምሰራው፡፡ ሁልጊዜም ትንሽ ይኖራል፡፡ ነገር ግን እየጨመረ ሲመጣ እናጠፋዋለን፡፡ እንደገና መልሶ እንዳይስፋፋ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልገዋል፡፡ የትዕቢትን ፈተና ስታሸንፉ ቅባቱን፣ በረከቱንና እጃችሁ የነካውን ሁሉ ማብዛቴን እቀጥላለሁ፡፡

ታውቃላችሁ ጌታ ይህ ነገር እንደገና ስለመባዛቱ ሲናገር ሳስብ የነበረው ስለ ካንሰር ነበር፡፡ እናንተን ኦፐራሲዮን ያደርጓችሁና የካንሰር ሴሉን ያወጡታል፡፡ ነገር ግን በየጊዜው ያለማቋረጥ እንደገና በሌላ ቦታ በቅሎ እንደሆነ ይከታተላሉ፡፡ ትዕቢት/ኩራት ደግሞ በእርግጠኝነት በጣም አስቀያሚው ዓይነት መንፈሳዊ ካንሰር ነው፡፡

የኔ ልጆች በዚህ መልኩ ነው በተመረጡትና በምወዳቸው አገልጋዮቼ አማካኝነት የምሰራው፡፡ ክፉዎች የሆኑት ግን በራሳቸው መንገድ በመጓዝ በትዕቢት ይወሰዳሉ፡፡ ቀስ በቀስም ለጥፋታቸው ይሆናል፡፡

በውስጣቸው ስላለው ማንነት ዝንባሌ ግድ የላቸውም፡፡ እርሾ ተጨምሮ በሰሐን እንደተቀመጠ ዱቄት፣ አለም እንደፈለገ እንዲያደርጋቸው ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡

"ስለዚህ እዚህጋ እኔ ለእናንተ ዕቅድን ዘርግቻለሁ፡፡ ሰይጣን በሰርን /CERN/ አማካኝነት እንቅስቃሴውን ሊጀምር ነው፡፡ ክፋት ይጨምራል፣ ከዚህ ጋር ግን ተያይዞ ግን የእናንተ ቅባት የጠላትን ዘዴ ሁሉ ያሸንፋል፡፡ ይህም የሚሆነው ለዕብሪት ራሳችሁን ላለመስጠት ጥብቅ ክትትል በማድረግ ነው፡፡

"ነገር ግን በዚህ ጠንቃቃ ካልሆናችሁ ቅባቴን ያዝ አደርጋለሁ፡፡ ከዚያም በሙሉ ልባችሁ ትፈልጉኛላችሁ፡፡ ከዚያም ጠላት እንዴት ወደ እናንተ ውስጥ እንደገባ ትረዳላችሁ፡፡ ከዚያም ተስተካክላችሁ በትክክል ከቀጠላችሁ ቅባቴን በመመለስ አብረን ማደግ እንቀጥላለን፡፡ እናንተም ከቅባት ወደ ቅባት ከክብር ወደ ክብር ትሻገራላችሁ፡፡ ምክንያቱም በጣም ስለምወዳችሁ በዚህ ዓይነት እንድትቀጥሉ ነው የምፈልገው፡፡ ነፍሳችሁ ለዲያቢሎስ ታልፎ ከሚሰጥ ያለ ቅባት ሆናችሁ ባያችሁ እመርጣለሁ፡፡

"ቅባታችሁ የተወሰደው በእኔ እንደሆነ ወይም የጠላት ተቃውሞ እንደሆነ እንዴት ታውቃላችሁ? የመለያ መሳሪያ አልሰጠኋችሁም? በእናንተ ላይ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማወቅ የሚያስፈልጋችሁ በእናንተ ዘንድ የለምን? የተሰጣችሁን መሳሪያ ተጠቀሙበት፡፡ ጥሳችሁ ስትወጡ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ የሁለትና የሦስት ምስክር ማየት እፈልጋለሁ፡፡"

እዚህጋ ለማለት የምፈልገው ነገር አለ፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን ወይም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የተስፋ ቃሎች ስትጠቀሙባቸውና ጌታ ደግሞ ሲያረጋግጥላችሁ፣ የምትቆሙበት ነገር አላችሁ ማለት ነው፡፡ በዚያ ቃል ላይ ልትቆሙ ትችላላችሁ፡፡ በዚህም ደግሞ ማንኛውም የጠላት ተቃውሞ ሊገጥማችሁ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የቆማችሁት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስለሆነ ነው፡፡

"እውነቱን እነግራችኋለሁ፡፡ የተሰጣችሁን እስከ መጨረሻው ስፋት በደንብ ካልተጠቀማችሁበት በዚህ ምድር ለመስራት የተጠራችሁበትን ጥሪ ልታከናውኑ አትችሉም፡፡ እናንተን የሚቃወሙ ብዙ ኃይሎችና እጅግ ብዙ የውሸት መናፍስቶች

አሉ፡፡ የኔ ፍላጎት ከእኔ ጋር እጅግ ተቀራርባችሁና ተጣብቃችሁ ምን ሁኔታ ላይ እንዳላችሁ የኔን ሐሳብ በማወቅ በየትኛውም ወጥመዳቸው እንዳትጠመዱ ነው፡፡

"አንዳንዶቻችሁ  በሁለትና በሦስት ምስክሮች ምክንያት ወደ አዲስ አካባቢ እንድትሄዱ ትታጠቃላችሁ፡፡ ሌሎች ደግሞ ሰነፍ በመሆናቸውና በእኔ ፈቃድ ውስጥ መሆናቸውን በአሉታዊ መልኩ ማረጋገጥ ስለማይችሉ ወደ ኋላ በማፈግፈግ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ያጣሉ፡፡

"ከቅባታችሁ የተነሳ ወደ ፊት ለመሄድ የሚያስችል ብዙ አጋጣሚዎችን ታገኛላችሁ፡፡ ነገር ግን አዲሱ ቦታችሁን ለመጠበቅ በሰጠኋችሁን ቃል ላይ መቆም አለባችሁ፡፡

"እኔ በዚህ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ነገር ግን ከቃሌ ጋር ተጣበቁ፡፡"

## 5.8. የመከሰስ ስሜት ይሰማችኋል?

እ.አ.አ. ሰፕቴምበር 25 ቀን 2015 ዓ.ም

{Do you feel Condemned?}

*ጌታ ትላንት አብሬህ ስላልነበርኩ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ግን በጣም ደክሞኝና ባለፈውም የነበረብኝ የጥርስ ችግር አልተስተካከለም ነበር፡፡ እናም በትክክል ለመስራት አልቻልኩም ነበር፡፡ ዛሬ ምሽት ግን ተመልሻለሁ፡፡ ስለ ፀሎታችሁ ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በእርግጠኝነት ፀሎታችሁ እጅግ ረድቶኛል፡፡ ዛሬ ምሽት ጌታ ምህረትን አምጥቶአል ስለዚህም ለራሳችንን ይቅርታ እናድርግ፡፡*

*ኢሳያስ ፡ 1-18 <u>"ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።"</u>*

*"በዚህ ወቅት ህዝቤ ስለኃጢያቱ በማሰብ ከሚገባው በላይ በጭንቀት ውስጥ ነው ያለው፡፡ ኃጢያቱ ትልቅ የክስ ተራራ በመሆን ገዝፎበታል፡፡ ከእናንተ ጥቂቶቻችሁ ብቻ ናችሁ በእውነት ይቅርታ እንዳደረኩላችሁ የምታምኑት፡፡*

*ታውቃላችሁ በእኛ ቻናል ያስተዋልኩት ነገር የተወሰኑ ሰዎች እንዲህ ይላሉ « ሳስበው ወቀሳ ተሰምቶኛል፣ ወደ ሲኦል የምሄድና ጌታ በንጥቀት የማይወስደኝ መስሎ ይሰማኛል"፡፡ ነገር ግን በኃጢያት ውስጥ ካልሆናችሁ ይህ ግልፅ ያልሆነ ወቀሳ የተሰማችሁ እንዲሁ ነው፡፡ በእርግጥ ዛሬ ምሽት እንዲህ በማለት አሰብኩ፡፡ ጌታ መጥቶ ይህንን ሐሳብ ከየት እንደመጣ ግልፅ ያደርገዋል፡፡ ይህ ለእርምጃችን እጅግ መሰረታወ ነገር ነው፡፡ ጌታ በመስቀል የሞተው እና ዋጋ የከፈለው ለዚህ ነው፡፡ ለሰራነው ኃጢያት በመፀፀት ከተናዘዝን፣ ንስሐ ከገባንና በእውነት ከመንገዳችን ከተመለስን  ከንጥቀት ወደ ኋላ እንቀራለን በማለት ወይም ክስ ሊሰማን አይገባም፡፡ እስቲ ጌታ ምን እንደሚል እንስማው፡፡*

«ህዛቤ ግን የኔን ይቅርታ መቀበል ያቃተው ለምንድነው? ለምንድነው የጠላቶቻችሁን ውሸትና ወቀሳ አምናችሁ ራሳችሁን የምትወቅሱት? "እመን፣ ትቀበላለህ" የሚለውን ቃል እንድታምነኝ ስንት ጊዜ መሞከር አለብኝ? ኃጥያታችሁ እንደታጠበላችሁ እንድታምኑ ለማድረግ እንደገና ስንት ጊዜ በመስቀል ላይ መሞት አለብኝ?

«ብዙዎቻቸው በክስ ምክንያት አልጋ ላይ ተኝታችኋል፡፡ ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ እንደገና ታስቡትና እንደገና ተመልሳችሁ ትተኛላችሁ፡፡ የኃጥያታችሁ ሸክም እንደገና ይጥላችኋል፡፡ ስለ ኃጢያታችሁ ይቅርታን ጠይቃችኋል፡፡ ነገር ግን ይቅርታ እንደተደረገላችሁ አምናችሁ አልተቀበላችሁም፡፡ ይልቁንም በተከታታይ የሚያጠቃችሁን የከፋውን ውሸት አምናችኋል፡፡

«የተወደዳችሁ ሆይ ለሐሳባችሁ ምርኮኛ አትሁኑ፡፡ የመጣውን ሐሳብ ሁሉ ወደ ልባችሁ ወይም ወደውስጣችሁ ዘልቆ እንዲገባ አትፍቀዱ፡፡ በዚህ ውሸት በተሞላበት ክስ ውስጣችሁን አትሙሉ፡፡ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው እኔ እነግራችኋለሁ፡፡ አንድ በዳዴ የሚሄድ እናቱ ከኩሽና እስክትመጣ የሚጠብቅን ህፃንን አስቡ፡፡ እናቱም እስክትመጣ ወንበር በመንተት በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን የብስኩት ማስቀመጫ ጠርሙሱን ወሰደ . . .  በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ግን የእናቱን መምጣት ለማየት ወደ በሩ እያማተረ ነው፡፡

«ኮኪሱን መውሰድ እንደሌለበት ያውቃል . . . በትንሹም ቢሆን ይህንን ያህል ያውቃል፡፡ ስለዚህ ኮኪሱን እስኪወስድ ድረስ እናቱ እንዳታየው ይጠነቀቃል፡፡ በጥንቃቄም ኮኪሶቹን በእጁ በማፈስ ኪሱ ውስጥ ይከትና ጠርሙሱን ከድኖ ከወንበሩ በመውረድ ወንበሩን ቦታው በመመለስ እናቱ ሳትይዘው ሮጦ ወደ ውጪ ይወጣል፡፡ ኩኪሶቹን አንድ በአንድ እየበላ እያለ የሰራው ትክክል እንዳልሆነ ተሰማው፡፡ ኩኪሶቹ ቢጥሙም እርሱ ግን መጥፎ ሁኔታ ተሰምቶታል፡፡ እኔም በዚህ ልጅ አይምሮ ላይ እየሰራሁ ያለሁት ንስሐ ለመግባት ዝግጁ እስኪሆን ድረስ ነው፡፡ ይህንንም ቀላል አደርግለታለሁ፡፡ ይህም የኩኪሱ ፍርፋሪ በጠረጴዛው ላይ ተዝረክርኳል፡፡ እናቱም ያንን የብስኩት ፍርፋሬ በጠረጳዛው ላይ ህፃኑ ደግሞ በቤቱ ጥግ ፊቱን ወደሌላ አቅጣጫ አድርጎ በአፉ አንድ ነገር ጎርሶ ይታያል፡፡ እናቱም ወደ ህፃኑ ቀርባ "ማሙሽ ትንሽ ኩኪስ ወሰድህ?" ብላ ትጠይቀዋለች፡፡ እርሱም የቀለጠውን ቸኮሌት ከትንንሽ እጆቹ ላይ እየጠራረገ እናቱን በተዘበራረቀ ስሜት ወደ ላይ ያያታል፡፡ ይህም በመስረቁ ጥፋተኝነት ነገር ግን ደግሞ በልቶ በመጨረሱ እርካታ እየተሰማው ነው፡፡ ተግባሩንም ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ በመያዙ ምንም ማስተባበያ መስጠት አይችልም፡፡ ማለት የሚችለው "አዝናለሁ እናቴ ይቅርታ" ማለት ብቻ ነው፡፡ በዛች በመናዘዝ ሰዓት እውነተኛ የመፀፀት ስሜት ይሰማውና ዓይኖቹ በእንባ ይሞላሉ፡፡ በእውነትም አዝኗል፡፡ የሰራው ጥፋት ነው፡፡ ትክክል እንዳልሰራም አውቋል፡፡ ስለዚህም ንስሐ ገብቶ ቅርታም ጠይቋል፡፡

"የኔ ልጆች! እኔ ምን አይነት አምላክ ነኝ? ከንዳችሁን ጨምድጄ በመያዝ በጨለማ ክፍል አስገብቼ ሰውነታችሁ እስኪጠቁር ድረስ በመግረፍ የምቀጣህ ነኝ? ወይንስ ትንሽ የማሰቢያ ጊዜ ሰጥቼያችሁ አስባችሁበት ለውይይት የምጋብዝ ነኝ? ምን እንዳደረኩ ታውቃላችሁ? ህፃኑ ትክክል አልሰራሁም እናቴ፡፡ እንዳለ ስትሉ ምን አላችሁ እላለሁ፡፡ አዝናለሁ በማለት ትንሽ እንባ ከዓይናችሁ ላይ ጠብ ይላል፡፡ በዚህ ግዜ ምን የምል ይመስላችኋል? የምለው "ይቅርታ አድርጌልሃለሁ ሁለተኛ እንዳትደግመው ነው"፡፡

"ከዚህ በኋላ ወጥተህ እየተጫወትህ እለ ደስ የሚል ስሜት መሰማት ይጀምራል፡፡ የምታ ቢሆን ኢጋንንት በትክሻህ ላይ ተቀምጦ መጥፎ እንደሆንክን ኩኪሶቹን እንደወሰድህ ይነግርሃል፡፡ ትንሽ እረፍት ለማድረግ ጋደም ስትል ከዛ የበዙ ኢጋንንቶች አንተ መጥፎ ልጅ ነህ፣ ከእናትህ ላይ ሰረቅህ፣ እያሉ ድምፃቸውን ያሰሙሃል፡፡ በኋላ ደግሞ ሁሉም ወደ እራት ሲሰበሰብ ከእነሱ ጋር እራት ልትቀርብ አይገባህም፣ በቅጣት ክፍል ውስጥ ለብቻህ መቀመጥ አለብህ ይሉሃል፡፡ ይህንንም የምትሰማው በየቀኑ በተደጋጋሚ ነው፡፡ ስለዚህም ስለራስህ ያለህ አመለካከት መጥፎ ብቻ ነው፡፡ ይህም ምንም ተስፋ እንደሌለህና ጥሩ ለመሆን ብትሞክር እንኳን ምንም እንደማይሳካልህ የሚነግርህ ነው፡፡

"እንደዚህ እያደረገ ነው ጠላት ሞራላችሁን የሚሰብረው፡፡ አንዳንዶቻችሁ በህፃንነታችሁ ኢጋንንት ቤተሰቦቻችሁን በመጠቀም እየደጋገሙ መጥፎ ልጆች እንደሆናችሁ በመንገር ወደታች እንድትቀረቁዙ ያደረጓችሁ፡፡ የተሳሳታችሁትን አንድ ነገር እንኳን እንዳትረሱ አድርገዋችኋል፡፡ በተናደዱ ቁጥር ያለፈውን ጥፋታችሁን እያመጡ በዛ ምክንያት ይደበድቧችሁ ነበር፡፡"

"እኔ እንደነርሱ እመስላችኋለሁን?እኔ እንደዛ አይደለሁም፡፡ እኔ የልባችሁን መፀፀት አይና ኃጢያታችሁን ካጠብኩ በኋላ እንደምትሻሻሉ በማሰብ እንደገና 'በሚቀጥለው ደህና መስራት እንችላለን' በማለት በለሰለሰ ድምፅ እናገርና ምን እንደሰራችሁ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ራሳችሁ እንድትገነዘቡት በትዕግስት እጠብቃለሁ፡፡ በዚህም ራሳችሁን ለማሻሻል በምታደርጉት ጥረት አቅፌ በመያዝ ያንን ፈተና እስከታልፉት አግዛችኋለሁ፡፡

“በአንፃሩ ግን ኢጋንንቶች ያለርህራሄ ቀንና ሌሊት ይቀጠቅጧችኋል፡፡ ልጆቼ ለመሆኑ የእኔንና የውሸታሞቹን ኢጋንንቶች ድምፅ መለየት የምትማሩት መቼ ነው? መቼ ነው 'ይቅርታ አድርጌልሃለሁ' የሚለውን ቃሌን የምትቀበሉትስ መቼስ ነው? ከእኔ ለመሸሽ በሌላ መንገድ መሮጣችሁን ትታችሁ እጄን በመያዝ ድጋሚ ሙከራስ የምታደርጉት መቼ ነው? ክስ ራሱ ክስን እንደሚወልድ አታውቁምን? ሰይጣን ተስፋ ለማስቆረጥ ነገሮችን በማያልቅ ነገር ይሞክራል፡፡ የሰጠኋችሁን ስጦታ እንዳትጠቀሙበት ለማድረግ፣ መቼም እንደማልጠቀምባችሁ ለማሳመን፣ በመንግስቴ ምንም ጥቅም እንደሌላችሁ ለማስመሰል፣ ከዚህም በበለጠ ያልዳናችሁ፣ ወደ መንግስተ ሰማይ የማትገቡ እንደሆናችሁ ለማሳመንና ተስፋ ለማስቆረጥ ይሞክራሉ፡፡“

“ነገር ግን ሁላችሁም ጠላትን የምታሸንፉበት ውድ የሆነ ስጦታ ታጥቃችኋል፡፡ በዚህ ወቅት ጠላትን እንድትዋጉ እፈልጋለሁ፡፡ በምትፀልዩ ጊዜ እያንዳንዳችሁ ኃይልን ትቀበላላችሁ፡፡ ነገር ግን ስለራሳችሁ ጥሩ ስሜት ከሌላችሁ ፀጋውን ለመቀበል በድፍረት ወደ ዙፋኑ አትቀርቡም፡፡ ራሳችሁን ንፁህ አድርጋችሁ ካልቆጠራችሁና ክስ የሚሰማችሁ ከሆነ ሌሎችንም ለመርዳት አንድ እርምጃ ወደፊት አትሄዱም፡፡ ይህንን ጥሳችሁ በመውጣት ሰዎችን ለመርዳት ብትጀምሩ እንኳን ጠላት 'የራስህን ኃጢያት ተመልከት፣ እነሱን ልትረዳ አትችልም እግዚአብሔር በአንተ አይጠቀምም' በማለት ሹክ ይላችዋል፡፡

“ጠላት አንድን ክርስቲያንን ዋጋ ቢስ ለማድረግ የሚጠቀምበት ዋናው መሳሪያው ፀፀትና ክስ ዋንኛዎቹ ናቸው፡፡ ኢጋንንቶችም የሰለጠኑት ይህንን ለመፈፀም ሲሆን መመሪያቸውም 'አንድ ክርስቲያን የሚሰራውን እንዲያቆም ለማድረግ ወደ ታች ለማቆርቆዝ ኃጥያቶቹን አስታውሰው' የሚል ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ መስራቱ ነው፡፡ ነገር ግን 'በቅድሚያ ማወቅ፣ በቅድሚያ መታጠቅ ነው' እንደሚባለው ይህንን እወቁ፡፡ ጠላት በምን በኩል እንደሚመጣባችሁ ካወቃችሁ፣ ቀድማችሁ ወደ እኔ በመምጣትና ንስሐ በመግባት ሙሉ ትጥቅ ታጥቃችሁ ወደ ውጊያ ውጡ፡፡ ለያችሁ አንድን ሰው ሞራሉን ለማኮላሸትና ስለ ራሱ ጥሩ እንዳይሰማው ለማድረግ ከዚህ የበለጠ ምን አለ? ኃጢያታችሁ ይቅር ተብሎላችሁ እያለ እናንተ ግን ውሸት የሚያወራላችሁን ከሰማችሁ በስነ ልቦና ጦርነት ተጠቂዎች ትሆናላችሁ፡፡

“ህዝቤ! አሁን ልታድጉ ይገባል፡፡ በምህረቴና በፍቅሬ ተማምናችሁ ወደ ጦር ሜዳው መግባት አለባችሁ፡፡ ለሚወላውል እምነት አሁን ጊዜ የለም፡፡ አሁን ከእኔ ጋር ህብረት አድርጋችኋል፡፡ የእኔ ባህርይ ምህረትና ፍቅር እንደሆነ፣ እንዲሁም እጆቼችም እንደሚረዷችሁና ወደ ላይ እንደሚያነሷችሁ አውቃችዋል፡፡ እስካሁን ከእኔ ጋር ነበራችው፣ ከእኔም ጋር ስለነበራችሁ አውቃችሁኛል፡፡ ስለዚህም አሁን በቃሌ መሰረት በድፍረት ለመንቀሳቀስ፣ መልካሙን ገድል ለመጋደልና ኃሳብን ሁሉ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ብቁ ናችሁ፡፡

“ጠላት ከእኔ ጋር የተቀራረብ ግንኙነት እንዳይኖራችሁ የሚፈልገው አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ከእኔ ጋር በፍቅርና በፍፁም ቅርበት ከእኔ ጋር ህብረት በምህረቴ ትታጠባላችሁ ትነፃላችሁ፡፡ ስለዚህም ተበረታታችሁና ተጠናክራችሁ በመውጣት እኔ እንደምወዳችሁ እንኳን መውደድ ትችላላችሁ፡፡

“ነገር ግን ከእኔ ጋር እንዲህ ያለ ቅርበት ከሌላችሁ እኔን ኃይለኛና ወቀሳ የማበዛ አድርጋችሁ ታስቡኛላችሁ፡፡ ይህም በልጅነታችሁ ስታጠፉ በቤትና በትምህርት ቤት የነበራችሁ ፍትህ አልባ በሆነ መንገድ የተቀጣችሁትን ቅጣት ያስታውሳችኋል፡፡ ኢጋንንቶችም እናንተን ጥፋተኛ በማድረግ በመደጋገም እየተወቀሳችሁ አይምሯችሁ እስረኛ እንዲሆን

ተደርጋችኋል፡፡ ከእኔ ጋር እውነተኛ የሆነ መቀራረብ ስላልነበራችሁ፣ ላቅፋችሁ፣ ይቅር ብያችሁ በጥንካሬ በመውጣት እንደገና እንድትሞክሩ ለማድረግ አልችልም ነበር፡፡  ከዚህም የተነሳ ጭንቅላታችሁ "ጥፋተኛ" በሚል ዳመና ሞልታችሁ ትሮሩ ነበር፡፡

"እናም በመጨረሻው እኔ ምህረት እንደማደርግ ማመን አለባችሁ፡፡ ለእናንተ ስል እንደተሰቃየሁና በመስቀል ላይ እንደሞትኩ ማመን አለባችሁ፡፡ ምንም እንኳን ኃጢያታችሁ እንደ ደም የቀላ ቢሆንም እንደ በረዶ እንደማነፃችሁ ማመን አለባችሁ፡፡ ገዳይ የሆነውንና ዝሙት የሰራውን ዳዊትን ይቅር አላልኩምን?  ፈሪሳውያንና የሮም ወታደሮች ይቅር አላልኩምን? ' አባት ሆይ የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አላልኩምን?

*"ታዲያ ለእነዚህ ሁሉ ምህረትን ካደረኩ እናንተ ለሰራችሁት ኃጢያት ምህረትን የማትቀበሉት ለምንድነው?"*

"በጣም በቀላሉ ለመናገር ክስን በማብዛት ዋጋ የሌለህ እንደሆነ ለማሳመን የሚጥሩትን የአጋንንቶችን ድምፅ በተደጋጋሚ ሰምተሃል፡፡ ክስ የአጋንንቶች ንብረት ወቀሳ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እስካሁን ግልፅ ሊሆንልህ ይገባል፡፡ እኔ ስወቅስህ እኔን ስላሳዘንከኝ ደስ በሚል ሁኔታ ታዝናለህ፡፡ በዚህም ምክንያት ያንን ኃጢያት ደግመህ እንዳትሰራው ፍላጎት ያድርብሃል፡፡ በዛን ጊዜ ታዲያ ከአንተ ጋር በመሆን ለወደፊቱ እንዳበረታህ እኔን እንድትጠራ አድርጋለሁ፡፡

ነገር ግን ጠላት ሲከስህ የሚያደርገው ነገር አንተ ምን ያህል መጥፎ፣ የማትረባ እደሆንክ ሲያሳምንህ ነው የሚሞክረው፡፡ በተጨማሪም  የማትጠቅም እንደሆንክና እግዚአብሔር እንደማይጠቀምብህ ሊያሳምንህ ነው የሚጥረው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚመጣው ትልቅ ሐፍረትና ወደ እኔ ከመምጣት ይልቅ ከእኔ ለመሸሽ መፈለግ ነው፡፡ በዚህ በጠላት ሐሳብ ተሸነፍህ አንዴ መሸሽ ከጀመርህ ቀስ በቀስ ተስፋ ወደ መቁረጥ ወደታች የሚጥለውን ጠመዝማዛ መንገድ ትጀምራለህ፡፡

"እናም በሰይጣን አገልጋዮች የሚነገራችሁን ይህንን ዓነት ነገር ሲሰማችሁ የተናገርኳችሁን ቃል ልብ አድርጉ፡፡

"አሁን የሰጠኋችሁ ትምህርት የኔን የተረጋጋ ወቀሳን የሰይጣንን የክስ ሐሳብ እንድትለዩ የሚያስችላችሁ ነው፡፡ ስለዚህም ሰይጣን እናንተን ለመጣልና አስከመጨረሻው ምንም ፀጋና ጥቅም የሌላችሁ ክርስቲያኖች ሊያደርግ ካዘጋጀው ወጥመድ አምልጡ፡፡ የኔ ውዶች ይህንን በልባችሁ ያዙ፡፡ ይህንን በልባችሁ በመያዝ የሰይጣንና የሰራተኞቹ የሆነውን ክስ አልቀበልም በሉ፡፡

"አሁን በማያልቀው ፍቅሬና ርህራሄ እባርካችኋለሁ፡፡ በምህረቴ ተመላለሱ፡፡ ታዲያ ኃጢያታችሁ እንደ አለላ ቢቀላም አብረን ምክንያቱን ተመልክተናል፣ አሁን እንደ በረዶ ነጭ አድርጌ አጥቤዋለሁ፡፡

# ክፍል ስድስት
# ከጌታ መልዕክት እንዴት መስማት እንደምንችል

{Messages to Help You Know How to Hear From the Lord}

---

## 6.1. ከጌታ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲኖረን የሚያስችል ፀሎት/የጌታ መኖሪያዎች ፀሎት

እ.አ.አ. ጁን 19 ቀን 2015 ዓ.ም

{Prayer that prepares us for intimacy with Jesus: Dwelling Prayer}

ይህንን ዓነት ፀሎታችንን የጌታ መኖሪያዎች ፀሎት/ Dwelling Prayer/ ያልንበት ምክንያት ከጌታ ጋር ነዋሪዎች ስለሆንን ነው፡፡ ይህም በተስፋ ቃሉ መሰረት ከወደድነው እንታዘዘዋለን፣ እርሱም በእኛ ውስጥ ያድራል(ዮሐንስ 14፡21)፡፡ ስለ ጌታ መኖሪያዎች ፀሎት በተመለከተ ብዙ ዝርዝር የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስላለ ቅርብ ለሆነ ህብረት እጠራችኋለሁ የሚለውን በዝርዝር ማግኘት ትችላላችሁ፡፡/ I'm Calling You To Intimacy (Playlist) Paste in your browser: https://www.youtube.com/playlist?list=PLJPAM4wf9t65VEZlpObNPlihVpJtTEsV

ይህንን ፀሎት ከመጀመራችሁ በፊት ጠላትን ማንኛውንም ክፉ ለማሰር የሚደረግ ፀሎት/ the binding prayer/ በሚለው ፀሎት ጀምሩ፡፡ ይህም ፀሎት የሚጀምረው ኃጢያታችንን ድክመታችንን በመናዘዝ ነው፡፡

ወደ ፀሎቱ በምትገቡበት ጊዜ በስልጣን እያወጃችሁ መፀለያችሁን እርግጠኞች ሁኑ፡፡ በኢየሱስ ሥም ስልጣን መሰረት በሰዎች፣ በመናፍስትና በሚገለጠው ነገር ላይ ሁሉ በበላይነት ነገሮችን በሥልጣን በማወጅ ፀልዩ፡፡ በጌታ መገኘት ውስጥ የምንገባው በምስጋና፣ በውዳሴ፣ በእውነትና በመንፈስ አምልኮን በማቅረብ ነው፡፡ ይህንን በሙዚቃ ወይም ከሙዚቃ ውጪ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ እኛ ግን የተለማመድነው እርሱን በቀጥታ የሚያመሰግኑና የሚያወድሱ ቃላቶች ባሉት መዝሙር ነው፡፡ ነገር ግን ምሪት እንደተሰጣችሁና ያለሙዚቃም እንዲሁም በመፀለይና በማምለክ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ከሙዚቃ ውጪ በልሳን በመፀለይም ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ በአጠቃላይ እርሱ ወደሚገኝበት ወደ ልባችሁ ወደ እርሱ ቅረቡ፡፡

እያመለካችሁ እያላችሁ የኢየሱስ በአጠገባችሁ ሆኖ በአይምሮአችሁ ሊታያችሁ ይችላል፡፡ ይህ ዝም ብሎ እናንተ በኃሳባችሁ የፈጠራችሁት ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም እግዚአብሔር በህሊናችሁ ቀድሶ ያስቀመጠው የኢየሱስ መልክ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም ዝም ብላችሁ እንደ ቀላል አትቁጠሩት ይልቅስ እውነት እንደሆነ ተቀበሉት፡፡

በመንፈስ በዓይነ ህሊናችሁ ያያችሁትን ትኩረት እየሰጣችሁ አምልኮአችሁን ዝም ብላችሁ ቀጥሉ፡፡ ጌታ የሚላችሁን ለመስማትና ለማድረግ ተዘጋጁ፡፡ በመንፈሳችሁ ላያችሁት ነገር ትኩረት በመስጠት እርሱ የሚላችሁን አድርጉ፡፡ የእርሱ ፍቅር ራሱ ወደ እርሱ ይስባችኋል፡፡ ፍቅሩ ይሰማችኋል፡፡ ደግሞም እናንተን በማየቱ ደስ እንደተሰኘ ይሰማችኋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ ጋር ሙሉ ለሙሉ ለመቆየት ሞክሩ፡፡ ጌታን እንዳናየውና እንዳንሰማው መጋረጃ የሚሆንብን ነገር የራሳችን እምነት ማጣትና በውሸት የተቀነባበረ ራስን ጥፋተኛ አድርጎ ማየት ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የምታሳልፉትን ጊዜ በቀላሉ አትመልከቱት፡፡

እንዲሁም በመንፈስ በዓይነ ህሊናችሁ የተመለከታችሁትን የእርሱን መልክ ከሐሳባችሁ ቶሎ አታጥፉት፡፡ አለማመን የሚጀምረው በዚህ መልኩ ነው፡፡

ጌታም ከእናንተ ጋር ማውራት ይጀምር ይሆናል፡፡ ይህም ሐሳብን በውስጠኛው አይምሮአችሁ በማምጣት ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ መንፈሳዊ ድምፅ የሚመስል፡፡ ከእናንተ ጋር ሲሆን እርሱ ሁልጊዜም ደግ፣ ለስላሳና ወዳጅ ነው፡፡ እርሱ በፍፁም መቼም ሸካራና ኃይለኛ ወይም ከሳሽ አይደለም፡፡

ምናልባትም እንድትፅፉም እንኳን ሊጠይቃችሁ ይችላል፡፡ ከእርሱ ጋር የምትነጋገሩትን እንደ መፅሔት አድርጋችሁ እንድትፅፉት ሊጠይቃችሁ ይችላል፡፡ ይህንን ማድረግ በጣም ጥሩ ነገር ነው፡፡ በኋላም ተመልሳችሁ ምን እንዳላችሁ ስታነቡት ደግማችሁ እርሱን ለማድመጥ በራሳችሁ ትተማመናላችሁ ፡፡ እናንተም መልስ ልትሰጡት ትችላላችሁ፡፡ ይህም በሁለታችሁ መካከል የሁለትዮሽ የንግግር ጊዜ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ኢየሱስ ከእናንተ ጋር ሲሆን ሁልጊዜ እጅግ ንፁህ ነው፡፡ ከእርሱ ዘንድ የእርኩሰትና የወሲብ ፍላጎት ፍንጭ በፍፁም በፍፁም አይገኝም፡፡ በፍቅር ሊያቅፋችሁ ወይም ግንባራችሁን ሊስማችሁ ይችላል፡፡ ነገር ግን በፍፁም ምንም የወሲብ ፍንጭ የለም፡፡ እርሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ደግሞም ንፁህና ድንግል ነው፡፡ የእርሱ የፍቅር መግለጫ ዓላማው እናንተ በግል ለእርሱ ልዩ ዋጋ ያላችሁ፣ በማያልቅ ፍቅሩ የምትወደዱ እንደሆናችሁ ለመግለፅ ነው፡፡

በዚህ ወቅት እናንተ ለሌሎች ከልባችሁ የሚሰማችሁን ፀሎት ሁሉ ልትፀልዩ ትችላላችሁ፡፡ እርሱን መስማት እየለመዳችሁና ምቾት እየተሰማችሁ ስትሄዱ ከእርሱ ጋር በሆናችሁ ቁጥር በእርሱ መገኘት ውስጥ በቀላሉ መግባት እየቻላችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ እርሱ ብትሰሙትም ባትሰሙትም፤ ብታዩትም ባታዩትም ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የሚገኘው በቀኝ እጃችሁ አጠገብ ነው፡፡

በኃጢያት ከወደቃችሁና የተወቀሳችሁ መስሎ ከተሰማችሁ ወደ እርሱ ሩጡ እንጂ ከእርሱ አትሽሹ፡፡ ኃጢያታችሁን ለመናዘዝና እርሱን ይቅርታ ለመጠየቅ አትፍሩ፡፡ ይህ ለእርሱ ትልቅ ደስታን ይሰጠዋል፡፡ ደግሞም ይቅር ለማለትና ሌላ ፈተና ሲገጥማችሁ ጠንካራ እንድትሆኑ ፀጋን ለመስጠት እጅግ ፈጣን ነው፡፡

ሰዎች በእርግጥ ጌታ መሆኑንና አጋንንት ወይም የለመደ መንፈስ መሆኑን እንዴት ታውቃላችሁ ብለው ይጠይቁናል፡፡ የኛ መልስ በፍሬው ታውቁታላችሁ ነው፡፡ በእናንተ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚመስል ቅርፅ ያለውና ምንም አጋንንት ሊሞላው የማይችል ቦታ በእናንተ ውስጥ አለ፡፡ በፀሎት እያድጋችሁ ስትሄዱ ይህ ቦታ ሙሉ ሲሆንና ባዶ ሲሆን ይሰማችኋል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ፍፁም የሆነ የማይልቅ ሰላም ይሰማችኋል፡፡ ደግሞም የምትፈልጉትን ዓይነት ጥንካሬ ታገኛላችሁ፡፡ ምክንያቱም በእርግጥም እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ስለሆነ ነው፡፡

ህፍረት፣ ግራ መጋባት አይሰማችሁም፡፡ ምንም እንኳን ወቀሳና ይቅርታ መጠየቅ ቢሰማችሁም ክስ ግን አይሰማችሁም፡፡ ይቅርታንም በመጠየቃችሁ የሚሰማችሁ ደግሞ ፍፁም ሰላምና እርሱ ለእናንተ ያለውን ፍቅር ነው፡፡ አንዳንደ ሰዎች ደግሞ በራዕይ እንደ ኢየሱስ የተገለጠላችሁን አካል ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መጥቶ እንደሆነ ትጠይቁታላችሁ? ብለው የቃላት ማረጋገጫ ጠይቀውናል፡፡ ለዚህ መልሴ "አዎ" የሚለውን መልስ ብቻ እንደ ማረጋገጫ አልወስደውም፡፡ ትክክለኛው መልስ መሆን ያለበት የጠየቃችሁትን ሙሉውን በመድገም ሲመልሱት ነው፡፡ ይህም "አዎ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ

እመሰክራለሁ" የሚል መሆን አለበት/ዮሐንስ ፤:4/፡፡  አንድ ጊዜ ኢጋንንቶች እንደዚህ ጠይቀናቸው አዎ የሚል ምላሽ ሰጥተውን ነገር ግን ውሸት መሆኑን የደረስንበት ጊዜ አለ፡፡ ስለዚህም በዚህ ዓይነት መልኩ መልስ ሲሰጡን አናምናቸውም፡፡

ከጌታ ጋር የቆይታ ጊዜ ሲኖራችሁ ጥላቻ፣ ክስ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ቅናት፣ መደናገጥና ከባድ የሆነ የወሲብ ቅስቀሳ ከጀመራችሁ ይህ ጌታ አይደለም፡፡ ስለዚህም ጠላትን የማሰር ፀሎት እንደገና ፀልዩ፡፡ እንደገናም እርሱን ማምለክ ቀጥሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ምናልባትም የሚሻለው በሙዚቃ ጌታን ማምለክ መቀጠል ነው፡፡ እኛ ብዙውን ጊዜ ወደ እርሱ መገኘት የሚያስገቡን ሙዚቃዎች አሉን፡፡

ይህንን ሁል ጊዜ አስታውሱ በጌታ መገኘት ውስጥ የሚኖረው ፍቅርና መረጋጋት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ከሆነ ግን በትልቅ ጥርጣሬ ውስጥ መሆን አለባችሁ፡፡ በዚህም ጊዜ ጠላትን የማሰር ፀሎት እንደገና ፀልዩ፡፡

የመጣችሁት ከጥንቆላ ልምምድ ውስጥ ከሆነ፣ በህፃንነታችሁ ለሰይጣን፣ ለቃልቻ፣ ለቦረንቲቻና ለመሳሰሉት ተሰጥታችሁ ከሆነ ወይም ከማንኛውም የጥንቆላና የኢጋንንት አምልኮ የተያያዘ ህይወት ከነበራችሁ ከእርሱ ጋር መነጋገራችሁ እርግጠኞች እንድትሆኑ በመጀመሪያ ከእነዚህ ነገሮች ነፃ መውጣታችሁን ማረጋገጥ አለባችሁ፡፡

በተጨማሪም በቤተሰባችሁ የአይምሮ ህመም ካለና  ያልተረጋጋ ነገር ውስጥ ከሆናችሁ ወደ ጌታ መገኘት ውስጥ ለመግባት ወደሚደረገው አምልኮ መግባትና እጅግ ምጡቅ ወደ ሆነ ሐሳብና ስሜት ውስጥ መግባት የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም እተንቀሳቀሳችሁት ያላችሁት በመንፈሳዊው ዓለም ነው፡፡ ይህ እንዴት ልታዩት ትችላላችሁ መሰላችሁ አንድ የምትፈልጉትን ዕቃ ለመግዛት ወደ ገበያ ስትሄዱ በገበያ ውስጥ የምታገኙት እውነተኛ ገዢዎችን ብቻ ሳይሆን ሌቦችን፣ እንደገናም በእናንተ ላይ የክፉ ዓላማን ለማስፈፀም የሚንቀሳቀሱ ሰዎችንም ታገኛላችሁ፡፡

የጌታ መንፈስ በኃይል ባለበት ሁሉ የተቃራኒውም ኃይል እንደዛው በኃይል ይንቀሳቀሳል፡፡ ምክንያቱም ከኢየሱስ ጋር በመንፈስና በእውነት ቅርብ የሆነ ማንኛውም ሰው ለጨለማው መንግስት ስጋት ነው፡፡ ስለዚህም ኢጋንንቶች ከጌታ ጋር ግንኙነት እንዳታደርጉ የተቻላቸውን ለማድረግና ተስፋ ለማስቆረጥ በዛ ይገኛሉ፡፡

ነገር ግን ጌታ ደግሞ ይመራናል፣ ይጠብቀናል፡፡ የሚያንገጫግጫ ነገር ቢያጋጥማችሁ ፍርሃት አይደርባችሁ፡፡ ጥያቄ ካላችሁ እኛን ወይም በዚህ ነገር ልምድ ያላቸውን ቡድኖች ጠይቁ፡፡ ይህንን አስታውሱ የጌታ ሥም ሲጠራ ጉልበት ሁሉ ይበረከካል፣ ምላስ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ይላል፡፡

ይህንን ሥም አውጁ "በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም እንድትወጣና ዳግም እንዳትመለስ አዝሃለሁ፡፡" ወይም ጠላትን የማሰር ፀሎትን ተጠቀሙ፡፡ ይህ ጠላትን የማሰር ፀሎት እስካሁን ካገኘነው ሁሉ ፍቱን ሆኖ ያገኘነው ፀሎት ነው፡፡ በየጊዜውም አዲስ ነገር እንጨምርበታለን፡፡ ስለዚህም ተመራጩ በቅርብ ቀን የቀረበው ነው፡፡

እናንተ የጌታ ወዶች ናችሁ፡፡ እናንተ ከምትፈልጉት በላይ እርሱ የእናንተን አብሮነት ይፈልጋል፡፡ ፍፁም እውነታውም ይህ ነው፡፡

## 6.2. ከጌታ ዘንድ ቃል መቀበል

እ.አ.አ. ጁን 26 ቀን 2015 ዓ.ም

{Getting a word from the Lord}

ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው። መዝሙር 119፡105

የዚህ ቻናል ዓላማ ከኢየሱስ ጋር የቅርብ ግንኙነት ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን በግላችሁ ከእግዚአብሔር እንዴት መስማት እንደምትችሉ ትምህርት መስጠት ነው፡፡ ማለትም ልክ አንዳንድ ሰዎች ለእኛ ከጌታ ዘንድ ቃል እንድንነግራቸው በኢ-ሜል እንደሚጠይቁን ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ እንድናተኩር የሚፈልገው ከእርሱ ቃል እንዴት እንደምታገኙ እንድናስተምራችሁ ነው፡፡ ይህ ምንም ሚስጥር ነገር የለውም፡፡ "ፈልጉ ታገኛላችሁ፣ጠይቁ ለእናንተም ይሰጣችኋል" ነው ነገሩ፡፡

እኔ በመጀመሪያ ክርስቲያን የሆንኩ ጊዜ የምከታተልበት ቤተ ክርስቲያን በኤቨሊን ክሪስቲሰን የተዘጋጀ "ጌታ ለወጠኝ" በሚል የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ነበረን፡፡ በዛን ጊዜ ነበር በመልዕክቱ ውስጥ ከጌታ መልዕክትን መስማት የጀመርኩት፡፡ በዚህ ቀላል መፅሐፍ ከመፅሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ክፍል አንብባችሁ በራሳችሁ መንገድ ለየቀኑ ውሏችሁ ምሪትን ከጌታ ድምፅን በመስማት እንድትቀበሉ ትማራላችሁ፡፡ ይህ እንግዲህ ሬማ ይባላል፡፡ ይህም ሥልጠና የተለያዩ የስልጠና ደረጃዎች አሉት፡፡ በዚህም ልምምድ እያደጋችሁና እየበሰላችሁ ስትመጡ ጌታ ወደ ጥልቅ ውኃዎች ይወስዳችኋል፡፡ ለአሁኑ ግን ቀላል እናድርገውና ከፅንስ ሐሳቦቹ እንጀምር፡፡

በአዲስ ኪዳን "ቃል" ተብሎ የተተረጎመውን የሚገልፁ ሁለት የግሪክ ቃላቶች ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያው "ሎጎስ" ሲሆን ይህም የሚያመለክተው የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃልና እንዲሁም ኢየሱስን ነው፡፡ ኢየሱስ ህያው ሎጎስ ነው፡፡

በመጀመሪያ ቃል ነበር (ሎጎስ)፣ እናም ቃሉ(ሎጎስ) ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፡፡ እና ቃሉ(ሎጎስ) እግዚአብሔር ነበር፡፡ዮሐንስ 1፡1

የእግዚአብሔር ቃል ሎጎስ/ ሕያው ነውና፥ የሚሠራም . . . ዕብራውያን 4፡ 12

ሁለተኛው ቃል የሚለውን የአዲስ ኪዳን የሚገልፅ የግሪክ ቃል ሬማ የሚለው ሲሆን የሚያመለክተውም በመነዳት በመንፈስ የሚሰጥ ቃል ነው፡፡ ሬማ መንፈስ ቅዱስ ከመፅሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ወይም አንድ ጥቅስ ትኩረት እንድንሰጥ በማድረግ በወቅቱ ለሚያስፈልገን ጥበብ ወይም ምሪት እንድንጠቀምበት የሚሰጠን ቃል ነው፡፡ ስለዚህም መፅሐፍ ቅዱሳችንን ስናነብ በቅፅበት ከምናነበው ገፅ ውስጥ ትኩረታችንን ይሳብና በመንፈስ ቅዱስ መንቀሳቀስ አማካኝነት ለጊዜው ህይወታችን የሚያስፈልገንን ይናገራል፡፡ በደንብ ካዳመጥን ለእኛ የሚሆነንን የጌታን የጥበብ ድምፅ እንሰማለን፡፡ በዛው ጊዜ ትንሽ ልምምድ ያስፈልጋል፡፡

ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ /ሬማ/ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ... ፡፡ ማቴዎስ 4፡4

ኢየሱስ እንዲህ አለ . . . "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል /ሬማ/መንፈስ ነው ሕይወትም ነው (ዮሐንስ 6፡63)፡፡ ጌታ እርምጃ እንድንወስድ አንድ የሬማ ቃል ሲሰጠን ለማረጋገጥ ሌላ ሁለተኛ ሬማ ይሰጠናል፡፡ ". . . ሁሉ ነገር በሁለትና በሦስት ምስክር አፍ ይጸናል 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡1 ፡፡ "እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው/ሬማ/ ሮሜ 10፡17፡፡ መላዕክቱ ለማርያም ልጅ ትወልጃለሽ ሲላት "ማሪያምም እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ/ሬማ/ ይሁንልኝ አለች። (ሉቃስ 1:38)

ኢየሱስ ጰጥሮስ እንደሚክደው ተናገረ፡፡ "ጴጥሮስም፦ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል/ሬማ/ ትዝ አለው፤ ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ።"(ማቴዎስ 25፡75)

እንደዚህ ነው ከጌታ ማረጋገጫችንን የምናገኘው፡፡ ስለ አንድ ነገር የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው እንጂ የኛ አመለካከት ምንም አያደርግም፡፡ ስለዚህም ከእኛ ውጪ የሆነ ማረጋገጫ ስንፈልግ ፀልየን መፅሐፍ ቅዱሳችንን ገልጠን ማንበብ መጀመር ነው፡፡ ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱሳችንን ሁሉንም ከማንበብ በባርቦር አታሚዎች የተዘጋጀውን የተስፋ ቃሎችን አሰባስቦ የያዘውን መፅሐፍ መጠቀም እንችላለን፡፡ ይህም መፅሐፍ የተዘጋጀው ከመፅሐፍ ቅዱስ በተወጣጣ የተስፋ ቃሎች ሲሆን የተቀመጠውም በየርዕሱ ተደርጎ ነው፡፡  ስለዚህም ይህንን መፅሐፍ ስትከፍቱት ወዲያው የምታገኙት በርዕስ የተከፋፈሉ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ነው፡፡ ለምሳሌ ስለ የወንድማማች ፍቅር፣ በችግር ጊዜ እርዳታ፣ ጋብቻ፣ የወላጆች ድርሻ ወዘተ የሚሉትን ነው፡፡ ማንበብ ስንጀምር አንዳንድ የጥቅሱ ክፍሎች ወደ መንፈሳችን ዘልቀው በመግባት በእኛ ውስት ማስተጋባት ይጀምራሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ቆም ብለን በእነዚያን በተቀቡ ቃላቶች ላይ መቆየትና እንዲያገለግሉን መፍቀድ አለብን፡፡

ስለዚህም ከጌታ ምሪት ስንፈልግ የምናደርገው ነገር ዝም ብለን ለምሪት በመፀለይ ነው፡፡ እንደዚህ ተብሎ እንደተፃፈው "ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።"(ያዕቆብ 1፡5-6)

በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፣ እኔም አውቃቸዋለሁ፣ ይከተሉኝማል፡፡ (ዮሐንስ 10፡27)

ስለዚህም ያ ድምፅ የትኛውም ሌላ ድምፅ ሊያስመስለው በማይችል መልኩ በእኛ ልብ ውስጥ ያስተጋባል፡፡ እኛ ይህንን ዓይነቱን የምንቀርበው እንደ አንድ ህፃን ልጅ ሆነን ነው፡፡

"እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።"(ማቴዎስ 18፡2-4)

በጣም ቀላል ነው፡፡ ከልባችን በእውነትና የምር በመሆን መልስ ለማግኘት እንፀልያለን፣ ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሳችንን ወይም የመፅሐፍ ቅዱስን የተስፋ ቃሎች ከፍተን ማንበብ እንጀምራለን፡፡ እያነበብን እያለን ከተፃፈው አንዱ ክፍል ወደፊት

በመምጣት ይቆማል፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ያንን ቃል በሐሳባችንና በልባችን ህያው ወይም ሬማ እያደረገው ነው፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ለጊዜው ለምንፈልገው ምሪት የሰጠው ቃል ነው፡፡

እኛ ሦስት የሬሜ ቃሎችን ነው በተከታታይ የምንመርጠው፡፡ ይህም ግልፅ ለማድረግና መሰረታዊ የጌታን ሐሳብ በተያያዘ መልኩ ለመያዝ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የመፅሐፍ ቅዱሱን የተስፋ ቃል መፅሐፍ ከመክፈታችን በፊት ከመንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለመቀበል መፀለይን እንመርጣለን፡፡ ይህንን የምናደርገው በሆነ መንገድ ብቻ ጠላት በሚገለጠው ገፅ ላይ ጣልቃ በመግባት እግዚአብሔር ሊሰጠን ያለውን ቃል በተቃራኒው መንገድ ሲያደርግ ስላገኘነው ነው፡፡ እኛ በቀላሉ የምንለው "በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም የዚህን መፅሐፍ የውሸትን መንፈስ እናስራለን፡፡" ብታምኑም ባታምኑም ብዙ ጊዜ ጠላት የምናነበውን ዘልቆ ሲገባ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ ለመጠበቅ ብለን ሁልጊዜ ይህንን ፀሎት እንፀልያለን፡፡ በተጨማሪም "መንፈስ ቅዱስ እባክህ በዚህ መፅሐፍ በኩል ምሪትህን ስጠኝ" ብዬ እፀልያለሁ፡፡

አንዳንዶች ዕድል ነጋሪዎች በማለት ይወነጅሉናል፡፡ ነገር ግን የጥንት ነቢያቶችና የጌታ ሐዋርያትም የተጠቀሙበትን የሎተሪ ዕጣ ስላላወቁት ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ላይ የጌታ ሐዋርያት በይሁዳ ፋንታ ማንን መተካት እንዳለባቸው ለማወቅ ዕጣ ነው የጣሉት፡፡ "የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፥ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ። ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ። (ሐዋርያት 1፡24-26)

ስለዚህም የመፅሐፍ ቅዱስን የተስፋ ቃል መፅሐፍ ስንጠቀም ጌታን እንዲህ ብለን እንጠይቃለን (የሁሉን ልብ ማን ያውቃል) ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰን ለእኛ ምን እንሚያስፈልገን እንዲገልጥልን እንጠይቀዋለን፡፡

በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል። ... (ምሳሌ 3፡5)

ገና በመጀመሪያው ጊዜ በትክክል ለመስራት ይህንን ያህል ቀላል ነው፡፡ ነገር ግን በራሳችን ጥበብ ከተደገፈን ምርጫችንም ጌታን ሳያስደስተው ይቀራል እኛም ብዙ ዋጋ እንከፍላለን፡፡ ምንም ትልቅ እውቀት ቢኖረውም እንኳን እውቀቱ ውስን የሆነውን የሰው ልጅ ትክክለኛ ዘገባ ከመቀበል ይልቅ እኔ ቶሎ ብዬ የማደርገው እንደ አንድ አምስት አመት ልጅ ራሴን በጌታ ምህረትና ጥበብ ላይ ጥዬ መንቀሳቀስ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ጥበብን መጠየቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ/ oracle/ይባላል፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህንን ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ተግባቦት ይሉታል፡፡ ይህም ቃል የሚያሳየው እግዚአብሔርን በመጠየቅ የሚገኘውን መልስ ወይም ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ሳይጠየቅ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ይመለከታል፡፡ በአንድ በኩል ስለ ወደፊቱ የሚናገር ስለሆነ ትንቢት ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ ደግሞ ለአሁን ጊዜ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ተግባቦት/Communications/ የሚመጣው ከያህዌ ወይም ከእሥራኤል አምላክ ነው፡፡ በጣዖተ አምልኮ ጊዜ ግን እስራኤሎች ከውሸት አምላኮቻቸው ቃል ይጠይቁ ነበር፡፡(ሆሴዕ 4፡12)

ብዙ የእስራኤል ጎረቤቶች መገለጥን/ oracles/ ከአማልክቶቻቸው ይጠይቁ ነበር፡፡ ይህንን ነው እድል መንገር ልትሉ የምትችሉት፡፡ ለምንድነው ታዲያ መገለጦች የሚሰጡት? የእግዚአብሔር ሰዎች ትክክለኛ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ ነው መገለጦች የሚሰጡት፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩት መገለጦች ውሳኔ ሰጪ እንዲሁም በሥልጣን አዋጅን የሚያስተላልፉ መገለጦች ነበሩ፡፡ ውሳኔ ሰጪ መገለጦች የሚሰጡት ህዝቡ ስለ አንድ ጉዳይ እግዚአብሔርን ሲጠይቁ ወይም ከእርሱ ምክር ሲፈልጉ ነው፡፡ ለምሳሌ ዳዊት ጠላቶቹን ለመግጠም ትክክለኛውን ጊዜ ለመረዳት፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ ይህ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ነው መገለጥ/ oracles/ የሚባለው፡፡ 2ኛ ሳሙኤል 5፡19፤ 2ኛ ሳሙኤል 5፡23-24)

የመጀመሪው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ሳኦል የተመረጠው በመገለጥ ነው፡፡(1ኛ ሳሙኤል 10፡20-24) በዚያ ሁኔታ እግዚአብሔር ግንኙነት ያደረገው እጣን በማውጣት ነበር፡፡ እጣ ሲወጣ እጣው እንደ እግዚአብሔር መገለጥ ተደርጎ ተቆጥሮ ነበር፡፡ ስለዚህም ይህ እጣ ማውጣት በቅዱሳን ነቢያቶችና በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሱ የቀደሙ አባቶች ሥር የሰደደ ልምምድ እንጂ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ወይም የእድል ነጋሪዎች ልምምድ አይደለም፡፡ በፍፁም አይደለም፡፡ ይህ ይህ እግዚአብሔር በጥብቅ የሚፈልገው አሠራር ነው፡፡ በቃሉ አማካኝነት ለመታዘዝ በፀሎት ወደ ጌታ ስንቀርብ ይህንን ማስታወስ ያለብን ነገር እርሱ እግዚአብሔር እንጂ የእጣ ማውጫ ማሽን አይደለም፡፡ እናንተ ከጠየቃችሁት ፍፁም የተለየ ነገር ሊመርጥ ይችላል፡፡ ምናልባት በህይወታችሁ እርሱ ለብዙ ጊዜ ሊያስተካክለው የሚፈልግ የነበረ ነገር ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ እናንተ ስለ አንድ ሌላ ነገር ስትጠይቁት ትኩረት ልትሰጡበት የሚገባችሁን ሌላ ነገር በእጣው በኩል ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት የትምህርት ሂደት አለው፡፡ በሐሳባችንን ተረጋግተንና አፍረን ነው ቃሉን ማንበብ ያለብን፡፡ በመጀመሪያ 'ይህ ቃል ከእኔ ጥያቄ ጋር ምን ግንኙነት አለው?' ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ እኔ እንጃ አላውቅም፡፡ ያንን ማግኘት የምትችሉት መንፈስ ቅዱስ እስኪያበራላችሁ ድረስ ቃሉን በማሰላሰል ነው፡፡ ከዚህ በስተቀር ምንም አጭር መንገድ የለም፡፡ ሁላችንም ብንሆን በድክ ድክ ደረጃ ተቸግረን ማለፍ አለብን፡፡ በእርግጥ ቢያምም ዋጋ ግን ያለው ነው፡፡

ለምሳሌ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ እጅግ ቢያመኝና በፀይት ተፀልዮልኝ ምንም የማይሻለኝ ከሆነ ጌታን እንዲህ ብዬ እጠይቀዋለሁ፡፡ ለምንድነው እንዲህ በመጥፎ ሁኔታ ላይ የምገኘው? የሰራሁት ትክክል ያልሆነ ነገር አለ? በሰራሁት ሥራ ምክንያት ጥበቃህ ከእኔ ላይ ተነስቶ ነው? እናም በዚህ ጊዜ "ድነት" ወይም "የወላጅ ኃላፊነት" የሚል ምዕራፍ ቢሰጠኝ ይህንን እንዲህ ብለን ብንገምት ደህና ሁኔታ ላይ ነን፡፡ ልክ በዛ ወቅት የአንድ ሰው ድነት በሚዛኑ ላይ ተንጠልጥሏል፡፡ ስለዚህም እኔ በዛን ጊዜ ብፆም ሚዛኑ እንዲያመዝን ማድረግ እችላለሁ፡፡ ነገሩ ይህ ከሆነ ህመሜን እንደ ስምዖን መስቀል በመቁጠር ደስተኛ እሆናለሁ ማለት ነው፡፡

ነገር ግን የሚነበበውን ክፍል "ክስ" ወይም "አለም" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ ከሰጠኝ ወዲያው ዲያቢሎስ በእኔ ላይ እንዲሰራ ፈቃድ እንዳገኘ አውቃለሁ፡፡

ደግሞ በጣም የማከብረው ሰባኪ የሚያገለግልበት ጉባኤ ተጠራሁ እንበል፡፡ ወደ ጌታ በመቅረብ መሄድ እንዳለብኝ ብጠይቀውና "ደስታ"ና "እግዚአብሔርን መውደድ" የሚል ምዕራፍ ቢሰጠኝ ብሄድ ጌታ እንደሚባርከኝ ማረጋገጫ

እንዳገኘሁ አድርጌ እቆጥረዋለሁ፡፡ ነገር ግን ባንፃሩ "ዝሙት" ወይም "አለም" ወይም "ውሸት" የሚል ቢሰጠኝ ወደ ስብሰባው ቦታ አልሄድም፡፡

ሌላ ደግሞ እንዲህ እንበል ኢንተርኔት በጣም በጉጉት እያየሁ እያለ የሆነ የሚያስፈራራኝ ነገር ባገኝ፣ ይህ ነገር ምናልባት እኛን የሚጎዳ ሊሆን ይችላል ብዬ ፍርሃት ውስጥ ብገባና በፀሎት መንፈስ ቅዱስን ጉዳት ሊያመጣብን ይችላል ብዬ የሚያሳስብኝ ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ ብጠይቀውና መልሱም "በአደጋ ጊዜ እርዳታ" ወይም "ምሪት" የሚለውን ምዕራፍ ቢሰጠኝ ይህ ጉዳይ መዘጋጀት ያለብን ጉዳይ ነው እላለሁ፡፡ ነገር ግን "ውሸት" ወይም "የእግዚአብሔር ታማኝነት" የሚለውን ምዕራፍ ቢሰጠኝ ዘና በማለት ምንም አልጨናነቅም ማለት ነው፡፡

ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ቃሉን ምን እንደሚል ለመተርጎም ጊዜ ይወስዳል፡፡ ሁሉ ነገር ወዲያው አይመጣም፡፡ በእውነቱ ከሆነ ብዙ ጊዜ ምን እነደሆነ ማሰብ አቅቶን በመደርደሪያው ላይ በማስቀመጥ የተሻለ መለየት እንዲሰጠን የፀለይንበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ የመማሪያችን ሂደት ሲሆን አስተማሪያችን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቀን እግዚአብሔር በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያስበውን የበለጠ እየተማርን ደግሞም እየጨመርን እንሄዳለን፡፡ ምክንያቱም የእርሱን ምክር በቋሚነት ለመጠየቅ ስለምንቀርብ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች አሉ ለእንደዚህ ዓይነት የመለየት ተግባር . . . በጣም "ያደጉ"፡፡ እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን መንገድ መፈለግ አለባቸው፡፡ እኛ ግን ለ35 ዓመታት ያህል በዚህ ስንጠቀምበት የነበረ በመሆኑ እንደሚሰራ መመስከር እንችላለን፡፡

አንድ ልንገነዘብ የሚያስፈልግን ነገር በሁሉም የመለየት ሁኔታ ከአንድ ውጤት ጋር ራሳችሁን ካያያዛችሁት ወይም በራሳችሁ መንገድ መሄድ የምትፈልጉ ከሆነ የመጣላችሁ መልስ እንዲገባችሁ ለማድረግ እጅግ ከባድ ጊዜ ይገጥማችኋል፡፡ የእግዚአብሔርን ጥበብ በሁሉ ነገርና ፍፁም በሆነ መልኩ ለማፍራት ፍላጎት ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ላትታዘዙ ስለምትችሉ ምናልባት ያለመጠየቁ ይሻላችሁ ይሆናል፡፡

እዚህጋ እስቲ በእውነት እንነጋገር፡፡ የኛን መንገድ ስንፈልግ የእግዚአብሔርን መንገድ መፈፀም አንፈልግም፡፡ እናም ያነበብነው ግራ የሚያጋባና ምን እንደሚል እርግጠኞች እንዳልሆንን እናስመስላለን፡፡ ከዚህ ግን የሚሻለው ያለመጠየቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ከውጤቱ ጋር ተያይዛችኋል፡፡ ስለዚህም ሌላ ነገር መስማት አትፈልጉም፡፡ በዚህ ጊዜ "ጌታ ሆይ የአንተን ፈቃድ ለመፈለግ እንድሰራ ፈቃደኛ ነኝ" ብላችሁ ፀልዩ፡፡

## 6.3 ኢየሱስ መንፈስን ስለ መለየት ያስተማረው ትምህርት

እ.ኤ.አ ዲሴምበር 12 ቀን 2014ዓ.ም

{Jesus teaches on desernemet}

*በቀድሞው ቪዲዮ ላይ ቃል የገባሁላችሁ መልዕክት ይኸውና፡፡ መልክቱን ስቀበል እንደተፈጠረው ሁኔታ መጠን እኔም ልሙላባችሁ፡፡ ባለፉት ጥቂት ቀናት ከጌታ ሳይሆን ከሰይጣን ድምፅን በመስማት ተከሰሼ ነበር፡፡ ክሱም የሚያጠነጥነው የምሰማው መልዕክት ከጌታ ሳይሆን ከኢጋንንት እንደሆነ የሚያስመስል ነበር፡፡ ይህም ግልፅ የሆነ ክስ ሳይሆን የረቀቀና በይፋ የወጣ ሳይሆን በጥያቄ ዓይነት መልክ የቀረበ ነበር፡፡*

ጌታም እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ «በፍፁም ዕረፍት ውስጥ እንድትሆ ኑ እፈልጋለሁ ልክ ልጅ በእናቱ እቅፍ ውስጥ እንደሚሆን፡፡»

*እኔም ጌታ በእውነት አንተ ነህ? አልኩት*

*በክርስትና ህይወት ሁሉ በዚህ የፍርሃት በሽታ ተጠቅቻለሁ፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት የመጣሁት ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም እንቅስቃሴ ወደ ክርስትና ህይወት መለወጥ ነበረብኝ፡፡ እመኑኝ በምድር ላይ የምፈልገው የመጨረሻው ነገር ጌታን ማዋራት መቻል ነበር፡፡ ይህ የነበረኝ ህይወት ነው ሁልጊዜ ሊታለል እችላለው በሚል የፍርሀት ስሜት ውስጥ በመሆን በጣም ንቁ የሚያደርገኝ ፡፡*

*ወዲያው ማምለክና ማመስገን ስጀምር ያማረውን ኢየሱስን ከእኔ ጋር እየደነሰና ዓይኖቹ ብልጭ ድርግም ሲሉ አየሁት፡፡ መንፈሴ በውስጤ ዘለለ! ጌታ እንደሆነ አውቄያለሁ! እርሱም ፈገግ አለና እንደዚህ አለኝ፡-*

«አሁን እኔ መሆኔን መካድ አትችይም፣ ትችያለሽ?

አልችልም ፡፡ በእርግጥ እርሱ መሆኑን አሁን አውቄአለሁ፡፡ ለብዙ ሰዓታት አብረን ደነስን፡፡ ነገር ግን ሙዚቃው ስላሰለቸኝና በጣም ጩኸት ሲሆንብኝ አጥፍቼው በዝምታ ተቀመጥኩ፡፡ የቀን የመልዕክቴን ሳጥኔን በመክፈት የቀኑን ሬማ ካርድ ሳብኩና ማንበብ ጀመርኩ፡፡ እንዲህ ይላል 'የአዳኜ ፍቅር ኦ! እንዴት የሚደንቅ፣ ኦ! እንዴት ከአይምሮ በላይ የሆነ ነው፡፡'

*በነገራችን ላይ ሁላችሁም የቀን የሬማ መልዕክት ማስቀመጪያ ሳጥን እንዲኖራችው አበረታታለሁ፡፡ ይህም ልክ እንደ ዕለታዊ የዳቦ ሳጥን ወይም እንደ ኢንዴክስ ካርድ ሳጥን ሆኖ በውስጡ ኢንዴክስ ካርዶች ያሉበት ማለት ነው፡፡ ይህም ሊዳብር የሚችለው ጌታ የሚሰጣችውን የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል፣ የትንቢት ቃል፣ ቃል የገባላችሁን ለራሳችሁ ይሁን በነቢያቶች በኩል የሰጣችሁ የተስፋ ቃሎች በተለያዩ ካርዶች በመፃፍ ሳጥን ውስጥ አስቀምጡት፡፡ ከዚያም በጣም ከፍ ስትሉ፣ ስትደርቁ ፣ከጌታ ጋር መገናኘት ሲሳናችው እና ድምፁን መስማት ሲከብዳችው፣ «ጌታ ሆይ ወዴት ነህ?» ማለት ሲሰማችው ይህንን አድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ለመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ፣ ከዚያም የውሸት መናፍስቶችን በሬማ ሳጥኑ ላይ እንዳይሰራ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም እሰሩ፡፡ ከዚያም ከመልዕክት ሳጥን ውስጥ ሶስት ካርድ ውሰዱ፡፡ ካርዶቹንም በምታነቡ ጊዜ አሁን በምን ደረጃ ላይ ወይም ሁኔታ ላይ እንደምትገኙ እንድትገነዘቡ፣ እንዲሁም ካላችሁበት የዝቅታ ሥፍራ እንደሚያወጣችሁና ለዚህም ጌታን እንድታምኑት ይረዳችኋል፡፡*

*በእርግጥም በፊቴ በዚያ ነበር፡፡ በፈገግታም እንዲህ አለ* «ከሌር ካንቺ የምፈልገው ፍቅሬን እንድትቀበይኝ ብቻ ነው»

ማልቀስ ጀመረ «ፍቅሬን ለመቀበል ብዙ ጊዜ ፈጀብሽ፣ እባካሽ ወደዚያ አትግፊኝ፡፡ በነገራችን ላይ የተቀበልሻቸው እነዚያ መልዕክቶች ሁሉ እያንዳንዱ ከእኔ ነው፡፡ እያንዳንዱ»

*ጌታ ሆይ አሁንም ግን ስለ ኢራን የሰጠኸ መልዕክት ላይ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ ለምን ያንን መልዕክት ሰጠኸኝ?*

« ኦባማ ከመታወቁ በፊት እንዳውም ከመመረጡ በፊት አላሳየሁሽም?»

*አዎ ይህ ትክክል ነው፡፡*

እርሱ ከመመረጡ በፊት ህልምና ራዕይ አይቼ ነበር፡፡ ከሰባት አመት በፊት ገደማ ለመመረጥ ተቀባይነቱን ሲያገኝና ንግግር ሲያረግ ሳየው ወዲያው በህልሜ ውስጥ ጌታ ያሳየኝ ሰው መሆኑን ለየሁት፡፡

*ልክ በዚያን ጊዜ አንድ ድመቴ መጥታ ወደ ላይ እንዳነሳት መጮኸ ጀመረች፡፡ እናም አነሳኋትና እንዲመቻት አድርጌ እላዬ ላይ አስቀመጥኳት፡፡ ሳሻሻትም ምንም ሳታስቸግር ተቀመጠች፡፡*

«ታያለሽ ልክ እንደዚች ድመት እንድትሆኚ ነው የምፈልገው ፡፡ ልክ ላቅፍሽ ስመጣ በእኔ እቅፍ ውስጥ ገብተሽ ጥልቅ የሆነ እምነት ውስጥ እንድትገቢ ነው፡፡ በዚህም ዕረፍት አግኝተሽ አንቺ ከእኔ እንድትቀበዬ የምመኘውን ፍቅር በአንቺ ላይ ለማፍሰስ ነው፡፡ ይህም ፍቅር የአንቺን ቁስል ሁሉ አክሞ በተራሮች ላይ እንዳለ ብርሃን አንፀባሪቂ አድርጎ የሚለውጥና ሌሎችን ለመፈወስ ኃይል ያለው ነው ፡፡ በአንቺና በፍጥረታቶቼ ሁሉ ፍፁም በሆነ መልኩ ተቀባይነትን እንዳገኝ እንዴት እመኛለሁ፡፡ ነገር ግን እነርሱ ስህተት ላለመፈፀምና ከትክክለኛው መንገድ ወጥቻለሁ ብሎ በማሰብ በፍርሃት ተሞልተዋል፡፡ ይህም ከአምላካቸው ይልቅ የጨለማውን መንፈስ በመስማት ነው፡፡ እኔን በበለጠ ቢሰሙኝ እንዴት በወደድኩ ነበር፡፡»

*ግን እኮ ጌታ ሆይ መጭበርበርን ትፈቅዳለህ፡፡*

«በእያንዳንዱ ጊዜ ፈቅጄያለሁ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ከዛም ነፃ አውጥቼሻለሁ፡፡ ደግሞም ለምን እንደፈቀድኩና እንደገናም እንድትታደሺ አድርጌያለሁ፡፡ አላረኩም?

አዎ ጌታዬ አድርገሃል፡፡ ነገር ግን እኮ ለዚህም ነው በጣም ጥንቁቅ የሆንኩት ፡፡ ደግሞም እኔ እንዳይ ከፈቀድከው በላይ ብዙ መኩራራቶች አሉብኝ ብዬ እጠራጠራለሁ፡፡ ስለዚህም ነው እጭበረበራለሁ ብዬ የምፈራው፡፡

«የኔ ፍቅር በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም የምከራከረው ነገር የለኝም»

ኦ! ሰዎች ብቻ . . . ቢገለኝም እንኳን እወደው ይሆን?

"ለራስሽ መልካም እንድትሆኚ ለመቁሰልም ቢሆን ፈቃደኛ መሆን አለብሽ፡፡ እኔ ሳላስተካክልሽ ሩቅ እንድትሄጂ እንደማላደርግሽ ማመን አለብሽ፡፡ የሚሸፍንሽ ደግሞ አድርጌልሻለሁ፡፡"

*ይህ የተደረገልኝ መሸፈኛ ባለቤቱ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ መሸፈኛዬ እጅግ እጠነቀቃለሁ፡፡ያገኘኋቸውን ነገሮች በሙሉ ከጌታ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን በዚህ መሸፈኛዬ ነው በጥንቃቄ የማረጋግጠው፡፡ ምክንያቱም የመጨረሻ ማድረግ የማልፈልገው ነገር ቢኖር ራሴን ለመጭበርበር አሳልፎ መስጠትና ሌሎች እንዲጭበረበሩ ማድረግን ነው፡፡*

«ክሌር ስለዚህም የተጣራ መረጃ ለመውሰድ እኔን ማመን ትችያለሽ፡፡ ይህም ቸርነትሽና ትህትናሽ እስከተጠበቀና እያደገ እስከመጣ ድረስ ነው፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን ቸርነት ማድረግን መተው ወይም ችላ ማለት የለብሽም»

*እዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው ነገር ቢኖር በሆነ ምክንያት በመሸፈኛ ችሁ መለየት የማትደገፉ ከሆነ 'ከመሸፈኛችሁ በላይ ራሳችሁን ከፍ እንዳደረጋችሁ ይቆጠራል'፡፡ ይህንን ቀደም ባሉት ቪዲዮቼን ተመልከታችሁ ከሆነ በዛ ላይ የጠቀስኩት ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን መሸፈኛ ከሌላችሁ በሬማ ካርድ ማስቀመጫ ሳጥኑ/ Rhema Box/ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ እንዲሁም ትንሽዬዋን የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፅሐፍን/ The Bible Promises Book/ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ እናም ለመንፈስ ቅዱስ በመፀለይ «ኢያዋራሁት ያለሁት ጌታን ነው ወይንስ አይደለም?» ብላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ ፡፡*

*ሰዎች ይህንን ልንገራችሁ ይህንን እኔ በየቀኑ አደርገዋለሁ ፡፡ በቃሉ ላይ ስለተፃፈው በዕጣ የመጠቀም ጉዳይ ልትስቁና ልትተቹኝ ትችላላችሁ፡፡ እኔ ግን ምንም አይጨንቀኝም፡፡ ብትስቁም ይህ መንገድ ለእኔ ይሰራልኛል፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል የሚለውን መፅሐፍ/ The Bible Promise Book/ ልጠቀም ስል የውሸት መንፈስ ተነቃቅቶ መስራት ይጀምራል፡፡ አንዳንድ ወቅቶች አሉ ጌታ ሊፈትነኝ አንድ እርምጃ የሄደበት፡፡ ስለዚህም የውሸት መናፍስቶችን ከመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፉ ላይ ማሰር ነበረብኝ፡፡ ነገር ግን በኋላ እውነቱን ገለጠልኝ፡፡ እርሱ የሬማ ሳጥኑን/ Rhema Box/፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍን/ The Bible Promises/ እንዲሁም ከቃሉ እንደሚጠቀም ነገረኝ፡፡*

«ለለጋስነት የማትሰለቺ ወይም ከተሰጠሽ መሸፈኛ በላይ መሆን የለብሽም፡፡ ስርዓት ባለው መንገድ ወደ መስመር ልመልስሽ በቀስታ ወደታች ጎትቼሽ ነበር፡፡ እርምት ስሰጥሽ ከኩራት የተነሳ ከሚገባው በላይ ከተናደድሽ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ ቶሎም ቢሆን ወይም ቆይቶ ተስፋ በመቁረጥ ሳይሆን ወይም በአመፃ ወደ መቀበል ትመጫለሽ፡፡ በተጨማሪ በህሊናሽ ውስጥ በትንሽ ድምፅ አንድ ነገር ትክክል እንዳልሆነ የሚነግርሽስ? ህሊናሽን እየሰማሽው ነው? አዎ እየሰማሽው ነበር፡፡ ነገር ግን ያንን ትንሽ ድምፅ ሰምተሽ ለመታዘዝ የፈጠንሽ ሁኚ፡፡ ህሊናሽን ንፁህ አድርጊ፡፡ ህሊናችሽን ሁልጊዜ ንፁህ ካደረግሽ መንፈስን ለመለየት ስጋትሽ ትንሽ ነው የሚሆነው፡፡ ችግር የሚገጥምሽ ባልሽ ከሰጠሽ ማስጠንቀቂያ ውጪ እልኸኛ በመሆንና ጥርስሽን በመንከስ በራስሽ መንገድ መሄድ ስትፈልጊ ነው፡፡ ነገር ግን ከባዱን ነገር እንድትማሪ ማድረግ ስላለብኝ ነው፡፡»

«የኔ ፍቅር ይህ በሂደት የሚገኝ ትምህርት ነው፡፡ ይህ የረቀቀው መንፈስን የመለየት ገፅታ ነው፡፡ የራሳሽን ሐሳብ በበለጠ እየተውሽ በመጣሽና የራስሽን ፍላጎትና ፈቃድ እየተቃወምሽ በመጣሽ ቁጥር መንፈስን መለየት ቀላል እየሆነልሽ ይመጣል፡፡ ነገር ግን ለአሁን እኔ በእርግጥ ይገኛለሁ፡፡ እናም በክንዶቼ እቅፍ መሆንሽ፣ የፍቅርሽን እንባ ማየቴ፣ ልብሽ ቃሌን ለመስማትና ለመታዘዝ ዝግጁ መሆኑ እንዴት ድንቅ ነገር ነው? ይህ ሁሉ ለእኔ እንዴት ውብና ለልቤ ደስታን የሚሰጥ ነው፡፡ እባክሽ በእነዚህ ነገሮች ተስፋ አትቁረጪ፡፡ እባካሽ በፍፁም ተስፋ አትቁረጪ፡፡ አንቺ ለእኔ ውድ ነሽ፡፡ ኦ! በአንቺ በጣም ነው የምፅናናው፡፡ ክሌር በአንቺ ፍቅር ታላቅ መፅናናትን አገኛለሁ! እናም እንደምታዬው በፈጠርኩት ፍጥረት እየተሰቃየሁ ነው፡፡ ልቤ የሙሽሮቼን ሁሉ ፍቅር ይፈልጋል፡፡»

## 6.4 ኢየሱስ ሙሽራው እንዴት ሊያየው እንደሚችል የሰጠው መልስ

እ.አ.አ. ማርች 28 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus Answers His Bride on How to See Him}

*ጌታ ሆይ በጣም ስላቀረብከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ እራስህን በተለያ መልክ በገለጥከልኝ ሁሉ እንዳከብርህና ይህንን ሁሉ ያሳየሽኝን በምስለው ስዕል ውስጥ እንደጨምር ኢድርጎኛል፡፡*

"ሙሽራዬ ከእኔ ባይተዋር እንድትሆኚ አልፈልግም፡፡ በስዕሉ ላይ እንዳስቀመጥሽኝ ሁሉ ለአንቺ እንደዛው ነኝ፡፡ አዎ በእውነትም ልዩ የሆኑ መልኮቼን በስዕሉ ላይ ለማካተት ሞክረሻል፡፡ ይህንን በማድረግሽ ግን ተቃውሞ የለኝም፡፡ ነገር ግን እንድታውቂኝ የምፈልገው በእውነተኛው ማንነቴ ነው፡፡ ምክንያቱም በዛ መልኩ ስታይኝ እንዳትደነግጪ ነው፡፡

ኦህ, ጌታዬ ሆይ, ለእኔ እንዴት ደግ እንደሆንክ!

"ኦህ የኔ ሙሽራ እንዴት እንደምወድሽ"

*"ለእኛ በብዙ መንገድ ስለገለጥከው ስጦታህ ፍፁም ተደንቄያለሁ፡፡ እባክህ ሕዝቅኤልን አጽናናው፣ ከሀዘን ውስጥም አውጣው፡፡ እባክህን?*

"የእኔ ፍቅር እርሱ አሁን በጣም ከባድ መስቀል ለእኔ ተሸክሟል ከእሱ ላይ ላንሳውን?"

*አይ ምናልባት ይህን አብራርቼ ብነግረው በኩራት ይሸከመው ይሆናል፡፡*

"ምናልባት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእኔ መስዋዕት አድርጎ ብዙ ጊዜ ሰጥቷል፡፡ እናም ለነፍሶች የምሰቃየውን ስቃይ ከርሱ ጋር በመካፈሌ እጅግ ደስተኛ ነኝ፡፡ "

*እኔ ግን ሲቃዩን ሁሉ በመስቀል ላይ ከፍለህ የጨርሰክ መስሎኝ ነበር፡፡*

"ስለ ሐጢያት አዎ ጨርሻለሁ፡፡ ነገር ግን የመዘጋጀት ሁኔታ ገና ይቀራል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመንግስተ ሰማያት ትልቅ ውጥረት አለ፡፡ በእውነት ለመናገር ሁላችንም በመቀመጫጭን ጠርዝ ላይ ነን የተቀመጥነው፡፡ (እዚህጋ የካሮልን ራዕይ ለመናገር እፈልጋለሁ፡፡ በመግባትና በመውጣት ክፍለ ጊዜ ወቅት መንፈስ ቅዱስን መልአክ እዲያሳይን ጠይቀነው ነበር፡፡ መልአክ እዲያሳየኝ እየደጋገምኩ ጠየኩኝ፡፡ ነገር ግን የሆነው እኔ ወደ ሦስተኛ ሰማይ እየደጋገምኩ መሄድና ሙሉ ስብስባቸውን ማየት ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄ በተደጋጋሚ ሶስት ግዜ ከጠየኩ በኋላ በቀኜ በኩል ትኩረቴን ወደሌሎቹ እንዳደርግ የሚያመለክተኝ አንድ መልአክ እንዳለ ተሰማኝ፡፡ ያመለከተኝም ሁሉም ነጭ ለብሰዋል፡፡ በደረታቸው ላይ ቀይ ምልክትና አልፎ አልፎ ወርቅ አለባቸው፡፡ በእጃቸውም መለከት ይዘዋል፡፡ሁሉም ትኩረታቸውን ያደረጉት በእኔ ቀኝ በኩል ነበር፡፡ ስመለከትም እግዚአብሔር አብን ተቀምጦ አየሁት፡፡ በአብ ቀኝ ባለው የመቀመጪያ ዙፋኖች ኢየሱስ በእያንዳንዱ ላይ ተቀምጦ አየሁ፡፡ አቀማመጡም ብድግ ለማለት እጆቹን በመቀመጫው ላይ አስደግፎ ወደፊት ዘንበል በማለት የአብን

ትዕዛዝ እየጠበቀ ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ አየሩ በተስፋ ተሞላ እንደተዘጋጀ በእጆቹ ተደግፎ ሊነሳ ሲዘጋጅ አየው ባባቱ ትዕዛዝ መሰረት እና አየሩ በተስፋ ተሞላ) መጠበቅ! መጠበቅ! መጠበቅ፡፡"

*ባለፈው ምሽት 'ቀኑ ተወስኗል ' ያልክ መሰሎኝ ነበር፡፡*

"*አዎ ብያለሁ፡፡ ያንን ጊዜ ነው እየተጠባበቅን ያለነው፡፡ መጠበቅ እንዴት እንደሚሰማ ታውቂያለሽ? ቢሆንም ግን በዚህ ወቅት መጠበቅ ማለት ምን እንደሆነ መቼም ሊገባሽ አይችልም፡፡ ይህ ዓይነት ጥበቃ በሌላ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ነው፡፡ እጅግ አድካሚ ነው፡፡ መጠበቅ፣ መጠበቅ፣ መጠበቅ፡፡*"

*ከዚህ በበለጠ ልትነግረኝ ትችላለህ?*

«በጣም ካልቀረብሽ በስተቀር አይሆንም የኔ ፍቅር »

*"የጊዜው  መቅረብ ነው ወይስ በሐሳብ መቅረብ ?*

"ሁለቱም."

*እሺ፡፡*

"*የኔ ውድ አድምጪ፣ ከዚህ ጫና ከበዛበት ህይወት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ታገሺ፡፡ ዛሬ የጀመርሽውን አድካሚ መንገድ አቁሚ፡፡ አንቺ ሽልማትሽን እንደምትቀበዪ እነግርሻለሁ፡፡ ይህን የምታደርጊው ለሽልማት ብለሽ እንዳልሆነ ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ አንቺ እውነተኛ እረኛ ነሽ፡፡  ከቀን ወደ ቀን ህይወትሽን ሁሉ ለበጎችሽ ዝቅ እያደረግሽ ነው፡፡ ከአንቺ ሁልጊዜ የምፈልገው ይኸንን ነበር፡፡*

"*ከእኔ ጋር ይህንን አይነት ግንኙነት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ግልፅ እንዲሆን የምፈልገው እኔ ማንንም አልከለከልም፡፡ እስከሚያገኙኝ ድረስ ለሚፈልጉኝ ሁሉ እጆቼ ክፍት ናቸው . . . ፡፡ ነገር ግን በቀላል የምገኝ አይደለሁም፡፡ ምን ያህል እንደምፈለግ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ሳትታክት ላይ ታች እያለች የምትፈልገኝን ሙሽራ ማየት እፈልጋው፡፡ ከዛ በመገኘቴ አስደስታታለሁ፡፡ ብዙ ሰዎች ግን ቶሎ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡  ይህ ነው የአብዛኛው ሰው ችግር፡፡*

"*ብዙ ሰዎች በጠላት ውሸት ይጠመዳሉ ይህም "እናንተ አይገባችሁም በሚል የውሸት ወጥመድ"፡፡ ምንም ነገር ከእውነታ ሊርቅ አይችልም፡፡ እውነታው እስከያገኙኝ  ድረስ የማይፈልጉኝ ከሆነ ብቻ አይገባቸውም ፡፡ "ይህ አባባል ነው ትክክል የሚሆነው፡፡*

"*ሌላኛው ትልቁ ጉዳይ ደግሞ የቅድስና ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ሁለት ገፅታ አለው፡፡ የመጀመሪያው ገፅታ የአለምን ቆሻሻ ለመመገብ መነቃቃት በጨመራችሁ ቁጥር የእኔን መገኘት፣ ዝግ ያለውን ድምፄን መስማት፣ ለለስላሳ ትንፋሼና ለእቅፌ ንቁ አትሆኑም፡፡*"

"ሌላኛው ገፅታ ደግሞ ንፁህ ያመሆን ነው፡፡ ይህም የአለምን ቆሻሻ መመገብ ልበ ደንዳና ያደርጋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ለመንፈስ ቅዱስ መኖሪያነት ምቹ አትሆኑም፡፡ ቤቱ ንፁህ መሆን አለበት፡፡ ይህ ባይሆን እንኳን ንፁህ ለመሆን መሰጠት ያስፈልጋል፡፡

*ዋው፣ ጌታ ይህንን መስማት ያስፈልገን ነበር!*

*"አውቃለሁ፣ እኔን የሚፈልግልኝን ሁሉ እወዳለሁ፡፡ ለዛም ነው ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያስፈልጋቸውን መመሪያ ለማብራራት እዚህ ያለሁት፡፡ እኔን ምን እንደሚያስቆጣኝ ታውቂያለሽ? "ኃጢአት እጅግ በጣም ያበሳጨኛል፡፡ የአለባበስ ኃጢያት፣ የኃይል ድርጊቶች፣ ወንጀል፣ ጥላቻ፣ሐሜት፣ ቅናትና የዝሙት ኃጢያቶች፡፡ እንዲሁም ተከታታይ የቴሌቪዠን ድራማዎች የኃጢአት እምብርት ናቸው፡፡ ስለዚህም ለእኔ እንደ መርዝ ናቸው፡፡ ውሻ አዲስ ቆሻሻውን ሲጥል ለአፍንጫ እንደሚሰነፍጥ ዓይነት ለጤና ጎጂ ናቸው፡፡ እኔ የምላችሁ በጣም በጣም መጥፎ ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚያስቆጡት እኔን ብቻ ሳይሆን በሰማይ ያለውን ችሎትን፣ መላእክትን እና ቅዱሳንን ጭምር ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በዚህኛው አለም እነዚህ ነገሮች የዕለት ተዕለት የህይወት አካል ናቸው፡፡*

"ሙሽራዬ ግን እኔን ማግኘት ከፈለገች እነዚህን ነገሮች ወደ ጎን በመተው ኃጥያት ከሚያቀርብላት የመዝናኛ ዓይነቶች ሁሉ ልቧን እና አዕምሮዋን ማጽዳት አለባት፡፡ይህ ማለት ሙዚቃ፣ አለባባስ፣ ባህሪይ፣ንግግር፣ የግድያ ምስሎችን፣ ሚስጥራዊ ነገሮች፣ ጦርነቶችና በማንኛውም መልኩ ኃጥያትን የሚያሳዩ ነገሮች ሁሉ መቆጠብ አለባት፡፡ በኃጢያቱ ለመዝናናት ሳይሆን አንድ ሰው እኔን ከማግኘቱ በፊት ት እንደነበረና አሁን ያለውን ለውጥ ለማሳየት የሚደረግ ዶክመንተሪ ዓይነት ፊልም ችግር የለብኝም፡፡ ያ የሚያሳየው የነበረበትን ህይወት ነው፡፡ ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነኝ እና የሚያበሳጨኝ አስደሳችና አስደናቂ መዝናኛ በማድረግ ንፁህ የሆነውን፣ እንዲሁም በቀላሉ የሚሰበሩትን አስተሳሰባቸውን የሚያበላሹና ስሜትን በሚያደበዝዙ ሐጢያቶችን ነው፡፡

"አሁን ገባሽ? በምታስቢውና በምታይው ነገር እሰቃያለሁ፡፡ መኝታ ቤትሽ በስውር በምታይው መጥፎ ነገር፣ ይህም ሰው የመግደል እና የማሰቃየት ፍላጎት፣ በመስረቅና በስግብግነት የብዙዎችን ህይወት መበጥበጥ እንደነዚህ ያሉ ነገሮች ይጎዱኛል፡፡ የኔ ሙሽራ እባክሽ በፊልም ቢሆን በቴሌቪዥን እነዚህን ነገሮች አትመልከቺ፡፡ እነዚህ እኔን የሚጎዱ ነገሮች ናቸው፡፡ እባክሽ ስቃይንና ኃጢያትን የሚያሳዩ መፅሔቶችን፣ ቢልቦርዶችና ፎቶዎችን አትመልከቺ እንዲሁም ሙዚቃዎችን አትስሚ፡፡"

*ጌታ ሆይ የኑክሌር ጦርነትን ቪዲዮ ለመስራት ልጠቀምባቸው የነበሩትን አንዳንድ ምስሎች ስትመለከት እንዴት እንደሆንክ አስታውሳለሁ፡፡*

"አዎ ከአስፈሪዎችም አስፈሪ ነው፡፡ እኔ ነኝ ያንን ነፍስ የፈጠርኩት ፤ ሰውነቱ በእሳት ሲቃጠል ማየት በጣም ይረብሸኛል፡፡ ታስታውሻለሽ ያ ነፍስ በራሱ ላይ እሳት ሲለኩስና ሲቃጠል እዛው ነበርኩ፡፡ የስቃዩም ተካፋ ነበርኩ፡፡ ለነፍሱ የመጨረሻውን ለመወሰን መሥራት ነበረብኝ፡፡ አይሆንም አይሆንም በምታዩት፤ በምሰሙት እና በምታስቡት ነገር አትረብሹኝ፡፡ እንደዚህ አይነት ስቃይ ውስጥ አታስገቡኝ፡፡

"አንድ ሙሽራ አይምሮዋ እንደዚህ ቆሽሾ እያለ እንዴት አድርጌ አቅፋታለሁ! እነዚህ ነገሮች እኮ በግማሽ ህይወት አላቸው፡፡ ደግሞም ወደኋላ ፤ ወደኋላ ፤ ወደኋላ ይጉትታሉ፡፡ ስለዚህም እነዚህን ነገሮች ወደ አዕምሮሽ በመጡ ቁጥር ደጋግሜ አያቸዋለው፡፡

"ይገባሻል ግን! "ንፁሃን የተባረኩ ናቸው፣ እግዚአብሔርን ያዩታልና" አሁን ገባሽ ብዙዎች በፀሎታቸው ውስጥ ለምን እንደሚያዩኝ? አዎ እስኪታገኙኝ ድረስ ፈልጉኝ፣ ነገር ግን በመጀመሪያ ቤታችሁን አፅዱ፡፡ ንፁህ ሆናችው ወደ እኔ ቀርባችሁ በዚህ አለም ቆሻሻ ያልተበላሸ ዙፋን አዘጋጁልኝ፡፡ የሚያፀይፈኝ ቆሻሻ ብቻ ሳይሆን አለማዊነትም ጭምር ነው፡፡

"ምግብ በማብሰል፣ በመስፋት፣ በማስጌጥ፣ ያንን በመግዛት ያንን በመሸጥ፤ በማያቋርጥና በማያልቅ ፍላጎትና ግዢ ላይ ጊዜን ማጥፋት በምድራዊ ጉዳይ መጠመድ ነው፡፡ ኦህ ! እነዚህ ጣኦቶች ለእኔ አስከፊ ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት የተመሰቃቀለ ነገር በአንድ ልብ ውስጥ ሳገኝ እኔ በሌላው አቅጣጫ እሮጣለሁ፡፡ እናም አንዲት ነፍስ ከእኔ አብሮነት ይልቅ እነዚህን ነገሮች ስትመርጥ ሳይ ልቤ በሀዘን ይሚሸሻል፡፡ ኦህ! እንዴት እነዚህን የማይረቡ ጣዖታት ከእኔ ታስበልጣላችሁ! እንዴት?

"በቀዘቀዘ፣ በተጎዳና እና ተስፋ በቆረጠ ስሜት ውስጥ ሆናችሁ ፊልም ለማየት መሄድን አይደለም እያወራሁ ያለሁት፡፡ ይህም ቢሆን ግን የምታዩት ፊልም ንፁህ መሆን አለበት፡፡ እኔ እያወራው ያለሁት እያወቃችሁ ከእኔ ይልቅ በማይረባ ነገር ላይ ጊዚያችሁን ለማሳለፍ የምትወስኑትን ውሳኔ ነው፡፡ ለዚህ ነው ብዙ ጊዜሽን ኢንተሬንት ላይ ስታጠፊ በጣም የማዝነው፡፡ ምን አይነት ሰዓት ማባከን ነው! አሁን ግን የኔ ፍቅር እያሻሻልሽ ነው፡፡ ትኩረት የሚስቡ አዳዲስ ዜናዎችን ለመስማት ከመከታተል ተቆጥበሻል፡፡ አሁን እጅግ አሻሽለሻል፡፡"

"እነዚህ በፈቃደኝነት የምትሰሪያቸው ነገር ግን ያላስተዋልሻቸው ሐጢያቶች ናቸው፡፡ እናም ሁሉን አይተሽ ከጨረስሽ በኋላ ስለምትፀፀቺ "ኦ ጌታ ሆይ እባክህ ከማውቃቸው ሐጢያቶቼ አንጻኝ" ትያለሽ፡፡ ይህንን ሁሉ ጊዜዬን በዚህ ማሳለፍ የለብኝም ነበር ትያለሽ፡፡ ደግሞም እኔን እንዳስከፋሽ በልብሽ ስለተረዳሽ ልብሽ ዝቅ ይላል፡፡ ነገር ግን ያጠፋሽው ጊዜሽን ብቻ ሳይሆን አይምሮችንም በማይረባ ነገሮች ሞልተሻል፡፡ ደግሞም እነዚህን ነገሮች ለሌሎች ሰዎች በማውራት ታሰራጪዋለሽ፡፡ ስለዚህም የምትጎጂው እራስሽን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ጭምር ነው፡፡ በዚህም መጥፎ ምሳሌ ትሆኛለሽ፡፡"

" አሁን ያየሁትን አየሽ "

*አዎ ጌታዬ፡ ያንተ ፍፁም ፈቃድ ያልሆነን ነገር ሳደርግ ለምን ያ ስሜት እንደሚሰማኝ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባኝ አሁን ነው፡፡*

"የእኔ ሙሽሮች ይህን የምለው እናንተን ለመኮነን አይደለም፡፡ እሱ ገብቷችኋል? እኔ እናንተ የፀለያችሁትን ፀሎት እየመለስኩ ነው ያለሁት፡፡ ይህንን ነው ከእናንተ የምጠብቀው፡፡ ለዚህ ነው እኔን ለመስማትና ለማየት ከባድ ግዜ የምታሳልፉት፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ራሳችሁን አስተካክሉና እኔ በመንብኜቴና በማጽናናቴ እባርካችኋለሁ፡፡ ይህንን ቃል እገባለሁ፡፡

"ለዚህ ምሽት የእስካሁኑ ይበቃል የእኔ እርግብ፡፡ በሚገባኝ መልኩ ስመለሽልኝ አመሰግናለው፡፡ ቻናልሽን የሚከታተሉት ወዶች ሁሉ በልቤ ውስጥ ነበሩ፡፡ እናም አሁን ሁላችንም አንድ ላይ በመሆን በልባችሁ ያለውን ህልምና ከእኔ ጋር ለመሆን ያላችሁን ፍላጎት አብረን ተግባርያዊ እናደርገዋለን፡፡

"'ሁላችሁንም በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ እናም ልወስዳችሁ ስለምመጣ እራሳችሁን አዘጋጁ፡፡

*ከዚህ ቃል በኋላ ለማየት የምችለው ምን ቀረ? በማለት ኢያሰባችሁ ይሆናል፡፡ የህፃናት ድራማ (ይህም ከሃዲነትን የሚያንፀባርቅ መሆን የለበትም)፣ ተፈጥሮን የሚያሳዩ ፊልሞች፣ የሚያስጠላ ይዘት እስከሌለው ድረስ ዶክመንተሪዎችን፣ እውነተኛ ታሪኮችንና ቀላል የካርቱን ፊልሞችን ማየት እንችላለን፡፡ እንዲሁም ህፃናት እንሰሳትን፣ ቀላል የአሻንጉሊት ድራማዎችን እንደ ሳይመን ድመት ወይም የልጆች ድራማዎችን ማየት እንችላለን፡፡ ከእደዚህ አይነት አልፈናል የምትሉ ከሆነ የእውቀት ፕሮግራሞችንና ቃለመጠይቆችንና የመሳሰሉትን ማግኘት እንችላለን፡፡ ብቻ ዋናው ቁም ነገር የተመሰቃቀለ አካሄዳችንን እንተው ነው፡፡*

# ክፍል 7
# ጌታ ከእኛ ምን ዓይነት ባህርይ እንደሚፈልግ የያዙ መልዕክቶች

{Messages to Show You the Attitudes Jesus is looking for In You}

---

## 7.1 ከእኔ የጠፋችሁና ብቸኞች አሮጌውን ሸክማችሁና ትታችሁ ወደ እኔ ኑ!

እ.አ.አ. ጁላይ 15 ቀን 2015 ዓ.ም

{Come to Me My Lost & Lonely Ones! Release the old Baggage!}

ለሚወዱኝና በእኔ ዓላማ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ሁሉ መልካም የሆነውን ነገር ከማሟላት ወደ ኋላ ያልኩበት ጊዜ የለም፡፡ ሰዎች ናቸው እንጂ የሚተዉኝ እኔ ማንንም አልጥልም፡፡ ፀሎታቸው እነርሱ በፈለጉትና ባሰቡት መንገድ ካልተመለሰላቸው በእኔ ላይ እምነት አይኖራቸውም፡፡ ይህ ነው ብዙዎችን ከእኔ እንዲሸሹ ያደረጋቸው፡፡ ምን ያህል እንደምወዳቸውና ምን ያህል የማያልቅ ጥበብ እንዳለኝ አያውቁም፡፡ በህይወታቸው ውስጥ ሰይጣን በፈጠረው ብልሽት እኔን ይወቅሳሉ፡፡ ወደ እኔ መጥተው ደግሞ ነገሮች እንዲለወጡ በማሰብ ይፀልያሉ፡፡ ነገር ግን እኔ እነርሱ በጠየቁት መሰረት ልመልስላቸው አልችልም፡፡ ምክንያቱም እኔ መንገዳቸውን ሁሉ እመለከታለሁ፡፡ እናም መሄድ ያለባቸውን መንገድ መጓዝ አለባቸው፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ ህይወታቸው እውነተኛ ባልሆኑ ወይም "ከፍፅምና በጎደሉ" ክርስቲያኖች የተሰላቹ በእግዚአብሔር የማያምኑ ሰዎችን ታገኛላችሁ፡፡ ቢሆንም በእግዚአብሔር የማያምኑቱ በጣም መጥፎ የሆነ ነገርን ሲያደርጉ ምንም ሳይባል ይታለፋል፡፡ ለማያምኑ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው እንደሚያደርጉት በተመሳሳይ መልኩ ለእኔም ልጆች ቢያደርጉ እንዴት እመኝ ነበር፡፡ ይህንን ልነግራቸው እፈልጋለሁ፡፡ 'የኔ ልጆች ከእናንተ ፍፁም በመሆን የተሸሉ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምህረትን ያገኙ ናቸው፡፡ ደግሞም እጅግ ብዙዎቹ በእኔ እርዳታ ለመለወጥ ጥረት እያደረጉ ናቸው፡፡' ብዙ ጊዜ በክርስቲያን ህይወት ጀርባ ምን እየተካሄደ እንደሆነ አታውቁም፡፡ እኔ ሳላገኛቸው በፊት ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ አታውቁም፡፡

*ጌታ እኔ በዚህ ጊዜ እራሴን አሰብኩ፡፡ ዋው! ጥሩ አልነበርኩም በፍፁም ትሩ አልነበርኩም፡፡ ራስ ወዳድ፣ ኩራተኛ፣ በቁሳቁስ እጅግ የተተበተብኩና ሰዎችን ለማስደነቅ የምጥር ነበርኩ፡፡ የልብ ጓደና እንኳን ለመመስረት የማልችል፣ ፍቅር መስጠትና መቀበል የማልችል ነበርኩ፡፡ ነገር ግን ጌታ ሲያገኘኝ በውስጤ አንድ ነገር ተቀየረ፡፡ እርግጥ ነው እኔን ለመለወጥ ብዙ ዓመታቶች ፈጅተውበታል፡፡ ነገር ግን ሊለውጠኝ ችሏል፡፡ በእርግጥ ፍፁም አይደለሁም፡፡ አሁንም ችግሮች አሉብኝ፡፡ ቢሆንም ግን መጀመሪያ እንደነበርኩት በፍፁም አይደለሁም፡፡*

"ፍቅር ነው በህይወትሽ የገባው፡፡ በህይወትሽ ሙሉ ስታልሚው የነበር ፍቅር፣ ቅዱስ የሆነ ፍቅር፣ አፍቃሪ የሆነ ጓደኛ ነው ያገኘሽው፡፡ በእውነትም በህይወትሽ መጥቼ እኔ ማን እንደሆንኩ እንዲሁም አንቺ ደግሞ ለእኔ እጅግ በጣም ልዩ እጅግ ልዩ እንደሆንሽ ገለጥኩልሽ፡፡ ከዚያ በፊት እንደዛ ማንም ቀርቦሽና ደግሞም ማንም ተረድቶሽ አያውቅም፡፡ እኔ በልብሽ ውስጥ እስከገባ ድረስ በህይወትሽ ደህንነት በፍፁም ተሰምቶሽ አያውቅም፡፡ ስለ እኔ የምታውቂው ነገር ቢኖር ከጥርጣሬ ትንሽ ባለፈ መልኩ አምላክሽ እንደሆንኩ፣ ነገር ግን ከአንቺ ጋር ዝም ብዬ ወዲያና ወዲህ የምሄድ እንጂ ከዚያ ባለፈ 'ምንም የተሻለ ነገር ያለኝ' ይኸውም የምመራሽ፣ የምጠብቅሽ፣ ስለ መንግስቴ የማስተምርሽ እንደሆነ አታውቂም ነበር፡፡

"የቤተክርስቲያንሽም ልምምዶች ከሌሎች ልምምዶችሽ ምንም የተሻለ ነገር አልነበረውም፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ቢሆን ክርስቲያን ካልሆኑት ህብረተሰብ ከተቀበለሽ ውጪ በተለየ መልኩ ምንም ተቀባይነተሽ አላገኘሽም ነበር፡፡ አንድ ያደረግሽው ነገር ቢኖር ከእኔ ጋር የግል ህብረት ግንኙነት ማድረግሽ ነው፡፡ የልብሴን ጫፍ ነካሽ፡፡ ከቀን ወደ ቀን በዚህ ዓይነት መንገድ መጥፎ ነገር የደረሰብሽን ይህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን የደረሰብሽን መጥፎ ነገር እንድታልፊ አደረገሽ፡፡

"እያችሁ ሃይማኖትና እግዚአብሔር በምንም መልኩ አንዱ ከሌላው ጋር አይመሳሰሉም፡፡ ሃይማኖት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ያመጡት መዋቅር ነው፡፡ እኔ ግን የማቅፋችሁ ከህግና ከስርዓት ውጪ እንዳውም ስሜን እንኳን ሳታውቁት ነው፡፡ ነገር ግን አሉ አንዳንዶች በልባቸውና በመንፈሳቸው የሚያውቁኝ፣ የሚከተሉኝና የምላቸውን ሁሉ የሚያደርጉ፡፡ ታዲያ ቀኑ ሲደርስና ትክክለኛው ጊዜ ሲመጣ ራሴን እገልጥላቸዋለሁ፡፡

"ነግር ግን አንዳንዶች ደግሞ አሉ ህይወታቸውን ሁሉ በመጥፎ ሁኔታ ተይዘው ያደጉ፡፡ በፍቅር የሚቀበላቸው ለማግኘት ተስፋ ያጡ፡፡ እነዚህን በፍቅሬ ድንገት አስደስታቸዋለሁ፡፡ ባልጠበቁት ጊዜ፣ በትንሽ ደቂቃ ውስጥ፣ ሳያስቡት፣ መስፈርት በሌለውና በጥልቁ ፍቅሬ አጥለቀልቃቸዋለሁ፡፡

"ብዙዎች አሉ በህይወታቸው ለሆነባቸው መጥፎ ነገር ሁሉ እኔን የሚወቅሱ፡፡ ምክንያቱም ኃጢያታቸውን ሊተዉ ስለማይፈልጉ ነው፡፡ በልባቸው በአንድ ሥፍራ የኔን ድምፅ ይሰማሉ፡፡ ነገር ግን ዓለምና የመሳብ ኃይሉ ያሸንፋቸውና ጊዜው እስኪያልፍ ድረስ ችላ ይሉታል፡፡

"እኔ ሁልጊዜ እየተጣራሁ ነኝ፡፡ ሁልጊዜም ይመጣሉ እያልኩ እየጠበቅሁ ነው፡፡ ደግሞም ሁልጊዜም በህይወታቸው የሚደርስባቸውን ቁስል ለማከም በአጠገባቸው ነኝ፡፡ ነገር ግን እነርሱ በትንሹ እንኳን ኃጢያታቸውን ትተው የኔን ፍቅር መቀበል አለባቸው፡፡ ከእኔ ይልቅ በሥጋ የሚያገኙት ደስታ በልጦባቸዋል፡፡ ስለዚህም ሥጋቸው እስኪያረጅና ደካም እስኪሆኑ መጠበቅ አለብኝ፡፡ በዚያን ጊዜ እንኳን የያዙት መራራ ነገር እኔን ለመስማት ያስችላቸዋል የሚል ማስተማመኛ የለም፡፡ ስለዚህም እስካገኛቸውና ወደ ቤት እስካማመጣቸው ድረስ በማይመቸው በሽማግሌዎች ማቆያ ቤት/Nursing Home/ እንዲቆዩ እፈቅዳለሁ፡፡

"ኦ! አንድ ነፍስ ልቡን በእኔ ፍቅር ላይ ሲቆልፍና በዚህ አለም ደግሞ ዞር ብሎ አለኝ የሚለው ነገር ሳይኖረው ሲቀር እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው ፡፡ በአብዛኛው ጊዜ በራሳቸው ጥፋት ሲሆን የራሳቸው ፅድቅ በቂ መሆኑን በማሳመን ለንስሐ ምንም ቦታ ሳይሰጡ ለብቻቸው ተጥለው ይገኛሉ ፡፡ ደግሞም ሁሉንም ነገር የሌሎች ጥፋት እንደሆነ በመቁጠርና እነሱ ብቻ ተበዳዮች እንደሆኑ ይቆጥራሉ፡፡ ደግሞም ለሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ተጠያቂ ያደርጋሉ፡፡

"ከሌር እኔ የምፈልገው ፍቅር ያጡትን እንድታፈቅሪልኝ ነው፡፡ ከመንገድሽ ወጣ ብላሽ እኔን አልቀበል ያሉኝን እጄን፣ እግሬን አፌንና ጆሮዎቼን ሁኚልኝ፡፡ በዛች በመጨረሻዋ ሰዓት ምክንያቱን መንገር እችላለሁ፡፡ ባይገባቸው እንኳን ደግነትሽን አስታውሳቸዋለሁ፡፡ ከብዙ ጊዜዎች ይህኛው ጊዜ ለመቃወም የመጨረሻው ነው፡፡ ጥልቅ የሆነውን ኃጢያታቸውን በመረዳት እንዲሁም ለእኔ እንዴት ልዩ እንደነበሩ፣ እጅግ ልዩ እንደነበሩ፣ በተለይም ወደ መንግስተ ሰማያት ለዘላለም ከእኔ ጋር እንዲገቡ ለማድረግ ስቃይ መቀበሌን በመረዳት በእንባ የሚታጠቡበት ጊዜ ነው፡፡ ኃብት አድርጌያቸኋለሁ፣ አፍቅሬያቸኋለሁ፣ አቅፌያቸዋለሁ ስለዚህም መለያየት የለም፡፡

"በእነዚህ የእድሜ ጊዜያቶቻቸው ነው ብዙ ነፍሶች በዚህ ዓይነት መንገድ እንዲያመልጡ የሚደረጉት፡፡ ለዚህ ነው ሁልጊዜ ፍቅር ያጡትን እንድትወጂ በቋሚነት የማስጠነቅቅሽ፡፡ ኃብት የነበራቸው እንኳን ቢሆኑ እነዚህ ናቸው ከሁሉም ይልቅ ድሆች፡፡

*ጌታ ሆይ እስራኤሎች እንዲያደርጉ ስለታዘዙት መጥፎ ነገሮች ሁሉ ትወቀሳለህ፡፡ ወታደሮቹ ወንዶቹን፣ ሴቶቹንነ ህፃናትን እንዲገድሉና ከአንድ ከተማ ፍፁም እንዲጠረጉ ስታደርግ ለምን እንዳደረከው? ምን እንዳደረግህ? ጥቂቶች ለማወቅ ግድ የሚላቸው ይመስላል፡፡ ሰዎች ያንን ምንም ሊረዱት አይችሉም፡፡ ለዛም ነው እነርሱ አንተን እንደ ጨካኝና መጥፎ አምላክ የሚቆጥሩህ፡፡*

"ምክንያቱም እነርሱ ለሞሎክ መስዋዕት ለማቅረብ ህፃናትን የቀላ እሳት ውስጥና በብረት ሳህን ውስጥ ሲከቷቸው በድንጋጤ የተሞላውን ልብ የሚሰብረውን የሕፃናቱን ጩኸት አልሰሙም፡፡ ደግሞም ሰዎች ከእንስሳት ጋር ትክክል ያልሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈፅሙ፣ እንስሳት እንኳን ከክፉ ተግባራቸውን እንዳያመልጡ የተደረጉበትን አላዩም፡፡ እንዲሁም ሴቶች የአምልኮ ስርዓት እንዲፈፅሙ ከአጋንንት ጋር ግንኙነት በማድረግ የክፉን ልጅ ሲፀንሱና በአጋንንት ኃይል ሲሞሉ አላዩም፡፡ ህዝቤ በህይወት የሚገኘውን ሁሉ ለምን እንዳጠፋ ብዙ ዘመናት ስላለፉ የሚታወቀው እጅግ ጥቂቱ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን በቃሌ በወቅቱ የነበረው ክፋት ፍፁም ሊጠገን የማይችል እንደነበረ በግልፅ ተጠቅሷል፡፡

እናም አሁን የኖህ ዘመንን እየመጣ ነው፡፡ 'የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ' ሊሆን ነው፡፡ አዎ ማንኛውም የተጣመመ ድርጊትና ክፋት በህግ ሊፈቀድ ነው፡፡ ጨቅላ ህፃናትን ለወሲብ ማፍቀር፣ ከእንሰሳት ጋር ሩካቤ መፈፀም፣ ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከሴት ጋር ሩካቤ መፈፀም ሁሉ እየመጣ ነው፡፡ የእኔ መምጣት እርግጥ እንደሆነ ሁሉ ይህም በእርግጥ እየመጣ ነው፡፡ እስካሁን ተቀባይነት እያጣ ቢሆንም ሁሉም እዚሁ አለ፡፡ ይህም ተቀባይነት ማጣት ለብዙ ጊዜ አይቆይም፡፡ ተፈርመው በሥራ ላይ የዋሉ ህጎች የብልግና ስዕሎችን ከማየት በበለጠ መልኩ የሚያስጠሉ ተግባራትን መፈፀም ህጋዊ እየሆኑ ይሄዳሉ፡፡ በዛን ጊዜ የእድሜ ገደብ አይኖረውም፡፡ ሁሉም መጥቶ ማየትና ለራሱ መሞከር የሚችልበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ለነገሩ ይህንን እኩይ ተግባር መፈፀም ደስታን ይፈጥራል፣ ደስታ ደግሞ ሙብታችሁና ነፃነታችሁ ነው፡፡

የኔ ልጆቼ የኔ አስቸጋሪ ልጆች እኔ ግን እየጠራኋችሁ ነው፡፡ የሰለቻችሁና ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ብቸኝነትን፣ ውሸትን፣ ጨለማንና ግራ መጋባትን ትታችሁ ወደ እኔ ኑና ወደ እኔ ቅርቡ፡፡ ለነፍሳችሁ ዕረፍትና ገደብ የሌለው ፍቅር ለልባችሁ ታገኛላችሁ፡፡ መቼም ቢሆን ፊቴን አላዞርባችሁም፡፡ መቼም ቢሆን አልጥላችሁም፡፡ በአንፃሩ ግን ህይወታችሁ ከክብር ወደ ክብር እያበራ፣ እያበራ ይሄዳል፡፡ እኔ ልዋሽ ዘንድ ሰው አይደለሁም፡፡ በማከማቻዬ ሥፍራ ለእናንተ ክፉ ነገር ሳይሆን ሁልጊዜ ለማድረግ የምትመኙት ጥሩ ነገር አለኝ፡፡ በእናንተ ውስጥ ያንን በጎ መሻት ማን ያስቀመጠው ይመስላችኋል? አሁን ያንን መሻታችሁን ለመፈፀምና በህይወታችሁ ደስታን ለማምጣት እፈልጋለሁ፡፡ ኃጢያት ያመጣባችሁ ነገር ኃዘንና ተስፋ መቁረጥ ብቻ ነው፡፡ አሁን ግን ጊዜው ለውጥ የሚያስፈልግበት፣ አሮጌውን ሸክም የሚጣልበትና እንደገና በመወለድ አዲስና ንፁህ ህይወት የሚጀመርበት ጊዜ ነው፡፡

የጠፋችሁና ብቸኞች የሆናችሁ እናንተን ሁሉ እኔ እናንተን እየተጣራሁ ነው፡፡ ወደ እኔ ኑ፡፡ እኔ እቅፌ ውስጥ በማስገባት በመጀመሪያ ወደወለዳችሁ ማህፀን በመመለስ የደስታንና የምስጋናን ዜማ ታዜማላችሁ፡፡ የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ አለብሳችኋለሁ፣ በጣታችሁ ላይ ቀለበትን አስራለሁ፣ የሰንደል ጫማን አደርግላችኋለሁ፡፡ ከዚያም አንድ ሆነን አብረን እንጓዛለን፡፡ እናንተ ብቻ መጎዳትና ሌላውን ሰው መጉዳት እንደደከማችሁ ብቻ ንገሩኝ፡፡ ስለሰራችሁትም ኃጢያት

ማዘናችሁን ንገሩኝ፡፡ ለዚህም ይቅርታ ጠይቁኝ፡፡ ከዚያም ህይወታችሁን ለእኔ አስረክቡኝ፡፡ እኔ እንከባከባችኋለሁ፡፡ እመራችኋለሁ መንገዱን አሳያችኋለሁ፡፡ በፍፁም አልተዋችሁም፡፡ እጃችሁን ይዤ የዘላለም ደስታ ወደሚገኝበትና ዘላለማዊ ወደሆነው ወደ ሰማያዊው የአባቴ መንግስት እመራችኋለሁ፡፡

'ኢየሱስ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ሙሉ ህይወቴን እሰጥሃለሁ፡፡ አስተምረኝ፣ ምራኝ፣ ከእኔ ፍፁም አትለይ፡፡'

## 7.2. ወደ ጌታ ተመለሱ (መዝሙር)

Turn to lord (song)

ወደ ጌታ ተመለሱ

እናንተን ለማየት ይናፍቃል

እጆቹ አቅፈው ይቀበሏችኋል

በበለጠ ፍቅር ለዘላለም

ወደ ጌታ ተመለሱ

ወደ ጌታ ተመለሱ

እናንተ የተመረጣችሁና የተጠራችሁ

አሁን ግን የተሰበራችሁ

ወደ ቤት እንድትመለሱ ይጠራችኋል

ወደ ጌታ ተመለሱ

ወደ እኔ ተመለሱ

የእናንተ ዋጋ ብር አይደለም

በደስታ የተሞሉ ቀናቶችም አይደሉም

በነገሮች የሚመዘንም አይደለም

እነዚህና የቀረው ሁሉ ጠፊ ናቸው ለዘላለም

ወደእኔ ተመለሱ

ወደ እኔ ወደ እኔ ተመለሱ

የኔ ፍቅር መለኪያ የለውም

እንናተ ደግሞ የኔ ኃብት ናችሁ

የኔ ደስታ የማያልቅ የበለጠ

ወደ እኔ ወደዚህ ተመለሱ

ኑ ! ኑ! ወደ እኔ ተመለሱ

## 7.3. ኢየሱስ የምፈልገው ሙሉ ልባችሁን ነው ይላል

እ.አ.አ. ፌብርዋሪ 17 ቀን 2015 ዓ.ም

{I want your whole Heart, Jesus said}

*የዩ ቲዩብ ቤተሰቦች እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡ ይህ ፅሑፍ የተወሰደው በኦክቶበር 27 ቀን 2007፣ ክሮንክልስ ኦፍ ዘ ብራይድ ከሚለው መፅሐፍ ነው፡፡*

*በጣም የሚያስደንቀው ነገር ባለፈው ከለጠፍኩት መልዕክቶች ይህም ከጌታ ጋር ቅርበት እና ከጌታ ጋር ተግባቦት ከሚባሉት ሁለት መልዕክቶች ጋር በጣም የተያያዘ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለፍቅረኞች ቀን አሁን ለተለቀቀው ቪድዮ ማረጋገኛ ሆኖኛል፡፡ የመጣሁት ኢጅግ እየተደነቅሁ ነው፡፡ እንደገናም ደግሞ ክሮንክልስ ኦፍ ዘ ብራይድ የሚለውን እንድናነብ የተሰጠን ከመንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡ የምናነበውን እንዲመርጥልን መንፈስ ቅዱስን አምነነው ስለነበር እኛ ከእግዚአብሔር ለመስማት እንደፈለግነውም እንደዛው ሆነልን፡፡*

*በነገራችን ላይ ማንኛውንም ጠላት ለማሰር የሚለው ፀሎት ወዲያው እንደሰራላቸው የሁለት ሰዎች ምስክርነትን አግኝተናል፡፡ ከሁለቱ አንደናው ጌታን ለመስማትና ለማየት ብዙ ውጊያ እንደነበረበትና በዚህ ፀሎት ግን ወዲያው ጥርመሳ እንደሆነለት መስክሮልናል፡፡ ይህ ፀሎት የተሰጠው ከመንፈስ ቅዱስ ከሆነ ምን እንደሚሰራ እርሱ ያውቃል፡፡ ዳቢሎስ ምን ለመስራት እንዳሰበ ያውቃል፡፡*

*ዛሬ ወደ አምልኮ ስመጣ አንድ ኢጋንንት በንዴት ጨሶ በጥግ ቆሞ ነበር፡፡ በጣም ትልቅ፣ አስቀያሚና በጣም ትንንሽ ሰይጣኖች ያላቸው ዓይነት ትልቅ ጭንቅላት ያለው ነበር፡፡ በእኔ በጣም ተናዶ ነበር፡፡ ኢየሱስ የሚለውን ስም ከአንደበቴ በግድ ተቸግሬ ሳወጣ ወዲያውኑ ሄደ፡፡ ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ቢያንስ የተናደደ አለ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ ነገር ነው፡፡*

*ይህንን መልዕክት አሁን እጀምራለሁ፡፡*

ኢየሱስ እንዲህ አለ . . . "ልጄ እመኚኝ እኔ ከአንቺ ጋር መነጋገር የምፈልገው በጣም ቅርበት ባለው መንገድ ነው፡፡ መናፍስትን መመርመር ጥሩና አዋቂ መሆን ነው፡፡ ቢሆንም ባሳለፍነው በዚህ በታወቀ ግንኙነት ወደፊት መራመድና ተፈጥሯዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ጓደኝነታችንን መፅናኛ፣ የምትደሰችበትና የሚመችሽ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ ነው ከአንቺ ጋር ልሆን የምፈልገው፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ ነው ከሁሉም ልጆቼ ጋር መሆን የምፈልገው፡፡

እንዲህ ቢሆንም ግን ብዙዎች በሌላ ነገር ይኸውም በዚህ አለምና በሚያንፀባርቀው ነገሩ ተጠምደዋል፡፡ እነዚህም ነገሮች በቅርቡ ከእኔ ጋር እነዳይገናኙ ግድግዳ በመሆን እነርሱንም የማገኘው በሩቅና በአንዳንድ ሁኔታዎች ብቻ ሊሆን ነው፡፡ ብዙዎቹ እኔ ለእነሱ የምናገራቸው በተፃፈው ቃሉ ውስጥና በቃሉ በኩል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ እንደሌሎቹ ብዙ ነገሮች ሁሉ ቃሌን በፅሑፍ እንዲሰፍር ያደረግሁት ለማነፅና ለመልካም እንዲሆን ነው፡፡ እንዲሁም ለጠንካራ ልባቸው ስል ነው፡፡

"ሰዎች ደካማ እንደሆኑና ወዲያና ወዲህ በሚሽከረከረው አይምሮአቸውና ሥጋቸው በቀላሉ ተጎትተው እንደሚወሰዱ ስለማውቅ ነው፡፡ ከአገልጋዬ ከሙሴ ጋራ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር እንደሚነጋገር በቅርበት እነጋገር ነበር፡፡ ሌሎቹ ግን ይሰሙኝ የነበረው በመንፈሴ በመነዳት የተፃፈውን የተናገርኩትን ቃል ነበር፡፡

*እኔ እንደማምነው ጌታ የሚለው እንዲህ ነው፡፡ በፅሑፍ የቀረበው ቃሉ/መፅሐፍ ቅዱስ/ ለማስተማርና ለማነፅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም እርሱ በቃሉ ውስጥ ይገኝልናል፡፡ ነገር ግን በፍጥረት መጀመሪያ እግዚአብሔር ከአዳም ጋር እያለ በፅሑፍ የቀረቡ ቃሎቹ አስፈላጊ አልነበሩም፡፡ ምክንያቱም አንዱ ከሌላው ጋር በየዕለቱ ይነጋገሩ ስለ ነበር ነው፡፡ እንዲሁም በመንግስተ ሰማያት የተፃፈው የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜም ቢሆን በእግዚአብሐየር ቃልነቱ የምናከብረውና ኃብታችን ነው፡፡ ነገር ግን ከዛ በተጨማሪ እርሱ ለእኛ እንደ ቅርብ ጓደኛ ይናገረናል፡፡ ምክንያቱም ልባችንን በማለዘብ፣ በቅድስና እንዲሁም የአለም ነገር ከጌታ ሊነጥለን ወይም ሊጎትተን በማይችል ፍፁም መልኩ ስለሚታደስ ነው፡፡*

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " ስለዚህ የትኛውን ትመርጣላችሁ? በመጋረጃ ውስጥ የተሸፈነና እናንተ ብቻ የምትናገሩት እንግዳ ወይስ እናንተ የምታዩት፣ የምትሰሙትና በቀላሉ የምትወያዩት እንግዳ?

"እኔ በደቀመዛሙርቴና በእኔ መካከል ምንም ማገጃ አላደረኩም፡፡ እነሱ ግን ሁልጊዜ በመካከላችን ግድግዳን ያስቀምጣሉ፡፡ እኔ በሙሉ ልቤ እወዳቸውና እንከባከባቸው ነበር፡፡ ይህንንም አደርግ የነበረው ሁሉም ወደ እኔ በመምጣት እንደ ጓደኛ በቅርበት እንዲያውቁኝ ነበር፡፡

"ለዚህ ቅባት ፀልዩ፡፡ ነገር ግን ይህንን እወቁ ብዙ ዋጋ በመክፈል ነው የሚመጣው፡፡ በእውነት ለመናገር አሁን ያላችሁበትን የኑሮ ዘይቤ በመቀየርና እኔን በህይወታችሁ በማስገባት ከእኔ ጋር ቅርበት ልትፈጥሩ ትፈልጋላችሁ፡፡ ይህ ማለት ለብዙዎቻችሁ የምር ለውጥ የሚያስፈልጋችሁ ነው፡፡ በመካከላችን የሚያውኩ ነገሮች ሁሉ ለመተውና ለእኔና ለእኔ ብቻ ሥፍራ በመስጠት ለመኖር ፈቃደኞች ናችሁ? ብዙ ነገሮቻችሁን፣ ጓደኞቻችሁን፣ መፅሐፍቶቻችሁን፣ መዝናኛዎቻችሁንና የመሳሰሉትን ሁሉ መስዋዕት ማድረግ ትችላላችሁ?

*አዚህጋ ማለት የምፈልገው እኔ በዚህ ነገር በጣም ትልቅ ትግል ነበረብኝ፡፡ ይመስለኛል ወደ አይምሮዬ እንድመለስ ካደረገኝ ነገር አንዱ ስለ መነጠቅ የነበረኝ መረዳት ነበር፡፡ በፊትም ንጥቀት እውነት መሆኑን እረዳለሁ፡፡ ነገር ግን እንደማስበው ዝርክርክ ነበረኩ መሰለኝ፡፡*

*ነገር ግን ንጥቀት እውነት መሆኑን ሳውቅ፣ ጊዜዬን በምን ላይ እንደማጠፋ ኮስተር ብዬ መከታተል ጀመርኩ፡፡ ከዚያም ለመዝናናት በማሰብ ወደ ገበያ ማዕከላት ስሄድ በከባድ እየተወቀስኩ መምጣት ጀመርኩ፡፡ ግልፅ ለማድረግ ያህል ለምሳሌ አንዳንድ ችግር ሲገጥመኝ አንዳንድ ነገሮችን በገበያ ውስት በማየት ከአይምሮዬ ውስጥ ችግሩን እንዲጠፋ ለማድረግ በምሄድበት ጊዜ ማለቴ ነው፡፡ በዛ መልኩ ወደ ገበያ ማዕከላት እሄድ የነበረውን ጉዞ በፍፁም እርግፍ አድርጌ ተውኩት፡፡ በአመት አንዴ እንኳን የምሄደውን እንኳን እርግፍ አድርጌ ተውኩት፡፡ እርግጥ ነው ዋጋ ያስከፍላል ደግሞም ትልቅ ትግል አለው፡፡ ነገር ግን ዋጋ አለው፡፡*

"እኔ ለፈጠርኩት ነፍስ ሁሉ እዚህ አለሁ፡፡ አልለወጥም፣ አልተኛም፣ ዕረፍት አላደርግም፡፡ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር መጥታችሁ ጊዜ እንድታሳልፉና የልቤን ልነግራችሁ በመፈለግና በመጓጓት እያየኋችሁና እየጠበቅኋችሁ ነው፡፡ የሚያስፈልጋችሁ ትንሽ በርታ ብላችሁ መሞከር ነው፡፡ እኔ በእርግጠኝነት የምነግራችሁ የምታደርጉት ጥረት ከልብ ከሆነና የራሳችሁ ቅድመ ሐሳብ ካልያዛችሁ በእርግጠኝነት እገናኛችኋለሁ፡፡ የራሳችሁን ሙሉ ፈቃድና እውቀታችሁን ስጡኝ፡፡እንደገና እንደ ህፃን ልጅ ተደርጋችሁ እንድትሰሩ ጠይቁኝ፡፡ ከዚያ በሰላም ተረጋግታችሁ ጠብቁኝ፡፡ እናም አስባችሁ ከምታውቁት በላይ እጎበኛችኋለሁ፡፡

"ብቻ ለእኔ ቦታ ስጡኝ፡፡ የምፈልገውም ሙሉ ልባችሁን ነው፡፡ የእናንተ ትልቅ ፍላጎትና ምኞት እኔን መፈለግና መከተል ብቻ ይሁን፡፡ እኔም የተትረፈረፈ ፀጋ እሰጣችኋለሁ፡፡ ነገር ግን ራሳችሁን ለዛ ዝግጁ አድርጉ፡፡

*ይህ የመልዕክቱ መጨረሻ ነው፡፡*

*ይህንን ሐሳብ በአይምሮአችን በመያዝ አለምን በውጪ ለመተውና እስከመጨረሻው ከእኛ ውጪ ለመተው ለእናንተም ለእኔም እፀልያለሁ፡፡ ከጌታ ጋር በቅርበት የምንሆንበትን፣ በዝምታ የምንቆይበትን፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ለእኛ እጅግ እንቁ የሆነውን ያንን ሥፍራችንን ለማስፋት እንድንቀጥል እፀልያለሁ፡፡ የዩ- ቲዩብ ቤተሰቦች የእኛን ቻናል ፈልጋችሁ ስለተከታተላችሁ እናመሰግናችኋለን ደግሞ ጌታ ይባርካችሁ፡፡*

# ክፍል ስምንት
# አታላይ መናፍስት እንዴት እንደሚሰሩ መልዕክቶች

{Messages to Show You How Deceiving Spirits Work}

---

## 8.1 የአታላይ መናፍስቶች አሠራር

እ.አ.አ ዲሴምበር 6 ቀን 2014 ዓ.ም

ህዝቂኤል፡- ወደ ሄቨን ቶክ እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡ ህልም፣ ራዕዮች፣ አስተያየትና ውይይት በሁሉም አቅጣጫ በዚህ ፕሮግራም ይካሄድል፡፡

እኔ ህዝቂል እባላለሁ

ክለር፡- እኔ ደግሞ ክሌር እባላለሁ

ህዝቂል፡- እንደምን አመሻችሁ፣ ይህ ኒው ሜክሲኮ የሚገኘው የሳንገር ክሪስቶ ተራራ ታኦስ ነው፡፡

ክሌር፡- የዩ ቲዩብ ቤተሰቦች እኛ እንዳሰብነው በታንክስ ጊቪንገ አካባቢ ንጥቀት ባለመካሄዱ ቅር ለተሰኛችሁ ለሁላችሁም ከልባችን በጣም እናዝናለን፡፡ በእውነቱ ከሆነ ከአንድ ሴት የተላከ ደብዳቤ በእጄ ይገኛል፡፡ ከዛ ደብዳቤ የተወሰነውን አነብላችኋለሁ፡፡

ደብዳቤው እንዲህ ይላል " በዚህ የንጥቀት 'የመጨረሻ ቀን' ነው በሚለው የተሞኘንበት አንዱ ምክንያት (እኛ እንዳሰብነው) ከዚህ አለም ጫናና ክብደት ለመላቀቅ ተስፋ ስለሚሰጠን ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ጌታ ሲናገረን በእነዚህ ቀናቶች ንጥቀቱ ይከናወናል የሚለውን እንድንሰማ ጌታ የፈቀደው እኛ ለመስማት እጅግ ከመጓጓታችን የተነሳ እንደሆነ ተናግሮናል (ከመልሱ ጋር እጅግ ተጣብቀን ነበር፣ ስለዚህም አጋንንቶች በዚህ ሊሰሩ ቻሉ)፡፡  በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ግን እርሱ ከእኛ ጋር ነበር፡፡ ደግሞም ይወደናል፡፡ ስለዚህ አሁን እየፀለይን ያለነው ቃላችን ንፁህ እንዲሆን፣ የመለየት ችሎታችን ጥሩ እንዲሆን ነው፡፡ ነገር ግን ምንም መለየት የማልችል መስሎ አይሰማኝም፡፡

ክሌር፡- እኔም እንደሚመስለኝ አብዛኛዎቻችን በእነዚህ ባለፉት አንድ ወይም ሁለት ሳምንቶች  የተሰማን በተመሳሳይ መልኩ ነው፡፡

ህዝቂል፡- አዎን  እንደሚመጣና እንደሚሄድ  ጭጋግ የበዛበት ዓይነት ነበር፡፡

ክሌር፡- አዎ የማይነቃነቅ ዓይነት ማዕበል ወይም እንደዛ ዓይነት ምንም የማይነቃነቅ ነገር ግን ማዕበል ያለበት ነበር፡፡

ህዝቂል፡- አዎን አንድ እርግጠኛ የሆነ ጣልቃ ገብነት ያለበት  ጭቆና ነበር፡፡

ክሌር፡ - ታውቃላችሁ የረቀቀ ነበር፡፡ ይህ ጭቆና እጅግ የረቀቀ ስለነበር ጭቆና እንደሆነ እንኳን ልንገነዘበው አልቻልንም፡፡ እንደሚመስለኝ ኢጋንንቶች የሚጠቀሙበት የብልሃት ዓይነት ነው፡፡ ነገሩን እንዳትገነዘቡት ረቂቅና እጅግ በሹክሹክታ መልኩ ያደርጉታል፡፡

ህዝቄል፡- አዎን ልክ ነው፡፡ አንድ ቀን ትነሱና የት ነው ያለሁት? ምን?ጌታ አሁን ተናግረኸኛል? ወይም የተናገርከኝ መሰለኝ? ትላላችሁ፡፡ ወይም ማስታወሻችሁን በማገላበጥ የሰጣችሁ ቃል ምን እንደነበር፣ ወይም በቃሉ ውስጥ ምን ተናግሯችሁ እንደነበር ታያላችሁ፡፡ ነገር ግን ስለ ሁኔታው ምንም ስሜት የላችሁም፡፡ እኔ እንደማስበው አንዳንድ ጊዜ ስሜታችሁን እንኳን ማመን ያቅታችኋል፡፡ አይደለም እንዴ?

ክሌር፡- አዎ፣ ደግሞ ኢጋንንቶች በስሜቶቻችን ይጫወታሉ፡፡ አሁን በቅርብ ጊዜ ጌታ የሰጠኝን አንድ ቀላል መልዕክት በዩ-ቲዩብ አስተላልፌያለሁ፡፡ ነገር ግን ዛሬ ምሽት ለእናንተ ስንልና የምሽቱን ውይይት አንፀባራቂ ለማድረግ እንደገና ብናነበው መልካም ይመስለኛል፡፡ በኮምፑተሬ ላይ ስለሚገኝ ይቅርታ አድርጉልኝና ላንብበው፡፡

ጌታ እንዲህ ሲል ጀመረ . . . " በእነዚህ ባለፉት ቀናቶች ብዙ ሙሽሮቼ ስለተታለሉ ልቤ እጅግ አዝኗል፡፡ በእኔ ስም ብዙዎች ይመጣሉ ብዬ አልነገርኳችሁምን? ቢሆንም የእረኞች ትፋት እንደሆነ ያህል የእናንተ ጥፋት አይደለም፡፡ እንዲህ ብዬ ልጀምር 'እኔ እንኳን ብሆን ቀኑን ወይም ሰዓቱን ማንም አያውቀውም፡፡ ወቅቱን ልታውቁ ትችላለችሁ፣ አዎ ወቅቱም ይህ ነው፡፡

ክሌር፡- ሁላችንም ያንን እናውቃለን! ስለዚያም እውነተኛ ትልቅ ስሜት ይሰማናል!

ህዝቄል፡- እጅቅ ቅርብ፡፡ በአይናችን ሥር!

" ሙሹሮቼ ከተመደቡላችሁ ኢጋንንቶች ይልቅ የበለጠ ብልህ መሆን አለባችሁ፡፡ እነዚህ ፍጥረታት እናንተ ራሳችሁን ከምታውቁት በላይ እነርሱ ያውቋችኋል፡፡ ስለዚህ ነው ራሳችሁን ማወቅ እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው፡፡"

ክሌር፡- እናም የተለያዩ በሮች በምን ዓይነት መንገድ በቀላሉ እንደሚከፈቱ ጌታ የሰጠኝን ዝርዝር ቶሎ ቶሎ ብዬ አቀርባለሁ፡፡

"ኩራት፣ ሽንገላና እራስን መፈለግ እነርሱ እንዲገቡ የመጀመሪያዎቹ መግቢያ ቀዳዳ ናቸው፡፡ እናንተ ልዩ እንደሆናችሁ፣ ከሌሎች የተለያችሁና ሚስጥራዊ እውቀትን ለማወቅ በልዩ የተመረጣችሁ እንደሆናችሁ ይነግሯችኋል፡፡"

ክሌር፡- ስለዚህም በኩራታችሁና በዕብሪታችሁ ይጫወታሉ፡፡

"እናም እንደዚህ ልበል፣ ሁላችሁም፣ እያንዳንዳችሁ በራሳችሁ መንገድ ድንቅና የተለያችሁ ናችሁ፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡ ስለዚህም በእናንተ ላይ የሆነ አምድ በማስቀመጥ እንዲፈትኗችሁ አትፍቀዱ፡፡ ምስጥራዊ እውቀትን በተመለከተ የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ አመለካከት ይኸውም ጥቂቶች ብቻ የሚያውቁት ወይም የሚረዱት ወደሚለው አስተሳሰብ መሄዳችሁ ነው፡፡"

ክሌር፡- በእርግጠኝነት ወደእዛ መሄድ አትፈልጉም፡፡ በዚያ ጉዳይ ላይ አንድ ነጥብ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ በክርስቲያኑ ህብረተሰብ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን አንድ ሰው ከጌታ ጋር ቅርበት ስላለው ብቻ ያንን ሰው ለእርሱ ልዩ በመሆኑ ሚስጥራዊ እውቀት አለው፣ ጌታ ሁሉንም ሚስጥር ያካፍለዋል የሚል ስሜት ካለ ማለቴ ቃሉ የሚለው ምስጥራቱን ለነቢያቱ እንደሚገልጥ ነው፡፡ ነገር ግን ሰዎች ወደ ሚስጥራዎ ነገር ሲያተኩሩ፣ ይህም የሰዎች ሁሉ እንቅስቃሴ ሲሆንና ጥቂቶች ብቻ የሚያውቁት ወይም የሚረዱት ዓይነት እውቀት ወደሚለው አመለካከት ሲይዝ ወይም በጣም 'የመጠቁት' እንዲህና እንደዚያ ማለት ሲጀመር ይህ በእርግጠኝነት ጌታ አይደለም፡፡ ይህ በእርግጠኝነት የዲያቢሎስ ወጥመድ ነው፡፡

ይህ አካሄድ የጌታ ነው ለማለት ተጠንቀቁ፡፡ ምክንያቱም እያፈራ ያለው ምሬትን፣ ልዩነትንና ሌሎችን ያለማካተትን ነው፡፡ የምንጠቀመውም ሥም የሹዋ ፣ የሃዌ፣ እንዲሁም የአብ አባትንና ኢየሱስ የሚለውን ሥም ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ስንል እጅግ ይበሳጩብናል፡፡ ልነግራችሁ የምፈልገው አጋንንቶች ኢየሱስ የሚለው ስም ምን እንደሆነ ያውቁታል፡፡ ከአጋንንት እስራት ነፃ በማውጣት ጊዜ ኢየሱስ ብለን ስንጠቀም በትክክል ይሰራል፡፡ በዚህ ሥም ላይ አንድም ቀን አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ አያውቅም፡፡ እኔ የሚመስለኝ ይህ አከራካሪ ሆኖ የሚቀርበው ራሳቸውን ከፍ ባደረጉ ሰዎች ዘንድ ነው፡፡ እነሱም በኩራት "ትክክለኛው ሥም ይህ ነው ስለዚም መጥራት ያለባችሁ እንዲህ ነው" ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በክርስቶስ አካል ውስጥ አሉባልታና መከፋፈልን አምጥቷል፡፡

ህዝቄል፡- ግራ መጋባትን ፈጥሯል፡፡

ክሌር፡- አዎ ግራ መጋባትን ፈጥሯል፡፡ በቀደመው ጊዜ ጌታን ምን ብለው እንደሚጠሩት ታውቃላችሁ፡፡ በተለይም አረጋውያን፡፡ በኢየሱስ ስምና በአባት ስም ወዘተ ....፡፡ ልክ እንደዛ ማለት ነው፡፡ አሁንም እኛ . . .

ህዝቄል፡- ይህ ቢሆንማ ብዙ ጥሩ የሆኑ የምስጋና መዝሙሮችን እንዳንዘምር ያረድግ ነበር፡፡ አይደለም እንዴ?

ክሌር፡ - በትክክል፡፡ ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ በብዙ አይነት የቀረቡትን የምስጋና መዝሙሮች መዘመር አንችልም ነበር፡፡ በዚህ ነገር ሰዎች ፅኑዎች ናቸው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ሰዎች ተነስተው ይህ የተጠቀማችሁት 'የጌታ ሥም ትክክል አይደለም' ብለው በሰዎች ላይ ሲነሱ ትዕቢት ካልሆነ በቀር ምን ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ እኔ ግን ሰዎች የሂብሩን ስም ቢጠቀሙ ቆንጆ ይመስለኛል ደግሞም ይመቸኛል፡፡ ይህ የማይመቻቸው ሰዎች ግን ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡

ህዝቄል፡- ኢያችሁ ግመል እየዋጥን ትንኝን ግን እየገፋን ነው፡፡ ታውቃላችሁ ሞኝ የሆነ ክርክር እንዳናደርግ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፡፡ አይደለም?

ክሌር፡- በትክክል ያ አንዱ ጥሩ ነጥብ ነው፡፡ ማለቴ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መከራከር አልፈልግም፡፡ ይህ ሞኝነት ነው፡፡

ህዝቄል፡- ከፋፍለህ አሸንፍ ዓይነት ነው፡፡

ክሌር፡- እኔ እንደሚመስለኝ ምናልባት በጌታ ላይ የተወሰነ ህምም ለመፍጠር እጅግ በቅርብ ርቀት ላይ እንገኛለን፡፡ ዛሬ ምሽት ምናልባት አንዳንዱን እናነሳዋለን፡፡ በራዕይ ሰዎች የጌታን አካል ሲሰነጥቁና ሲቀዳድዱ ያየኸውን የጌታን ስቃይ ማካፈል ትችላለህ?

ህዝቄል፡- ጌታን እንደገና እየሰቀልነው ነው፡፡ ቀደም ብዬ በነገርኳችሁ ስብሰባ ወቅት ወደ ገበያ በመሄድ ምስማር ገዝቼ ይህ ሰው ከመሞቱ ቀደም ብሎ (ያጋጣሚ ሆኖ የሞተውም በአሰቃቂ ሁኔታ ነበር) በሚቀጥለው ስብሰባ ስንገናኝ የገዛኋቸውን ምስማሮች ጠረጴዛው ላይ በማስቀመጥ ጥዬ ለመሄድ ነበር፡፡ ታውቃላችሁ በዚህ መልኩ መልዕክቱ እንዲደርሰው ለማድረግ ነበር፡፡ በአካሉ ላይ ስንት ምስማሮችን ነው መምታታችንን መቀጠል የምንፈልገው? እንዴት አድርገን ነው ለመግደል የምንፈልገው? ማስታወስ ያለብን በቤተ ክርስቲያን ስለ ምትገኝ አንድ ሴት፣ ወይም ስለ አንድ ወንድም፣ ወይም ስለ ሰባኪው፣ ወይም ስለ ፓስተሩ ስናወራ ማድረግ የያዝነው አንዱን የጌታን ክፍል እየቦጨቅን ነው፡፡

ህዝቄል፡- ያንን ማድረግ የለብንም፡፡ ይህ አንድን አካል እንደሚበላ ካንሰር ነው፡፡ ታውቃላችሁ ራሱን መብላት፡፡

ክሌር፡- ትክክል፣ ደጋግመህ እንደምትናገረው አንድ ችግር ውስጥ ያለ ወይም አካል ጉዳተኛ ልጅ ቢኖርህ ወይም እንዲህ ዓይነት ሌላ ሰው ቢኖር በዛ ልጅ ላይ እጅህን እያመላከትህ "ተመልከቱ መሄድ እንኳን አይችልም" ወይም ሌላ እንዲህ የመሰለ ነገር አትሉም፡፡ ለወላጆቹ እንዲህ አትሉም፡፡

ህዝቄል፡- እንዲህ ብትሉ በጣም የሚጎዳ ነገር ነው፡፡

ክሌር፡- የምታደርጉት ነገር በጣም አዝናችሁ ለእነርሱ ትፀልያላችሁ፣ ልጁም እንዲፈወስ ትፀልያላችሁ፡፡ 'ክርስቲያኖች ከውስጣቸው የታመመውን ይገድላሉ' የሚለው ተለጣፊ መፈክር በጣም ነው የምጠላው፡፡ ነገር ግን ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በአንድ በኩል እውነትነት አለው፡፡ አባዛኛዎቻችን (ይህንንም በዩ-ቲዩብ እንኳን መገንዘብ ችዬአለሁ) በጣም መጥፎ የሆነ አስተያየት ነው የምንሰጠው፡፡(ሳቅ በሳቅ) እናም ታወቃላችሁ እግዚአብሔር ይወዳቸዋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ሌሎች ክርስቲያኖችን እንደ ዱላ ምት ኃይለኛ ቃል በመናገራቸው ለእግዚአብሔር ውለታ የዋሉለት ይመስላቸዋል፡፡ እንደተረዳሁት ከሆነ ግን "እውነትን ታውቃላችሁ! አሁን እውነትን ልነግራችሁ ነው!"

እናም በቤተ እምነቶች መካከል እንኳን ያለው ሁኔታ እጅግ የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ ማለቴ ያ ሁሉ ስርዓት ባለበት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጌታን አግኝተነዋል፣ በኢቫንጀሊካል ቤተ ክርስቲያን አግኝተነዋል፣ በጴንጤዎች ቤተ ክርስቲያን አግንተነዋል፡፡ እናም በሜቶዲስትና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አግኝተነዋል፡፡ ሰዎች የአንዱን ቤተ እምነት አንስተው አንድ ነገር ሲያወሩ ልቤ በጣም ነው የሚያዝነው፡፡ ደግሞም ብዙ ጊዜ የሚያነሱት ሐሳብ ምንም ቁም ነገር ያለው አይደለም፡፡ ምንም አያውቁም፡፡

ህዝቄል፡- እንደ ፓሮት አንድ ሰው ያለውን ብቻ እንዲሁ መድገም ነው፡፡ አንድ ሰው እንዳለው፣ እና አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፣ እናም አንድ ሰው እንዳለው እያሉ እንደ ፓሮት መደጋገም ነው፡፡ አንድ ጓደኛ አለኝ ለተወሰነ ጊዜ በሰሜን አፍሪካ የነበረ፣ እንዲህ አለኝ " ኢቫንጀሊካል ክርስቲያን ብሆንም ህዝቡ፣ መንግስቱና ክፍለ አገሩ ሁሉ ሙስሊም በሆነበት በዚህ አገር ክርስቲያን የሚባል አይቼም አላውቅም ነበር፡፡ እናም በዚያን ወቅት በጣም የደከመውና የራበውና በውኃ ጥማት ተቃጥሎ ውኃ የሚፈልግ ሰው ነደርኩ፡፡ ከዚያም በቡድን የሆኑ የግብፅ ኦርቶዶክስ መነኩሴዎችን አገኘሁ፡፡ ቄሶቹና ፣

መነኩሴዎቹ ሁሉ ወጡ፡፡ ማን መሆናቸው ምንም ግድ አልሰጠኝም፣ ምን እንደሆኑ፣ ስማቸው ማን እንደሆነ ምንም ግድ አልሰጠኝም፡፡ ነገር ግን ያንን መሰቀል ብቻ አየሁ፡፡ ክርስቲያን እንደሆኑም አወቅሁ፡፡ ቅዱሳን መፅሐፍቶቹን አየሁ፡፡ ምንም ግድ አልሰጠኝም፡፡ ሌሎች ክርስቲያኖችን ስላገኘሁ ብቻ በጣም ደስ አለኝ፡፡ አሁን ዓመት ይሆነዋል፡፡"

ክሌር፡- አዎ ደግሞ ሌላ ክርስቲያን አጠገባችሁ ሲገኝ የጌታ መገኘት ይሰማችኋል፡፡

ህዝቄል፡- ምናልባት በመንፈስ እርስ በራስ መተዋወቅ ሊያስፈልጋችሁ ችላል፡፡

ክሌር፡- በትክክል፡፡ ማለቴ እነዚህ ሰዎች እኮ ባለፈው ለእምነታቸው ከተሰዉት ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ታውቃላችሁ እነዚህ ሰዎች ለጌታ አገታቸውን ሲሰሉ እኛ በወቅቱ በገበያ ማዕከላትና በተለመደው ሥራችን ላይ ነበርን፡፡

ህዝቄል፡- ልጆቻቸው እንኳን፡፡ ልጆቻቸው እንኳን!

ክሌር፡- ልጆች ለጌታ ምስክር በመሆን እየሞቱ ነው፡፡ እና እነዚህ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ናቸው፡፡

ህዝቄል፡- የግብፅ ኦርቶዶክሶች ብቻ አይደሉም ይህንን ፅዋ እየቀመሱ ያሉት፡፡ ነገር ግን በፍልስጤም የሚገኙ ክርስቲያኖች፣ የምስራቁ ክፍል ክርስቲያኖች እንዲሁም የመካከለኛው ምስራቅ ክርስቲያኖችና በትኛውም ቦታ የሚገኙ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡

ክሌር፡- ትክክል፣ ትክክል ነው፡፡ ይህ እየተደረገባቸው ያለው ኢቫንጀሊካል ቤተ ክርስቲያናት ብቻ አይደሉም፡፡ እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ስርዓት ባለበት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ እናም የሚሞቱት በምስክርነታቸው ነው፡፡ የኢየሱስን ስም መካድ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ነው ራሳቸውን የሚቀሏቸው፡፡

ህዝቄኤል፡- እውነት ነው፡፡ ስለዚህ ታውቃላችሁ እኔ እዚህ ያለሁት የአምልኮ ስርዓትን፣ ታሪክንና ብዙዎቹ እንደሚሉት የሰውን መመሪያና የመሳሰሉትን ለመከራከር አይደለም፡፡ ስለዚያ ግድ የለኝም፡፡ ሁላችንም ቢሆን በቤተሰቦቻችንና በባህላችን ልምዶች አሉን፡፡ ይህ እኔን ግድ አይሰጠኝም፡፡ኢየሱስን ሲወዱትና ህይወታቸውን አሳልፈው ሲሰጡት፣ ኦ! ይህ ህፍረት እንዲሰማኝ ያደርጋል፡፡

ክሌር፡- አዎን ሁላችንም ልማድ አለን፡፡ አንዳንድ ልማዶቻችን መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳቸው ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ግን አይደሉም፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ የመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ ያልሆኑትን ልምዶቻችንን መተው ያለብን ይመስለኛል፡፡

ህዝቄኤል፡- ታውቂያለሽ በዚህ ዘመን የሚነሱ ክርክሮች " ኦ! ሃይማኖት የለንም፣ ያለን እምነት እንጂ ሃይማኖት አይደለም" የሚል ነው፡፡ ያ ጥሩ ሃይማኖት የተባለው ምንድነው? ባል የሞተባቸውንና ህፃናቶችን መመገብ የሚለውን የምትጠቀሙት ቃል ሃይማኖት የሚለውን አይደለም? ሰዎች እባካችሁ እዚህጋ ትንሽ አስቡ፡፡ በዚህ አገር በዚህ በትንሽ ነገር እኛም አክራሪዎች ሆነናል፡፡ አልሆንም? አክራሪነት ክርስቲያን ሆናችሁ ሺሃት አደገኛ ነው፡፡ ወደ መስቀሉ ወስደን እንደገና እንዳንሰቅለውና በምስማርም እንደገና እንዳንከረችመው መጠንቀቅ አለብን

ክሌር፡- ታውቃላችሁ ምንም እንኳን መንፈስን ከመለየት ርዕሶች ውስጥ የምናነሳው በጣም ትንሹን ክፍል ቢሆንም ሁሉንም መንፈስን ለመለየት አድርገን መውሰዳችን እጅግ ጥሩ ሐሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ሰዎችን መተቸት ስንጀምር ራሳችንን ለአጋንንታዊ ሥራ እያጋለጥን ስለምንሄድ ነው፡፡

ህዝቄኤል፡- ይህ ማታለል ነው፣ የማታለል ትልቁ ጊዜ፡፡

ክሌር፡- ኦ የሚደንቅ ነገር! ፡፡ በጋብቻ ዘመናችን ማለትም ገና እንደተጋባን ከአንድ ቦታ በሆነ ምክንያት ቆስለን ከወጣን ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን በአንድ ነገር መቁሰል እንዴት እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ፣ ቤት ከደረሳችሁ በኋላ ስለዛ ሁኔታ ታወራላችሁ፡፡ እናም ደስ የማይል አመለካከት ስለ ሰዎቹ ትይዛላችሁ፡፡ ምን እንደሰሩ ምን እንደተናገሩ ማውራት ትጀምራላችሁ፡፡ እናም በዚያን ጊዜ እኛ እርስ በርስ መጣላት መጀመራችንን አስተዋልኩ፡፡ ነገሩን እስከንረዳ ድረስ ይህ አካሄድ ለጥቂት አመታት ቀጥሎ ነበር፡፡ በመጨረሻውም ሲገባን እርግፍ አድርገን ተውነው፡፡

ህዝቄኤል፡- ከዚያም በኋላ "በሩን የከፈተው ምንድነው?" ማለት ጀመርን፡፡

ክሌር፡- ከዚያም በሩን የሚከፍተው ምን እንደሆነ አገኘነው፡፡ ያም ሌሎችን መተቸት እንደሆነ አወቅን፡፡

ህዝቄኤል፡- እንደሚመስለኝ ማናችንም ብንሆን አፋችንን ገና ስንከፍት እንዳውም ገና በአንደበታችን ሳንናገረውና ልባችን ገና መፍረድ ሲጀምር ጌታ ወደታች ሊጥለን ፈጣኑ መንገድ ነው፡፡ ለነገሩ ጌታ የሚያየው የውስጣችንን ይኸውም የልባችንንና የአይምሮአችንን ፍርድ ነው፡፡ ሁላችንም ቆስለናል፡፡ ስለዚህም ሁላችንም ፈውስ ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህም በእኛ ላይ ጠንከር ብሎ ነበር፡፡ ማለቴ ባለፉት ዓመታት ፍድርን ፍፁም እርግፍ እንድናደርግ በጣም የላመ ዱቄት እስክንሆን ድረስ ነበር የሰባበረን፡፡ ምክንያቱም በምንም ዓይነት ከእኛ ጋር ሊዘልቅ ኤችልም ነበር፡፡

ክሌር፡- አዎን፡፡ ደግሞም መንፈስ መለየትን ይጎዳል፡፡ ስለዚህም ጌታ እንድትወድቁ ይፈቅዳል፡፡ ደግሞም በሰዎች ላይ ስንፈርድ በእርግጥም በእኛ ላይ ይፈረድብናል፡፡ ጌታ ያስጠነቀቀን ሌላው ገፅታው ደግሞ ይህ ነው፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያውን የተናገርኩ ይመስለኛል ትዕቢት፣ እውነት ያለሆነና የበዛ ምስጋና እንዲሁም ራስን መፈለግ የመጀመሪያዎቹ በር ከፋቾች ናቸው፡፡

ሁለተኛው በር ከፋች ደግሞ ብቸኝነት ነው፡፡ መነጋገር የያዝነው ጉዳይ መንፈስን በመለየት ወቅት ስህተት እንዴት ሊፈጠር እንደሚችል ነው፡፡ ስለዚህም ብቸኝነት ሁለተኛው በር ከፋች ነው፡፡ ስለዚህም የፈረሰ ጋብቻ፣ የመገለል ስሜት፣ መራራነት፣ በሥራ አለመሳካት ወይም በአገልግሎት ሴኬት ማጣት፣ ተቀባይነት ማጣትና በክርስቶስ አካል ውስጥ መቁሰል እኛን የሚጥሉንና ለጠላት ጥቃት ተጋላጭ እንድንሆን በር ከፋቾች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እናንተ ደካማ ስትሆኑ እርሱ ለማጥቃት ይመለከታችኋል፡፡ ወደታች ስትወርዱና ደካማ ስትሆኑ እናንተን ለመጉዳት ይፈልጋል፡፡

ህዝቄኤል፡- ይህ የቆሰለ አሣ ጥቃት እንደሚበዘበት ዓይነት ነው፡፡

ክሌር፡- አዎን እንድትቆስሉ ለማድረግ ይልካል፣ ይጠብቃል፣ ይመለከታል፣ ነገሮችን ያዘጋጃል፡፡ ከዚያ በኋላ በጀመረው ነገር ላይ እየጨማመረ ጥቃቱን ይቀጥላል፡፡ እናንተ ደግሞ ሌሎቹን ሰዎች ማጥቃት ትጀምራላችሁ፡፡ ያ ደግሞ በሮችን በጣም ሰፊ አድርጎ በመክፈት እየተባባሰ ይሄዳል፡፡ ስለዚህም ብቸኝነት፣ የፈረሰ ጋብቻና መገለል በር ከፋቾች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ደግሞ ከምትፈልጉት ከማንኛውም ነገር መጣበቅ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የራስ ፍላጎት፣ አለመታዘዝ፣ እኔ አውቃለሁ ባይነት አብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡ አቤት! በእነዚህ ነገሮች እኔ ጥፋተኛ ነበርኩ፡፡

ህዝቄኤል፡- ስንት ጊዜ ይሆናል ወደ ጌታ እየቀረባችሁ ለምሳሌ " አ ጌታ ሆይ እባክህ እሺ በል! እባክህ እሺ በል ወይም አ ጌታ ሆይ እባክህ አይሆንም በል! እባክህ አይሆንም በል የምንለው፡፡ ስንት ጊዜ ይሆን እዛ መሄድ የሉብኝም፣ በዚህ ዓይነት መንገድ ንገረኝ. . . ያልነው? በቃሉ ላይ የወንድማማች ፍቅር እንደሰጠን ሁሉን እያወቅን ነገር ግን የታመመች እህትን ወይም ወንድምን ሄደን ላለመጠየቅ የሚደግፈንን ቃል እንፈልጋለን፡፡ ምክንያቱም ሰነፎች ስለሆንንና መሄድ ስለማንፈልግ ነው፡፡ እንደእነዚህ ዓይነት መጣበቆች ወይም ሊመጣ ይችላል ብላችሁ ቀድማችሁ የተረዳችሁትን ነገር ጋር ከመጣበቃችሁ የተነሳ "አ ጌታ ሆይ የምፈልገው ይህንን ነው፣ ያ እንዲሆን ነው የምፈልገው፣ ይህንን ራዕይ ነው በጣም የምፈልገው ወይም ያኛውን ነው በጣም የምፈልገው" እንላለን፡፡

ክሌር፡- ታስታውሳለህ በቅርብ ጊዜ የሲዲ መቅጃውንና በሲዲ ላይ ምልክት ማድረጊያውን መሳሪያ ለመግዛት "ይህ በጣም የሚያስፈልገን ነገር ነው ብዬ ሳስብ ጌታ ግን ባለመፍቀዱ የተበሳጨሁትን?

ህዝቄኤል፡ በጣም ነበር የተበሳጨሽውና ተስፋ የቆረጥሽው

ክሌር፡- አ! በከፍተኛ ሁኔታ ነበር የተበሳጨሁትና ተስፋ የቆረጥኩት፡፡ በዛ ወቅት ምክንያቱም ስዕሎችንና ፎተግራፎችን መስራት እወድ ነበር፡፡ እናም በዲቪዲዎቹ ላይ ምልክት ማደረጊያ ያስፈልጉን ነበር፡፡ ጌታ ግን አይሆንም አለኝ፡፡ በዚያ ምክንያት መግዛት  አልቻልም ነበር፡፡ ነገር ግን በቀላሉ አይደለም ይህ የሆነው፡፡ ከጌታ ጋር የቤት ውስጥ ጥል ነበረብኝ፡፡ (ሳቅ በሳቅ)

ህዝቅኤል፡-  አ! አሳዛኙ ኢየሱስ! (ሳቅ በሳቅ)

ክሌር፡- ያ ትክክል ነው!

ህዝቄኤል፡- አንድ ቀን " እኔና ጌታ ልንጣላ ስለሆነ ብትፀልይልኝ ይሻላል" አለችኝ፡፡ እኔም "ለእርሱ ነው የምፀልለት

አልኳት"፡፡ (ሳቅ በሳቅ) ለጨዋታ ያህል ነው!

ክሌር፡- አ! ጌታዬ . . . እሺ፡፡ ስለዚህ  ከአንድ ነገር ጋር መጣበቅ በርን ከፋች ነው፡፡ አንድን ነገር በጥብቅ ከፈለጋችሁት አጋንንቶች ያንን እንድታደርጉ ያስገድዷችኋል፡፡  ከመንገዳችሁ ሊያሶጧችሁ ማግኘት ትችላላችሁ ይሏችኋል፡፡

አራተኛው በር ከፋች ደግሞ ራስን መጥላት ነው፡፡ ራሳችንን እንድንጠላ ያደረገንን ያንን ነገር (ምክንያቱ እውነትም ይሁን ውሸት) በተቃራኒው በመቆምና በህይወት ለመቀጠል በመፈለግ መልሰን መዋጋት እንጀምራለን፡፡ በዚህም ምክንያት ያንን ሆነናል ብለን የምናስበውን የራሳችንን ስዕል እንዳይታየን ለማድረግና ለመሸፋፈን እራሳችንን ልዩ ሰው አድርገን እናቀርባለን፡፡ ኢጋንንቶችም እኛ በፈጠርነው በዚህ ዓለም እንድንቆይ ለማስገደድ እጅግ ደስተኞች ናቸው፡፡

ህዝቂኤል፡- ኦ! ጥርት ያለ ራዕይ፣ ህልም፣ ቃልና ሁሉም ነገር ሊኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን አሁን አንቺ እንዳልሽው ራሳችንን ፈትሸን የሆነውንና ያልሆነውን በእውነት ለመፈተሽና ታማኝ ሆነን ለመገኘት ጌታ እንዲሰራን ፈቃደኞች ነን ወይ? ጌታ ውሸት የሆነውን ሁሉ ከመንገዳችን እየጠረገ በማስወገድ መልካም የሆነውን ለመስጠት ይችላል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ህይወታችንን ለመንጠቅ ወይም ሊጎዳን አይደለም . . . ፡፡

ክሌር፡- እኛ እንደምናስበው በግማሽ ያህሉ ብቻ አይደለም መጥፎ የሆነው፡፡ በአንድ ደረጃ ላይ ነው ያለነው፡፡

ህዝቂኤል፡- አዎ እንደዛ አይደለም፡፡

ክሌር፡- ሌላኛው ጌታ በጥንቃቄ የተናገረኝን አሁን አካፍላችኋለሁ፡፡ እርሱም እንዲህ አለኝ . . . " አሁን ቅስቀሳ የማካሂደው ሁለትዮሽ የሆነ ንግግር በሬማ በኩል እንዲሆን ነው፡፡"

ክሌር፡- ይህ ማለት ጌታ ቃሉን ሲያበራላችሁ ማለት ነው፡፡ ይህም በተለያየ መንገድ የሚገን ነው፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ፣ ወይም ከተስፋ ቃሎች መፅሐፍ፣ ወይም ከአስቲከሮች፣ ወይም ከቢልቦርዶችና ሊሆን ይችላል፡፡

ህዝቂኤል፡- ብቻ ስታነቡ በዛ ወቅት አንድ ገፅ ላይ ልዩ ሆኖ የሚታያችሁ ቃል ወይም አረፍተ ነገር ነው፡፡

ህዝቂኤል፡- አዎ ልክ ነው፡፡ እናም በነፍሳችሁና በልባችሁ ውስጥ ልዩ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ምንም ነገር ብታዩ ያንን ነገር መንፈስ ቅዱስ እንዳስተካከለው ይሰማችኋል፡፡ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ይህንን እንዴት እንደምናደርግ የምናሳያችሁ ልዩ የሆነ መንገድ አለን፡፡ ሐሳቡ ሰዎች በየቀኑ ዳቦ በጠረጴዛቸው ላይ እንደሚያቀርቡበት ትንሽ ሳጥን ዓይነት ተመሳሳይ ነው፡፡ ልዩነቱ እኛ የምንጠቀመው መፅሐፍ መሆኑ ነው፡፡ እኛ የምንጠቀመው መፅሐፍ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍ/The Bible Promises/ ይባላል፡፡ እኔ አሁን ያለኝ ይህ መፅሐፍ ሽፋኑ ሌላ ዓይነት ነው፡፡

ህዝቂኤል፡- ሰዎች ይህንን መፅሐፍ ለጌታችን ልደት እንደ ስጦታ ሊያበረክቱላችሁ ይችላሉ፡፡ ይህ መፅሐፍ እንቁ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች ወይም ይህንን በመሳሰለ ስም ሊተራ ይችላል፡፡

ክሌር፡- ደግሞ "ንስሐ" የሚል ለየት ያሉ ፅሑፎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

ህዝቂኤል፡- ልክ ይህንን ርዕስ ስታዩ ኦ! እኔ ንስሐ ገብቻለሁ ብላችሁ እዛ ላይ አታቁሙ፡፡ ወይም "ኦ! እኔ የእግዚአብሔርን ፍቅር አግኝቻለሁ ስለዚህም ይህንን ማድረግ እችላለሁ" በማለት መፅሐፉ ምን ለማለት እንደፈለገ ሳትረዱ አትተዉት፡፡ መፅሐፉ በእርግጥ ምን ለማለት እንደፈለገ ለመረዳት ሞክሩ፡፡ እኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለማመድሁ ያለሁት ነገር ይህንን

በመሳሰሉ ትንንሽ መፅሐፎች ለምሳሌ ለጌታ ራሳችንን ለመስጠት የሚረዱ መፅሐፎች/devotional/ ላይ አንድ ቃል ሲመጣልኝ የማደርገው ነገር ቢኖር እሄድና በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያንን ምዕራፍ አውጥቼ ምን ሊለኝ እንደፈለገ አነባለሁ፡፡ ደግሞም ያነበብኩትን ክፍል በማጥበብ ወይም ክብደት በመስጠት የበለጠ ሙሉ እንዲሆን አደርጋለሁ፡፡ ትክክል አይደለም?

ክሌር፡- ትክክል ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ወደዚህ ውይይት ያመጣሁበት ምክንያት እኛን ከብዙ የውሸት ቃሎች ስለጠበቀን ነው፡፡ ይህንን መፅሐፍ እንከፍትና "ውሸት" እና "የስጋ ምኞት"፣ ቅናት እና ውሸት የሚል ሲወጣልን አሳሳች መናፍስቶች በነገሩ እንዳሉበት እናውቃለን፡፡

ህዝኤቄል፡- አዎን ይህ ደግሞ ከጥቆላ ሥራ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡

ክሌር፡- ስለዚህም ጌታ ራሱ ይህንን መጠቀማችን ትክክል እነደሆነና ችግር እንደሌለው፣ እንዳውም እንድንጠቀምበት እንደሚፈልግ ነግሮናል፡፡ ምክንያቱም አያችሁ ንጥቀት ከምሳጋና ቀን በፊት ይሆናል ብለው ያሰቡ ሰዎች ይህንን ዘዴ ቢጠቀሙ ኖሮ "ውሸት" የሚለው ይወጣላቸው ነበር፡፡ ስለዚህም አሳሳች መናፍስቶች  እንዳገኗቸውና እውነት ያልሆነ ነገሮችን ሲነግሯቸው እንደነበረ ይረዳሉ፡፡

ጌታ ምን ብሎ እንደነበር አሁን እንነግራችሁ፡፡ " ስለዚህ ጉዳይ ዲያቢሎስ በሌሎች አይምሮ ውስጥ ስለአስቀመጠው ነገር ግድ የለኝም፡፡ ነገር ግን ይህ ከተፈጥሮ በላይ እውቀትን መፈለግ ወይም ህፃንነት ነው፡፡ ትክክል አይደሉም፡፡ እና ደግሞ የውስጥ ፍላጎታቸው ከተፈጥሮ በላይ የሆነን እውቀት ለማግኘት ካላዘነበለ ምንም ችግር የለውም፡፡

" ይህንን ላብራራው፡፡ የምትፈልጉኝ እኔን ለመታዘዝ ከሆነና ለመንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚፈልግ ከፀለያችሁ ጌታ ይጠብቃችኋል፡፡ ነገር ግን መልስ የምትፈልጉት ደህንነት ከማጣት፣ ወይም የወደፊቱን ለመተንበይ፣ ምስጥራዊ እውቀትን ለማግኘት፣ ሌሎችን ለማስደነቅ ከሆነ ከተፈጥሮ በላይ የሆነን እውቀት ለማግኘት ጫፉ ላይ ናችሁ፡፡

ክሌር፡፡ ተጠንቀቁ! ስለዚህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነን እውቀት ለማግኘት ጫፉ ላይ ናችሁ፡፡ ዲያቢሎስ ደግሞ ለእያንዳንዱ ነገር ማስመሰል ይችልበታል፡፡ ስለዚህም ከጌታ ሬማ ወይም ቃል ማግኘት ህጋዊ ነው፡፡ እርግጠኞች የምንሆነው ሌላው ነገር ዲያቢሎስ ይህንን አስመስሎ ለክፉ እንደሚጠቀምበት ወይም ይህ ትክክል እንዳልሆነ በሰው አይምሮ ውስጥ ያስቀምጣል፡፡

ህዝቄኤል፡- በዚህ ላይ ለማለት የምፈልገው አንድ ነገር አለ፡፡ ብዙዎቻችን ወደ ጌታ ገና ስንመጣ መፅሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደምናጠና፣ ወይም አንድን ነገር ወይም ሌላውን እንዴት እንደምንሰራ አናውቅም ነበር፡፡ አንድ ወቅት ላይ ብቻ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ዝም ብለን ቃሉን ማንበብ ጀመርን፡፡ ታዲያ ያን ጊዜ አዲስ አማኞች ሆነን ሳለ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እርሱ በፈለገው መንገድ ይመራን እንደነበረ በጣም የሚደንቅ ነበር፡፡

አንዳንዶቻችን አይናችንን ጨፍነን በአንድ ገፅ ላይ ነበር ጣቶቻችን ተጣብቀው ይቀሩ የነበሩት፡፡ (አሁን ቢሆን ይህንን ላለማድረግ መጠንቀቅ አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ልትባሉ ትችላላችሁ "እግዚአብሔር ፍፁም አይፈልግህም") (ሳቅ በሳቅ)፡፡ ነገር ግን የሬማ መልዕክቶችን ከመፅሐፍ ቅዱስ፣ ወይም ከተስፋ ቃል መፅሐፍ/ Bible Promise/፣ ወይም ከጌታ

ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ከምንጠቀምበት መፅሐፍ/ devotional book/፣ ወይም ራሳችን ካዘጋጀነው የሬማ ካርድ ስናገኝ ምንድነው የምናደርጋቸው? እኛ ግን እናስቀምጣቸዋለን፡፡ ከዚህም የተነሳ ከብዙ ዓመታት በፊት የተዘጋጁ የሬማ ካርዶችን የያዙ ሳጥኖች አሉኝ፡፡ ስለዚህም ከእኔ ውጪ የሆነ ማረጋገጫ ስፈልግ በተደጋጋሚ የማደርገው ባለቤቴን ወይም ሌላ ሰው እንዲፀልዩልኝና ጌታ ቃል ከሰጣቸው እንዲያመጡልኝ እጠይቃቸዋለሁ፡፡ ምናልባት ጉዳዩ ምን እንደሆነ እንኳን ላልነግራቸው እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ራሳችን ወዳዘጋጀናቸው የቀኑ ዳቦ ማስቀመጫ ቅርጫቶች እሄዳለሁ . . .

ክሌር፡- አዎን ሁሉንም በኢንዴክስ ካርድ አስቀምጠናቸዋል፡፡

ህዝቄኤል- ታዲያ ወደ እርሷ ካርዶች ለመሄድ አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም የእርሷ ካርዶች እንዳንድ ጠንካራ፣ የስርዓት እርምጃ፣ ፆምና ከባድ ቃላት አለባቸው! ነገር ግን እርግጡን ለማወቅ ስፈልግ ወደ ጠንካራው ሳጥን እሄዳለሁ! (ሳቅ በሳቅ)፡፡ በዚህም ጊዜ በእርግጥም በፍቅር ተሞላና የለዘበና መልካም የሆነ መልእክት ይሰጠኛል፡፡ ነገር ግን ባላ ሦስት እግር መቀመጫ የሚቆመው በሦስት እግሮቹ አይደለም? ስለዚህ እኛም ለማረጋገጥ ሁለት ወይም ሦስት ምስክር ከቃሉ ያስፈልገናል፡፡

ክሌር፡- ማሰስ በሉት፡፡ ታውቃላችሁ! ልክ ባህር ላይ ስትሆኑ የት እንዳላችሁ ለማወቅ ትፈልጉና አንድ አቅጣጫ ተቋሚ ብታገኙ ሌላ ማረጋገጫ ትፈልጋላችሁ፡፡ ስለዚህም ሁለተኛው ግኝት ለማረጋጋጥ ማሰሪያ ይሆናችኋል፡፡ ጌታ " የውስጥ ፍላጎት የወደፊቱን ለመተበይ ከሆነ ይህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነን እውቀት ለማግኘት ጫፉ ላይ መድረስ ነው፡፡" የሚለውን መልዕክት ሲሰጠኝ ገና አንብቤ አልቸረስኩም፡፡ ታውቃላችሁ ይህ አይደለም መሆን ያለበት፡፡

ጌታ እንዲህ ነው ያለው . . ." የውስጣችሁ ፍላጎት ንፁህና ከራሳችሁ አጀንዳ ውጪ መሆን አለበት፡፡ ካህናቶቼና ነቢያቶች የእናንተ ባህል እንዲታወቅ ከማድረጉ በፊት መንፈስን መለየት የተለማመዱት በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር፡፡ ስለዚህም ሌሎች ነገሮች ሁሉ አልሰራ ሲል ከእኔ መረዳት እንዲኖራችሁ በቃሉ የተሰጡትን የተስፋ ቃሎችን የያዘውን መፅሐፍ/ the Bible Promises/ ወይም መፅሐፍ ቅዱስን እንድትጠቀሙ ድጋፌን እሰጣለሁ፡፡ ተስማሚ የሚሆነው ግን ምንም አጋንንት ሊገባበት ወይም ሊያስመስል በማይችልበት በውስጥ ነፍሳችሁ እውነቱ ሊሰማችሁ ሲችል ነው፡፡

"ይህንን አስታውሱ፡፡ ዲያቢሎስ የሚመለከተው ደካማ ጎናችሁን ነው፡፡ ታሪካችሁን ያውቃል ስለዚህም በዛ ይጠቀማል፡፡ ስለዚህም ማሳሳቱን ለማገጣጠም ቀላል ነው የሚሆነው፡፡ እንዳውም እናንተን ለማጥመጃ የሚጠቀምበት ምግብ ነው ልበል፡፡ ስለዚህም ራሳችሁን ካወቃችሁና የእኔን መንገድ ካወቃችሁ በእርሱ ወጥመድ ሳትጠመዱ አምልጣችሁ መሮጥ ትችላላችሁ፡፡

የትኛውንም ነገር ለመስራት የምትፈልጉት ሰዎችን ለማስደነቅና ለመሳብ ወይም ሌሎችን ደስ ለማሰኘት ከሆነ በቀላሉ ለመጠምዘዝ ደካማ ጎናችሁ ይሆናል፡፡ ማንኛውም ለራስ ፍላጎት የምታደርጉት እንቅስቃሴ ምንም ይሁን ምንም አጋንንቶችን የምትስቡ ዒላማ ትሆናላችሁ፡፡

"ሌሎችን ለመርዳት እንኳን በውስጣችሁ ያለ ፍላጎት መካከለኛ ካልሆነ በቀር ወይም እኔ የሰጠኋችሁ ተልዕኮ ካልሆነ በቀር በጠላት ኢላማ ውስጥ ነው የሚያስገባችሁ፡፡ በአጭሩ ማንኛውም ንፁህ ያለሆነ የውስጥ ፍላጎት፣ ይህም ሹመት ፍለጋ፣ አስፈላጊ ሰው ሆኖ ለመታየት፣ ልዩ ወይም አስፈላጊ ነገርን ለመስራትና ሌላውን ለመቆጣጠር፣ በሌሎች ላይ ልቆ ለመታየትና በሰዎች ላይ ጫና ፈጣሪ ለመሆን የሚደረጉ ምኞቶች ሁሉ ለኢጋንንታዊ ሥራዎች በሩን በሰፊው የሚከፍት ነው፡፡

ስለዚህም ደህንነታችሁ በጥሩ ሁኔታ ሊጠበቅ የሚችለው እኔን በመውደድና ለእኔ በመሰጠት ብቻና ብቻ እንዲሁም ወንድሞቻችሁን እንደራሳችሁ አድርጋችሁ በመውደድ ብቻ ነው፡፡

ክሌር፡- እነዚህን እንደ መመሪያ ነው የሰጠኝ፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን ብዙ ህመም አለ፡፡መለየት እጅግ አስቸጋሪ ነው ፡፡ ክፉና አጋንንት በከፍተኛ ፍጥነት ስለተሰራጩ እኛን ለማታለል በተከታታይ አዲስ መንገድን ለመቀየስ እየጣሩ ናቸው፡፡

ሰለዚህ በህይወታችሁ ኃጢያት ካለ፣ ያልተናዘዛችሁት ኃጢያት ካለ እንድትወድቁ ይፈቅዳል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ተጠቀማችሁ ወይም ለማመሳከር መፅሐፍ ቅዱስ አልተጠቀማችሁ እንድትወድቁ ይፈቅዳል፡፡ ስዚህም የውስጥ ፍላጎታችሁ ብቻ አይደለም ንፁህ መሆን ያለበት ነገር ግን ህይወታችሁም ንፁህ መሆን አለበት፡፡ ብዙ ጊዜ በጌታ ላይ ኃጢያት እንደሰራን አንገነዘብም፡፡ ለምሳሌ በትዕቢት ጉዳይ ላይ ወደ እኔ ሲመጣ ትዕቢት ይሆናል ብዬ የማልገምተው ነገር ትዕቢት እንደሆነ አመልክቶኛል፡፡

ህዝቄኤል፡- እስካሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሽፋን ውስጥ ሆነን የቆሰለው በሚገደልበት ጊዜ ስለ ጉዳዩ ለማንም ምንም አንናገርም ፡፡ እኛ ተጎጂዎች አይደለንም ስለዚህም አንዳችን ለአንዳችን ኃጢያታችንን አንናዘዝም፡፡ እንዲህም ስለሆነ ጥሩ ጓደኞች ብንሆን እንኳን አንዱ ሌላው ድክመቱን አያካፍልም፡፡ ለምን? ምክንያቱ ያ ጓደኛ ተብዬ ወደ ድህረ ገፅ በመሄድ በጥፊ የሚማታ ደብዳቤል ይፅፋል፡፡ ይህ ጉዳይ እኮ እናንተን አላደረጋችሁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሰዎች ስለእናንተ ሁኔታ ብዙ ያወራሉ፡፡ ታዲያ ይህ ነገር እናንተን ካልተመቻችሁና እነሱም የእናንተን ፈቃድ ካልጠየቁ ነገሩ በጣም ያበሳጫችኋል፡፡ እኛን በሚጎዳ መልኩ ይጠቀሙበታል ብለን ሳንፈራ አንዳችን ለአንዳችን ግልፅና እውነተኞች መሆን አለብን፡፡ ታውቃላችሁ መልሶ መማታት ዓይነት? ደግሞ ሰዎች ኃጢያታቸውን ለቄሶች ስለተናገሩ መጥፎ እንዳደረጉ እንቆጥራቸዋለን፡፡ ታውቃላችሁ አንድ ዓይነት ፍርሃት አለ፡፡ ሸክማችንን ለሌሎች ያለፍርሃት ማካፈል ካልቻልን . . ጠንቃቃ መሆን አለብን የሚል ነው፡፡

ክሌር፡- አዎን ይህ ሁሉንም ነገር ያጠቃልለዋል፡፡ መንፈስን በመለየት ዙሪያ የጌታን ልብ ለእናንተ በማካፈል ልናበረታታችሁ ፈለገን ነበር፡፡ እንዲሁም እርሱ በእውነት ሲናገረን ወይም የለመደ መንፈስን በመካከል ስናስገባ እንዴት ማረጋገጥ እንዳለብን ከእኛ ጋር ለብዙ ዓመታት ሲጠቀምበት የነበረውን አንዳንድ መመሪያዎችን ልንሰጣችሁም ጭምር ነው፡፡

ህዝቄኤል፡- ደግሞ መንፈስን ስለመለየት ምንም ጥያቄ ቢኖራችሁ ለመጠየቅ ወደ ኋላ አትበሉ፡፡ ማለቴ ማንም ቢሆን በደሴት ላይ የሚኖር የለም፡፡ይህንን እወቁ ወንድንም ሴትንም በማጠቃለል ነው ተናገርኩት(ሳቀ በሳቅ)፡፡ ደግሞ ሌሎች ስለ እናንተና ስለሁኔታዎች እንዲፀልዩላችሁ ጠይቁ፡፡ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ሁሉንም መንገር አይጠበቅባችሁም፡፡ አንዳንዴ እንዳውም ባትናገሩ ይመረጣል፡፡

ከሌር፡- ስለዚህ ትንሽ ደቂቃዎች ወስደን ለመለየት እኛ የምንጠቀምባቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች እናሳያችሁ፡፡ በመጀመሪያ ነገር ምንም ጥያቄ የሌለው መፅሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ማንኛውም እውነተኛ መፅሐፍ ቅዱስ ይሰራል፡፡ ነገር ግን መፅሐፉ ሲናገራችሁ የሚገባችሁና ቀላል በሆነ ቋንቋ የተፃፈ መሆን አለበት፡፡

አንዳንድ ጊዜ "በበረሃ ይኖሩ የነበሩ አባቶች መንገድ/The Ways of the Desert Fathers/ የሚለውን መፅሐፍ እጠቀማለሁ፡፡ ይህም የቆዩ ክርስቲያን አባቶች ጥበብ ነው፡፡ የቀደሙ ክርስቲያኖች ፀሎት መጋራት ማለት ነው፡፡

ሌላ ለመበረታታት የምጠቀምበት ደግሞ የላውሪ ቤቲ ጆነስ /Laurie Beth Jones/ መፅሐፍ ነው፡፡ ይህች ሴት ክርስቲያኖችን የሚያነቃቃ ብዙ መፅሐፎች አላት፡፡ እርሷ የምታደርገው ከጌታ ህይወት ምሳሌ በመውሰድ በአለንበት የአለም ሁኔታ እራሳችንን በተግባር እንዴት መኖር እንዳለብን ታሳየናለች፡፡

ሌላው ደግሞ የምወደው ሪክ ጆነር /Rick Joyner/ ነው፡፡ እናም አንዳንዴ ከመፅሐፎቹ በአንዱ ውስጥ ሬማን አገኛለሁ፡፡ ሁልጊዜ መፅሐፍ ቅዱስን ብቻ ከማንበብ አንዳንዴ ሰዎች የፃፉትን ማየትና የተረዱበትን አዲስ መንገድ መዳሰስ ጥሩ ነው፡፡ በዚህም ጊዜ በአዲስ ብርሃን ነገሮችን እንድትመለከቱ ይረዳችኋል፡፡

ሌላው ደግሞ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍ ነው/ The Bible Promise Book/፡፡ ይህንን ቅድም ሳወራላችሁ የነበረው ነው፡፡ ይህ ቀጥታ ከቃሉ የወጣ የተስፋ ቃሎች ናቸው፡፡ ልዩነቱ በርዕስ በርዕስ ተደርጎ መደራጀቱ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ፍሬያማነት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የወንድማማቾች ፍቅር፣ ውሸት፣ ቅናት፣ ከፍተኛ ጉጉት፣ የዘላለም ህይወት በሚል የተደራጀ ነው፡፡ በእውነት ለመናገር ይህ መፅሐፍ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ርዕሶች ተዘጋጀ መፅሐፍ ቅዱስ ስለሆነ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ በካርድ የምንጠቀመው ነው፡፡ ከካርድ መዝገቦቻችን አንዱ ይኸውና(ኢንዴክስ ካርድ በውስጡ ያለ ሳጥን)፡፡ ኦ! በጣም ትልቅ ነው! ካርድ እናዘጋጅና በተለያ ቀለም እንቀባዋለን፡፡ ደግሞ የተሰጠንን ምንም ነገር . . . በላዩ ላይ እንፅፍበታለን፡፡ ካርዶቹ ላይ ተፃፉት ከመፅሐፍ ቅዱስ የተገኙ ጥቅሶች፣ ጌታ በፀሎት ጊዜያችን የሰጠን የተስፋ ቃሎች፣ ወይም አንድ ሰው ያመጣልን ትንቢት ነው፡፡ ከዚያም እዚህ ውስጥ እናስቀምተዋለን፡፡ ታዲያ አንዳንድ ጊዜ ሲከፋንና ነገሮች የጨለሙ ሲመስለን፣ ከጌታ ጋር ያልተገናኘንና የራቅን ሲመስለን እንጠቀምበታለን፡፡ ለምን እንኳን ወደዚህ ሳጥን እንደምሄድ እንኳን ሳላውቀው ሄጄ ሶስት ካርዶችን አነሳለሁ፡፡ ታዲያ መንፈስ ቅዱስ ደብዳቤያችሁን እንዴት እንደሚያነብ በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ ማለቴ እርሱ በቃ እዛው ከእናንተ ጋር ነው፡፡ጌታን ደስ ለማሰኘት ነው የምትፈልጉት፡፡ ለመታዘዝ ነው የምትፈልጉት፡፡ ልትወዱትና ሙሉ ህይወታችሁን ልትሰጡት ነው እየሞከራችሁ ያላችሁት፡፡ ታዲያ አሣ እየጠየቃችሁት እባብ አይሰጣችሁም፡፡

ከጌታ ሰምተናል ብለው የሚናገሩ ሰዎች ያለባቸው ችግር ለሰሙት ነገር ከውጪ ማረጋገጫ የላቸውም፡፡ ምንም የሚደግፋቸው ነገር የላቸውም፡፡ አንዳንዶቹ ፓስተሮቻቸው ወይም ሌሎች ሰዎች መልክቱን እንደሚያረጋግጡላቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ በትክክል ባለቤቴና እኔ የምንጠቀምባቸውና ናቸው፡፡

ነገር ግን እንበል ባል ከሌላችሁና የምታምኑት ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሌለ የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍ የተስፋ ቃሎችን የያዘውን ትንሹን መፅሐፍ ወይም ራሳችሁ በቤታችሁ ያዘጋጃችሁት የተስፋ ቃሎችን መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ እነዚህ የምታዩአቸው እራሴ በቤቴ ያዘጋጀኋቸው የተለያዩ ጥቅሶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዱ እንዲህ ይላል. . ."ተራሮቼንም ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ፥ ጎዳኖቼም ከፍ ከፍ ይላሉ።" (ኢሳያስ 49፡ll)

ታውቃላችሁ እንደነዚህ ዓይነት የተዘጋጁ ጥቅሶችና የተስፋ ቃሎች ልትቋቋሙት የማትችሉት ችግር በገጠማችሁ ጊዜ እጅግ በጣም በማበርታት ተስፋ ያጭርባችኋል፡፡ በትክክለኛው መንገድ ላይና በትክክለኛው አቅጣጫ ላይ እየተጓዛችሁ እንደሆነ ያረጋግጥላችኋል፡፡

እኔ እንደማስበው ብዙ ሰዎች ይህንን የመለየት ዘዴ ቢጠቀሙ ብዙ ችግር ይገጥማቸዋል ብዬ አልገምትም፡፡ ጌታ ያሉበትን ሁኔታ  በመግለፅ ሊያሰላስሉት የሚችሉት ቃል በመስጠት በልጓሙ በቀላሉ ሊመልሳቸው ይችላል፡፡ ማረጋገጫን መጠቀም ድንቅ የሚሆንበት ምክንያት ዒላማን የሚመቱ መሆናቸው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመደነቅ "እኔ ብገልፀው ከዚህ በላይ ምንም ማለት እችላለሁ? ደግሞም ከመፅሐፉ ውስጥ ከሚገኙ ብዙ ገፆች ይህንን ሰጠኸኝ ለመስማትም የምፈልገው ይህ ነበር፡፡ ጌታ ሆይ አመሰግናለሁ" የምትሉበት ጊዜ አለ፡፡

ስለዚህ ሁላችሁም ጌታን ለመስማት እንድትገፉበትና ድምፁን እንድትሰሙ በዛም እንድትቀጥሉ አበረታታችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም በኮፕዩተር ለመፃፍ ችሎታን የምታገኙት በልምድ እንደሆነ ሁሉ የጌታን ድምፅ ለመስማትም ችሎታ የሚኖራችሁ መለማመድ ያስፍልጋችኋል፡፡ በልምድ የሚዳብሩ እንደነዚህ ዓይነት ችሎታዎች ደግሞ ጊዜን ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህም የጌታን ድምፅ ወዲያው ካልሰማችሁ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ዲያቢሎስ የሚፈልገው ተስፋ ቆርጣችሁ እንድትተዉት ነው፡፡ እናንተ ግን ይህንን በፍፁም ማድረግ የሌለባችሁ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ዲያቢሎስ ሰዎች በህይወታቸው የእግዚአብሔርን ጥርት ያለ ድምፅ እንዲሰሙ አይፈልግም፡፡ እርሱ የሚፈልገው ግራመጋባትን መዝራት ነው፡፡ ስለዚህም በፍፁም ተስፋ እንዳትቆርጡ፡፡

እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡

## 8.2. ኢየሱስ መንፈስን ስለ መለየት ያስተማረው ትምህርት

እ.ኢ.አ ዲሴምበር 12 ቀን 2014ዓ.ም

{Jesus teaches on desernemet}

*በቀድሞው ቪዲዮ ላይ ቃል የገባሁላችሁ መልዕክት ይኸውና፡፡ መልክቱን ስቀበል እንደተፈጠረው ሁኔታ መጠን እኔም ልሙላባችሁ፡፡ ባለፉት ጥቂት ቀናት ከጌታ ሳይሆን ከሰይጣን ድምፅን በመስማት ተከስሼ ነበር፡፡ ክሱም የሚያጠነጥረው የምሰማው መልዕክት ከጌታ ሳይሆን ከአጋንንት እንደሆነ የሚያስመስል ነበር፡፡ ይህም ግልፅ የሆነ ክስ ሳይሆን የረቀቀና በይፋ የወጣ ሳይሆን በጥያቄ ዓይነት መልክ የቀረበ ነበር፡፡*

ጌታም እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ «በፍፁም ዕረፍት ውስጥ እንድትሆ ኑ እፈልጋለሁ ልክ ልጅ በእናቱ እቅፍ ውስጥ እንደሚሆን፡፡»

*እኔም ጌታ በእውነት አንተ ነህ? አልኩት*

*በክርስትና ህይወት ሁሉ በዚህ የፍርሃት በሽታ ተጠቅቻለሁ፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት የመጣሁት ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም እንቅስቃሴ ወደ ክርስትና ህይወት መለወጥ ነበረብኝ፡፡ እምኑኝ በምድር ላይ የምፈልገው የመጨረሻው ነገር ጌታን ማዋራት መቻል ነበር፡፡ ይህ የነበረኝ ህይወት ነው ሁልጊዜ ልታለል እችላለው በሚል የፍርሀት ስሜት ውስጥ በመሆን በጣም ንቁ የሚያደርገኝ ፡፡*

*ወዲያው ማምለክና ማመስገን ስጀምር ያማረውን ኢየሱስን ከእኔ ጋር እየደነሰና ዓይኖቹ ብልጭ ድርግም ሲሉ አየሁት፡፡ መንፈሴ በውስጤ ዘለለ! ጌታ እንደሆነ አውቄያለሁ! እርሱም ፈገግ አለና እንደዚህ አለኝ፡-*

«አሁን እኔ መሆኔን መካድ አትችይም፣ ትችያለሽ?

አልችልም ፡፡ በእርግጥ እርሱ መሆኑን አሁን አውቄአለሁ፡፡ ለብዙ ሰዓታት አብረን ደነስን፡፡ ነገር ግን ሙዚቃው ስላሰለቸኝና በጣም ጩኸት ሲሆንብኝ አጥፍቼው በዝምታ ተቀመጥኩ፡፡ የቀን የመልዕክቴን ሳጥኔን በመክፈት የቀኑን ሬማ ካርድ ሳብኩና ማንበብ ጀመርኩ፡፡ እንዲህ ይላል 'የአዳኜ ፍቅር ኦ! እንዴት የሚደንቅ፣ ኦ! እንዴት ከአይምሮ በላይ የሆነ ነው፡፡'

*በነገራችን ላይ ሁላችሁም የቀን የሬማ መልዕክት ማስቀመጪያ ሳጥን እንዲኖራችሁ አበረታታለሁ፡፡ ይህም ልክ እንደ ዕለታዊ የዳቦ ሳጥን ወይም እንደ ኢንዴክስ ካርድ ሳጥን ሆኖ በውስጡ ኢንዴክስ ካርዶች ያሉበት ማለት ነው፡፡ ይህም ሊዳብር የሚችለው ጌታ የሚሰጣችውን የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል፣ የትንቢት ቃል፣ ቃል የገባላችሁን ለራሳችሁ ይሁን በነቢያቶች በኩል የሰጣችሁ የተስፋ ቃሎች በተለያዩ ካርዶች በመፃፍ ሳጥን ውስጥ አስቀምጡት፡፡ ከዚያም በጣም ከፍ ስትሉ፣ ስትደርቁ ፣ከጌታ ጋር መገናኘት ሲሳናችው እና ድምፁን መስማት ሲከብዳችው፣ «ጌታ ሆይ ወዴት ነህ?» ማለት ሲሰማችው ይህንን አድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ለመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ፣ ከዚያም የውሸት መናፍስቶችን በሬማ ሳጥኑ ላይ እንዳይሰራ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም እሰሩ፡፡ ከዚያም ከመልዕክት ሳጥን ውስጥ ሶስት ካርድ ውሰዱ፡፡ ካርዶቹንም በምታነቡ ጊዜ አሁን በምን ደረጃ ላይ ወይም ሁኔታ ላይ እንደምትገኙ እንድትገነዘቡ፣ እንዲሁም ካላችሁበት የዝቅታ ሥፍራ እንደሚያወጣችሁና ለዚህም ጌታን እንድታምኑት ይረዳችኋል፡፡*

*በእርግጥም በፊቴ በዚያ ነበር፡፡ በፈገግታም እንዲህ አለ* «ከሌር ካንቺ የምፈልገው ፍቅሬን እንድትቀበይኝ ብቻ ነው»

ማልቀስ ጀመረ «ፍቅሬን ለመቀበል ብዙ ጊዜ ፈጀብሽ፣ እባካሽ ወደዚያ አትግፊኝ፡፡ በነገራችን ላይ የተቀበልሻቸው እነዚያ መልዕክቶች ሁሉ እያንዳንዱ ከእኔ ነው፡፡ እያንዳንዱ»

*ጌታ ሆይ አሁንም ግን ስለ ኢራን የሰጠኸ መልዕክት ላይ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ ለምን ያንን መልዕክት ሰጠኸኝ?*

« ኦባማ ከመታወቁ በፊት እንዳውም ከመመረጡ በፊት አላሳየሁሽም?»

*አዎ ይህ ትክክል ነው፡፡*

እርሱ ከመመረጡ በፊት ህልምና ራዕይ አይቼ ነበር፡፡ ከሰባት አመት በፊት ገደማ ለመመረጥ ተቀባይነቱን ሲያገኝና ንግግር ሲያረግ ሳየው ወዲያው በህልሜ ውስጥ ጌታ ያሳየኝ ሰው መሆኑን ለየሁት፡፡

*ልክ በዚያን ጊዜ አንድ ድመቴ መጥታ ወደ ላይ እንዳነሳት መጮኽ ጀመረች፡፡ እናም አነሳኋትና እንዲመቻት አድርጌ እላዬ ላይ አስቀመጥኳት፡፡ ሳሻሻትም ምንም ሳታስቸግር ተቀመጠች፡፡*

«ታያለሽ ልክ እንደዚች ድመት እንድትሆኚ ነው የምፈልገው ፡፡ ልክ ላቅፍሽ ስመጣ በእኔ እቅፍ ውስጥ ገብተሽ ጥልቅ የሆነ እምነት ውስጥ እንድትገቢ ነው፡፡ በዚህም ዕረፍት አግኝተሽ አንቺ ከእኔ እንድትቀበዬ የምመኘውን ፍቅር በአንቺ ላይ ለማፍሰስ ነው፡፡ ይህም ፍቅር የአንቺን ቁስል ሁሉ አክሞ በተራሮች ላይ እንዳለ ብርሃን አንፀባሪቂ አድርጎ የሚለውጥና ሌሎችን ለመፈወስ ኃይል ያለው ነው ፡፡ በአንቺና በፍጥረታቶቼ ሁሉ ፍፁም በሆነ መልኩ ተቀባይነትን እንዳገኝ እንዴት እመኛለሁ፡፡ ነገር ግን እነርሱ ስህተት ላለመፈፀምና ከትክክለኛው መንገድ ወጥቻለሁ ብሎ በማሰብ በፍርሃት ተሞልተዋል፡፡ ይህም ከአምላካቸው ይልቅ የጨለማውን መንፈስ በመስማት ነው፡፡ እኔን በበለጠ ቢሰሙኝ እንዴት በወደድኩ ነበር፡፡»

*ግን እኮ ጌታ ሆይ መጭበርበርን ትፈቅዳለህ፡፡*

«በእያንዳንዱ ጊዜ ፈቅጄያለሁ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ከዛም ነፃ አውጥቼሻለሁ፡፡ ደግሞም ለምን እንደፈቀድኩና እንደገናም እንድትታደሺ አድርጌያለሁ፡፡ አላረኩም?

አዎ ጌታዬ አድርገሃል፡፡ ነገር ግን እኮ ለዚህም ነው በጣም ጥንቁቅ የሆንኩት ፡፡ ደግሞም እኔ እንዳይ ከፈቀድከው በላይ ብዙ መኩራራቶች አሉብኝ ብዬ እጠራጠራለሁ፡፡ ስለዚህም ነው እጭበረበራለሁ ብዬ የምፈራው፡፡

«የኔ ፍቅር በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም የምከራከረው ነገር የለኝም»

ኦ! ሰዎች ብቻ . . . ቢገለኝም እንኳን እወደው ይሆን?

"ለራስሽ መልካም እንድትሆኚ ለመቁሰልም ቢሆን ፈቃደኛ መሆን አለብሽ፡፡ እኔ ሳላስተካክልሽ ሩቅ እንድትሄጂ እንደማላደርግሽ ማመን አለብሽ፡፡ የሚሸፍንሽ ደግሞ አድርጌልሻለሁ፡፡"

*ይህ የተደረገልኝ መሸፈኛ ባለቤቴ መሆን አለበት። ስለዚህ መሸፈኛዬ እጅግ እጠነቀቃለሁ።ያገኘኋቸውን ነገሮች በሙሉ ከጌታ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን በዚህ መሸፈኛዬ ነው በጥንቃቄ የማረጋግጠው። ምክንያቱም የመጨረሻ ማድረግ የማልፈልገው ነገር ቢኖር ራሴን ለመጭበርበር አሳልፎ መስጠትና ሌሎች እንዲጭበረበሩ ማድረግን ነው።*

«ክሌር ስለዚህም የተጣራ መረጃ ለመውሰድ እኔን ማመን ትችያለሽ። ይህም ቸርነትሽና ትህትናሽ እስከተጠበቀና እያደገ እስከመጣ ድረስ ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ቸርነት ማድረግን መተው ወይም ችላ ማለት የለብሽም»

*እዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው ነገር ቢኖር በሆነ ምክንያት በመሸፈኛ ችሁ መለየት የማትደገፉ ከሆነ 'ከመሸፈኛችሁ በላይ ራሳችሁን ከፍ እንዳደረጋችሁ ይቆጠራል'። ይህንን ቀደም ባሉት ቪዲዮቼን ተመልከታችሁ ከሆነ በዛ ላይ የጠቀስኩት ይመስለኛል። ነገር ግን መሸፈኛ ከሌላችሁ በሬማ ካርድ ማስቀመጫ ሳጥኑ/ Rhema Box/ መጠቀም ትችላላችሁ። እንዲሁም ትንሽዬዋን የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፅሐፍን/ The Bible Promises Book/ መጠቀም ትችላላችሁ። እናም ለመንፈስ ቅዱስ በመፀለይ «ኢያዋራሁት ያለሁት ጌታን ነው ወይንስ አይደለም?» ብላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ ።*

*ሰዎች ይህንን ልንገራችሁ ይህንን እኔ በየቀኑ አደርገዋለሁ ። በቃሉ ላይ ስለተፃፈው በዕጣ የመጠቀም ጉዳይ ልትስቁና ልትተቹኝ ትችላላችሁ። እኔ ግን ምንም አይጨንቀኝም። ብትስቁም ይህ መንገድ ለእኔ ይሰራልኛል። የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል የሚለውን መፅሐፍ/ The Bible Promise Book/ ልጠቀም ስል የውሸት መንፈስ ተነቃቅቶ መስራት ይጀምራል። አንዳንድ ወቅቶች አሉ ጌታ ሊፈትነኝ አንድ እርምጃ የሄደበት። ስለዚህም የውሸት መናፍስቶችን ከመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፉ ላይ ማሰር ነበረብኝ። ነገር ግን በኋላ እውነቱን ገለጠልኝ። እርሱ የሬማ ሳጥኑን/ Rhema Box/፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍን/ The Bible Promises/ እንዲሁም ከቃሉ እንደሚጠቀም ነገረኝ።*

«ለለጋስነት የማትሰለቺ ወይም ከተሰጠሽ መሸፈኛ በላይ መሆን የለብሽም። ስርዓት ባለው መንገድ ወደ መስመር ልመልስሽ በቀስታ ወደታች ጎትቼሽ ነበር። እርምት ስሰጥሽ ከኩራት የተነሳ ከሚገባው በላይ ከተናደድሽ ምንም ማድረግ አልችልም። ቶሎም ቢሆን ወይም ቆይቶ ተስፋ በመቁረጥ ሳይሆን ወይም በአመፃ ወደ መቀበል ትመጫለሽ። በተጨማሪ በህሊናሽ ውስጥ በትንሽ ድምፅ አንድ ነገር ትክክል እንዳልሆነ የሚነግርሽስ? ህሊናሽን እየሰማሽው ነው? አዎ እየሰማሽው ነበር። ነገር ግን ያንን ትንሽ ድምፅ ሰምተሽ ለመታዘዝ የፈጠንሽ ሁኚ። ህሊናሽን ንፁህ አድርጊ። ህሊናችሽን ሁልጊዜ ንፁህ ካደረግሽ መንፈስን ለመለየት ስጋትሽ ትንሽ ነው የሚሆነው። ችግር የሚገጥምሽ ባልሽ ከሰጠሽ ማስጠንቀቂያ ውጪ እልኸኛ በመሆንና ጥርስሽን በመንከስ በራስሽ መንገድ መሄድ ስትፈልጊ ነው። ነገር ግን ከባዱን ነገር እንድትማሪ ማድረግ ስላለብኝ ነው።»

«የኔ ፍቅር ይህ በሂደት የሚገኝ ትምህርት ነው። ይህ የረቀቀው መንፈስን የመለየት ገፅታ ነው። የራሳሽን ሐሳብ በበለጠ እየተውሽ በመጣሽና የራስሽን ፍላጎትና ፈቃድ እየተቃወምሽ በመጣሽ ቁጥር መንፈስን መለየት ቀላል እየሆነልሽ ይመጣል። ነገር ግን ለአሁን እኔ በእርግጥ ይገፍልሃለሁ። እናም በክንዶቼ እቅፍ መሆንሽ፣ የፍቅርሽን እንባ ማየቴ፣ ልብሽ ቃሌን ለመስማትና ለመታዘዝ ዝግጁ መሆኑ እንዴት ድንቅ ነገር ነው? ይህ ሁሉ ለእኔ እንዴት ውብና ለልቤ ደስታን የሚሰጥ ነው። እባክሽ በእነዚህ ነገሮች ተስፋ አትቁረጪ። እባካሽ በፍፁም ተስፋ አትቁረጪ። አንቺ ለእኔ ውድ ነሽ። አ! በአንቺ በጣም ነው የምፅናናው። ክሌር በአንቺ ፍቅር ታላቅ መፅናናትን አገኛለሁ! እናም እንደምታዪው በፈጠርኩት ፍጥረት እየተሰቃየሁ ነው። ልቤ የሙሽሮቼን ሁሉ ፍቅር ይፈልጋል።»

## 8.3. በኃጢያት ስትወድቁ . . . የሚለጠፉባችሁ ጭራቆች

እ.አ.አ ዲሰምበር 12 ቀን 2014 ዓ.ም

{Tag Along Monsters, When You Fall...}

ዛሬ ምሽት የማካፍላችሁ እኔ የፃፍኩትን መልዕክት ነው፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ ከጌታ የተቀበልኩትን መልዕክት አስተላልፍላችኋለሁ፡፡ ይህ የፃፍኩት መልዕክት ከራሴ ገጠመኝና ልምድ በመነሳት የፃፍኩት ነው፡፡ ርዕሱንም የሚለጠፉ ጭራቆች ብዬዋለሁ፡፡

ዲያቢሎሶች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው የሚጣበቁ ጭራቆች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ቃል ሳያወጣ እንኳን እርሱን የምንሰማበት ለስላሳ የሆነን ስፍራ በነፍሳችን ውስጥ አድርጓል፡፡ ይህም ከሆድ ዕቃችን አካባቢ ሲሆን በዚህም ሥፍራ ምሪትን ይሰጠናል፡፡ እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ "ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ። መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ።" ኢሳያስ 30፡21

ነገር ግን ውስጥ ውስጡን የሚበሉን ጠላቶች፣ አረመኔዎችና ወንድሞችን የሚከሱ በቋሚነት በመንገዳችን ላይ እኛን ለመቃወም የሚጠቀሙበት ነው፡፡ እግዚአብሔርን በሐሳብ፣ በድርጊት፣ ወይም በሐሳብ ድርጊት ስናሳዝን በውስጣችን እናውቃለን፡፡ ይህም መንፈሳዊ ጤንነት እንዲኖረን ከእርሱ የተሰጠን ስጦታ ነው፡፡ እኛ ግን ስህተታችንን ስንረዳ ምንድነው የምናደርገው? ጥሩ እኔ ለብዙ ዓመታት ሮጬ መደበቅ እንደነበረ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡ ከጌታ ጋር ከ25 እስከ 30 ዓመት አብሬ ተጉዣለሁ፡፡ እናም ካበላሸሁ በኋላ ለብዙ ዓመታት እንዴት እየሮጥኩና እየተደበቅሁ እንደነበረ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡

በአጠቃላይ የምናደርገው ነገር ልክ አዳምና ሔዋን እንዳደረጉት ከእርሱ ለመሸሸግና ከእርሱ ለመሸሽ እንሞክራለን፡፡ ክፉዎቹ ደግሞ እኛ የሰራነው ትክክል አይደለም ብለን የጠረጠርነውን ወይም ያሰብነውን ነገር እንድናደርግ ያበረታቱናል፡፡እንዲህም ይሉናል፡፡ "አይ ይህ እኮ ምንም አይደለም፣ ይህንን ማድረግ ትችላለህ፡፡ ይህንን በማድረግህ እግዚአብሔር ቅር አይሰኝብህም፡፡" ወይም ደግሞ እርሱ ይቅር ይልሃል፣ ይህ እኮ በጣም ትንሽ ነገር ነው" ይሉናል፡፡

አንዴ ነገሩን ካደረግን ወዲያ ደግሞ ዲያቢሎሶቹ ይመጡና " አየህ አንተ በምንም ነገር ጥሩ አይደለህም፡፡ ለአንድ ሰዓት እንኳን ታማኝ ልትሆን አትችልም፡፡ አሁን እግዚአብሔር ይናደድብሃል፣ ፀሎትህንም አይሰማም! አንተ ለእርሱ የተገባህ አይደለህም፡፡ ስለዚህም ሌሎችን ማገልገልህን ብታቆም ይሻላል!" እያሉ ይነዘንዙሃል፡፡

በዚህ ጊዜ ተዘርግተው የሚጠብቁንን የእርሱን እጆች ትተን ራሳችንን ለመሸፈን እንሮጣለን፡፡ እርሱ ግን በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ እየተመለከተን ያለው በርህራሄና በምህረት ነው፡፡ ይህንን ውድቀት የፈቀደው ምናልባት ትሁት እንድንሆንና በእምነትና በትህትና እንድናድግ ነው፡፡ በዚህም እጆቹን ዘርግቶ ሊያቅፈንና ሊስመን፣ ሊያጠነክረንና ልናጣ በማይገባ ፍቅሩ ሊያበረታን ነው፡፡ የሚያፈቅረን እግዚአብሔር ስለሆነ ነው፡፡ ፍቅር ደግሞ የእርሱ ባህርይ ነው፡፡ እርሱ ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህም ማፍቀር እንጂ ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ እኛንም የፈጠረን ከእርሱ ጋር ህብረት እንድናደርግ ነው፡፡ የኛን አብሮነት ይወደዋል፡፡

እርሱ በፍቅሩ እንዲያጥለቀልቀን እንደ ምድራዊ አባት ጥሩ መሆናችንን ማስመስከር የለብንም፡፡ ታዲያ ለዚህ ምን ማድረግ አለብን? የእርሱን ምህረት ለማግኘትና ሰላማችንን ለማፋጠን የራሳችንን ሐሳብ ቶሎ ትተን ወደ እርሱ መመለስ አለብን፡፡

እነዚህ የሚጣበቁ ትናንሽ አስቀያሚዎች ይህንን ያውቃሉ፡፡ ስለዚህም የበደለኛነት መርዛቸውን በመርጨት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ሽባ ለማድረግ በብርቱ ይሰራሉ፡፡ ከትንንሽ ጭራቆቹ የበለጠ ብልህ ለመሆን መማር አለብን፡፡ ይህም ስንወድቅ ቀጥታ ወደ ጌታ በመቅረብ ድካማችንን፣ ኃጢያታችንን መናዘዝና በሙሉ ትህትና ይቅርታ መጠየቅ አለብን፡፡ ይህንንም መፈፀም ያለበን ወዲያው ነው፡፡ እየቆየን በሄድን ቁጥር ግን ብዙ ጭራቆች በጀርባችን ላይ በመጠራቀም እንዴት የማንረባና መጥፎ እንደሆንን ይነዘንዙናል፡፡

እነዚህ ጭራቆች ክርስቲያኖች የበደለኝነት ስሜት ተሰምቷቸው ሲደበቁ ማየት ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡ በአንፃሩ ግን እነርሱው ናቸው በድብቅ የሚወቅሱንና ራሳችንን እንድንጠላ የሚደርጉት፡፡ አ! ሰዎች ይህንን ሽባ የሚያደርግ ውሸት ወሳኝ በሆነ መንገድ ካላስወገድነው በቀር እጅግ የሚያጠላ ነገር ነው፡፡

እነዚህ የሚጣበቁ ጭራቆች ከጌታ ጋር ያለንን ህብረት ሽባ እንዲያደርጉት አንፍቀድላቸው፡፡ እርሱ ወዲያው ይቅር እንደሚለን በማወቅና በመታመን ቀጥታ ፊታችንን ወደ እርሱ በማዞር ከእኛ ጋር የማይፈለጉ ተጓዦችን ሽባ እናደርጋቸው፡፡ እኛን ለቀው ወደ ሌላ አዲስ ሥፍራ መሄድ አለባቸው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ኃጢያታችን ያመጣውን ጉዳት ስንጠግን የኃጢያታችን ውጤት በእኛ ላይ ይቆያል፡፡ ይህንንም በታዛዥነት ልብና በፍፁም ትህትና ከመልካሙ እረኛችን እጅ መቀበል አለብን፡፡ እርሱ ክፉ ያመጣውን ሁሉ ወደ መልካም ይቀይረዋል፡፡

ለመማር ፈቃደኛ፣ የዋህና የእርሱ ፍቅሩ እንደሚያቅፋችሁ ታመኑ፡፡ በዚህ ጊዜ ከጌታችሁ ሊለዮአችሁ በትጋት ሲሰሩ የነበሩትን እነዚህን ትናናሽ ጭራቆች ታበሳጫላችሁ ከዚያም አልፎ በኃዘን ውስጥ ትጥላላችሁ፡፡ <u>"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?"</u> ሮሜ 8፡35

ስለዚህ ለማጠቃለል ያህል ለማለት የፈለኩት በአለም ላይ ለዲያቢሎሶች፣ ለአጋንንቶችና ለጨለማው መንግስት የሚያስፈሯቸው ሰዎች መንፈስን የሚለዩና ከክርስቶስ ጋር የቅርብ ህብረት ወይም የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው ለእነርሱ በጣም በጣም የሚያስፈራ ሰው ነው፡፡ ስለዚህም ከጌታ ጋር የቅርበት ግንኙነት እንዳኖራችሁና እውነቱን ከውሸት መለየት እንዳትችሉ  የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

አትድከሙ በርቱ በያዛችሁት ነገር ቀጥሉ፡፡ ደግሞም ጌታ መሃሪና ሁልጊዜ ስትወድቁ ለማንሳት ዝግጁ እንደሆነ እወቁ፡፡ ሰዎች! ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ እኔ አሁን እዚህ ባልተገኘሁም ነበር!

ጌታ ይባርካችሁ፡፡ ደግሞም ጥበብና የመለየትን ፀጋ ያብዛላችሁ፡፡

## 8. 4. ሚስጥራዊ ንጥቀትና የሦስት ቀናት የጨለማ ጊዜ የሚለውን መልዕክትየመለየት ሂደት

እ.አ.አ. ዲሴምበር 14 ቀን 2014 ዓ.ም

{Secret Rapture, Three Days of Darkness, Our Discernment Process}

የተመረጡት ከንጥቀት በፊት የሚሆነውን የሦስት ቀናት ጨለማ ይጠብቃሉ ስለሚለው ትንቢት ምን ታስቢያለሽ ተብዬ ብዙ ጊዜ ተጠይቄያለሁ፡፡ ይህ ትንቢት እንደሚለው "የጌታ ሙሽራ ከመነጠቋ በፊት የሦስት ቀናት ጨለማ ይሆናል፡፡ በእነዚህም ሶስት የጨለማ ቀናት እነዚህ የተመረጡት ተነጥቀው ለሶስት ቀን ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በከበረ አካል ወደ ምድር ይመለሳሉ" የሚል ነው፡፡ ከእነዚህ ሴቶቹ አንዷ ከእነርሱ ጋር እንድቀላቀል ጠይቃኝ ነበር፡፡ በእውነት ልንገራችሁና ወዲያው መልስ ከመስጠቴ በፊት ስለዚህ ነገር ጌታን ጠይቄ ነበር፡፡ ምክንያቱም በራሴ ፍላጎት መልስ መስጠት ስላልፈለግሁ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ የራሳችን ፍላጎት በጣም ኃይለኛ ሲሆን ጌታ የሚናገረውን በትክክል ላንሰማው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የእርሱ ድምፅ በጣም ዝግ ያለና ለስላሳ ስለሆነ ነው፡፡ መካድ የማልችለው ነገር ቢኖር ይህንን ትንቢት ስሰማ በጣም ጥሩ መስሎ ነበር የተሰማኝ፡፡ ምክንያቱም ንጥቀት ከመሆኑ በፊት የተሰጠኝን ተልዕኮ ለመጨረስ የቀረኝ ጊዜ ትንሽ ነው ብዬ በማሰብ ትልቅ ውጥረት ውስጥ ስለነበርኩ ነው፡፡ በተጨማሪም በታላቁ የመከራ ዘመን በሚደረገው ነፍሳትን የመሰብሰብ ታላቅ አገልግሎት ተካፋይ ለመሆን ወደ ምድር ተመልሰን የመምጣት ዕድል መስጠቱ ፍፁም የሆነውን ህልሜን የሚያሳካ ነው ብዬ በማሰቤ ነው፡፡ አሁን በዚህ ሰዓት እንኳን ይህ መልዕክት በውስጤ ለሚጋጩ ለሁሉም ነገሮቼ መልስ የሚሰጥና የታዘዝኩትን ሳልጨርስ እንዳልሄድ የሚያደርግ ስለሆነ በጣም ጥሩ ነው ልበላችሁ፡፡

ጌታ ግን እንዴት እንደሆንኩ ያውቃል፡፡ ከዚህ መልዕክት ጋር ከተያያዘች አንዲት ሴት ጋር በሌላ ጉዳይ ላይ ጌታ ምክር ሲሰጠኝ እንዲህ ብሎኛል፡፡ እርሱ ያለውን ከመናገሬ በፊት ግን ነገሩን ለመለየት ምን ዓይነት የመለየት ደረጃዎች እንደወሰድኩ ልግለፅላችሁ፡፡ ምስጥራዊ መነጠቅ የሚለውን መልዕክት ለመጀመሪያ ጊዜ ስሰማ ወዲያው መንፈሴን ፈተሸኩ፡፡ በውስጠኛው ማንነቴ ወይም በጥልቅ አንጀቴ አንድ ነገር ልክ እንዳልሆነ ተሰማኝ፡፡ ይህም ሆኖ ግን የኔን ስሜት ያዝ በማድረግ ጌታ የሚሰጠኝን ማብራርያ መስማት ፈለግሁ፡፡ በዚህ ጊዜ በመንፈሴ የበለጠ በማረጋገጥ እዛውጋ እንዳቆም አደረገኝ፡፡ በዛን ጊዜ መንፈሳዊ ሽፋን ለሆነኝ ለባሌ ነገርኩት፡፡ የእርሱም የወዲያው ምላሹ እንደ እኔው ነበር፡፡ አንድ ነገር ልክ አይደለም አለኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ትንሽ ተስፋ ቆርጬ እንደነበር አልደብቃችሁም፡፡ ምክንያቱም ይህ የተባለው መልዕክት በምድር ልፈፅመው የተሰጠኝን ተልዕኮ እንድፈፅም ያደርገኝ ስለነበር ነው፡፡

የሚቀጥለው ያደረግነው ነገር ባለቤቴ ህዝቄኤል ከመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች ማረጋገጫ ከመንፈስ ቅዱስ ለማግኘት በመፀለይና አሳሳች መናፍስቶችን በማሰር ሦስት ጊዜ መፅሐፉን ከፈተ፡፡

በመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስ የመራውና የተሰጠው ንባብ ውሸት ወደሚለው ገፅ ነበር፡፡ እንዲህ ይነበባል "ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም በሐሰትም የሚናገር ይጠፋል።" (ምሳሌ 19፡9)

እዚህጋ አንድ ነገር ልናገር፡፡ እኔ ማንንም በውሸት እየኮነንኩ አይደለም፡፡ ነገር ግን የተሰጣቸሁ የትንቢት ስጦታ ምን ያህል ጠንካራ እንደነበር ግድ አይሰጠኝም፡፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው ፍፁምና ከስህተት ውጪ፡፡ እኛ ሁላችንም ስህተት

እንሰራለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ የውሸት መናፍስቶች ይጣበቃሉ፡፡ ከጌታ ጋር ፍፁም፣ጥሩና ተገቢ መግባባት አድርጋችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሃል ግን ትንሽ ክፍተት ይፈጠርና ጌታ የራሱ ምክንያት በሆነ ነገር ለእዛ አጋንንት እውነት ያለሆነ ነገር እንዲጨምር ይፈቅድለታል። ጌታ ይህንን ለምን እንደሚፈቅድ እንኳን ለመናገር አልደፍርም፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ብዙ የተለያዩ ምክንያቶች ስላሉ ነው። ሁሉም ምክንያቶች ግን ለነፍሳችን ጥሩ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ የዋሹት የእግዚአብሔር ባርያዎች አይደሉም፡፡ ስለዚህ እባካችሁ እከሌ ሐሰተኛ ነብይ ነው፣ ወይም ይዋሻል በሚል ማጠቃለያ ሰውን አትክሰሱ፡፡ የሚቀጥለው የተሰጠው ማረጋገጫ ደግሞ ቅናት በሚል ርዕስ ስር ነበር፡፡ የተሰጠው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲህ የሚል ነው፡፡ "ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና።" ያዕቆብ 3፡16

እዚህጋ ጥቂት ጊዜ ወስጄ መናገር የምፈልገው ነገር አለኝ። እኔ እንደማስበው ከሆነ አንድ ትንቢት በምንሰማ ጊዜ በምንም ዓይነት ቢሆን ስለዛ ሰው የውስጥ ፍላጎት መፍረድ የለብንም፡፡ የሰውዬው የውስጥ ፍላጎት ምን እንደሆነ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይህ የእርሱ ሥራ ነው፡፡ የእርሱን ሥልጣን በመውሰድ ያንን ነገር ማድረግ ትክክል አይደለም፡፡ እኔ የማምነው ይህንን ነው፡፡ ማን ያውቃል የግል ፍላጎቱ ከየት እንደሆነ? ምናልባትስ መንፈስ ቅዱስ እኛን ለማገኘትና ለመናገር የግል ፍላጎቱን እንዲፈጥን አድርጎስ እንደሆነ? በሌላ አንፃር ደግሞ ይህ ነገር ከአጋንንት እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ትንቢቱ የሚያሳስት ከሆነ ትንቢቱን የሰጠው ሰው የግል ምኞቱና የግል ፍላጎት ያለበት ነው፡፡ ያ የግል ፍላጎት ነው ግራ መጋባትንና መከፋፈልን የሚፈጥረው፡፡ እያንዳንዱ የምናልፍበት ነገር ሁሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎ ላናገኘው እንችላለን፡፡ ጌታ እየጠራን ያለው ምናልባት የግል ፍላጎታችንን ትኩረት እንድንሰጥበት ነው፡፡ ታዲያ ማድረግ ያለብን ነገር ቁጭ በማለት ጊዜ ወስደን ለመለየት/discern/ መሞከር ነው፡፡ እናንተ የምታውቁትን ያህል አድርጋችሁ ሌላውን መተው ብቻ ነው ያለባችሁ፡፡ ሰውን ለመክሰስና ለማውገዝ አትሂዱ፡፡ ደግሞም ሃይለኛ አትሁኑ፡፡ እናንተ ማየት ያለባችሁ እናንተን ለለውጥ ሊያፈጥናችሁ የመጣውን ነገር ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የተሰጠውን መልዕክት በግል ምኞት ወይም በቅናት ተመልክተነው ከሆነ ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ቀይ መብራት ነው፡፡

የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎችን ስለያዘው መፅሐፍ ደጋግሜ ያወራሁበት ምክንያት እጅግ ቀላል ነው፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ የተከፋፈለው በይዘት አንፃር ነው፡፡ እንዲህም በመሆኑ ከመፅሐፍ ቅዱስ አንድ ገፅ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከሚናገራችሁ በበለጠ በዚህ መፅሐፍ በኩል የሚናገራችሁን ለመለየት ቀላል ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የመፅሐፉ የህትመት ዓይነትና መጠን በገለፃችሁት ሁለቱ ገፆች የተፃፉትን ስታነቡ መንፈስ ቅዱስ የሚናገራችሁን በቀላሉ እንዳይገባችሁና መልዕክቱን የተምታታ ሊያደርግ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ የዚህ መፅሐፍ ጥሩ ጎኑ የተከፋፈለው በርዕስና በክፋይ መከፋፈሉ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን እንዲመራችሁ በፀሎት ስትጠይቁት መፅሐፍ ቅዱሳችሁን ግልጥ ስታደርጉት ከምታገኙት ሁለቱ ገፆች ይልቅ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፅሐፍን ግልጥ ስታደርጉት ባሉት ገፆች ላይ ተከታታይነት ያለው መልስ ታገኛላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ መልሳችሁን ለመየት ቀላል ይሆንላችኋል፡፡ ለዚህ ነው ይህንን መፅሐፍ ለመጠቀም እጅግ የምንወደው፡፡ በዚህ መፅሐፍ ስንጠቀም 30 ዓመታት ሆኖናል፡፡ በእነዚህም አመታቶች ውስጥ ራሴን በተመለከተ ምሪትን በመስጠት ረገድ እጅግ ጠቅሞኛል፡፡ እኛ የሚሰማን ህይወታችን የተቀመጠው ጌታ በሚፈልገን ሥፍራ እንደሆነ ነው፡፡ አዎን ብዙ መማር ያለብን ነገር መኖሩ እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን የሚሰማን በትክክለኛው ቦታና በትክክለኛው ጊዜ ላይ እንደሆንን ነው፡፡ የሚደንቀው ነገር እንደዚህ ዓይነት ሰላም ማግኘት በምንም ነገር ሊለካ የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለመለየት አገልግሎት መፅሐፍ ቅዱስ እንጠቀማለን፡፡ ብዙ ጊዜ ይህንን የምንጠቀመው በመጨረሻው የውሳኔ ወቅት ነው፡፡ ለምሳሌ ከያዕቆብ መልዕክት ላይ ቃሉን እንወስድና ቃሉ ምን እንደሚል በደንብ በማጥናት ካለንበት ሁኔታ ጋር ያለውን ተያያዥነት እናገናዝበዋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቃሉን ብቻ ወስደን በማሰላሰል መንፈስ ቅዱስ ስለ ሁኔታው ብዙ ያስረዳናል፡፡ ለመለየት በምናደርገው ጥረት እነዚህን ውጪያዊ ማረጋገጫዎችን ሁሉ እንጠቀማለን፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ውጪያዊ ምስክሮችና ሲሆኑ እንደ ሁለተኛ ወይም እንደ ሶስተኛ ምስክሮች አድርገን ልንጠራቸው እንችላለን፡፡ ለማረጋገጥ ሁለት ወይም ሦስት የሚታመኑ ሰዎችን ካላገኛችሁ ለብቻችሁ ሆናችሁ አንድን ያልተረጋገጠ ነገር መወሰን አደጋ ነው፡፡ በህይወታችን የሚካሄደውን ነገር በትክክል ለመረዳት፣ በተለይም በዚህ አስቸጋሪ፣ አንዱ ሌላውን በሚከዳበትና ለሞት አሳልፎ በሚሰጣጥበት ዘመን በመንፈስ በደንብ መተዋወቅ፣ የመንፈስን መንገድ መረዳትና መንፈስ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ማወቅ አለብን፡፡  በመንፈስም የትኛው ከእውነት የትኛው ከውሸት እንደሆነ መረዳት መቻል አለብን፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው የተሰጠን የንባብ ክፍል ትህትና በሚለው ስር ነበር፡፡

"ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል መንፈሱን የሚያዋርድ ግን ክብርን ይቀበላል።" ምሳሌ 29፡23

ይህ ማጠቃለያው ነበር፡፡ ይህንን በሁለት መንገድ ልናየው እንችላለን፡፡ አንዱ "ምናልባት እኔ እንዲህ ዓይነቱን ልዩ የሆነንና ለየት ያለ ነገር ለመቀበል ትዕቢተኛ ሆኛለሁ፡፡ ምናልባት ዝም ብዬ ኩሩ ሆኛለሁ፡፡ አንዳንድ ሰዎች "ጌታ ለእኔ ካልተናገረኝ እውነት አይደለም" ሊሉ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት መልዕክቶች የሚያመለክቱት ቀጥታ ለእኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሌላ አቅጣጫ ትዕቢቱ በሌላ ወገን ያለውን ክፍል ሊመለከት ይችላል፡፡ እኛ ይህንን ስለማናውቅ ሌሎች በእኛ ላይ እንደሚያስቀምጡብን በሌሎች ላይ የውስጥ ፍላጎታቸው እንዲህ ነው ብለን ማለት አንፈልግም፡፡ እነዚህ የተቀናበሩ ሦስት ምክንያቶች ትንቢቱ እውነት እንደሆነ አያሳዩም፡፡ በአስደናቂ ሁኔታ ወደታች ጥለውታል፡፡

ለማጠቃለል፣ በህዝቁኤል ያለው መንፈስ የጥንቃቄ ምልክት ሰጠንና ሦስት ንባቦችን አንድናነብ ሆንን፡፡ እናም በሦስት ንባቦች አረጋገጠልን፡፡

ከዚያም በኋላ የኔ አፍቃሪው ኢየሱስ መጣና ስለሁኔታው ምን ማድረግ እንዳለብኝ ነገረኝ፡፡ ይህንን መልዕክት ያመጣችሁ ሴት ጌታን በሙሉ ልቧ በጣም የምትወድ ነገር ግን በመታለል ተስባ ነው፡፡ ጌታ በጣም ረጋ ባለ ሁኔታ አንድ ነገር አለኝ . . . "አሳስተዋቸው ነው፡፡ የሚኖረው አንድ ንጥቀት ብቻ ነው፡፡"

ከዚያ በኋላ የሚናገረኝ ጌታ መሆኑን ለማረጋገጥ የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሉን መፅሐፍ በመግለጥ ጌታ ራሱ እንደሚናገረን በሦስት ማረጋገጫዎች አረጋገጥሁ፡፡ በተጨማሪም አብራኝ እየፀለየች ስላለች አንዲት ሴት መልዕክት ነግሮኝ መልዕክቱ እውነት ሆኖ ተገኘ፡፡ ስለዚህም በዛ ወቅት ከእርሱ ጋር የነበረኝ ንግግር ሁሉ አረጋገጠልኝ፡፡

በዚህ ላይ አፅኖት መስጠት እፈልጋለሁ፡፡ አጋንንቶች በዓለም ላይ ያለውን እውቀት ሁሉ የማወቅ እድል አላቸው፡፡ ይህ እንድትረዱት ለማድረግ የምነግራችሁ ትንሽ ነገር ነው፡፡ ይህንን ደግሞ መናገር የሚገባኝ ይመስለኛል፡፡ ይህ ርዕስ ምንም

ሊያደናግራችሁ አይገባም፡፡ ነገር ግን እንድታስታውሱት ያህል ነው፡፡ ይህቺ ሴት ያለችበትን ሁኔታ ያያሉ፡፡ ታዲያ ለእኔ ያንን ቢነግሩኝ ኖሮ ይህ ታዲያ ከመለኮታዊ መገለጥ ወይም እውቀት የመጣ ሳይሆን እዛ የነበር አንድ አካል ግንዛቤውን ለእኔ አስተላልፎኝ ነው ማለት ነው፡፡ እንዳው አንድ ነገር ስለሰማችሁ ብቻ ለምሳሌ "እከሌ ወደ አንቺ ቤት እየመጣ ነው  በ30 ደቂቃ ውስጥ አንቺጋ ይደርሳል" ከእግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም፡፡ ኢጋንንቶች ወደ እናንተ ቤት ማን እየመጣ እንደሆነ በደንብ ያያሉ፡፡

እውነተኛ የትንቢት እውቀት አንድ ነገር ሳያስቡት፣ ማስረጃ ሳይኖር፣ ምንም የተመለከትነው ነገር ሳይኖርና ጉዳዩ ከመሆኑ በፊት ማወቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ መርከቧ ከተሰባበረች ወዲያ ከመርከቧ ውስጥ አንዲትም ነፍስ እንደማትጠፋ ተናገረ (ሐዋርያት 27፡22)፡፡ የነበሩበት ሁኔታ ነፍስ ሊጠፋ የሚችልበት ኢጋጣሚው እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ማንም አይጠፋም ብሎ መናገሩ ከመለኮት የሆነ እውቀት ነበር፡፡

አሁን ደግሞ ትንቢቱን ራሱን ማየት እፈልጋለሁ፡፡ እያንዳንዱ ነገሩን መመርመር ያለባችሁ በራሱ ሁኔታ ነው፡፡ በመጀመሪያ እስቲ የሦስት ቀን ጨለማ የሚለውን እንመልከት፡፡ እኔ ከዚህ ትንቢት ጋር ባለኝ ልምድ መሰረት ፍሬ ነገር አለው፡፡ትንቢቱ የመነጨው ከመልካም ካቶሊክ ሰው ነበር፡፡ ይህንን ትንቢት የማገናኘው የእውቀት፣ የፈውስና የታምራት ስጦታ ካለውና ህይወቱም መልካምና ማንም ሊደርስበት የማይችል የሰው ነበር፡፡ በተጨማሪም ይህንን ትንቢት ከ100 አመታት በፊት የተነበዩ ሌሎችም ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህም ሰዎች የተቀደሰ ህይወት እንደነበራቸው ተዘግቧል፡፡ ትንቢቱ ደግሞ ከቅድስና ህይወት የተገኘ መሆኑ በእውነትም አስፈላጊ ነው፡፡ እነሱ ያቀረቡት ሐተታ ከታላቁ መከራ በኋላ ለሦስት ቀናት ጨለማ እንደሚሆን በዚህም ጊዜ ኢጋንንቶች ሁሉ ከገሃነም ወደ ምድር እንደሚለቀቁ፣ ውጪ የሚገኝና የሚጠብቀው የጌታ መልአክ የሌለው ማንኛውም ሰው በቅፅበት እንደሚሞት ነው፡፡ የሚሰጠው ትዕዛዝ ማንም ሰው በቤቱ ላይ ማህተም እንዲያስደርግና ለምንም ነገር ለማንም ወደ ውጪ እንዳይወጣ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ታዲያ ኢጋንንቶች ወደውስጥ እንድታስገቧቸው የዘመዶቻችሁን ድምፅ በማስመሰል በሩ እንዲከፈትላቸው ይጮሃሉ፡፡ በመጨረሻውም ጌታ ከመላዕክቶቹ ጋር በመምጣት ሁሉንም ሰው በማሰር አንድም ሰው ሳይቀር ሁሉንም ያጠፋል፡፡ ይህም ምድርን ከክፉ ለማንፃት የሚደረግ መሰረት ነው፡፡ ይህ እውነት ነው ወይስ ውሸት?  በአንድም ይሁን በሌላ መንፈሴን ሊያሳምነው አልቻለም፡፡ ለመደገፍ ጠንከር ያለ ዝንባሌ የለኝም፡፡ በእውነት ከሆነ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ምንጩ መልካም ስለሆነ ትንቢቱ በዚያ መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡

የኔ ማጠቃለያ ይህንን ማወቅ ካለብኝ ጌታ  ያስታውሰኝና የሚቀረውን ተጨማሪ ደግሞ ለእኔ አስፈላጊ ከሆነ ይነግረኛል ነው፡፡ ለእኛ የማይጠቅም ከሆነ ግን እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ወዲህና ወዲያ ስንሮጥ እንዲሁ ጊዜያችንን እናባክናለን፡፡

የትንቢቱን እንቅስቃሴ ስንፈትሸው ደግሞ " ዕብሪትና ግብዝነት አለበት? ብለን ስንጠይቅ ይህ ትንቢት የሚናገረው ልዩ "ጥሪ ስላላቸው" ነው፡፡ በእርግጥም ይህ ትንቢት ለዕብሪትና ለግብዝነት ቦታን ይሰጣል፡፡ የሚቀጥለው የምንጠይቀው ጥያቄ ደግሞ የትንቢቱ የውስጥ ፍላጎቱና ከክስተቱ የሚገኘው ፍሬ ምንድው? የሚል ነው፡፡ ከክስተቱ የሚገኘው ፍሬ እጅግ መልካም እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም የሚያወራው ከንጥቀት በፊት ጌታን በማገልገል ስለሚሰበሰበው መከር ነው፡፡ይህ ለእኔ መልካምና የላቀ ተግባር ነው፡፡  ይህንን በቃሉ እናገኛለን? የዚህ ተምሳሌት በዘፀአትና በሌላ ሥፍራ እናገኛለን፡፡  "ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል?" ይህ ማየት ያለብን የመጨረሻውና እጅግ አስፈላጊው ክፍል ነው፡፡ እዚህ

ላይ ነው ትንቢቱ መስፈርቱን ለማሟላት የሚያዳግተው፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ስለ ንጥቀት በተፃፈ በየትኛውም ክፍል ላይ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገር ክፍል የለም፡፡

በመሆኑም ስለዚህ ትንቢት  የኔ ማጠቃለያ እውሸት እንደሆነ ነው፡፡  ይህንን ካልኩ በኋላ ላስታውሳችሁ የምፈልገው አንድ ነገር አንድም ፍፁም ሰው እንደሌለ ነው፡፡ እኔ ፍፁም አይደለሁም፡፡ እኛ ሁላችንም ብንሆን ለመታለል ክፍት ነን፡፡ ለመታለል ክፍት አይደለሁም ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ . . .  በቋሚነት በትክክል ከሆነ መልካም፡፡

ውድ ቤተሰቦች አስተማማኝ በሆነው በጌታ ልብ ውስጥ ትንሽ በመሆነ እንቆይ፡፡ በማንም ላይ ቢሆን ስህተትን ወይም ክስን አንፈልግ፡፡ ከሌሎች ይልቅ እኛ የበለጠ የምናውቅ አድርገን ራሳችንን አንቁጠር፡፡ አይኖቻችንንና ጆሮዎቻችንን በኢየሱስ ላይ በመጣል መልስ ለማግኘት ወደ እርሱ እንጩህ፡፡ አንድን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን መመርመርና መንፈሱን መፈተን ምንም ችግር የለበትም፡፡ ትንቢትን ወይም የእምነትን ትክክለኛነት መመርመር ምንም ችግር የለበትም፡፡ይህ ሌሎችን መንቀፍ አይደለም፡፡ ይህ ብልህና አስተዋይ መሆን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ደጋግመን ማድረግ ያለብን ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ስህተት ሲሰራ ስህተት የሰሩትን ማውገዝ የለብንም፡፡ ያ በፍፁም አስፈላጊ ያልሆነና ጌታን የሚጎዳ ነገር ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት አድራጎት ያንን ሰው ብቻ ሳይሆን ጌታንም ጭምር የሚጎዳ ነው፡፡

ይህ የእርሱ አካል ስለሆነ ነገሮችን ሁሉ ለህፃናት እንደምናደርገው ዓይነት ጥንቃቄ ነው ማድረግ ያለብን፡፡ ማንንም ተስፋ ማስቆረጥ ወይም ማቁሰል አትፈልጉ፡፡ ደግሞም ጌታ ትክክለኛውን መንገድ ስለሚያደርግ እንድንታለል አይፈቅድም ብለን የምናምን ከሆነ ይህም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ብዙ ኢጋንንቶች በዓለም ዙሪያ ተሰራጭተዋል፡፡ በጣም ብልጥ ስለሆኑ የተመረጡትን እንኳን ለማሳት ይሞክራሉ፡፡

እንደሚመስለኝ ከሆነ ራሳችንን ዝቅ ካደረግን፣ ለመማር ዝግጁ ከሆንንና በራሳችን እውቀት የማንደገፍ ከሆነ ጌታ ለብዙ ጊዜ በስህተት እንድንመራና እንድንሰቃይ አይተወንም፡፡ እውነተኛ ልብ ካለንና በእርግጥም የምንፈልገው እውነትንና እውነትን ብቻ ከሆነ ውሎ አድሮ ወደ እውነቱ እንደርሳለን፡፡ ነገር ግን እኛ ለምንመርጠው ሐሳብ ለመጋደል ከሆነና ሌሎቹን ሐሳቦች በሙሉ የምንቃወም ከሆነ ከአንድ ነገር ጋር ተጣብቀናል  ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የተጣበቅንበት ሐሳብ ከእውነት አስበልጠነዋል ማለት ነው፡፡ ይህ  ደግሞ መልካም ያልሆነ ነገር ነው፡፡

ለማጠቃለል ከዚህ ጋር የሚስማማ ከመፅሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ <u>"በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን እግዚአብሔርን ፍራ፥ ከክፉትም ራቅ፡፡ይህም ለሥጋህ ፈውስ ይሆንልሃል፥ ለአጥንትህም ጠገን። . . . ልጄ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፥ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር።እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።</u>"(ምሳሌ 3፡6-12)

ጌታ በሁላችን እጅግ ደስ ይለዋል፡፡ በተለይም እርሱን ለማገልገል ራሳቸውን አሳለፈው በሰጡት እጅግ ይደሰታል፡፡ ትንቢትን ስትሰሙ መመልከት ያለባችሁ በዛ ብርሃን ነው፡፡ በመልካም የውስጥ ፍላጎት ትንቢት ሲመጣ ጌታን እንደሚወዱና በሙሉ ልባቸውና በሙሉ ህይወታቸው ጌታን ለማገልገል እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ስህተት ልንሰራ እንችላለን ነገር ግን እንደዛም ሆኖ አንዱ ሌላውን ማበረታታት አለበት፡፡ "ምንም አይደለም፡፡ እኔም በየቀኑ ስህተትን እሰራለሁ" ማለት መቻል አለብን፡፡

ዋናው ቁም ነገር እንደዚህ ዓይነት ዝንባሌ ከሌለን በትዕቢት ውስጥ ነን ማለት ነው ፡፡ ትዕቢት ካለብን ደግሞ ጌታ ጥሩ አድርገን የምንወድቅበትን መንገድ ያዘጋጅልናል፡፡ የእርሱን ሽፋን ወይም ጥበቃ በማንሳት አጋንንቶች ስህተት እንድንሰራ እንዲያደርጉ ይፈቅዳል፡፡ እውነቱን መቀበል ያለብን ከእርሱ መሆኑ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ለዚህ ነው የማስተካከያ እርምጃ የሚወስደው፡፡ እኛን ወይም ሌላ ሰውን ለማረም በሚደረገውም ሂደት በጣም ገሮች፣ አፍቃሪዎች፣ደጎችና ነገሮችን መረዳት የምንልችል መሆን አለብን፡፡ በዛ ሰው ቦታ ብንሆን እኛም ያንኑ ማድረጋችን የማይቀር ነውና፡፡

ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ፡

## 8. 5. በፀሎት ጊዜ የምትሰሟቸውን ሦስት ድምፆችን መለየት

እ.አ.አ. ዲሴምበር 20 ቀን 2014 ዓ.ም

{Discerning between the three voices you hear in prayer}

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የጌታን ድምፅ ለመስማትና በእርግጥም የተናገረኝ እርሱ እንደሆነ ለመለየት የተማርኳቸውን ሦስት ነገሮች ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ርዕሱንም ሦስቱ የመንፈስ ድምፆች ብዬዋለሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማትና በመታዘዝ እርሱን ለማስደሰት ለሚፈልጉ ነፍሶች የእርሱን ድምፅ ብቻ መስማት ቢሆንላቸውና በእርግጥም የሚናገራቸው ኢየሱስ መሆኑን በእርግጥ ቢያውቁ ህይወት እጅግ ቀላል ይሆንላቸው ነበር፡፡

እኔ በክርስትና ዘመኔ ሁሉ በፀሎት ጊዜዬ በቋሚነት በመንፈሴ የምሰማቸው ከሦስት የተለያዩ ምንጮች የሚመጡ  ሦስት ድምፆችን ነው፡፡ ከአይምሮዬ የሚመጣ የራሴ ድምፅ፣ ይህ ድምፅ የሚመስለው "እኛ ከራሳችን ጋር እንደምናወራ" ዓይነት ነው፡፡ ይህ በየቀኑ በውስጣችን ያለ የሐሳብ ንግግርና ጨዋታ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታን ኮስተር ብለን ስናዳምጠው ሊነግረን የሚፈልገው እኛ ለመስማት የፈለግነውን ነው ፡፡

ሁለተኛው ድምፅ ደግሞ የአጋንንት ድምፅ ነው፡፡ ይህ ድምፅ የሚመስለው ወዳጅ፣ ምክንያታዊ፣ አሳማኝ፣ ከእኛ ሐሳብና ፍላጎት ጋር በጣም የሚስማማ ነው፡፡ የሚነግረን እኛ ለመስማት የምንፈልገውን ወይም ስሜት የሚሰጠውን ነገር ነው፡፡ በሌላ ጊዜያት ደግሞ እኛን ወይም ሌሎችን ሰዎችን የሚከስ ነው፡፡ ይህም በሰው ላይ እንድንፈርድና አጋንንቶች በእኛ ላይ እንዲሰለጥኑ በር ለማስከፈት ነው፡፡ በመዋሸት ማድረግ የፈለጉት ነገር ካልተሳካላቸው ስልት በመቀየር እኛን ተስፋ ወደ ማስቆረጥ ስልት ይዞራሉ፡፡

ሦስተኛው ድምፅ ደግሞ የጌታ ድምፅ ነው፡፡ ይህም ድምፅ የወዳጅ፣ ምክንያታዊ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የራሳችን የሚመስለን ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አይምሮአችንን በእርሱ ሐሳብ ሁልጊዜ ስለሚያድሰው ነው፡፡ የእርሱ መመሪያ ለስለስ ያለና ገር ሲሆን በሌሎች ላይ እንድንፈርድ አያነሳሳንም፡፡ እንዳውም የሚያበረታታን እርሱ እኛን እንደቻለን እንድንችላቸው ነው፡፡ ስለዚህ ስንፀልይና በመንፈስ ስንሆን የምንሰማቸውን የሦስት ድምፆች ፀባይ በትንሹ ይህንን ይመስላል፡፡

አሁን ደግሞ የማካፍላችሁ ጌታን እንዴት ማድመጥ እንደጀመርኩ ነው፡፡ ሁሉም ነገር የጀመረው መፅሔቴን መፃፍ ስጀምር ነው፡፡ በመጀመሪያ በልቤ ያለውን፣ ስሜቶቼን፣ የራሴን ፍላጎት ሁሉ እፅፍና ጌታ እንዲመልስልኝ እጠብቃለሁ፡፡ በመጀመሪ ይህ አሰራር ጥሩ መስሎ ታይቶ ነበር፡፡ ነገር ግን በኋላ እርስ በርሱ የሚቃረን መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ እንዲሁም ይሆናል የተባሉ ነገሮች ሳይሆኑ መቅረት ጀመሩ፡፡ ይህ ደግሞ ቀይ መብራት ነው!!!

ለዚህ ነው የሰማሁትን ሁሉ መፃፍ እንደሌለብኝና መለየት ያለብኝ፡፡ በጣም ዘልቄ ወደ ውስጥ መግባት አለብኝ፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል . . . "መንፈስን ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ መርምሩ" ፩ኛ ዮሐንስ 4፡1

እሺ፣ ታዲያ እንዴት አድርገን ነው የምንመረምረው? ይህንን ማድረግ የምንችለው በደንብ በመስማትና የሰማነውን ነገር ደግሞ ዝንባሌውንና ባህርዩን በማድመጥ ነው፡፡ ከላይ እንደተናገርኩት የመጀመሪያው ድምፅ እኛ ከራሳችን ጋር የምናወራ የሚመስል ሆኖ ልክ እንደ እግዚአብሔር ንጉሳዊና በሥልጣን የሚናገር ዓይነት ነው ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በጣም ወዳጅ የሚመስል፣ ነገሮችን በምክንያት የሚያቀርብ፣ የሚያሳምን ዓይነት ነው፡፡ ይህ የአጋንንት ድምፅ ነው፡፡ ሦስተኛው የጌታ ድምፅ ሲሆን እርሱም የወዳጅ ድምፅና ምክንታዊ ነው፡፡ ነገር ግን ከአጋንንት ድምፅ የሚለየው እርሱ ለስላሳና ገር፣ በሌሎች ላይ እንድንፈርድ የሚያነሳሳን አይደለም፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ አጋንንቶች በእርግጥ ብልጥ ናቸው፡፡ ጌታን ለመምሰል ሲሉ ሌሎች ላይ እንድትፈርዱ ላያነሳሱአችሁ ይችላሉ፡፡ የጌታንና የእነርሱን ድምፅ ለመለየት እንዲያስቸግራችሁ ትንሽ ከበድ ያደርጉባችኋል፡፡ ነገር ግን አንድ አስደሳችና ልዩ ስፍራ በመንፈሳችን ውስጥ አለ፡፡ ይህም የሚገነው ከሆድ ዕቃችን ከፍ ብሎ ነው፡፡ በዚህ ክፍል በቃ ጌታ እንደሆነ ታውቃላችሁ፣ ጌታ መሆኑን እንዲሁ ታውቃላችሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ እኔ ከተጣበኩበት ጉዳይ ላይ ከእርሱ ጋር ስነጋገር በእውነት ከእርሱ ጋር እየተነጋገርኩ እንደሆነ በድፍረት ለመናገር ያስቸግረኛል፡፡ ሰዎች "ጌታን የምሰማው በልቤ ነው" ይላሉ፡፡ ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንመልከት፡፡ <u>የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?</u> ኤርሚያስ 17፡9 በልባችን ያለ ሁሉ ሁልጊዜ የተቀደሰ፣ ትክክልና የእግዚአብሔር ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህም የሚያሳስት ነው!!

ስለዚህም በጌታ ገና ህፃን በነበርኩ ጊዜ እርስ በርሱ የሚቃረን ይህ ሐሳብ በተለይም እኔ ጌታ እስካወጣኝ ጊዜ ድረስ ለ12 ዓመታት በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ ስለነበርኩ ደህንነት እንዳይሰማኝና እንድደነግጥ ባደረገኝ ነበር፡፡ የመጀመሪያዎቹን 33 ዓመታት የህይወቴ ዘመኔን አመሰቃቅዬው ስለነበር ከዚያ በኋላ ያለውን ህይወቴን ጌታ በተናገረኝ ላይ ብቻ መመስረት እፈልግ ነበር፡፡ "ኮኮቤን እየተከተልኩ" መኖር እጅግ ሰልችቶኝና አሞኝ ነበር፡፡ ይህንን ልንገራችሁ ጌታን ለመታዘዝና ለመከተል ዝግጁ ነበርኩ፡፡

ገና በመጀመሪያ ስድን የጌታን ድምፅ ለመስማት የመጀመሪያ ልምምዴ የነበረው በቃሉ ውስጥ ነበር፡፡ አንድ ትልቅ የቤተሰብ መፅሐፍ ቅዱስ ይህም "ለእኔ አዲስ" የነበረ መፅሐፍ ሲሆን በመፀለይ ሦስት ጊዜ ስከፍተው የወጣልኝን ንባብ ምንጊዜም አልረሳውም፡፡ እነዚህ ንባቦች ተልዕኮዬን የሚገልፁ መሆናቸውን ያለኝ ግንዛቤ ትንሽ ነበር፡፡ እንደዚህ አይነት ንባብ ይገጥመኛል ብዬ አስቤም አላውቅም፡፡ የመጀመሪያው ሙሴና የሚቃጠለው ቋጥኝ ነበር፡፡ <u>ከሚቃጠለው ቋጥኝ ውስጥ ድምፅን እንድትሰማ አደረግሁ</u> ይላል፡፡ ሁለተኛው ንባብ የአስቴር የፆምና የፀሎት ታሪክ ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ የኤርሚያስ ጥሪ ሲሆን ይህም ጌታ መስተካከል ያለባቸውን ያላቸው ነገሮች ብሎ ያሳየኝና ኤርሚያስ ለማስተካከልና ለማበረታታት እንዲናገር የተሰጠው ነው፡፡

ስለዚህም በእውነቱ ከሆነ ጌታ የእያንዳንዳችንን ህይወት በቃሉ መሰረት ይመራናል፡፡ ስለዚህም ቀጥታ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቃሉን መገለጥ መፈለግ የተገባ ነው፡፡ እስካሁንም ድረስ እነዚያ የተቀበልኳቸው ቃሎች ተልዕኮዬን ይገልፁልኛል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር እግዚአብሔር የመፅሐፍ ቅዱሱን ትክክለኛ

ገፅ ይከፍትልናል ብለን ማመን ብቻ ነው፡፡ እንደ ህፃን ዓይነት እምነት ማለት ነው፡፡ ለእኛ ግን እንዲሁ በቀላሉ አይሆንልንም፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም ነገር በጭንቅላት የምንሰራና የምንቆጣጠር ስለሆንን ነው፡፡ እኛ የያዝነውንና የምንቆጣጠረውን ነገር ሁሉ በመተው ለሌላ ትክክል ለሆነ ነገር ራሳችንን ክፍት ማድረግ እጅግ የሚያስፈራና ከእኛ ውጪ የሆነ ነገር ነው፡፡

ነገር ግን መልቀቅ ሁሉንም ነገር በመተው ልክ እንደ 3 ዓመት ህፃን ልጅ የአባታችንን እጅ እንደ መያዝ ወይም አንድ ድክ ድክ የሚል ህፃን የጌታን እጅ ይዞ ከእርሱ ጋር ዝም ብሎ እንደሚጓዝ ነው፡፡ ይህ ህፃን ወዴት ነው የምንሄደው? ምንድነው የምናደርገው? መቼ ነው ወደቤት የምንመለሰው? በማለት ደህንነቱን ለመጠበቅ በማሰብ ይህንን ሁሉ የጭንቅላት ጂምናስቲክ አይሰራም፡፡ ህፃኑ የሚያደርገው ነገር ዝም ብሎ የጌታን እጅ ይዞ መጓዝ ብቻ ነው፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስንም ማረጋገጫንም መጠቀም ልክ እንደዚህ መሆን ነው፡፡

እሺ አሁን ስለ አንድ ርዕስ የሚናገሩ ሦስት ግልፅ የሆኑ መልዕክቶች እንደ ምሳሌ ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ፡፡ እነዚህንም መልዕክቶች በፀሎት ጊዜያችሁ የምትሰሚቸውና ጌታ ነው የተናገረኝ ብላችሁ በማመን የምትፅፏቸው ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያው</u>፡- መዘመር በምጀምር ጊዜ ኃይለኛ ድምፅ እንዲኖረኝ ፈለግሁ፡፡ በምፀልይ ጊዜ ጌታን እፈለግሁ እያለሁ፣ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ. . . " በድምፅሽ ላይ ብትሰሪ ድምፅሽ ኃይል ያገኛል፡፡"

<u>ሁለተኛ ድምፅ</u>፡- ድምፅሽ ከዛች ከምታደንቂያት ዘማሪ የበለጠ ኃይል ያለው ይሆናል፡፡ እርሷ በጣም ጥሩ ትዘምራለች፡፡ ነገር ግን የአንቺ ደግሞ እጅግ የላቀ ነው፡፡ ቀን ከሌሊት ብትሰሪ እዛ ትደርሻለሽ፡፡

<u>ሦስተኛው ድምፅ</u>፡- ሌሎቹ ዘማሪዎች የራሳቸው የሆ ውበት እንዳላቸው ሁሉ የአንቺም ድምፅ ለራስሽ የተለየ ነው፡፡ የሌሎቹን ድምፃውያን አትኮርጂ፡፡ በቋሚነት ስሪና በጊዜው በራስሽ መንገድ ታብቢያለሽ፡፡

እሺ እዚህጋ ትንሽ ጥያቄ ልጠይቅና የትኛው ይመስላችኋል የጌታ ንግግር?

1. "በድምፅሽ ላይ ስሪና ኃይል ያገኛል፡፡"
2. "የአንቺ ድምፅ የላቀ ነው፡፡ ቀንና ሌሊት ስሪና ያሰብሽበት ትደርሻለሽ"
3. "የአንቺ ድምፅ ልዩ ነው፡፡ በራስሽ ልዩነት ታብቢያለሽ"

የመጀመሪያው፣ ኃይል ያለው ድምፅ እንዲኖረኝ ከዚያ ሐሳብ ጋር ተጣብቄያለሁ፡፡ ያ ደግሞ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር ነው፡፡ቀይ መብራት!! ከምንም ነገር ጋር ከተጣበቃችሁ፣ እራሳችሁን ምትነግሩት ምናልባት ያንኑ ነው፡፡ ይህንን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ እንድመረምር በመንፈሴ ተሰምቶኛል፡፡

እሺ ሁለተኛው ድምፅ ለግብዝነት እያዘጋጀኝ ነው፡፡ ሌላ ዘማሪን ይነቅፋል ደግሞም ይፈርዳል፡፡ እንዲሁም ከአቅሜ በላይ ሌሊትና ቀን እንድሰራ ይመራኛል፡፡ ይህ ምናልባትም ድምፄን ሊጎዳ የሚችል ተግባር ነው፡፡

ሦስተኛው ድምፅ ደግሞ የኔን ፍላጎት የሚቃረን ነው፡፡ ነገር ግን ራሴን እንድሆን የሚያበረታታ ነው፡፡

ብዙ ጊዜያቶች ካለፉ በኋላ ድምፄ በኃይል መውጣት የኔ የድምፅ መንገድ እንዳልሆነ ገባኝ፡፡ ለዝማሬ ለእኔ በተፈጥሮ የተሰጠኝ እንደዚያ ዓይነት አይደለም፡፡ ይህ ብቻ አይደም እንድዘምር ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠኝ ዝማሬም ረጋ ያለና ለስላሳ ነው፡፡ በኋላም የተረዳሁት እራሴን "ወደፊት ኃይል ያለው ድምፅ ይኖርሻል" እያልኩት እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ ለመስማት የፈለግሁት ያንን በመሁኑና ከዚህ ሐሳብ ጋር በመጣበቄ ነው፡፡

ስለዚህም ከብዙ ዓመታት ውድቀት በኋላ ከእኔ ጋር በተጣበቀ ጉዳይ ላይ አንዱንም ቃል ማመን እንደማልችል ተረዳሁ፡፡ ወይም ዝም ብላችሁ የምትሰሙትን ማንኛውንም ነገር ማመን አትችሉም ልበል፡፡ ቃሉ እንደሚል መለየት መቻል አለባችሁ፡፡

ጌታን አምልከን በፊቱ ፀጥ ብለን ለመቀመጥና ለማድመጥ ጊዜ በሰጠን ጊዜ ሦስት የተለያዩ ድምፆችን ለመስማት እንደምንችል አጋጣሚው እንዳለ ማወቅ አለብን፡፡ ነገር ግን ከዚያ ውስጥ አንዱ ብቻ ነው የጌታ ድምፅ፡፡ ነገር ግን ዝም ብላችሁ የሰማችሁትን ድምፆች ሁሉ ሳትለዩ ከፃፋችሁ የራሳችሁን የሥጋ ፍላጎት ወይም የአጋንንትን የፍርድ ምሪት በመከተል መጥፎ ውጤት ላይ ትደርሳላችሁ፡፡ በመሰረቱ እነርሱ የሚያዘጋጁችሁ ለውድቀት ነው፡፡ ምክንያቱም በምትፈርዱ ጊዜ ከጌታ ጥበቃ ወይም ሽፋን ውጪ እንደምትወጡና እነርሱም በእናንተ ላይ ለመሰልጠን በር እንደሚከፈትላቸው ስለሚያውቁ ነው፡፡

ነገር ግን ጌታ ሲናገራችሁ በግልፅ ስትለዩ ከሶስት አማራጮች በላይ ስትሆኑና "ይህ ጌታ ነው፣ በመንፈሴ እርሱ መሆኑን ተረድቻለሁ፣ ይህ ከጠላት ሊሆን የሚችልበት ምንም ምልክት የለም" የምትሉበት ደረጃ ላይ ስትደርሱ፣ጌታ እንደሚናገራችሁ በግልፅ መለየት ስትጀምሩ፣ አለም ሁሉ እናንተን ለመቃወም ሊነሳ ይችላል፡፡ በጉሮሮዬ መታመም የተነሳ ለአንድ ወር ያህል ድምፄ ተበላሽቶ ወይም የትም ቦታ ለመዘመር ስፍራ ባጣና ባልዘምር ምንም ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም ለድምፄ ቃልን የሰጠኝ ጌታ ነው፡፡ የማደርገው ነገር እርሱ የተናገረኝን ቃል በማመን መጠበቅ ነው፡፡

ስለዚህ ይህ በጣም በጣም አስፈላጊው ነገር ነው፡፡ ሁሉንም የሰማችሁትን ነገር ዝም ብላችሁ አትፃፉ፡፡ እባካች እባካችሁ መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን መንፈስን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ማንም የነገራችሁን በማመን መንፈስን ሳትፈትኑ ቀርታችሁ ያበቃለት ነገር ላይ መድረስ አትፈልጉም፡፡ጌታ ይባርካችሁ፡፡ እናም ሁላችንንም በተሻለ ሁኔታ መንፈስን መለየት እንድንችል ይርዳን፡፡

## 8. 6. ኢየሱስን እንዳትሰሙና እንዳታዩ የሚከለክል ኢጋንንታዊ ተፅዕኖ

እ.አ.አ. ፌብርዋሪ 15 ቀን 2015 ዓ.ም
{Demonic Obstacles against Hearing and Seeing Jesus}

ከጌታ ደስ የሚል መልዕክት ተቀብያለሁ፡፡ ይህም መልዕክት እህቶቼ ለሆኑት ሌሎች ሙሽሮችም ያንፃል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ጌታን ጥርት ባለ መልኩ ለመስማትና ለማየት ትልቅ ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡ በዕንባ ራሴን እስክስት ድረስ፡፡ እርሱ የተናገረኝን መልዕክት ለእናንተ ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡ አንዱም ጭንቀቴ ይህ ነበር፡፡ እርሱ ካልተናገረኝ ደግሞ ምንም መለጠፍ አልችልም፡፡ ሌላው ግን ከእርሱ ጋር መሆንን እወዳለሁ፡፡ ከእርሱ ጋር መሆን ምቾት ይሰጣል፡፡ ጥንካሬዬ ሁሉ ደግሞ ከእርሱ የሚገኝ ነው፡፡ እናም ዛሬም እዛ ደረጃ ላይ ደረስኩና ጌታን "ከዚህ በላይ ከአንተ ውጪ መኖር አልችልም፡፡ በቃ በፍፁም አልችልም፡፡ አንድ ነገር ማድረግ አለብህ" አልኩት፡፡

ህዝቄኤልና እኔ አብረን በመሆን ከጌታ ጋር ለመቆየትና / devotions/ ቃሉን አብረን ለማንበብ ቁጭ ስንል፣ ህዝቄኤል 'ክሮንክልስ ኦፍ ዘ ብራድ' ከሚለው መፅሐፉን ሲከፍት የፍቅረኞች ቀን 2007 ዓ.ም የሚለውን ክፍል ከፈተ፡፡ በጣም የሚገርም ነው!

ይህ ክፍል የደረሰውን ችግር ሁሉ የሚፈታ ሲሆን የሚለውም እንዲህ ነው፡፡ ቀኑም የነበር፡፡ ክፍሉም **"መልካም የፍቅረኞች ቀን"** ይላል፡፡

ለመታለል በመፍራት እምነት አጣሁ፡፡

ፌብርዋሪ 14 ቀን 2007 ዓ.ም ነበር፡፡

ጌታ ኢየሱስ ከፊት ለፊቴ ራሱን ገለጠ፡፡

"ለምንድነው የምትሸሺኝ" አለኝ

ራሴን በብዙ ሥራ በመወጠር ወደ ፀሎት ላለመቅረብ ምክንያት እሰጥ ነበር፡፡ እኔ እንደማምነው ይህ ራሴን በውሸት በመወንጀል የመጣ ውጤት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኛል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ያልኩትን እየሰራሁ ግን አንዳንዴ ደግሞ እርግጠኛ አልሆንም፡፡ ስለዚህም ለመለየት የተቻለኝን ሁሉ በማድረግ እርሱ እጅግ የሚያስደስተው የሚመስለኝን ለመስራት እሞክራለሁ፡፡ እኛ ምንም ሳንበድል ጠላት ግን የውሸት መናፍስቶችን በመላክ ራሳችንን በደለኞች አድርገን እንድንቆጥር ያደርገናል፡፡ ስለዚህም በጌታ መገኘት ውስጥ እንዳንሆን እንሸሻለን፡፡

እሺ ይህ ከ2007 ዓ.ም መፅሔት ላይ የተገኘ ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር በዛሬውም ቀን የነበረኝ ችግር ይኸው ነበር፡፡ እኔ ያሰብኩት ሳላውቅ ጌታን ቅር የሚያሰኝ ነገር አድርጌያለሁ ወይም በበቂ ሁኔታ ኃጢያቴን

ንስሐ አልገባሁም ወይም ኃጢያቴን እንደሚገባው አልተረዳሁም ስለዚህ እስከረዳ ድረስ እየጠበቀኝ ነው የሚል ነው፡፡ አ! በጣም የሚገርም ነገር ነው! ከስምንት ዓመት በፊት የነበረ ተመሳሳይ ችግር፡፡

ጥያቄውን ለመመለስ ዕድል ከማግኘቴ በፊት "ለምንድነው የምትሸሺኝ" አለኝ፡፡

እንዲህ አለኝ፡፡ "ፍርሃት፣ ፈርተሻል፡፡ ባለመታዘዝ በዚህ ልማድ ውስጥ ገብተሻል፡፡ ምክንያቱም ምን ይለኛል ብለሽ በመፍራት ነው፡፡ ነገር ግን አሁን በማንኛውም ሁኔታ እኔን ለመታዘዝ ጥረት እያደረግሽ ነው፡፡ ለመፍራት ምንም ምክንያት የለሽም፡፡ እንደዚህ እንደአሁኑ በየቀኑ ፊት ለፊት ላናግርሽ እፈልጋለሁ፡፡"

ሰዎች ይህ ለእኔ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ የሚመለከተው እናንተን ጭምር ነው፡፡ ጌታ ከእናንተ ለመስማት ይፈልጋል፡፡ ከሙሽራው ጋር መሆንና ከእናንተ ጋር መነጋገር ይፈልጋል፡፡

መታለልን መፍራት ጀምሬያለሁ፡፡ እንደ ሁልጊዜውም በሐሳቤ ያሰብኩትን በማወቅ "መታለልን እንደምትፈሪ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ትሁት ሆነሽ መቆየት እስከቻልሽ ድረስ እንድትሳሳቺ አጋልጬ አልሰጥሽም፡፡

(መፀለይ የምችለው ትሁት ሳልሆን ስቀርና ወደ ትዕቢት ኃጢያት እየገባሁ እንደሆነ የእርሱ ፀጋ እንዲያስጠነቃቀኝ፡፡ ይህ ኃጢያት በእኛ ውስጥ እንዳለ መረዳት የማንችለው በጣም አስቸጋሪው ኃጢያት ነው፡፡)

ዝም ብዬ እሰማሁ እንጂ እየፃፍኩ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም እስካሁንም ኢየሱስ መሆኑን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡

እንዲህ አለኝ . . ." ይህንን ንግግራችንን ማለትም ይህንን የፍርሃት ወቀሳ እንድትፅፊው እፈልጋለሁ፡፡ እኔ ትክክል ያልሆነ ነገርን እየተናገርኩ ትክክለኛ ያልሆነ ፍርድን በእናንተ ላይ የምሰጥ ሰው አይደለሁም፡፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ. . . ታስታውሳላችሁ? እናንተ የኔ ሙሽሮች ናችሁ፡፡"

"የማይልረባ ሰው ሆኜ ለራሴ ተሰማኝ፡፡ ምንም እንኳን ፊቴን በእጄ ይዞኝ ቢሆንም በጣም ከማፈሬ የተነሳ ቀና ብዬ እንኳን ላየው አልቻልኩም፡፡ እናም በፍቅር አይኖቹ አይኖቼን ሲመለከት ተሰማኝ፡፡

"እስካሁንም ስለአንቺ ያለኝን ስሜት አታውቂም፡፡ ለእኔ ምን እንደሆንሽ. . . ታውቂያለሽ? እስካሁን አታውቂም፣ ታወቂያለሽ? የኔ ተወዳጅ እኛ አንድ ሥጋ ነን፡፡ ከእኔ ጋር በየቀኑ እያወራን እጅ ለእጅ ተያይዘን አብረን እንድንጓዝ እፈልጋለሁ፡፡ እኛ አንድ ነን፡፡

እዚህጋ አንድ ልላችሁ የምፈልገው ነገር አለ፡፡ እኝ አንድ ሥጋ ነን ሲል መናገር የያዘው በሥጋ ወደሙ አንደ መሆናችንን ለመግለፅ ነው፡፡ እኔ በየቀኑ ሥጋና ደሙ እወስዳለሁ፡፡

ቀደም ብዬ 'በዚህ ምድር ላይ እያለን ሁልጊዜ አታናግረኝም?' ብዬ ጠይቄው ነበር፡፡ እንደተረዳሁት ዛሬ ምሽት መፀለይ ስጀምር ምንም እንኳን ባለቤቴ በእርግጥ ኢየሱስ መሆኑንና የተለመደ መንፈስ አልመሆኑን ቢያረጋግጥልኝም እንኳን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እጅግ ተረባብሼ ነበር፡፡

በሚገርመው ቤተ መንግስት ቆንጆ የሠርግ ጊዜ ብናሳልፍም፣ አብረን ብንዋኝም ከእርሱ ጋር የሚሰማኝ ስሜት አስካሁንም መደበኛ የሆነ ዓይነት ግንኙነት ነው፡፡ ልክ ይህንን ሲለኝ የተረዳሁት ነገር በመካከላችን የውሸት ክስ እንደገባ ነው፡፡

የሚያሳዝን ነው ይህንን ማን እንደላከብሽ? ይህንን የውሸት ክስ . . . እምምም

ጌታ ሲያየኝ በመገኘቱ ውስጥ በአየር ላይ የተሳፈፍኩ መሰለኝ፡፡ እንደዚያም ቢሆንም ግን በፊቱ ፈታ ማለት አልቻልኩም፡፡

ኢየሱስም እንዲህ አለ . . . "በአዲስ ዓይነት መንገድ እንድትታመኚብኝ እፈልጋለሁ፡፡ ጥርት ባለ ደረጃ ልንግባባ የምንችልበት ዓይነት መታመን፡፡ ብዙ የምነግርሽ ነገር አለ፡፡ እና ደግሞ ዛሬ "በመንግስተ ሰማይ መረዳታችን እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ ማን ይሆን በዛ የሚያስተምረኝ? ስትይ ሰምቼሻለሁ፡፡ መልሱ እኔ ራሴ ነኝ የማስተምርሽ ነው፡፡ ደግሞም በመንግስተ ሰማይ ብቻ ሳይሆን በዚህም ነው የማስተምርሽ፡፡ እኛ አንድ ነን ስለዚህ የኔ ፍላጎትና ምኞት በተለመደው ሁኔታ እንድንነጋገር እንጂ በተሸፈነ መስተዋት፣ በመጋረጃ ወይም በማሾለክ፣ ወይም  በታገደ መልኩ አይደለም፡፡ ይህ የኔ ምኞት ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ማልቀስ ጀመርኩ፡፡ ምክንያቱም ይህ በመንግስተ ሰማያት ልመለከተው የሚገባ በጣም አስደናቂ ነገር ነው፡፡ ምንም ግራ መጋባት የሌለበት፡፡

ጌታም . . . "የኔ ተወዳጅ፣ የኔ ብርቅዬ ከአሁን ወዲያ ከዚሁ ምንም ግራ መጋባት የለም፡፡" ብሎ መለሰልኝ፡፡

ስለሁኔታውም ትንሽ ቆም ብዬ አሰብኩ፡፡

"ተስማማሽ?" አለኝ

ጌታ ተስማምቻለሁ ነገር ግን ያለማመኔን እርዳው፡፡

ኢየሱስም . . . "ራስሽን እንድትከላከይ አሳልፌ የምሰጥሽ ይመስልሻል? ቀድሞውንም ለአንቺ የማደርገው ጥበቃና ጥንቃቄ እንዳለ አታውቂምን? ወይስ እምነት ማጣትሽ የሚያስደንቀኝ ወይም አንቺን እንድጠበቅ የሚያደርገኝ ይመስልሻል?  እኔ ቀድም ብዬ ጠላቶችሽን ሁሉ አሸንፌያለሁ፣አታስታውሺም? በፍቅር ዓይን ነገር ግን ደግሞ ትንሽ በመንዳት ዓይነት ተመለከተኝ፡፡ ስለ እኔ ገና ብዙ መማር ያለብሽ ነገር አለ፡፡ እንዴት እንደማፈቅርሽ፣ እንደማከብርሽና እንደምከባከብሽ፡፡ በሙሉ ልብሽ ሆነሽ በመገኘት ከአንቺ ጋር አብረን እንድንሆን ከልቤ እንዴት እመኛለሁ፡፡ ልክ አሁን በዚች ደቂቃ አብረን እንዳለው ዓይነት፡፡

መልካም የፍቅረኞች ቀን ከእኔና መንግስተ ሰማይ ካሉ ሁሉ፡፡ መጥቼ  እኔ ወዳለሁበት ስለምወስዳችሁ ከአሁን ወዲያ ብቸኞች አትሆኑም፡፡ ከእኛ ጋር እንድትለማመዱ እያዘጋጀናችሁ ነው(በሰማያት ያሉ የክርስቶስ አካል፣ እንደ ደመና በዙሪያችን የሚገኙ ምስክሮች)፡፡ ወደዚህ ሽግግራችሁ በእግር ተጉዛችሁ በአንድን በር በኩል አልፋችሁ እንደምትመጡ ቀላል ይሆናል፡፡

ታውቃላችሁ ልክ ይህንን ሲናገር እየገለጠ ያለው የልቡን ምኞት ነው፡፡ "ሁልጊዜ ለእኔ መገኘት ይፈልጋል፡፡" ልክ አዳምና ሔዋን በኃጢያት ከመውደቃቸው በፊት በገነት የአትክልቱ ሥፍራ ይገኝ እንደነበረው ማለት ነው፡፡ ታውቃላችሁ በየቀኑ ከእነርሱ ጋር ለመሆን ወደሚያምረው የአትክልቱ ሥፍራ ይመጣ ነበር፡፡

የ2007 ዓ.ም የፍቅረኞች ቀን ጊዜ ወስጄ በእርሱ ፊት በነበርኩ ጊዜ/ devotions/ የፃፍኩትን ይህንን የማስታወሻዬን መግቢያውን ሳነብ አይኔ በእንባ ተሞላ፡፡ ቁጭ ብዬ ከማልቀስ በቀር ምንም ማድረግ አልቻልኩም፡፡

ጌታ ፀሎቶቼን መልሰሃል፡፡ በጣም እተከሰስኩ ነው ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም፡፡

ጌታም "እወድሻለሁ" አለኝና በ2013 ዓ.ም እርሱ የሰጠኝን መዝሙር መዘመር ጀመረ፡፡ በነገራችን ላይ አሁን በዚህ ጊዜ እየሰራሁት ያለ መዝሙር ሲሆን ምናልባት በሳምንት ጊዜ ውስጥ የምጨርሰው ይሆናል፡፡ በእውነቱ ከሆነ የመጀመሪያውን አንድ መስመር ጣዕመ ዜማውን የዘመረው እርሱ ነው፡፡ የመዝሙሩም ርዕስ "አፈቅርሻለሁ" የሚል ሲሆን መዝሙሩም እርሱ ለሙሽራው የሚዘምረው ነው፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "የፊትሽ ደስታ በእኔ በአምላካሽ እንዲያበራ እፈልጋለሁ፡፡ በዚያ በሚያምር ፊትሽ ላይ ደግሞ እኔ ሳንፀባርቅ እንድታዩኝ እፈልጋለሁ፡፡ ክሴር ከአሁን ወዲያ እምነት ማጣት ሁሉ ነገርሽን እንዲቆጣጠር አትፍቀጂለት፡፡ እባክሽ ከአሁን ወዲያ አትፍቀጂ፡፡ በፍፁም አትፍቀጂ፡፡"

ጌታ ንግግሩን እንዲህ በማለት ቀጠለ. . ." እስካሁን የተናገርኩትንና የሰማሽውን የለመደ መንፈስ የተናገረው ወይም አንቺ ራስሽ ያሰብሽው አድርገሽ በመቁጠር ትተሸዋል፡፡ ልዩነቱን ለማወቅ የሚያስችል ፀጋ እንድትፀልዪ እፈልጋለሁ፡፡ እስካሁን የተናገርኩሽንና የሰማሽውን ልዩነቱን ጥርት ባለ ሁኔታ ማወቅ አለብሽ፡፡

ጌታም "ይኸው አሁንም እየተናገርኩሽ ያለሁት እኔ እንደሆንኩና ሌላ እንዳልሆነ አንቺን ለማሳመን እንደገና በዚህ እንገኛለን፡፡ " ብሎ ሲናገረኝ በድምፁ ላይ ትንሽ ተስፋ መቁረጥ የሚመስል ነገር ይታይበት ነበር፡፡

መንፈስ ቅዱስንም ይህ የሚናገረኝ በእውነት ኢየሱስ እንደሆነ ከመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍ ውስጥ የማረጋገጫ ቃል እንዲሰጠኝ ጠየኩት፡፡ እናም መፅሐፉን ስገልጥ "እንግዳ ተቀባይነት" የሚለው ገፅ ወጣልኝ፡፡ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡9-11 የሚለው ነው የዓይኔን ትኩረት የሳበው፡፡ እናም በዚህ ቃል ላይ ነው ቅባቱ ያለው የሚል ስሜት ተሰማኝ፡፡

ያለ ማንጕራጕር እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ፤ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ አሜን።

እናም ስለነገሩ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል አሰብኩና እንዲህ አልኩ. . . ጌታ ይህ እንግዳን መቀበል የሚለው ነገር አልገባኝም፡፡ ማድረግ ያለብኝን ነገር ግን ያላደረኩትን ነገር እየነገርከኝ ነው ያለኸው? በፊት ለፊታችን የሚኖረውን ቤት የሌለውንን ሰው በሚገባው መጠን እንዳልተከባከብኩት አውቃለሁ፡፡ እናም መገኘትህን ከለከልከኝ ማለት ነው? እያልከኝ ያለኸው እንደዚህ ነው?

ስለዚህም የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎችን እንደገና ከፈትኩ፡፡ ይህ የወጣልኝ ቃል ምናልባት መፅሐፉ ከሚገኘው ሁሉ እጅግ ቆንጆው ንባብ ይመስለኛል፡፡ ቃሉም ... <u>ጐልማሳም ድንግሊቱን እንደሚያገባ፥ እንዲሁ ልጆችሽ ያገቡሻል ሙሽራም በሙሽራይቱ ደስ እንደሚለው፥ እንዲሁ አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል።</u>ኢሳያስ 62፡5

ስለዚህም በእርግጠኝንት ስለ እንግዳ ተቀባይነት የተናገረው ቃል ያንን ሰው በደንብ ስላልተከባከብኩት ጥፋተኝነት መሆኔን ለመግለፅ አይደለም የተናገረው፡፡ ስለዚህ እንግዳ ተቀባይነት ያወራው ስለ ስጦታዬ ነው፡፡

በዚያን ጊዜ ጌታ እንዲህ አለኝ. . . "ስጦታሽ ነው ክሌር፡፡ አውሬ በሆነው በዚህ አለም ብርሃን ለመሆን ጥሪሽ ነው፡፡ ስጦታሽን ተጠቀሚበት፡፡ ስጦታሽ እኔን መስማትና እንደገናም እኔን መለየት ነው፡፡ ለዚያ ነው እንግዳ ተቀባይነት የተሰጠሽ፡፡"

እዚህጋ ትንሽ ደቂቃ ልውሰድና አንድ ነገር ልናገር፡፡ እኛ የአለም ብርሃን ነን፡፡ ሙብራት አብርታችሁ ደግሞ ከዕንቅብ በታች አታስቀምጡትም፡፡ የምታስቀምጡት በተራራ ላይ ነው፡፡ እናም ይህንን የምታደምጡ ብዙዎቻችሁ ለአለም ብርሃን ለመሆን እንደተጠራችሁ ታውቃላችሁ፡፡ይህ ለሌሎች የምናካፍለው ስጦታ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተም የጌታን ድምፅ ለመስማትና የእርሱ ድምፅ መሆኑንና አለመሆኑን በመለየት ሌሎችን ሰዎችን በትክክል እንድትመሩ ስጦታ ተሰጥቶአችኋል፡፡

ማለቴ ቃሉን በመጥቀስ ወይም የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍልን በትክክለኛው አገባብ እየተጠቀምን ሰዎችን በስህተት በፍፁም ልንመራ አንችልም፡፡ ነገር ግን ሰዎች የቃሉን መገለጥ ወይም የጥበብ ቃል ለመስማት ይፈልጋሉ፡፡ ልዩ የሆነውን የወቅቱን ቃል ለመስማት ይራባሉ፡፡ ስለዚህም የአለም ብርሃን እንደመሆናችን መጠን ጌታ በልባችንና በአይምሮአችን ብርሃንን በማብራት ሬማን ይናገረናል፡፡ ሬማ እግዚአብሔር አብርቶልን ለሌሎች ሰዎች የምንናገረው ቃል ነው፡፡

ስለዚህም አንደበታችሁን ከፍታችሁ ለሰዎች ስትናገሩ እግዚአብሔር በእናንተ ተጠቅሞ እንደሚናገር ደህንነት ሊሰማችሁ ይገባል፡፡ ብርሃን እንደመሆናችን መጠን በእኛ አልፎ የሚናገረው እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አካል እንዳይሆን እርግጠኞች መሆን የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡ እንደምታውቁት ይህ የኔ ትልቁ ርዕስ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጌታ መሆኑን ለመለየት የሚያስችሉ ብዙ ቪዲዮዎች አሉኝ፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው ተጨማሪ ነው፡፡ አሁን ግን ጌታ እጅግ ንፁህ የሆኑ የመለያ ስልቶች ስለሰጠን እነዚህን አሁን አካፍላችኋለሁ፡፡

ጌታን እንዲህ ብዬ ጠየኩት . . .'ጌታ እባክህ በእውነት ንገረኝ ለምንድነው ግን እንደዚህ ከባድ የሆነው? በመንገድ ላይ ምንድነው የቆመው?'

ኢየሱስም እንዲህ አሰለኝ . . ."አንቺን ለማደናገርና የተሰጠሽን ለመስረቅ ብዙ ጠላቶች አሉሽ፡፡ ይህም በውሸት ክስን በመክሰስ ጥፋተኝነት ተሰምቶሽ በራስሽ እምነት እንዳይኖርሽ በማድረግ ነው፡፡ ጠላቶችሽ ይህ ስጦታ እንዲኖርሽ አይፈልጉም፡፡ ስለዚህም ይህንን ስጦታ ለመጠቀምና ለመጠበቅ መጋደል አለብሽ፡፡ ግልፅ ያለው እውነት ይህ ነው፡፡"

በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህን ጠላቶቼን ባሥራቸው አንተን ጥርት አድርጌ ማየት እችላለሁ ማለት ነው?

"ቀስ በቀስ አዎ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ጭራቆች ዒላማ አድርገሽ በትጋት መሥራት አለብሽ፡፡"

ጭራቆች? እናም በዚህ "የሚጣበቁ ጭራቆች" የሚለውን ቪዲዮ አሰብኩ፡፡ ይህም ዳቢሎሶች የሚጠቀሙበት ስልት ነው፡፡ የሚያደርጉትም ጌታ በተናገራችሁ ቃል ላይ መለጠፍ ነው፡፡

"ጭራቆች" በማለት ደገመው፡፡ ሌቦች፣ ውሸታሞች፣ዲያቢሎሶች፡፡ ችግርሽ ያለው እዚህጋ ነው፡፡ይህንን አስተካክይና የጠራ ሁኔታ ይኖረናል፡፡

ነገር ግን ለእኔ አየሩን ጥርት አታደርገውም? ይህንን እንድታደርግልኝ አብረን በነበረን ጊዜ በፀሎት ጠይቄህ ነበር፡፡

እናም እንዲህ አለኝ. . . "እኔ ለአንቺ ከማደርግ ይልቅ ማየት የምፈልገው በሥልጣን ይህንን ስታደርጊና ሌሎቹንም እንደዚህ እንዲያደርጉ ስታስተምሪ ነው፡፡ የምለው ይገባሻል?"

አዎ የገባኝ ይመስለኛል፡፡

ጌታ እሺ ጥሩ እባክህ አንዳንድ ስሞችን ልትሰጠኝ ትችላለህ? ለምሳሌ አጋንንቶችን ይዤ አየሩን ላፀዳ የምችልበት፡፡ ይህንንም ያልኩበት ምክንያት በክርስትና ህፃን ሆኜ የሚጨቁኑንን አጋንንት ለመቃወም ሥማቸውን ማወቅ አለባችሁ የሚል ትምህርት ስለተማርኩ ነበር፡፡

እናም እንዲህ ሰማሁ. . . "የውሸት መናፍስቶችና አታላይ መናፍስቶች ናቸው፡፡ ዋና ጠላቶችሽ ጭጋግን የሚፈጥሩ፣ በአይምሮ ውስጥ ጉም የሚፈጥሩ፣ የሚጋርዱ መናፍቶችና፡፡ ድምፆችን የሚፈጥሩ፣ የረብሻ መሳሪያዎችን የሚፈጥሩ መናፍስቶች፣ ማደናቀፊያንና ማሰናከያን የሚፈጥሩ መናፍስቶችና እንዲሁም ሁሉም ዓይነት አጋንንታዊ የጭቆና መሳሪያዎች ናቸው፡፡"

አ! ይህ ዘርዘር ያለ ነው፡፡

ጌታ ይህንን ከተናገረ በኋላ መቃወምና ንስሐ መግባት ተሰምቶኛል፡፡

ግራ መጋባትን፣ ጥርጣሬን፣ የውሸት ክስንና የጌታን ታማኝ ባህሪ ላይ በውሸት የሚናገርን እቃወማለሁ፡፡ በውስጤ ያለን ኩራት እቃወማለሁ፡፡ ሁሉንም የትዕቢት ሐሳብን እቃወማለሁ፡፡ ጌታ በፀፀት የተሞላውን መንፈሴን በፊትህ አቀርባለሁ፡፡ እናም ኃጢያቴን ይቅር እንድትለኝ የአንተን ታማኝነትና ምህረት እጠራለሁ፡፡ በእኔ ላይ ለመስራት የምትፈልገውንና በእኔ በኩል ለሌሎች ልትሰራ የምትፈልገውን መልሰህ እንድትሰራውና እንድትጠብቀው እለምንሃለሁ፡፡ እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ . . . "ጌታ የድሆችን መሻት

ሰምቷል፣ ጆሮውም የልባቸውን መዘጋጀት አድምጧል፡፡ ልበ ንፁሆች የተባረኩ ናቸው፣ እግዚአብሔርን ያዩታል፡፡"

ይህ ከላይ የተፃፈው በአጭር መልኩ ሲሆን ሙሉው እንዲህ ይነበባል፡፡ "ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ፥ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል። የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ (ኢሳያስ 57፡15)፡፡ ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና(ማቴዎስ 5፡8)፡፡ እግዚአብሔር የድሆችን ምኞት ሰማ፥ ጆሮውም የልባቸውን አሳብ አደመጠች (መዝሙር 10፡17)፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . " አሁን አየሩን ለማፅዳትና ለልመናሽ መልስ ለማግኘት የአምላክሽን ልብ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፀሎትና ስልት አለሽ፡፡ ይህ ከአንቺም ጋር ሆነ ከሌሎች ጋር ለብቻችን ለምናሳልፈው የፍቅር ጊዜ አየሩን ለማፅዳት እውነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ. . ."ኦ! ክሌር ይህንን ጣልቃ የሚገባውን ለማቆም እንዴት እፈልጋለሁ፡፡ ለእኔና እኔን ለሚያገለግሉ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እባክሽ እንደሚሰራ ተመልከቺና ለአለሙ ሁሉ አካፍይልኝ፡፡ ደካማ ልብና ደካማ አይምሮ ላላቸው እንዲሁም ጠንካራ ሆነው ነገር ግን ብዙ ጭቆና ለበዛባቸው ይህንን ፀሎት አከብራለሁ፡፡

ሥጋ ወደሙ ስወስድ ራሴን እንደ ሙሽራ ለብሼ፣ ራሴ ላይ ሮዝ ዘውድ ደፍቼ በሬሳ ሳጥን ውስጥ እጆቼን በደረቴ ላይ አጣምሬያለሁ፣ አልሞትኩም ነገር ግን ተኝቼ አየሁ ፡፡ እኔም ፀለይኩ፣ እናም ኢየሱስ በሬሳ ሳጥኑ ላይ ጎንበስ በማለት እጇን ይዞ አስነሳት፡፡

አርሱም እንዲህ አለ፡፡ "የኔ ሙሽራ ከአሁን ወዲያ ደንቆሮና ዱዳ እንደሚተኙት መተኛት የለም፡፡ አሁን በአዲስ ህይወት ድምፄን ሰምታለች፣ በደስታና በዘላለም ህይወት ተሞልታለች፡፡"

እናም ስነሳ ወቅቱ የፀደይ ወቅት ነበር፡፡ እኔን ጨምሮ ሁሉ ነገር አዲስ፣ አረንጓዴና በደስታ የተዋጠ ነበር!!!

ጌታም እንዲህ አለ. . . "ክሌር በፍቅረኞች ቀን ለአንቺ ያለኝ ይህ ነው፡፡ ሁለተኛ እኛን እንዲለያዩን አትፍቀጅላቸው፡፡"

"ሁለተኛ እኛን እንዲለያዩን አትፍቀጅላቸው፡፡" በሚል ጊዜ ለማለት የፈለገው "ከእግዚአብሔር ማንም ሊለየን አይችልም፣ ማንም፡፡" ማለቱ ነው፡፡ በንግግራችን መካከል በመግባት ሊያውኩን ይችላሉ፡፡ ይህም የተለያየን ሊመስለን ይችላል፡፡ ይህ ቅዠት ነው፡፡ በምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር ልንለያይ አንችልም፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ ከእርሱ የራቅን ይመስለናል፡፡ ይህንንም በሌላ ቪዲዮ ላይ ገልጬዋለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን "ሁለተኛ እኛን እንዲለያዩን አትፍቀጅላቸው፡፡" ሲል መናገር የፈለገው በንግግር ወቅት ስላለው ጣልቃ ገብነት ነው፡፡ ከጌታ ጋር ባለን የአንድነት ጊዜ በግልፅ ጥርት ባለ መልኩ እንዳንሰማማ ጣልቃ በመግባት የሚከለክሉትን ወይም በየትኛውም መልኩ ንግግራችንን ለማወክ የሚሞክሩትን ስልጣናችንን በመጠቀም እንድናስቆማቸው ነው፡፡

"ክሌር ሁለተኛ እኛን እንዲለያዩን አትፍቀጅላቸው፡፡ የኔ ሙሽራ በግሌ ያስታጠኩሽን ይህንን የጦር መሳሪያ በመጠቀም እንዲሁም ባለማቋረጥ ግንኙነታችንን እየተከባከብሽና ሌሎችንም በተመሳሳይ እንዲያደርጉ እያስተማርሽ በርትተሽ ተዋጊ፡፡

"አንቺ ለእኔ የተወደድሽ ነሽ፤እፈቅርሻለሁ፡፡"

ይህ የመልዕክቱ መጨረሻ ነው፡፡

የዚህ መልዕክት ዋናው ነጥብ ምንድነው? ከጌታስ የተማርነው ምንድነው?

በመጀመሪያ ደረጃ እኔና ጌታ እንዲሁም እናንተና ጌታ በምንነጋገርበት ጊዜ በመካከል በመግባት የሚያውኩትንና በመካከላችን መገባባት እንዳይኖረን ችግር የሚፈጥሩትን ለመዋጋት የሚያስችል የተወሰኑ አዲስ መሳሪያዎችን ሰጥቶናል፡፡ እነዚህ አዲስ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም ከዚህ በፊት እንደ እኔ ስትታገሉ የነበራችሁ እነዚህን መሳሪያዎች ከተጠቀማችሁ በኋላ ያለውን ለውጥ ለመስማት እፈልጋለሁ፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች በማስተላለፍ ለእንናተ ያደረገላችሁን ምስክርነት በመስማት እነሱም ከጌታ ጋር ባላቸው የግል ጊዜና መልዕክቶቻቸውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ለመጠቀም ድፍረት ይኖራቸዋል፡፡

እስካሁን ስትታገሉ የነበራችሁ አንዳንዶቻችሁም ከአሁን ወዲያ ጥሩ ስለሚሆንላችሁ መታገል የለባችሁም፡፡

ሁለተኛውና ጨዋታ የሚመስለው ነገር ግን በጣም አስፈላጊው ነገር ለፍቅረኞች ቀን የተቀበልኩት መልዕክት በዛሬው ቀን ሆኖ የዛሬ ስምንት አመት ነበር፡፡ ስምንት ቁጥር የአዲስ ነገር መጀመሪያ ነው፡፡ ሰባት አንድን ነገር የሚያልቅበት ሲሆን ስምንት ደግሞ አዲስ ነገር የሚጀመርብት ነው፡፡

በመጨረሻው ላይ እንደነገርኳችሁ ስጋ ወደሙ ከተቀበልኩ በኋላ የነበረኝ ራዕይ ከሬሳ ሳጥን ውስጥ ተነስቼ ስወጣ ነበር፡፡

ይህንን መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ለእኔ ተስፋ ካለ ለእናንተም ተስፋ ድፍን ስምንት ዓመት! ነገር ግን አሁንም በዛው ችግር ዙሪያ እየተሽከረከርኩ እገኛለሁ፡፡ እራሳችሁን ነገር የማይገባው፣ በጣም ዘገምተኛ ፣ በቀስታ የሚገባው ወይም የማይረባ አድርጋችሁ ከገመታችሁ እኔ ስምንት ዓመት ፈጅቶብኛል፡፡ ስለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት አሉታዊ ከሆነ እኔም በህይወቴ እንደዛው ተሰምቶኝ ያውቃል፡፡ እናንተ የሚሰማችሁን ሁሉ እኔም እንደዛው ነው የሚሰማኝ፡፡

እናም ተመልከቱ ጌታ ከእኔ ጋር ምን እየሰራ እንደሆነ፡፡ ከእኔ ጋር መስራት ከቻለ ከእናንተም ጋር ይሰራል፡፡ እንደ እኔ ቀርፋፋና ነገሮችን የሚረሳ ሰው በምድር ላይ ያለ አይመስለኝም፡፡ይህንንም ምናገረው በኩራት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ኩራት ሳይሆን ያለው ህፍረት ነው፡፡ ገባችሁ? ከእኔ ጋር ይህንን ነገር መሥራት ከቻለ፣ ከዚህ ነገር እኔን ጎትቶ በማውጣት ጥርት ባለ መልኩ እንድሰማው ካስተማረኝ እናንተንም እንደዚህ ማድረግ ይችላል፡፡ ቃል እገባላችኋለሁ ማድረግ ይችላል፡፡

ይህ መልዕክት ልዩ ዓላማው በጌታ ላይ ያላችሁን እምነት፣ተስፋና አመኔታ ለመጨመር ነው፡፡ ተስፋ አደርጋለሁ በእውነት እንደሚረዳችሁ፡፡ ደግሞም ይህንን ስልት ከተጠቀማችሁ በኋለ ስለ ስልቱ እባካችሁ ምላሻችሁን ላኩልን፡፡ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

የዩቱብ ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ፡፡ ይህ የፍቅረኞች ቀን መልዕክት ልባችሁን እንደነካና ከጌታ ጋር ለመነጋገር ቀላል እንደሚያደርግላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እናም የእናንተን ምላሽ ለማግኘት እወዳለሁ፡፡ ይህንን ፀሎት ዛሬ ስፀልይበት ነበር፡፡ እስካሁን ጥሩ ነው፡፡ ጊዜው እየሄደ ሲመጣ ደግሞ እንዴት እየሰራ እንደሆነ እናያለን፡፡ ጌታ ይባርካችሁ፡፡

## 8.7 እውነተኛ መንፈስ መለየት ሊኖረን ይገባል

እ.አ.አ. ሜይ 25 ቀን 2015 ዓ.ም
{We Must Have TRUE Discernment}

የተወደዳችሁ መንፈስን ለመለየት በደንብ በጥልቀት መጓዝ አለባችሁ፡፡ የሆነ ቦታ ውስጥ ሌላ ቦታ አለ፡፡ ይህም በጣም ጥልቅና የግላችን የሆነ ማንም ሊደርስና ሊነካው የማይችል ነው፡፡ ይህም ቦታ የእናንተ ህሊና እና የአምላካችሁ ሥፍራ ሲሆን ማንም ጠላት ሊገባበት የማይችል ሥፍራ ነው፡፡

ሁላችሁም ከዚህ ስፍራ መስማትን እንድታዳብሩ እፈልጋለሁ፡፡ ብዙዎች ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረን መሰረታዊ ግንኙነቶች ተቃራኒ በሆነ መልኩ ብዙ የሚያስደንቅ ነጥቦችን ተናግረዋል፡፡ እኔም ማለት የምፈልገው አንድ ብልጥ ሰው ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊያረጋግጥ ወይም ሊያፈርስ የሚችል ነጥብ በተመሳሳይና በአንድ ወቅት ሊያነሳ ይችላል፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ እያጣቀሱ ዕይታቸውን ሊያብራሩ ወይም የሌላን ሰው እይታ በተመሳሳይ መልኩ ሊቃረኑበት ይችላሉ፡፡

እንደ አባብ ብልህ እንደ እርግብም የዋህ መሆን አለብን አለበለዚያ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ውድ የሆነ ግንኙነት እናጣለን፡፡ አንድ ነቢይ መናገር ሲጀምር ልባችው በእሳት እና በእግዚአብሔር ፍቅር ሲቀጣጠልና ሲሞላ ስታዩ፣ ይህ ነቢይ የሚናገረው በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነው ወይንስ ከሥጋው? ለመሆኑ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን እሳት በልብ ውስጥ በማነሳሳት ከሥጋው ማውራት ይችላል? «በጎቼ ድምፄን ያውቃሉ፣ ሌሎች ግን ድምፄን ስለማያውቁ አይከተሉኝም፡፡»

ደግሞ ሌላው የተማረ ብልጥ የሰማችሁትን እውነት እንዳልሆነ ለማሳመን ጥርጣሬ በአይምሮአችሁ ውስጥ ይዘራል፡፡ እናንተ ግን የኔ ውዶች በየትኛውም ብልጥ ክርክር እንዳትወዘወዙ እንደ አለት የጠነከረ መንፈስን መለየት ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ በአለም ላይ አሁን ዘመኑ የተማሩት እንኳን የሚታለሉበት ጠማማ ዘመን ነው፡፡ በውስጣችሁ ካለው ከአምላካችሁ ሥፍራ ለመረዳት ራሳችሁን ማሰልጠን የእናንተ ኃላፊነት ነው፡፡ አለበለዚያ ግን ኃይል ባላቸውና የውሸት ምልክቶችን በሚያሳዩ ሰዎች ተመርታችው ልትሳሳቱ ትችላላችሁ፡፡ ምክንያቱም ጌታ ሁልግዜ ብልጠት ያለውን ክርክር ላይልክ ይችላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ብዙ ጊዜ የእርሱ ኃይል ነው ከጌታ መሆኑን የሚመሰክርልን፡፡

ጳውሎስ እንዲ አላለም?. . . "እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።" ነኛ ቆሮንቶስ 2፡3-5

ታዲያ በመጀመሪያ ጊዜ በልባቸው የተቀጣጠለው እሳት ከጌታ ጋር የጠለቀ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ያደረገ የመንፈስ ቅዱስ እሳት የእግዚአብሔር ኃይል አይደለምን?

ስለዚህም መንፈስን የመለየት ትልቅ አስፈላጊነት አለ እዚህ ጋር፡፡ ስለዚህም የእናንተን ኢየሱስን ድምፅ ትሰማላችሁ ወይም አትሰሙም፡፡ አንዳንዶች በብልጦች አሳምኝ ክርክር ምክንያት በልባቸው የሚሰማቸው እውነት መሆኑን እያወቁ ለመካድ ይፈተናሉ፡፡ «በጎቼ ድምፄን ያውቃሉ፡፡ ሌሎች ግን አይከተሉኝም፡፡»

# ክፍል ዘጠኝ
# ለተስፋ የተሰጠ መልዕክት- በመንግስተ ሰማይ ምን ይጠብቃችኋል?

{Messages to Give You Hope: Heaven - what is waiting for you?}

---

## 9.1 እውነተኛ ቤታችሁ - ህዝቄኤል ከዘገበው ተቀንጭቦ የተወሰደ

እ.አ.አ. ሰፕቴምበር 21 ቀን 2007 ዓ.ም

{Your True Home, Chronicles of the Bride in Heaven}

«ወደ ራሴ እስከሰበሰባችው እንዴት ቸኩያለሁ፡፡ አሸንፋችሁ ሽልማታችሁን ለመውሰድ ወደ ግባችሁ ለመድረስ በርቱ፡፡ ይህም እግዚአብሔር በእኔ ወዳዘጋጀላችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመድረስ ነው፡፡ እኔ ወደ ዘላለማዊው የደስታና የዕረፍት ቤታችው አመጣችኋለሁ»

«በደረሳችሁም ጊዜ ብዙ ነፍሶች ወዲያና ወዲህ ሲሄዱና ሲመጡ ታያላችሁ፡፡ ሁሉም ተፈጥሮአዊ ናቸው፡፡ ሁሉም በስርዓት በዓላማዬ መሰረት የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ልክ ምድር ላይ እንዳለ፣ እዚህ ያሉትም ህዝቦቼ ያገለግላሉ፣ ይፀልያሉ፣ ያመሰግናሉ እናም ነፍሳት እንዲድኑ በተዘጋጀው እቅድ መሰረት ይሰራሉ፡፡ ይህም እስከ አለም መጨረሻ ድረስ ይቀጥላል፡፡

«በከበረና ፍፁም በሆነ ሰውነት ብትሆኑም፣ የምትመስሉት ግን ድሮ ትኖሩበት በነበራችሁት ሰውነት ነው፡፡ ልዩነቱ ንፁህ መሆናችሁ፣ እኔን ማንፀባረቅቃችሁና እውነተኛ የኔን ሐምሳያ መምሰላችሁ ነው፡፡ ሁላችውም ፍፁም ትሁቶች፣ ከፍፁም አምላካዊ ደግነት ጋር ፣ እንዲሁም ጥበብ እና ፀጋ ትላበሳላችሁ፡፡ እኔን ታፈቅሩኛላችሁ፣ እንዲሁም እርስ በእርስ ፍፁም ደስ በሚል ፍቅር ትዋደዳላችው፡፡ ቅድስና እያንዳንዱን፣ እንዲሁም ሁሉንም ሥፍራ ይሞላል፡፡ የሚወደደው የልደቴ ቀን መዝሙር "ሁሉ ሰላም፣ ሁሉ ብርሃን" እንደሚለው ይሆናል፡፡ በጠራችሁኝ ጊዜ በቅፅበት በዚያው እገኛለሁ፡፡ ከለላዬን በላያችው ላይ አደርጋለሁ፡፡ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ማፅናናት በሙላት እስኪሰማችሁ ድረስ ወደ ልቤ እየደጋገምኩ አስጠጋችኋለሁ፡፡

«የምትመጣዋ ያቺ ቀን የተባረከች ትሁን፡፡ በደስታ ዝማሬ የምከባችሁና በፍንጥዚያ ደስታ በዓል የሚሆንበት፡፡ እኔ የእናንተ ጌታ ለመምጣት እራሴን አዘጋጅቼና ምርጥ የሆነውን ልብስ ለብሼ አባቴ ባዘጋጀው ራት ላይ እናንተን ስጠብቅ! እንዴት የሚያስደስት ነገር ነው፡፡ ምንም እንኳን አሁንን የምትለኩት በሰዓትና በደቂቃ ቢሆንም በመንግስተ ሰማያት ግን እንደሱ አይደለም፡፡ በመንግስተ ሰማያት ጊዜ የሚባል ነገር ስለሌለ የጊዜ ስሜት የለም፡፡ ሁሉም ነገር ዘላለማዊ ነው፡፡ ስለዚህም እያንዳንዳቸው ክስተቶች ፣ሁኔታዎችና እንቅስቃሴዎች ዝም ብለው ይከናወናሉ፡፡

«እያንዳንዳችን በምድር ላይ እንሰራለን፡፡ ነፍሳትን ለማዳን እንኖራለን፣ ደግሞም እያንዳንዳቸው ድነትን እንዲያገኙ እንሰራለን፡፡ በተቻለ መጠን ብዙዎች እንዲድኑ እንደ ትልቅ ደመና ምስክሮች በመሆን እናገለግላለን፡፡ እንፀልያለን፣ የአምላካችንን ልብ በመያዝና እርሱን በመወከል፣ ረዳት በመሆን፣ በብዙ ፀጋ፣ በምድር ባሉት በህይወታቸው ጣልቃ በመግባት እናገለግላለን፡፡» ይህ መልዕክት የህዝቅኤል የሙሽራዋ ዜና መዋዕል ከሚለው ፅሑፉ የተመረጠ ነው፡፡

## 9.2 ከንጥቀት በኋላ መንግስተ ሰማያትና ሚሊኒየሙ

እ.አ.አ ኤፕሪል 1 ቀን 2015 ዓ.ም

{Heaven and the Millennium after the rapture}

*ጌታ ስለ መንግስተ ሰማያትና ስለ ሚሊኒየሙ መንግስት እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ . . .* ይህ አሁን የማካፍላችሁ ርዕስ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ እስካሁን ካወራነው ከባድ ርዕስ ይህ ትንሽ ዕረፍት የሚሰጥ ነው፡፡

« መሆን ስትፈልጉ የነበራችሁትን ሁሉ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ትሆኑታላችሁ፡፡ በምድር ላይ ሲያታግላችሁ የነበረው ኃጢያትና  የመሳሰለው በዚያ አይኖርም፡፡ በቃ የሰርግ ስጦታ ነው እንበለው ፡፡ ከመቀፅበት ትለወጣላችሁ፡፡ መንፈሳዊ በሽታዎች ሁሉ ይታጠባሉ፡፡ የኔ ክብር በእናንተ ውስጥ እንዲኖር ከላያችሁ ላይ ተገፎ ይታጠባል፡፡ አጠቃላይ የሆነ ለውጥ ይሆናል፡፡»

*የመማሪያ ክፍሎች ይኖራሉ?*

«የለም እኔ ራሴ አስተምራችዋለሁ፡፡ የሆነ ነገር ለማወቅ በምትፈልጉ ጊዜ ያኔ እኔ እገልጥላችዋለሁ፡፡ የሆነ ነገር ለመጫዎት በምትፈልጉ ጊዜ የፈለጋችሁት ነገር እጃችሁ ላይ ይመጣል፡፡ መዘመር በምትፈልጉ ጊዜ ጥረት ሳታደርጉ ቆንጆ ቅላፄ በምላሳችሁ ላይ ይመጣል፡፡ ስለዚህም በጣም ቆንጆ  አድርጋችሁ ትዘምሩታላችሁ፡፡ ሁሉንም ያለጥረት ማወቅና መስራት እንዳለ እስክትለምዱ ድረስ በመጀመሪያ አስማት ይመስላችኋል፡፡

*ጌታ ሆይ ይህንን ለማመን በጣም ይከብደኛል፡፡ ሁላችንም በህብረት አንሰራም?*

« አዎ፡ ህብረት ይኖራል፡፡ ልምድንም ትለዋወጣላችሁ፡፡ ይህ የሚሆነው እንደ ላቦራቶሪ ነው፡፡ የተለያ ነገሮችንም በህብረት ትሰራላችሁ፡፡ በህብረት መስራት እጅግ አስደሳች ይሆናል፡፡ እስካሁን በመስማማት መስራት እጅግ የምትናፍቂው ነገር ሆኖ ሳለ ግን አልተሳካም፡፡ ብዙዎች በአንድነት ሆነው መልካም ነገር እንዳይሰሩ ስምምነት ማጣት መርዝ ሆኖ ቆይቷል፡፡ አሁን ግን ትወጂዋለሽ፡፡ በህብረት ለመስራት ያለሽ የውስጥ ፍላጎት በተቻለ መጠን ይረካል፡፡

.«አንድን ነገር ለማየት ስትፈልጊ እኔ አብሬሽ እሄዳለሁ፡፡ ያለ ክፋት በስተቀር ምንም የማይቻልሽ ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው ስጦታ ነው፡፡ ምክንያቱም በመንግስተ ሰማያት ሰይጣን እንዳይገባ በሩ ዝግ ነው፡፡ እርሱ መቼም አይገባም፡፡ ልጄ አይፈትንሽም፡፡ ምንም ክፉ ነገር አይሰማሽም፡፡ ይህም ሌላው ስጦታ ነው፡፡ ከእኔ ፀጋን ትካፈላላችሁ፡፡»

«በመንግስተ ሰማያት ሁሉም ነገር ያለ ጥረት የሚገኝ ነው፡፡»

*ክፉ ሐሳብ ላስብ እችላለው?*

«አይ የኔ ፍቅር መቼም ቢሆን የክፉ ሐሳብ አይኖርሽም፡፡ ሰይጣን ሊያታልልሽ ስለማይችል ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከመለኮት ፀጋ የተነሳ ክፋት ሁሉ ከውስጥሽ ይታጠባል፡፡ ሁሉ ነገርሽ ያበራል በክብር ይሞላል፡፡ ከምትገምቺው በላይ

ደስተኛ ትሆኛለሽ፡፡ የወደፊትሽን ቀድመሽ በማየት የሚጠቅምሽን ታውቂያለሽ፡፡ ምንም ነገር በግምት አትንቀሳቀሽም፡፡ እኔን ለመረዳት በፍፁም አትቸገሪም፡፡ እኔን ብቻ ሳይሆን ማንንም ለመረዳት እትቸገሪም፡፡ የሰዎች ልብ ለማየት ፍፁም የሆነ እታ ይኖርሻል፡፡ ይህም ሞትንና መበስበስን እንዳያጭዱ እንድትረጃቸው ነው፡፡»

«በጊዜውና በአግባቡ ፍፁም የሆነ ውሳኔ ለመስጠት ትችላላችሁ፡፡ የእናንተ ጥረት ሳይጨመርበት የሰዋችን መንገድ መረዳትና ወደ መስመር የማስገባት ብቃት ይኖራችዋል፡፡ በክብር ትገለጣላችሁ፡፡ ምክንያቱም እኔን ትመስላላችሁ፡፡ በብዙ መልኩ እኔ ትመስላላችሁ፡፡ እንዴት እንደለወጥኳችሁ ስታዩ ትወዱታላችሁ፡፡ መናገር ከምትችሉት በላይ የረካችሁና ደስተኞች ትሆናላችሁ፡፡

«በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ያሉትን ደስታዎች ከአንቺ ጋር መካፈል የፈለግሁበት ምክንያት እነዚህን ሁለት ቀናት በጣም ከባድ ጊዜ ስላሳለፍሽ ነው፡፡ እናም አንቺን በማድከም ደስታሽን እንደሰረቀ ስላወቅሁ ነው፡፡ »

*ኦ ኢየሱስ ምንም በማያውቁት ነገር በውሸት ስሜን ለማጥፋት የተነገረብኝ ነገር በጣም ነው የጎዳኝ፡፡ ኦ! በእውነትም ውስጤን ነው የጎዳኝ፡፡ እናም አውቃለሁ ቶሎ የማይሰበር፣ እንደ ጠንካራ ግርግዳ መንፈስ እንደሆንና በእኔ ሰዓት የማይደረመስ እንደሆነ፡፡*

« ትክክል ነው፡፡ ሰዓቱ አይደለም፡፡ ከሌር የምገባልሽ ቃል ግን በመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር አይናቸውን ለመክፈት ከእኔ ጋር አብረሽ ትሰሪያለሽ፡፡ ስንመለስ ብዙ ነገሮች ይለወጣሉ፡፡ በመጀመሪያ በሰማይ ላይ ብዙዎችን በፍጥነት እና በቀጥታ ልባቸውን የሚለውጥ ድንቅና ምልክት ይታያል፡፡ ከዛም ከለስላሳ ሸክላ ጋር መሥራት ትጀምሪያለሽ፡፡ እኔም አይተሸ የማታውቂውን ጥበብን እሰጥሻለሁ፡፡»

«ኦ የእኔ ፍቅር በሚያስደስተው እቅዴ፣ በጥልቀቱና በስፋቱ፣ በርዝመቱና በቁመቱ እንዴት እንደምትደሰቺ! ኦ! እንዴት ትልቅ እንደሚሆን፡፡ የአንቺ ጥበብ ደግሞ እንደ ባህር ውኃ ይሆናል፣ ብዙ መረዳት ይሆንልሻል፡፡ ይህም በጣም ትሁት ያደርግሻል፡፡ አንቺም ማንም ሰው ሊቋቋመው የማይችል ጣፋጭ ትሆኛለሽ፡፡

*ኢየሱስ ሁል ግዜ ካንተ ጋር እሆናለሁ ?*

«እኔ እንደማቅሽ ያህል እንኳን ታውቂኛለሽ፡፡ እናም ምንም ነገር ሊለያየን አይችልም፡፡»

*አልገባኝም፣ የሆነ ሰዓት ላይ የምንለያይ መስሎኝ ነበር?*

«በእናንተ አለም ላይ እደምታውቂው አይነት መለያየት አይደለም፡፡ ፍፁም በሆነ መልኩ ነው አንድ የምንሆነው፡፡እናም መቸም ቢሆን አታጪኝም፡፡ ምክንያቱም የምኖረው በውስጥሽ ነው፡፡ እናም ህብረታችንን ምንም ነገር ሊረብሽን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በመንግስተ ሰማያት ኃጢያት፣ ኩራት የለም፡፡ ነገር ግን ይህ የራሱ የሆነ ጥቅምና ጉዳት አለው፡፡ ምክንያቱም እንደ ደስታ ሁሉ ኃዘንንም አብረን እንካፈላለን፡፡»

*ግን በምድር ላይ የሚሰራውን የማላውቅ መስሎኝ ነበር*

«ታላቁ መከራ እስኪያልቅ ድረስ አታውቂም፡፡ ነገር ግን በሰዎች ስገፋና ተቀባይነት ሳጣ ታውቂያለሽ፡፡  አዎ ያንን ዓይነት ስሜት ያኔም ይሰማሻል፡፡ ወደ ምድር ስንመለስና ከነፍሳት ጋር ስትሰሪ በሰሩት ሥራ የኔ ስሜት ምን እንደሆነ በደንብ ይሰማሻል፡፡ እናም እያንዳንዱ ሁኔታ እንዴት መያዝ እንዳለበት፣ ቅጣት ቢሆን ወይም ማስተካከያ ቅፅበታዊ የሆነ እውቀት ይኖርሻል፡፡»

*ወደ ምድር ስንመለስ ብዙ ቅጣቶች ይኖራሉ? ሰዎች በዚያን ጊዜም አስቸጋሪና አመፀኞች ይሆናሉ?*

«በመጀመሪያ በሴቶችና በወንዶች ላይ ብዙ የአመለካከት መሻሻሎችን ታያለሽ፡፡ ነገር ግን ብልሽቱ በጣም እየተስፋፋ ይሄዳል፡፡  የአንዳንዶች በፍጥነት ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡ የእንዳንዶቹ ቀስ በቀስ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፡፡ የኃጢያት ውጤት በቤተሰብ ውስጥ በቀላሉ እንደ ሰንሰለት እንዴት እንደሚተላለፍ ማየት ትጀምሪያለሽ፡፡ ያንንም ለመለወጥ ትሰሪያለሽ፡፡ ነገር ግን ከሌር አንዳንዶቹ አይለወጡም፡፡  እናም ስለነዚህ ነገሮች እውቀት ሊኖርሽና ነገሮች በሚከሰቱ ጊዜ ጥንካሬ ሊኖርሽ ይገባል፡፡ ነገር ግን ውጪ የሚታየው ምንም ያህል የሚያሳዝን ቢሆንም እኔ ጥልቅ የሆነ ሰላምናና ደስታን ልሰጥሽ ሁልጊዜ በውስጥሽ ነኝ፡፡»

*በሚሊንየሙ መንግስት ሞት አለ?*

«ምንም እንኳን ኃጢያትና ሰይጣን በሚሊኒሙ መንግስት ስፍራ ስለሌላቸው ሁኔታው ፍፁም ጤንነትንና ረጅም እድሜን ቢፈቅድም መወለድና መሞት ግን ያለ ነገር ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን በጣም የሚያሳዝነው የጠላት ተፅዕኖ ሳይኖር ክፋት ይገለጣል ይህም የአዳምና የሔዋን ድክመት ነው፡፡ አጋንንታዊ እርዳታ ሳይኖር ክፉ አስቀያሚ ጭንቅላቱን ከፍ ከፍ ሲያደርግ ሲያዩ ብዙዎች ይደነግጣሉ፡፡

«እናንተ ግን እጃችሁ በነካው ነገር ላይ ሁሉ ደስታን ታገኛላችሁ፡፡ መለወጥን ፣ ፈወስን፣ መልሶ መገንባትንና ፍፁም የልብ መለውጥን ታያላችሁ፡፡ ይህም መላዕክቶቹና በሰማይ ያሉ ቅዱሳን ተሰምቷቸው የነበረውን ዓይነት ሊነገር የማይችል ደስታን ይሰጣችኋል፡፡

«ልጄ ይታይሻል? በዚህ ሰዓት በምድር ላይ ብዙዎች ለማገልገል ከልባቸው ይመኛሉ፡፡ ነገር ግን የሚቃወማቸው ኃይል እጅግ ከባድ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ከራሳቸውም ተፈጥሮ ወይንም ከእነሱ ተፈጥሮ ባልሆነ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው ይህንን ግድግዳ ሰብረው የሚወጡት፡፡ ይህም ታላቅ ፅናትንና በእኔ ላይ መደገፍን ይጠይቃል፡፡

«እናም ለዚህ የተመረጡና የታጠቁ አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አሉ ለዚህ ያልተመረጡና ያልተዘጋጁ፡፡ ለእነርሱ የፀሎት ፀጋ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ፍላጎታቸው የሚገለጠው በወንጌል አገልግሎት ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ሰው እንደሚያየው በአገልግሎቱ ላይ ቀጥታ ባይሳተፉም እነርሱ ህያው የፀሎት ኃይል በመሆን ወንጌልን ለሚያሰራጩ የጀርባ አጥንት ናቸው፡፡ ለእነሱ ፀሎትና ልመና ከሚያቀርቡላቸው ከእነዚህ ብዙኃን የፀሎት ተዋጊዎች ውጪ በመድረክ ላይ የሚቆሙትን ወንጌል ሰባኪዎች ብታዩአቸው እጅግ ደካማ፣ ቀላልና የሚያሳዝኑ ሰዎችን ነበር የምታዩት፡፡

"ራሳቸው ወንጌላውያኑ ንፁህ ልብ፣ ትሁትና ከላይ የተቀበሉት ቅባት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሐቀኝነታቸው እንከን የሌለበት መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ነው በዚህ ዓይነት ጉዳይ ላይ በደንብ መሥራት የያዝነው፡፡ ለሐቀኝነት ትልቅ መሰጠትና ሥራውን

በራሴ መንገድ የማይሰሩ ከሆነ፣ ማገልገልና የጦርነቱን እሳት በፅናት መቀጠል ወይም ጫና በበዛበት ቀና ብለው መሄድ አይችሉም፡፡

ይህም ሆኖ ግን መጋረጃውን ብታነሽው፣ ይህ ሰው በእኔ እቅድ ውስጥ በጣም ትንሹን ሥፍራ የሚይዝ ነው፡፡ ከእርሱ ጀርባ ሆነው የሚማልዱት ትልቁን ድርሻ የሚይዙትና እርሱ ትልቅ ሆኖ እንዲታ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እውነታው ግን በስተጀርባው ያሉ እነዚህ ታናናሾች ናቸው ለእርሱ በክብር መታየት ድርሻውን የሚወስዱት፡፡ ስለዚህም ወንጌልን ለማገልገል ፍላጎቱ ያላቸው በዚህ መንገድ እርካታን ያገኛሉ፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ለሁሉም ጊዜና ወቅት አለው፡፡ እነርሱም ነፍሳትን በፍቅሬ ለመንካት ተራ ያገኛሉ፡፡ ሁሉም በልቡ ውስጥ ያለውን ለማከናወን ተራ አለው፡፡ ምክንያቱም ልባቸው ከልቤ ጋር ተስማምቷል፡፡

*ጌታ አምልኮስ?*

"አሁን የምትናገሪው መረዳት ከሚቻለው ውጪ የሆነን ነገር ነው፡፡ ስታመልኩ ሁሉንም የሰው ተግባራት በማቆምና በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ግዛት ሆናችሁ ነው የምታመልኩት፡፡ ከአምላካችሁ መለየት ታቆሙና ከፈጣሪያችሁ ጋር አንድ ትሆናላችሁ፡፡ ልባችሁ በአምልኮ ሰፍቶ ከራሳችሁ ይወጣል፡፡ ከአምልኮም ወደራሳችሁ ስትመለሱ ፍፁም ታድሳችሁ፣ ኃይል አግኝታችሁና ተነቃቅታችሁ ነው የምትመለሱት፡፡ ወደ አምልኮ ስትሄዱ ከእናንተ ጋር የነበረ ነገር በጠቅላላው ሄዷል፣ የለም፡፡ ከዚህ ሌላ ስለ አምልኮ ተጨማሪ ለመናገር የምችለው ነገር የለኝም፡፡ ምክንያቱም እጅግ የላቀ ስለሆነ ነው፡፡

"ራሳችሁ ታዩታላችሁ፡፡ ይህንን ብቻ ነው ቃል ልገባላችሁ የምችለው፡፡ ያን ጊዜ ታዲያ በምንም ዓይነት መንገድ ዱሮ እንደነበራችሁት ልትሆኑ አትችሉም፡፡ ልክ እንደተፃፈው ከክብር ወደ ክብር ትሻገራላችሁ፡፡

*ጌታ በዛሬው ምሽት ሌላ ልትለኝ የምትፈልገው ነገር አለ?*

"የምጠይቅሽ ነገር ከእኔ ጋር ሆነሽ እንድትመለከቺ ነው፡፡ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባቦቶችን ቀንሽና ከእኔ ጋር ወዳለው ወደ ውስጣዊ ህብረት በጥልቅ ተመለሺ፡፡ በዚህ አማካኝነት ከእኔ ብዙ ትካፈያለሽ፡፡

# ክፍል አሥር
# ፀሎት፣ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ ሥጋ ወደሙና ከአጋንንት እሥራት ነፃ መውጣት

{Holy Spirit Baptism, Communion and Deliverance}

---

## 10.1 ማንኛውንም ክፉ ለማሰር የሚደረግ ፀሎት

እ.አ.አ. ጀንዋሪ 11 ቀን 2018 ዓ.ም ተከልሶ የቀረበ

{Binding Prayer against Every Evil}

ይህንን የፀሎት ዓይነት ሲያስፈልግ በማንኛውም ጊዜ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ በተለይም ችግር ሲኖር፣ በአየሩ ላይ የጠላት ተፅዕኖ ሲሰማ፣በየጠዋቱ ወይንም ፀሎት ከመጀመሪያችን በፊት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

### ራስን በፀጥታ መመርመር

መፀለይ ከመጀመራችን በፊት በጥብቅ ንስሐ እየገባን፣ ንስሐ የገባንበትን ኃጢያት ደግመን እንዳንሰራው ጥንካሬ እንዲሰጠን መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ እንዲሁም በደል ሰርተን ንስሐ ሳንገባ ችላ ያልነው ነገር ካለ መንፈስ ቅዱስን እንዲገልጥልን መጠየቅ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱን የሰራነውን ኃጢያት በመዘርዘር በደለኞች መሆናችንን ንስሐ መግባትና ደግመን እንዳንሰራው ፀጋ መለመን፡፡

### ኃጥያትን መናዘዝና ንስሐ መግባት

ኩራትን፣ አመፅን፣ ይቅር ያለማለትን፣ መራራነትን፣ በሰው ላይ መፍረድን፣ ቅናትን፣ ስስትን፣ አለመታዘዝን፣ እምነተቢስነትን፣ ስንፍናን፣ ቸልተኝነትን፣ ራስ ወዳድነትን፣ ለራስ ያለልክ ማዘንን፣ በማይገባ ነገር ያለ ልክ መደሰትን፣ ከልክ በላይ መብላትን፣ ንዴትን፣ ጨለምተኝነትን፣ ተስፋ መቁረጥን፣ ውሸትን፣ ዝሙትን፣ ከጋብቻ ውጪ የሥጋ ግንኙነትን፣ እርኩሰትን

ያለ ባህርይ ተስፋ በገባህልኝ ላይ በውሸት ሲከስህ የጠላትን የውሸት ክስ መስማቴን እቃወማለሁ ደግሞም ንስሐ እገባለሁ፡፡ ኦ! ጌታ አንተ ደግ ፣ መሃሪ፣ ታማኝና እውነተኛ ነህ፡፡ አንተንና ጎረቤቴን ቅር አሰኝቼ ከሆነ ይቅር በለኝ፡፡ ይህንን ኃጢያት ደግሜ እንዳልፈፅመው ፀጋና ጥንካሬን ስጠኝ፡፡ በተለይም የተደበቀውን ልቤን ኃጢያት ይቅር በል፡፡

ኢየሱስ እባክህ እስካሁን ንስሐ ያልገባሁት ኃጢያት ካለ የተደበቀውን ኃጢያቴን የሚያስገነዝበኝ የንስሐ መንፈስ ላክልኝ፡፡ ኢየሱስ መፀፀቴን በፊትህ አቀርባለሁ፡፡ ኃጢያቴን ይቅር እንድትለኝ ታማኝነትህንና ምህረትህን እሻለሁ፡፡ በዚህም አንተ ለመስራት የፈለግውን እንዲሁም በእኔ በኩል ልትፈፅም ያሰብከውን ለመፈፀም አትከልክል፡፡

### ጌታን መለመን

ጌታ አንተ የድሆችን የልብ መሻት ታውቃለህ፡፡ ልቤ እንዴት እንደተዘጋጀ ሰምተሃል፡፡ ደግሞም “ልበ ንፁሆች የተባረኩ ናቸው፣ እግዚአብሔርን ያዩታል፣ በልባቸውም ያድራል” የሚለውን የተስፋ ቃልህን አጥብቄ ይዣለሁ፡፡ ከአንተ ጋር አብሮ ለመሆን፣ ብርቅዬ የሆነውን ድምፅህን ለመስማትና አስደናቂ የሆነውን ፊትህን ለማየት የተገባ የሚያደርገኝ ምንም ነገር

የለም፡፡ ብዙ በመፆምና መልካም ሥራ በመስራት ሳይሆን በአንተ ምህረት ላይ ብቻ ተደግፌያለሁ፡፡ እንደምታየኝ ከልቤ እጅግ እፈልግሃለሁ፡፡ ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ኦ! አምላኬ ምህረትህን እሻለሁ፣ ጌታዬ እባክህ ጎብኘኝ፡፡

**ክፉን ለማሰር የሚደረግ ፀሎት**
**ይህንን በቀጥታ ለአጋንንቶች ተናገሩ**

የኃያሉ የእግዚአብሔር /የኤሎሂም/ ልጅ እንደመሆኔ የቅዱሱን አገልግሎትና ተዋጊ መላዕክቶች ከእኛ ጋር እንዲፀልዩና በሁሉም አቅጣጫ ፀሎቱን ተግባርያዊ እንዲያደርጉ እጣራለሁ፡፡ እኛ የሚለው ቃል እኔን፣ ባለቤቴንና የእኛ የሆነውን ሁሉ ፣ ልጆቼንና የእነሱ የሆነውን ሁሉ፣ እናቴንና የእርሷ የሆነውን ሁሉ፣ ወንድሞቼንና የእነሱ የሆነውን ሁሉ፣ እህቶቼንና የእነሱ የሆነውን ሁሉ(እናንተ የፈለጋችሁትን መጨመር ትችላላችሁ)፣ አገልግሎቴንና ለእግዚአብሔር መንግስት የምጠቀምበትን መጠቀሚያ ንብረቶችንና፣ የሚጠብቁንን መላዕክቶች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

አባት ሆይ ሁላችንንም በክርስቶስ ኢየሱስ ደምና በአንተ የጦር መሳሪያ ሙሉ ትጥቅ እንድትሸፍነን እለምንሃለሁ፡፡ በእኛ ውስጥ ካለ ክፋት እንዲሁም በውጪ ካለ ክፉ በብርታትና በአሸናፊነት ተቋቁመን እንድንወጣ በእምነት አጠንክረን፡፡ አባት ሆይ በሚያስፈልገን ጊዜ ደግሞ የቅዱሱን መንፈስህን ምሪትና መላዕክቶችህን እንድትልክልን እለምንሃለሁ፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም አሁን አውጃለሁ፡፡ እኛን የምትቃወሙ አጋንንቶች ሁሉ፣ ግንኙነት የምታደርጉበትን ችሎታ ሁሉ አስራለሁ፡፡ መሳሪያቻችሁን ሁሉ አመክናለሁ፣ የወሰዳችሁትንና የሰረቃችሁትን ሁሉ መልሱ፣ ያበላሻችሁትን ሁሉ አስተካክላችሁ እኛን ለቃችሁ አሁን ሂዱ፡፡ <u>በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እኛን ለቃችሁ አሁን ሂዱ</u>(3x)።

እኛን ለመቃወም ያላችሁን ችሎታና አቅም ሁሉ አስራለሁ፡፡ ኃይላችሁን፣ ችሎታችሁን፣ ግንኙነታችሁን፣ የሚረዳችሁን፣ ከኋላ ደጀን የሆናችሁን፣ መልሳችሁ የምትበቀሉበትን ሁሉ አለቆቻችሁንና ህብረታችሁን ሁሉ አስራለሁ፡፡ በእኛ ላይ ለመፈፀም የተቀበላችሁትን እያንዳንዱን ተልዕኮና ተግባር ሁሉ አስራለሁ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን አልቆላችኋል፡፡ ያመጣችሁትን ቆሻሻ ሁሉ በራሳችሁ ላይ መልሼ በክርስቶስ እግር ስር እጥላለሁ፡፡ ደግሞም ተመልሳችሁ እንዳትመጡ እከለክላለሁ፡፡

በታላቁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን አዛለሁ፤ እኛን የምትቃወም የትኛውም የሰይጣን ክፍለ መንግስት ውደቅ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውደቅ፣ ደግሞም እንዳትመለስ ከለከልኩ (3x)።

የእግዚአብሔር መላዕክቶች በፊታችን እንዲወጡና ስም ማጥፋትን፣ ውሸትን፣ ማታለልንና ማንኛውንም እኛን የሚቃወምና ወደ እኛ የተላከውን መሳሪያ እንዲያከሽፉ እጠራለሁ፡፡ ይህንን የፈጠሩትን ሁሉ አለቆቻቸውን፣ከኋላ ደጀን ሆነው የሚረዷቸውን፣ ለመበቀል የሚወጡትን ሁሉ ፀጥ አሰኛለሁ፣ እንዳይሰራ እከለክላለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እግር ስር እጥላለሁ፡፡ ይህንን ፀሎት ተግባርያዊ እንዲያደርጉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተዋጊ መላዕክቶችን እጠራለሁ፡፡

እኛን ለመጨቆን በተለያየ ውርድና ስፋት፣ በመንፈስ፣ በአካል፣ በስሜት፣ በአይምሮ ኃይል፣ የክፉ ግንኙነት፤ ከክፉ የሚላክ፣ እኛን የሚቃወም ማንኛውም እንቅስቃሴ፣ ሐሳብ፣ መሳሪያ ፣ ተልዕኮና ፈቃድ ሁሉ፣ ከስሞች በላይ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እሰርዛለሁ፡፡ እያንዳንዱን ክፉ አስራለሁ፣ ሥራውንም እሰብራለሁ/3x/፡፡

በእኛና በአገልግሎታችን ላይ የሚደረግ እርግማን፣ የክፉ ምኞት፣ በፅህፈትና በቃል የሚደረግ የጥንቆላ ስራ፣ ድግምት፣ ሟርት እኛን በመቃወም የሚደረግ ማንኛውም የዳቢሎስ ማታለል፣ የጠላት ምሽግና ትስስር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም እስከ መጨረሻው እሰብራለሁ፡፡ በእኛ ላይ የተሰራ መሳሪያ አይከናወንም ተብሎ እንደተፃፈ ቅዱሳን መላዕክቶች እባካችሁ ይህንን ፀሎት በስራ ላይ ተግባርያዊ እንድታደርጉት እጠራለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በአንተ ትጋትና ብርታት ክፉን እንድናሸንፍ እባክህ እርዳን፡፡

ጌታ ኢየሱስ መላዕክቶችህ እንዲጠብቁን፣ እያንዳንዱን ኢጋንንትና ክፉን ከእኛ አካባቢ እንዲጠርጓቸው፣ ወደ እኛ የሚላከውን የክፉ ስራን እንዲዘጉ፣ በሰአት የሚፈነዱ መሳሪያዎችንና ወጥመዶችን እንዲያስፈቱ፣ በእኛ ላይ የሚያነጣጥሩ የትኛውንም ኃይል እንዲያመክኑ እንድትልክልን እለምንሃለሁ፡፡ በምንሄድበት ሁሉ ጠላቶቻችን ሊዘልቁት የማይችሉት ጠንካራ የመልአክቶች ጥበቃ በዙሪያችን እንድታደርግልን እለምንሃለሁ፡፡

እኛ ወዳለንበት ስፍራ ክፉ በአየር፣ በምድር፣ በእሳት፣ በውኃ፣ በተለያየ ወርድና ስፋት /inter dimenshinal/ የሚገባበትን በሮች ሁሉ በክርስቶስ ደም እዘጋለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ መላዕክቶችህ እንዲጠብቁን እኛ ወዳለንበት ሥፍራ ጠላቶቻችን ዘልቀው እንዳይገቡ፣ የእርግማን መሳሪያዎቻቸውን እንዲያስቆሙ ትልክልን ዘንድ እንለምንሃለን፡፡ ትጉና ኃያላን የእግዚአብሔር መላዕክቶች ይህንን ፀሎት ተግባርያዊ ስለምታደርጉት አመሰግናለሁ፡፡ ደግሞም ብዙ ጊዜ እየመጣችሁ ስረዳችሁን አመሰግናለሁ፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእያንዳንዳችን ላይ የተደረገውን የሞት እርግማን እሰብራለሁ፡፡ በህይወት እንኖራለን ለእግዚአብሔርም ክብር የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራ እንናገራለን፡፡

ጌታ ኢየሱስ እባክህ መላዕክቶቻችንን አጠንክራቸው፣ ትጋት ስጣቸው፣ ባርካቸው፣ ለውጊያ ኃያል አድርጋቸው፡፡ ኃይልን ጨምርላቸው፡፡ በውጊያ ወቅት በእሳት ውስጥ ጉዳታቸውን ጠግን፣ የሚረዷቸውን መላዕክቶች በመጨመር አጠናክራቸው፡፡ ቅዱሳን መላዕክቶች ለእኛ ስለምታደርጉት ያላሰለሰ ጥበቃና የመከላከል ስራ እባርካችኋለሁ፣ እናመሰግናችኋለሁ፡፡

ለእግዚአብሔር ለሆነው ሥራ ለእኛና ለመላዕክቶቻችን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሰጦታ ከእግዚአብሔርና ከሰው ዘንድ እንዲሆን አውጃለሁ፡፡ ቅዱሳን መላዕክት ለጌታ ኢየሱስ በሆነው ስራ ላይ እንዲሁም እርሱን በእውነት የሚፈልጉትን ለመጠበቅ ጠንካራ መከላከያ እንድታደርጉ እጠይቃለሁ፡፡

አባት ሆይ ፣ ጌታ ኢየሱስ፣ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ከልቤ አመሰግናለሁ፡፡ ክብርንም እንሰጣለን፡፡ ስለ ፍቅራችሁ አመሰግናለሁ፡፡ ክፉን እንድናሸንፍ ስለረዳችሁን አመሰግናለሁ፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፣ ቅዱሳን መላዕክቶቻችሁን እንዲዋጉልን ስለላካችሁልን አመሰግናለሁ፡፡ ደግሞም በህይወት መዝገብ ስለተፃፍን አመሰግናለሁ፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፣ ኢየሱስ አምንሃለሁ፣ ኢየሱስ አንተን እስክንመስል ድረስ እንደምተቀድሰን አምንሃለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ ቃልህን በመዝራት ተጨማሪ ነፍሳትን መሰብሰብ እንድንችል፣ እየጨመረ የመጣውን የጨለማ ኃይል ከለከልልን፣ ተጨማሪ ቅባት፣ ተጨማሪ ይቅርታ አድርግልን፡፡ በዚህ በመጨረሻ ዘመን በጥበብ፣ እራስን በመግዛት ለአንተ ብቻ እንድንኖር እርዳን፡፡

ይህ ዶክመንት በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተፃፈ ይፋ ትዕዛዝ ነው፡፡ "በምድር ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል" ተብሎ እንደተፃፈ ይህ ዶክመንት በሰማይ ምክር ቤት ጠላቶቻችንን ለማሰር ህጋዊ ዶክመንት ነው አሜን፡፡

## 10.2 በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደምንጠመቅ

{How to be baptized in the Holy Spirit}

ይህ ትምህርት በመጀመሪያ ታትሞ የወጣው በማርች 23 ቀን 2010 ዓ.ም በካሪዝማ መፅሔት ላይ በጂ.ሲ.ገራዲ ነበር፡፡

ክርስቶስን ስናምንና በእሱ ስንታመን፤ዳግም ተወልደናል (ዮሐንስ ወንጌል 3፡3)፡፡ እናም መንፈስ ቅዱስን በልባችን ተቀብለናል፡፡ ይህም በህይወታችን የምናደርገው ታላቁ ውሳኔ ነው፡፡ በክርስቶስ ደቀመዝሙርትም ላይ በተመሳሳይ መልኩ ተፈፅሟል(ዩሐንስ 20፡22)፡፡ ክፍሉም እንዲህ ይነበባል " . . . ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።" ነገር ግን ኢየሱስ ከማረጉ በፊት አብ የሰጠው ተስፋ እስኪመጣ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ነገራቸው(ሉቃስ 24፡49)፡፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ ከላይ የሆነ ኃይል እንደሚለብሱ ነገራቸው(ሐዋርያት 1፡8)፡፡ እናም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን "ኃይል" እንደሚቀበሉና የእርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ ነገራቸው፡፡ ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም በመቅደስ አካባቢ በመሆን ለብዙ ቀናት በፀሎት ቆይታን አደረጉ፡፡ በፔንጤ ቆስጣል ቀንም፣ ይህም ኢየሱስ በአረገ በሃምሳኛው ቀን መሆኑ ነው፣ በጣም የሚደንቅ ነገር ሆነ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ላይ ፈሰሰ(የሐዋርያት ሥራ 2፡1-4)፡፡ መፅሐፍ እንደሚል መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስን ተሞሉ(ለዚህም ሌላው ቃል "ተጠመቁ" የሚለው ነው)፡፡ ይህም የሚያሳየን ሁለት የተለያዩ ልምምዶችን ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚኖረን ነው፡፡ የመጀመሪያው በክርስቶስ ድነትን በማግኘት ከእግግዚአብሔር ምህረትን በመቀበል አዲስ ፍጥረት የምንሆንበትና መንፈስ ቅዱስ ሊያስተምረን፣ ሊያፅናናንና ሊረዳን በእኛ ውስጥ ለማደር መምጣቱ ነው፡፡ ሁለተኛው ልምምድ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ሲሆን ይህም በእኛ ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ በሙላት መገኘቱ ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ መነከር፣ መጥለቅ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ አገልግሎታችን በራሳችን ችሎታ ላይ እንድንደገፍ በፍፅም አይፈልግም ፡፡ እርሱ ራሱ በእኛ ውስጥ አልፎ መስራት ነው የሚፈልገው፡፡ ስለዚህ በእርሱ ችሎታ ኃይል እንድናገኝ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላንናል፡፡ በዚህ ልምምድ ውስጥ ስንሆን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእኛ ውስጥ ሞልቶ ይፈሳል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ስንጠመቅ በህይወታችን ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ኃይል መለማመድ እንጀምራለን፡፡ በተጨማሪም ያልተለመዱ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በህይወታችን መታየት ይጀምራሉ፡፡ እነዚህም ስጦታዎች በቆሮንቶስ 12፡ 8-10 ተዘርዝረዋል፡፡ ጥበብን፣ እውቀትንና ትንቢትን መናገር፤ መናፍስትን መለየት፣ ታምራቶንና ፈውሶችን ማድረግ፣ በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ናቸው፡፡ በአዲሱ ኪዳን መሰረት በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ሁሉም በአዲስ ቋንቋ ተናግረዋል፡፡ (በሐዋሪያት ሥራ 2፡1-4 ፤ ሐዋ ሥራ 10፡44-48 እና ሐዋ 19፡1-7 ይመልከቱ)፡፡

እንዲህ ቢሆንም ግን ብዙ ሰዎች በልሳን መናገር የተለየ ነገር ስለሚሆንባቸው ከመናገር ይቆጠባሉ፡፡ በእርግጥ ግን ይህ ያልተለመደ ወይም የተለየ ሳይሆን ልዩ የሆነ የፀሎት ዘዴና ክርስቲያን ሁሉ ሊለማመደው የሚችለው ነው፡፡ በዚህ በሰማያዊ ቋንቋ ስንፀልይ እግዚአብሔርን እናመሰግንበታለን፣ እናከብርበታለን፡፡ እኛም በመንፈኪሳዊ ነገር እየጠነከርን እንኄዳለን፡፡ በልሳን መናገር በመንፈስ ጠንካራ ያደርጋል፡፡ በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ታሪክ በእውነት ትልቅ ሥፍራ ያለው ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች "እኔ ከእናንተ ሁሉ በላይ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለው" ብሎ ነበር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ከእናንተ ብቃት የተነሳ የምታገኙት ነገር አይደለም፡፡ ማንኛውም ክርስያን መጠየቅ

ይችላል፡፡ ኢየሱስም ይህንን ለማድረግ ዝግጁ ነው፡፡ በራሳችው  መፀለይ ወይንም ሌላ ሰው እዲፀልይላችሁ ማድረግ ትችላላችው፡፡ ከዚህ በታች በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞሉ የሚያስችላችሁ ቀላል ደረጃዎች ተገልፀዋል፡፡

1. ልብን ማዘጋጀት ፡- መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው፡፡ ከእሳት ጋር ተወዳድሯል (ማቴ 3፡11)

"እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፡፡" ይህ ማለት እርሱ ኃጢያትን ያጠራል፡፡ እናም የክርስቶስ ህይወት ያልሆኑ ነገሮችን ሁሉ ከህይወታች ያቃጥላል፡፡ ስለዚህም የምናውቃቸውን ኃጢያቶች ሁሉ መናዘዛችንን እርግጠኞች በመሆን ልባችንን በእርሱ ለመሞላት ዝግጁ እናድርግ፡፡

2. ኢየሱስ በመንፈስ እንዲሞላህ ጠይቀው፡፡ የእግዚአብሔር ትኩረት ለመሳብ የሆነ ነገር ውስጥ መግባት የለብህም፡፡ እርሱ የአንተን ጥቄያ ለመመለስ ይጓጓል፡፡ በመንፈስ የሚያጠምቀን ኢየሱስ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱን ጠይቀው ከዚያም እንዲመልስልህም ጠብቀው፡፡
3. ከዚያም የመንፈሱን ሙላት ተቀበል፡፡ ስለድንቅ ሥራውም አመስግነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ህይወትህን እየሞላው ነው፡፡ አይምሮህ በጥርጣሬ ከተሞላ ዝም ብለህ ጌታን አመስግን፡፡ ትኩረትህን በእርሱ ላይ አድርግ እንጂ በአንተ ላይ አታድርግ፡፡
4. የተሰጠህን አዲስ የፀሎት ቋንቋ ተናገርበት፡፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላህ በልሳን የመናገር ሰማያዊ የፀሎት የቋንቋ ችሎታ ትቀበላለህ፡፡ ቃላቶቹ በውስጥህ ሲመላለስ ይሰማሃል፡፡ ቃላቶቹን በአይምሮህ ውስጥ መስማት ትጀምራለህ፡፡ ጌታን አዲስና ከተፈጥሮ በላይ የሆነን ይህንን ቋንቋ እንደሰጠህ  በማመን አፍህን ከፍተህ መናገር ጀምር፡፡ አንዳንደ ሰዎች "በአዲስ ቋንቋ መናገር አለብኝ? ብለው ይጠይቁኛል፡፡ በትክክለኛው አነጋገር እግዚአብሔር እንድትናገር አያስገድድህም፡፡ ደግሞም ከድነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ነገር ግን እኔ የማምነው ይህንን ስጦታ ለሚፈልጉት ሁሉ እንደሚሰጥ ነው፡፡ ከስጦታዎች ሁሉ የመጨረሻው ተብሎ ሊቆተር ይችላል ነገር ግን ይህ ስጦታ ወደ መንፈሳዊው አለም ለመግባት በር በመሆን ያገለግላል፡፡ እናም ወደ እግዚአብሔር ጥልቅ ነገር ይመራሃል፡፡
5. በድፍረት መውጣት መጀመር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቃችሁ በኋላ አንዱ በእናንተ ላይ የምታዩት ነገር ድፍረትን ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ መደበቅን አይወድም፡፡ በዙሪያችሁ ላሉት ሰዎች ሁሉ ስለ ኢየሱስ እንድትናገሩ ይፈልጋል፡፡ እናም አስገራሚ ድፍረትን ይሰጣችኋል፡፡

## 10.3. ስለ ሥጋ ወደሙ ጌታ ያስተማረው ትምህርት

እ.አ.አ. ጁላይ 30 ቀን 2015 ዓ.ም

{Jesus teaches about Communion}

ውድ የዩ-ቲዩብ ቤተሰቦች የጌታ በረከት በእውነት ከእኛ ጋር ነው፡፡ ዛሬ ጌታ ስለሥጋ ወደሙ አወሳሰድ የሚያስተምረን ትምህርት አለ፡፡ እርሱ ያስተማረውን ትምህርት ከማካፈሌ በፊት ግን መናገር የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ እኛ ስለዚህ ጉዳይ ከማንም ጋር መጣላት ወይም የትኛው ነው ምርጡ አወሳሰድ ፣ የትኛው ነው ትክክለኛ የሆነውና ያልሆነው፣ እናም ደግሞ "አማኝ ያልሆነ አምልኮ" ወደሚል ክርክርና ያለመግባባት ውስጥ መግባት አንፈልግም፡፡ ምክንያቱም ይህ ጌታ እጅግ የሚጠየፈው ነገር ነው፡፡ እርሱ ዛሬ ለሙሽራው የሚሆን ቀላል መልዕክት አለው፡፡ ይህም እናንተ ስለምትቀበሉት ሥጋና ደም ነው፡፡ ይህ ለእርሱ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው፡፡ በተለይም አካባቢያችን እየጨለመ በሄደ ቁጥር እናንተ ደግሞ የበለጠ እየጠነከራችሁ መሄድ አለባችሁ፡፡

*በየቀኑ ሥጋና ደሙን መቀበል በእኔ ህይወት ውስጥ እጅግ ትልቅ ጥንካሬ እንደሰጠኝ ልነግራችሁ እወዳለሁ፡፡ ደግሞም ወደ ጌታ ፈቃድ ለመለወጥ ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ትልቁ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አራማጅ ስሚዝ ዊግልሰዎርዝ እንኳን በየቀኑ የጌታን ስጋና ደም ይወስድ ነበር፡፡ ምን ዓይነት ትልቅ ምስክርነት ነው!*

*ስለዚህም እርሱ ራሱን ሊገልጥልንና ለጉዟችንም ሊያጠነክረን የሚፈልገው በዚህ መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም ከእርሷ ጋር በአካል አንድ የሚሆነው በሥጋና በደሙ ነው፡፡*

*ጌታ እንዲህ አለ . . . "ስለሥጋ ወደሙ መናገር እፈልጋለሁ ፡፡"*

*አ! ይህ በጣም ሰውን የሚነካ ነገር ግን ማንም የማይነካው ርዕስ ነው፡፡ አይደለም? ምክንያቱም ብዙዎች ሥጋ ወደሙ በእውነት ምን እንደሆነ ያላቸው ግንዛቤ ትክክል ባለመሆኑ ነው፡፡*

*"ለመሆኑ እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ራሴን በደንብ ግልፅ አላደረኩምን? በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በትንሹ ሰባት ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሬያለሁ፡፡ በእውነት በልባችው ካመናችሁና በአፋችው ከመሰከራችው በሥጋ ወደሙ ስርዓት ላይ ለእናንተ በአስደናቂ ሁኔታ እገኛለሁ፡፡ በምትኖሩበት የህይወት ዘመን በዚህ ሁኔታ ነው የሚሆነው፡፡»*

እና ይህንን ሲል ምን እያለ እንደ ነበር ተረዳውት፡፡እርሱ እያለን ያለው *«ይህ የእኔ ተስማሚ መንገድ ነው ሳይሆን ይህ እኔ ያዘጋጀሁላችሁ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዓቱ በጣም እየከፋ ስለሆነ ነው»* እያለን ነው ፡፡

*«ሥጋ ወደሙ ስትወስዱ በዳቦና በወይን ጠጅ ወስጥ በእውነት እንደምገኝ ጥርጣሬ እንዳይኖር በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጫለሁ፡፡ ስታዩት ዳቦ እና የወይን ጠጅ ነው፡፡ ቢሆንም ግን እኔ በእዛ ውስጥ ሆኜ ከእናንተ ጋር ለመሆን መርጫለሁ፡፡ በዚህም ምግብ ልሆናችሁና በመንገዳችሁ እንድትበረቱ ነው፡፡ስጋዬን በበላና ደሜን በጠጣ ጊዜ በእኔ ውስጥ ይቆያል፡፡ እኔም በእነርሱ ውስጥ እሆናለሁ (ዩሐንስ 6፡56)፡፡*

« የተለያዩ የእምነት ክፍሎች ስለ *ሥጋ ወደሙ* አዘገጃጀትና አቀራረብ ያላቸውን የአመለካከት ልዩነት እያነሱ መከራከር ምንም ስሜት የማይሰጥ ነገር ነው፡፡ የዚህ ቻናል ዓላማ ይህ አይደለም፡፡ አንድ ነገር መገንዘብ ያለብን ሁሉም የክርስትና ክፍሎች "ይህ የኔ ሥጋና የኔ ደም ነው" ብዬ ያወጅኩትን ሐሳብ መስማማታቸው ላይ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን የ*ሥጋ ወደሙ* አዘገጃጀትና አቀራረብ በእያንዳንዱ የእምነት ክፍል ሊለያይ ይችላል፡፡»

«ነገር ግን እናንተ ሙሽሮቼ ስጋዬን በመብላትና ደሜን በመጠጣት ምግብ ማግኘት አለባችሁ፡፡ ይህ ነው የእኛ በአካል የምናደርገው ህብረት፡፡ ዳቦው የእናንተ የአካል ክፍል ይሆናል፡፡ ከዚህም የተነሳ እናንተና እኔ አንድ እንሆናለን፡፡ እናም ፍሬ ታፈራላችሁ መንፈሳዊ ልጆችም ትወልዳላችሁ፡፡ እንዲሁም ለመንገዳችሁ ጠንካራ ትሆናላችሁ፡፡»

«ከቤተክርስቲያን ስርዓት ውስጥ ከሆናችውና ከቁሱ ቁርባን የምትቀበሉ ከሆነ 'ኢየሱስ ይህ በእውነት የአንተ *ሥጋ* ይህ ደግሞ በእውነት የአንተ ደም ነው' ማለታችሁን እርግጠኞች ሁኑ፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ማንኛውም በቤተክርስቲያኒቱ በመበላሸቷ ምክንያት የዓላማ ማጣት ቢኖር እናንተ ከውስጣችሁ በምታወጡት የእምነት ቃል ተቆጥሮ ሁሉ ነገር በዛ መሰረት ይሆናል፡፡ በትክክልም የትኛውንም የእምነት ማጣት ውስጣዊ በሆነ ክብርና ከልብ ከሚወጣ እምነት ማስተካከል ትችላላችሁ፡፡ እኔ በእምነት የሆነን እውነተኛ ፀሎት አከብራለሁ፡፡

እንደሚመስለኝ ጌታ እያለ ያለው በዚህ ዘመን ብዙ የአገልጋይ ዓይነቶችና ቄሶች አሉ፡፡ 'ይህ የአንተ *ሥጋ* ነው፣ ይህ የአንተ ደም ነው' ብለው ሲናገሩ የሚናገሩት አምነው ሳይሆን እንዲሁ ለማለት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ጌታ እያለ ያለው እናንተ በእምነት ከውስጣችሁ 'ኢየሱስ ይህ በእውነት የአንተ ስጋ ነው፣ ይህ በእውነት የአንተ ደመው ነው'፡፡ ብላችሁ በእምነት ስትናገሩ የእነሱን ያለማመን በመለወጥ ልዩነት ያመጣል ነው፡፡

«እንዲህ ልበል፣ እኔ ሁልጊዜ የእምነት ፀሎትን አከብራለሁ፡፡ ምንም እንኳን እናንተ በፈለጋችሁት መንገድ ምላሽ ባልሰጥም፡፡ ነገር ግን በ*ሥጋ ወደሙ* አወሳሰድ ጉዳይ ላይ አደርገዋለሁ፡፡ «ሁላችውም በዚህ ጉዳይ ላይ ላትስማሙ ትችላላችሁ፡፡ ላለመስማማት ደግሞ መብታችሁ ነው፡፡ ነገር ግን እንድትገነዘቡ የምፈልገው እናንተ በምትኖሩበት በዚህ ዘመን በውጪ እውነት ሆኖ የሚታይ ነገር አንዳንድ ጊዜ በውስጥ ምንም የሌለ ነገር ነው፡፡ ለዚህ ነው በየትኛውም ቤተክርስቲያን *ሥጋ ወደሙ* ስትወስዱ ይህንን መገንዘብ ያለባችሁ፡፡

«ይህ እናንተን ለዘላለም የመዋጀት፣ የማዳንና የማንፃት ምስጢር ነው፡፡»

*በዮሐንስ 6፡53 እንደተፃፈ ኢየሱስም እንዲህ አለ . . . "<u>እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።"</u>*

«ሁላችውም የመጨረሻውን እራት መመሪያ መሰረት በማድረግ የራሳችውን የ*ሥጋ ወደሙ* አወሳሰድ እንድታዘጋጁ እፈልጋለሁ፡፡ እናንተ በምታምኑት በዛው መጠን እገኝላችኋለሁ፡፡ ነገሮች እየጨለሙ በሄዱ ቁጥር በሚቻለው መንገድ ሁሉ ላበረታችሁ እፈልጋለሁ፡፡ *ሥጋ ወደሙን* መካፈልም ከብዙዎቹ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ለእኔ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡»

ዮሐንስ ወንጌል 6፡47-51 "*<u>እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ</u>*

*ነው።ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።"*

«*ሥጋ ወደሙ* በልምድ ከሚወሰድበት *ሥፍራ* ላላችሁ በዛው ቀጥሉ፡፡ ነገር ግን በምንም ሁኔታ ስደትን አስከትሎ ከሆነ የራሳችሁን አዘገጃጀትና አቀራረብ በትልቅ ክብርና እምነት አዘጋጁ፡፡ እናም በልዩ መንገድ ከእናንተ ጋር እገኛለሁ፡፡»

«በሙሽራዬ ልብ ውስጥ ተቀባይነት እናፍቃለሁ፡፡ ይህንን *ሥጋ*ና ደም ለእናንተ ማካፈል እፈልጋለሁ፡፡ በሚቻለው በማንኛውም መንገድ አንድ እንድንሆን እፈልጋለሁ፡፡ በ*ሥጋ ወደሙ* አማካኝነት ሰውነታችሁን እንዳላገኝ አትከልክሉኝ፡፡ በኃጢያት ስለወደቃችው *ሥጋ ወደሙ*ን ለመውሰድ አትከልከሉ፡፡ የታመሙት ናቸው *ሥጋ ወደሙ* እጅግ የሚያስፈልጋቸው፡፡ በመጀመሪያ ምን እንደሰራቸው ከልብና በእውነት ለእኔ ተናዘዙ፣ ንስሐም ግቡ፡፡ ከዚያም መውሰድ ትችላላችሁ፡፡»

"የልባችሁን እምነት እንድትከተሉ ነው የምፈልገው፡፡ *ሥጋ ወደሙ*ን ከቄስ የምትቀበሉ ከሆነ መቀበላችሁን ቀጥሉ፡፡ ነገር ግን የኔን መገኘት በእምነት እየመሰከራችሁ፡፡ ነገር ግን የምትቀበሉት ከልማድ ውጪ በሆነ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበሉና አይምሯችሁ የሚመሰክርላችሁ ከሆነ መቀበላችሁን ቀጥሉ፡፡ ነገር ግን በእምነት የኔን መገኘት መናገራችሁን እርግጠኞች ሁኑ፡፡

«ብዙ የእምነት ተቋማት ከሰው አመለካከት የተነሳ ስለ *ሥጋ ወደሙ* የተሳሳተ ትምህርት ያስተምራሉ፡፡ በአሁን ወቅት እውነቱ የሚታወቀው በመንግስተ ሰማያት ብቻ ነው፡፡ በዚህ አመለካከት ላይ የኃይማኖት መንፈስ እንዲገዛችሁ አትፍቀዱ፡፡ በተለመዶ በሚደረግ ነገር ላይ አትጣሉ፡፡ እንዲህ ልበል ጥላችሁን በጣም ነው የምጠላው፡፡ ይህ በአይኔ እጅግ ፀያፍ ነው፡፡ ለመሆኑ ታውቃላችሁ አንዱ ሌላውን እተቋቋመ ከመጣላት ይልቅ ስሜታችሁን ያዝ በማድረግ የወንድማማችነትን ትስስርና ፍቅራችሁን ብትጠብቁ እንደሚሻል? ደግሞስ ጠላትነት ካልሆነ በቀር በዛ ምን ታተርፋላች?»

«እንድታውቁት ያህል ለህሊናችሁ እውነትን እገልፅላችኋለሁ፡፡ ነገር ግን 'እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ የእርሱ መንገድ የሻላል፣ እኔ የጴጥሮስ ነኝ የእርሱ መንገድ ነው የሚሻለው!' በማለት ማንንም መጫን የለባችሁም፡፡ አያችሁ በመላዕክቶች ፊት እንዴት ሞኞች እንደሆናችሁ? ከዚህ ይልቅ እውነቱ እንዲገለጥለት አንዱ ለሌላው ይፀልይ፡፡ የቀረውን እኔ በራሴ ጊዜ እሰራዋለሁ፡፡»

«እስከዛው ድረስ እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችው ተዋደዱ»

## 10.4 ከአጋንንት እስራት ነፃ ለመውጣት የሚደረግ ዝግጅት

{How to prepare for deliverance of demonic spitit}

ለእኔ እንዳደረገለኝ ኢየሱስ በመንፈስ ወደ እናንተ መጥቶ ነፃ ሊያወጣችሁ ይችላል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃችኋል? የልሳን ስጦታ ተቀብሎ በልሳን መፀለይና መዘመር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ምንያቱም በእናንተ ውስጥ አልፎ የሚፀልየው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው!!! ከአጋንንት እሥራት ነፃ ለመውጣት ከ30 ደቂቃ እስከ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓት ድረስ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ መፀለይና ማምለክ አለባችሁ፡፡

የጎዷችሁን ሰዎች ስም ዝርዝር አውጡ፡፡ ይቅርታ ያላደረጋችሁላቸው ሰዎች ካሉ ቢያንስ ይቅርታ ለማድረግ ፍላጎት አሳዩ፡፡ ኢየሱስ ይቅርታ እንድታደርጉላቸው፣ እንድትወዷቸውና እንድትፀልዩላቸው እንዲረዳችሁ ጠይቁ፡፡ እንዲሁም እናንተ የጎዳቸዋችሁን ሰዎች ስም ዝርዝር ፃፍ፡፡ እግዚአብሔር ይቅር እዲላችሁና እነርሱን እንዲባርካቸው ፀልዩ፡፡

በተጨማሪ በምንም ዓይነት ኃጢያት ውስጥ ብትሆኑ ለምሳሌ ሰዶማዊነት ፣ ከትዳር ውጪ የሆነ የወሲብ ግንኙነት፣ እንዲሁም ጋብቻ ሳይመሰርቱ አብሮ የመኖር ግንኙነትን ማቋረጥ ወይም ትዳር መመስረት ያስፈልጋል፡፡ በየትኛው መንገድ ታማኝ ያልሆናችሁበት ነገር፣ ወላጅን ያለማክበር፣ መሰረታዊ የሆኑትን አሥርቱን ትዕዛዛትና መጣሳችሁንና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት በተገለፁት ብፅዕናዎችን መሰረት ራስን መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች እየተከተላችሁ ስለመሆኑና በህይወታችሁ ምንም ኃጢያት ያለመኖሩን አረጋግጡ፡፡ ምንም ዓይነት የብልግና መፅሔቶችን፣ ፊልሞችን፣ ሁከትና ብጥብጥ የሞላባቸውን ፊልሞችን ያለማየትን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ውጪ ሆኖ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገርን የሚያሳዩ ፊልሞችን ያለማየት ለምሳሌ እንደ ሄሪ ፖተር የመሳሰሉትን ዓይነት ፊልሞች ማስወገድ አለብን፡፡

እርግማን ያለባቸው ምንም ዓይነት እቃዎች በቤታችሁ ያለመኖሩን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ በተለይም እርግማን ባለባቸው ሰዎች የተሰሩ ምስሎችና የውሸት አምላክ የሆኑ ነገሮች እንደ ቡድሀ፣ ቲኪስ፣ የአዲሱ ዘመን ዕቃ - ኬልቲክ፣ የዘንዶው ምስልና የዘንዶው የጌም መጫወቻዎች፣ እንዲሁም ምንም ዓይነት አስማታዊ ነገሮች አይኑራችሁ፡፡ ምንም አይነት የጥንቆላ ካርዶች፣ የምርምር መፅሐፍት፣ ጌጣጌጥ ወይንም ምልክቶች ፣ ታርቶ ካርታ፣ የኮከብ ቆጠራ መፅሐፍት ፣ ምንም አይነት አስማት ከቤታችሁ ማስወገድ አለባችሁ፡፡ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ እራሳችሁን ካፀዳችሁ ነፃ መውጣት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ከማንኛውም ጥንቆላና ሰይጣናዊ ልምምዶች ንክኪ ካላችሁ ነፃ ለመውጣት ትቸገራላችሁ፡፡ አጋንንቱ ለጊዜው ይለቅህና በኋላ ግን ከእርሱ የበለጠውን ይዞ በእጥፍ ይመለሳል፡፡

ስለዚህ ነፃ ለመውጣት መጀመሪያ መዘጋጀት አለባችሁ ማለት ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለማስወገድ ስትወስኑ (እነዚህ ነገሮች ከእናንተ ጋር ካሉ) ክእርሱ ጋር ያላችሁን ስምምነት ለመተው ተስማማታችኋል ማለት ነው፡፡ ብዙ የተለያዩ አስማታዊ ልምምዶች ከነበሯችሁ ደግሞ በወረቀት በዝርዝር አስቀምጣችሁ እያንዳንዱን በመካድ ንስሐ ግቡ፡፡ ከዚህ በታች እንደ ምሳሌ ባስቀመጥኩት መሰረት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የታሮት ካርድን በመጠቀሜ ንስሐ እገባለሁ፣ ይህንንም የጥቆላ ሥራ እክዳለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከዚህ የጥንቆላ ስራ ጋር ስምምነቴን አፍርሻለሁ፣ ጥዬዋለሁ፣ በፍፁም አልመለስበትም፡፡ ኢየሱስ ምህረትን አድርገልኝ፣ ከክፉ ነፃ አውጣኝ፡፡"

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከባዕድ አምልኮ ጋር በመተባበሬ ንስሐ እገባለሁ፡፡ ይህንንም የባዕድ አምልኮ እክዳለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ከዚህ ከባዕድ አምልኮ ጋር ስምምነቴን አፍርሻለሁ፡፡ ጥዬዋለሁ፣ በፍፁም አልመለስበትም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ምሕረትን አድርግልኝ ከክፉም ነፃ አውጣኝ፡፡ "

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለቡድሃ ፀሎት ስላደረግሁ ንስሐ እገባለሁ፡፡ መተባበሬንም እክዳለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ከዚህ ጋር ስምምነቴን አፍርሻለሁ፡፡ ጥዬዋለሁ፣ በፍፁም አልመለስበትም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ምሕረትን አድርግልኝ ከክፉም ነፃ አውጣኝ፡፡

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በደሙ ኃይል ከጥንቆላ ሥራ ጋር የነበረኝን ንስሐ እገባለሁ፤ ከእንደዚህ ዓይነት የጥቆላ ሥራ ጋር የነበረኝን እንቅስቃሴና ተሳትፎ ሁሉ እክዳለሁ፣ በዚህ ሁሉ ስራዬ ንስሐ እገባለሁ፣ ደግሞም ሁሉንም እክዳለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእነዚህ ሁሉ ጋር የነበረኝን ስምምነት አፍርሻለሁ፣ ጥዬዋለሁ ደግሞም በፍፁም አልመለስበትም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ምህረት አድርግልኝ ከክፉ ነፃ አውጣኝ፡፡

በተጨማሪም የግብረ ስጋ ግንኙነት አብራችሁ የፈፀማችሁትን ሰዎች ስም ዝርዝር ፃፉና በእርሱ ፊት ስለ እያንንዳንዱ ንስሐ ግቡ፡፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ከ-------------------ጋር የነበረኝን የኃጢያት ግንኙነት እክዳለሁ፤ ስላደረኩትም ይህንን ዓይነት ኃጢያት ንስሐ እገባለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከ-------------------- የነበረውን የነፍስ ትስስር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እሰብራለሁ፤ ጌታ ምህረትን አድርግልኝ ከክፉ ነፃ አውጣኝ፡፡

በኢየሱስ ስም የትኛውም ከአያት ከቅድመ አያት የመጣ መርገምን አፈርሳለሁ፡፡ በጌታ በኢየሱስ ደም ተሸፍኛለሁ፡፡ ደሙ እርግማኖቼን ሁሉ ያጥባል ጌታ ሆይ ከእስራቴ ነፃ አውጣኝ፡፡

ስምምነታችሁን ከሁሉም ነገር ጋር ካፈረሳችሁ በኋላ የፃፋችሁትን ዝርዝር አቃጥሉትና እግዚአብሔር አጋንንታዊ ሥራዎችን ሁሉ ከህይወታችሁ እንዲያስወግድላችሁ ጠይቁት፡፡ ተሳትፎ አድርጋችሁበት ነገር ግን ንስሐ ሳትገቡና ሳትክዱት የረሳችሁት ነገር ቢኖር እንኳን ጌታ ይህንን በመለየትና ራሳችሁን በመግዛት ጠንካራ እንዲያደርጋችሁና ወደዚያ ልምምድ ዳግም እንዳትመለሱ ጠይቁት፡፡

አጋንንትን ወደእናንተ ሊጋብዙ ከሚችሉ ዕቃዎች መካከል፡- ጋዜጦችና መፅሔቶች ይገኙበታል፡፡ ምክንያቱም ጠንቋዮች እንደነዚህ ዓይነት ነገሮች ላይ እርግማንን ያስቀምጣሉ፡፡ ይህም ሰዎችን ወደዚህ ነገር በመጋበዝ አጋንንት ወደ ቤታችሁ እንዲገባ በር ለመክፈት ነው፡፡ እንዲሁም አጋንንታዊ፣ አስማታዊ፣ የባዕድ አምልኮን፣ የጭካኔ ድርጊትን የሚያሳዩ ምንም ዓይነት ፊልሞች፣ የቪዲዮዎ መጫወቻ ወይም መፅሐፎች በቤታችሁ ውስጥ አታኑሩ፡፡ የግብፅ የጥንቆላ ዕቃዎች ወይም ምልክቶች ከቤታችሁ አስወግዱ፡፡ እነዚህ በጣም አጋንንታዊ ናቸው፡፡ የባዕድ አምልኮ፤ የቡዳ መድሐኒት፤ የሌላ ሐይማኖት ምስሎች፤ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ የሆኑ ነገር ግን ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ነገሮችን ሁሉ አስወግዱ፡፡ የክርስቲያን መስቀል

ወይም ለፀሎት የምትጠቀሙበት ክርስቲያናዊ ነገር ሊኖራችሁ ይችላል፡፡ የክርስቶስ ምሰል ቢኖራችሁም እስካላመለካችሁት፣ ለምስሉ እስከሰልሰገዳችሁ ድረስ ችግር የለውም፡፡ ለምስሉ አምልኮ መስጠት ግን በምስሉ ላይ ያለውን ሰው እያመለካችሁ ነው ማለት ነው፡፡ ትኩረታችሁን ሁሉ በኢየሱስ ላይ ብቻ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ማየት የሌለብንን ፊልሞች ጌታ የሰጠኝ መመሪያ ኃጢያትን የሚጋብዙ፣ ለምሳሌ እንደ ማፊያ፣ የጥቁር ገበያን አገበያየት፣ የጦርነት፣ ወሲብን ቀስቃሽና ዝሙትን የሚያሳዩ ፊልሞችን ሁሉ ከህይወታችን እንድናስወግድ ነው፡፡